# የክርስትና

# ሕይወትና

# መንፈሳዊ ዕድገት

መንጌላዊ ሰሎሞን ወ/አምላክ

ታኅሣሥ 1989 ዓ. ም.
አዲስ አበባ

# ማ ው ጫ

ገጽ


መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

ክርስቲያን ስለ መሆን መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? . . . . . . . . . . . 5

ክርስቲያን ለመሆን የሚያበቁ እርምጃዎች . . . . . . . . . . . . . . . 17

ክርስቲያን ስንሆን በእግዚአብሔር ፊት የምናገኘው ሥፍራ . . . . . 40

በክርስትና ሕይወት የምናድግበት አቅጣጫ . . . . . . . . . . . . . . . 74

በክርስትና ሕይወት ለማደግ አስፈላጊ ነገሮች . . . . . . . . . . . 102

በክርስትና ሕይወት ለማደግ እንቅፋት የሚሆኑብን ነገሮች . . . . 131

የታማኝ ክርስቲያን ዋጋ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 145

# ምስጋና

ይህችን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ስጀምር ከባሕር ማዶ ሆና ያበረታታችኝን ወ/ሮ ምሥራቅ እስራኤልን፣ ከሥነ ጽሑፍ አኳያ መልክ እንዲኖረው ጊዜዋን ሰውታ እገዛ ያደረገችልኝን ወ/ሮ ጀሚላን እንዲሁም በኃሳብና በተለያዩ ነገሮች ድጋፍ ያደረጉልኝን አቶ ስዩም እሸቴን፣ አቶ ካሳሁን ደነቀን፣ አቶ ማርቆስ መኃላን፣ ወ/ሮ ፀሐይ ኪዳኔን እና በኮምፒውተር ሥራ በመሥራት የደከሙትን እህቶቼ ተዋበች መንግሥቴና ፍቅርአዲስ ሙሉን ከልቤ በጌታ ስም ምስጋና አቀርባለሁ።

ከሁሉም በላይ በመንፈስ ቅዱስ እያበረታኝ ለረዳኝ ጌታ ክብርና ምስጋና ዛሬም ነገም ከዘላለም እስከ ዘላለም አቀርባለሁ።

ወንጌላዊ ሰሎሞን ወ/አምላክ

# መግቢያ

የክርስትና እምነት ለሰው ልጆች ሁሉ እግዚአብሔር ያዘጋጀው የመዳን መንገድ ነው፤ የክርስትና እምነት መመሪያና መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ነው፤ ነገር ግን በክርስቲያኑ ዓለም መከፋፈል በመፈጠሩ ምክንያት ዲያብሎስ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ኃሳብ የሚያርቀበትን መንገድ ለማስፋፋት አመቺ ሁኔታ ፈጥሮለታል። የዲያብሎስ ሥራ እንዲፈርስና የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲስፋፋ ከተፈለገ ያለው አማራጭ የዲያብሎስን ሥራ ሊያፈርስ የተገለጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል ነው (1ዮሐ.3:8)። ለክርስቲያኖች መለያየት መንገድ የሆኑ ሁለት ነገሮች አሉ፤ አንደኛው፡- በጌታ የተሰጠውን እውነተኛ ወንጌል ትቶ ተጨማሪ ሌላ ወንጌል መቀበል ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የወንጌሉን ቀጥተኛ ትርጉም አለመከተል ነው (ገላ.1:6፣ 1ቆሮ.4:6፣ 2ጴጥ.1:20።

ብዙ ሰዎች የትርጉም ስህተት ላይ የሚደርሱት ማንም ያልደረሰበትን ልዩ መረዳት ለማግኘት ሲጥሩ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከያዘው እውነት ውጭ ለእያንዳንዱ የሚሆን የተለያየ ትርጉም አይኖረውም። ነገር ግን ጥልቅ የሆነ ምስጢር ቆፍረው ለማግኘት ሲሉ አንዳንዶች የቃሉን እውነት ማደፍረሳቸው አልቀረም። አቆፋፈሩንና አመጋገቡን ካወቅንበት መጽሐፍ ቅዱስ የማያልቅ ዕውቀትና ጥበብ የምናገኝበት ማዕድ ነው። ልዩ ትርጉም ከመፈለግ ባሻገር ለተለያየ ትርጉም የሚዳረጉበት ምክንያቶች ደግሞ አሉ፣ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

1. የግል መንፈሳዊ ልምምድ፡- አንዳንድ ወገኖች ከራሳቸው መንፈሳዊ ልምምድ ጋር የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል ወስደው ለማመሳሰልና ለማዛመድ ሲጥሩ ከተጻፈው እውነት ዘለው በማለፍ የትርጉም ስህተት ላይ ይደርሳሉ።

2. ከሌሎች በቀደምትነት የሰሙት ትምህርት የሚፈጥረው ተጽዕኖ፡- በትክክለኛ መንገድ ይሁን በተሳሳተ መልኩ በመጀመሪያ የሰማነው መንፈሳዊ ትምህርት በሕይወታችን የመጀመሪያውን ቦታ ስለሚይዝ ለሌላ አመለካከት ብዙውን ጊዜ ሥፍራ አለመስጠት አለ።

3. የአስተዳደግና የባሕል ተጽዕኖ፡- ማንም ሰው ለሚያያቸውና ለሚሰማቸው ነገሮች ትርጉም የሚሰጠው ቀደም ሲል ካያቸውና ከሚያውቃቸው ነገሮች ጋር በማመሳሰልና በማዛመድ ነው፤ ይሁን እንጂ

የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ቀደም ሲል ከሰማነውና ከምናውቀው ነገር ጋር አዛምዶና አገናኝቶ ትርጉም መስጠት የመጽሐፍ ቅዱስን ፍጹም እውነት አንጻራዊ ማድረግ ስለሚሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

4. የመጽሐፍ ቅዱስ ባሕርይ በቀላሉ ለመተርጎም አዳጋች መሆን፡-
የመጽሐፍ ቅዱስ አጻጻፍ በተለያየ ዘይቤ የተጻፈ ስለሆነ ማንም ሰው በራሱ በመደገፍ ሊተረጉም አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ማንኛውም መጽሐፍ የሚነበብ ቢሆንም ከሰው አዕምሮ የፈለቀ አይደለም። በክርስቲያኑ ዓለም መከፋፈል መፈጠር መጽሐፍ ቅዱስ ከሰው አእምሮ የፈለቀ አለመሆኑ ራሱ በቂ ማስረጃ ነው። ከሰዎች አእምሮ የፈለቁትን መጽሐፍት የሚያነቧቸው ሁሉ ወደ አንድ የመረዳት ደረጃ መድረስ ይችላሉ። መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት የምንችለው መንፈስ ቅዱስ ለጸሐፊዎቹ የሰጠውን መረዳት ሲሰጠን ብቻ ነው።

በሌላ በኩል ስናይ ወደ ደህንነት የሚያደርሰን የወንጌል ቃል ይህንን ያህል ውስብስብ የሆነና ለመረዳት የሚያዳግት አልነበረም፤ ነገር ግን በሕዝበ ክርስቲያኑ መካከል መለያየት የመጣው እውቀት ፍለጋ እንጂ እውነትን ፍለጋ ጥረት ሲደረግ አይደለም። በመንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍን ገሸሽ በማድረግ ሰዎች የደረሱበት እውቀት ላይ ለመድረስ ብቻ የሚደረግ እሽቅድምድም ፍቅር የጎደለው ሆኖ ወደ ትዕቢት ማድረሱ አይቀርም (1ቆሮ.8:1)።

በሌላ በኩል ደግሞ የደህንነታቸውን ወንጌል ይዘው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ለማደግ የዕድገት አቅጣጫው የጠፋባቸው ወገኖች መኖራቸው ተስተውለዋል። ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ማደግ እንደሚገባቸው በቤተ ክርስቲያን ይሰበካል፤ ይህ መልካም ነው ይሁን እንጂ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ለማደግ ዓላማ አድርገው እንዲነሱ የሚያድጉባቸውን አቅጣጫዎች አለማሳየት በሰቀቀን እንዲሞሉ ማድረግ ይሆናል። ስለዚህ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ማደግ እንዳለባቸው ማስተማሩ ብቻ በቂ አይሆንም፤ ተያይዞ መቅረብ ያለበት ትምህርት የሚያድጉበትን አቅጣጫ የሚጠቁም መሆን አለበት። በመንፈሳዊ ሕይወታቸውና በአገልግሎታቸው ማደግ እየናፈቁ የሚያድጉበት አቅጣጫ ጠፍቷቸው የራሳቸው መንፈሳዊ ሕይወት ለራሳቸው ጥያቄ የሆነባቸው ሞልተዋል።

ስለሆነም መንፈሳዊ ጥማታቸውን ለማርካት አዳዲስ ትምህርት በመጣ ቁጥር ጥንቃቄ ሳያደርጉ የተለያየ መንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ ገብተው የተወሰዱም አልታጡም። በእርግጥ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ጎልምሶና አድጎ እራሱን ማየት የማይናፍቅ ክርስቲያን የለም። በቅድሚያ ግን የምናድግበትን አቅጣጫ ማወቅና የእግዚአብሔርን ቃል መመሪያ አድርገን መነሳት ይኖርብናል። መንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ ገብተን ለማደግ የእኛ ምርጫ ወሳኝነት አለው። መንፈሳዊ ዕድገት የሚያስፈልገውን መንፈሳዊ ምግብ ወይንም መንፈሳዊ ልምምድ በማድረግ ብቻ ዝም ብሎ አይታደግም፤ መንፈሳዊውን ልምምድ ከመለማመድ በተጨማሪ ማደግ ወደተፈለገበት አቅጣጫ ለማደግ ፈቃደኛ መሆን ያስፈልጋል።

በተጨማሪም በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለማደግ ሰንሻ እንቅፋት የሚሆኑብንን ነገሮች አውቀንና ተገንዝበን እንዲገቱ ማድረግ ምርጫችን መሆን አለበት። እኛ ውሳኔና ምርጫ ስናደርግ የሚያግዘንን ጸጋ እግዚአብሔር አትረፍርፎ ይሰጠናል። ከዚያ በኋላ በክርስትና ሕይወት በድል መጓዝ እንጀምራለን፤ እንደንስር ሰንበር ያዩን ከእኛም በኋላ የሚመጡ ወገኖች ፈለጋችንን ተከትለው መብረር ይጀምራሉ። እግዚአብሔር ለእኛ ያለው እቅድ ዳግም በመወለድና ክርስቲያን በመሆን ብቻ የሚያበቃ አይደለም። በሚሰጠን ጸጋና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመታገዝ እየበረርን ይህንን የአሁኑን ዓለም አሸንፈን በሰማያዊ አገር ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንድንኖር ነው። ይህ ብቻ አይደለም፤ በዚህ ዓለም ስንኖር ስለ ስሙና ስለ ቃሉ ታምነን በመቆም የከበረውንና የላቀውን የክብር ሽልማት ከእጁ ለመቀበል እንድንሰለፍ ሁላችን ተጠርተናል (1ቆሮ.9:24)። በዚህች መጽሐፍ ለቀረቡ ኃሳቦች መነሻ መጽሐፍ ቅዱስን በማድረግ በሚከተሉት ሦስት አቅጣጫዎች ላይ ትኩረት አድርጌ ለማዘጋጀት ሞክሬለሁ።

1) ስለ ክርስትና እምነት ምንም ግንዛቤ ለሌላቸው የክርስትና እምነት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ በክርስቶስ ያዘጋጀው የመዳን መንገድ መሆኑን ማሳየት፤
2) ዳግም ልደትን ሳያገኙ በስም ክርስቲያን ተብለው ለሚጠሩት:-
   ሀ. ክርስቲያን ተብሎ በመጠራትና ክርስቲያን በመሆን መካከል ልዩነት እንዳለ ማስረዳት።
   ለ. ዳግም ለመወለድና ክርስቲያን ለመሆን የሚቀራቸው እርምጃ ምን እንደሆነ ማሳየት ነው።

3) ክርስቲያን ለሆኑት፦

ሀ. በክርስትና ሕይወት በድል ለመጓዝ የሚያስችላቸውን መንፈሳዊ ልምምድ ማስረዳት።

ለ. በመንፈሳዊ ሕይወታቸውና በአገልግሎታቸው ለማደግ እንዳይችሉ እንቅፋት የሚሆኑ ረቂቅ ነገሮች እንዳሉ ማሳየት፤

ሐ. በጌታ ታምነው እስከ መጨረሻ ለፀኑ ጌታ ለሚከፍለው ዋጋ አድናቆት እንዲኖራቸውና ሙሉ ደመወዝ ከጌታ ማግኘት እንዲችሉ ማነሳሳት ነው።

ከላይ እንደጠቀስኩት መሠረት አድርጌ የተነሳሁት መጽሐፍ ቅዱስን ስለሆነ የጥቅሶችን ቁጥር ብቻ ጽፎ ከማለፍ ጥቅሉን እንዳለ መጻፍ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። በተጨማሪም የመጽሐፉን ኃሳብ አቋርጦ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አውጥቶ ለማንበብ ብዙ ጊዜ ምቹ አይሆንም። አንዳንድ ጊዜም መጽሐፍ ቅዱስ በአቅራቢያ ላይኖር ስለሚችል የመጽሐፉን ኃሳብ ከጥቅሱ ጋር ለማገናዘብ አዳጋች እንደሚሆን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አስፈላጊ በሆነበት ሥፍራ ጥቅሱ እንዳለ ተጽፏል።

ከዚህ ባሻገር የመጽሐፉን ኃሳብ አጣጥሞ ለመያዝና አስፈላጊም ከሆነ ለማስተማሪያ እንዲሆን በየምዕራፉ መጨረሻ ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል። እነዚህ ጥያቄዎች በንባብ ጊዜ የተዘለሉ ጠቃሚ ነጥቦችን መልሰ ለማስጨበጥ የተዘጋጁ በመሆናቸው እራስንም ለማየት ያስችላል ብዬ እገምታለሁ።

"የክርስትና ሕይወትና መንፈሳዊ ዕድገት" በትንሽ የትምህርት ጅማሬ ተጀምራ ለመጽሐፍ በቅታለች። ሳስተምርና ስጸልይ በውስጤ የሚፈሰውን የእግዚአብሔርን ኃሳብ አምቄ ከመያዝ ይልቅ በየጊዜው በጽሑፍ አሰፍር ስለነበር ከልቤ ውስጥ በጸሎት ተፈልፍላ የወጣች በመሆኗ ጌታ ረድቶኝ ለሕትመት በመብቃቷ እጅግ ታላቅ እርካታ ይሰማኛል።

ወንጌላዊ ሰሎሞን ወ/አምላክ

## I. ክርስቲያን ስለመሆን መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

የክርስትና ሕይወት ከየት ይጀምራል? ክርስቲያን መሆን እንዴት ይቻላል? የክርስትና እምነት ከቤተሰብ ሊወረስ ይችላልን? የክርስቲያኖች መጽሐፍ አንድ ብቻ ሆኖ ሳለ የክርስትና ዓይነት ለምን በዛ? የሚሉ ተመሳሳይ ጥያቄዎች በአሁኑ ጊዜ በብዙ ሰዎች አእምሮ ውስጥ ይመላለሳሉ። ለእነዚህ ጥያቄዎች ተገቢ የሆነ መልስ ለመስጠት እንዲቻል በመጀመሪያ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማየት አስፈላጊ ነው።

ክርስቲያን ማለት የክርስቶስ የሆነ ወይም ክርስቶስአዊ ማለት ነው። ክርስቲያን የሚለው ስያሜ የተገኘው ከአረማውያን ነው፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው የመጀመሪያ አማኞች ደቀ መዛሙርትና ቅዱሳን ተብለው ይጠሩ ነበር። ነገር ግን በአንጾኪያ የነበሩ አማኞች ለመጀመሪያ ጊዜ በአረማውያን ክርስቲያን ተባሉ (የሐዋ.11:26)። አረማውያን የጌታን ደቀ መዛሙርት "ክርስቲያን" ሲሉ "የክርስቶስ የሆነ" ወይንም "ክርስቶሳውያን" ማለታቸው ነበር። በዘመኑ ክርስቲያን የሚለው መጠሪያ በዚህ ዘመን በመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ የሚያምኑት "ጴንጤ" ተብለው ከሚጠሩት ጋር ተመሳሳይነት ነበረው። (ጴንጠቆስጤ ማለት በዓለ-ሃምሳ ማለት ነው።)

ክርስቲያን የሚለው ስያሜ በዚህ መልክ ስለተፈጠረ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ቦታ ተጽፎ አይገኝም፤ ምናልባት ሦስት ቦታ ብቻ ተጠቅሶ እናገኘው ይሆናል። ያውም በእነዚህ ሦስት ቦታዎች ክርስቲያን ተብሎ የተጠቀሰው አረማውያን በሚሉት ዓይነት ነው (የሐዋ.11:26፤ 26:28፤ 1ጴጥ.4:15)። ስለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ አሥራ ሦስት የተለያዩ መልእክቶችን ሲጽፍ እንኳን "ክርስቲያን" የሚለውን ቃል ተጠቅሞ አያውቅም። ክርስቲያን በሚለው አባባል አፍሮ ሳይሆን እንደ አሁኑ ጊዜ የተለመደ ባለመሆኑ ነው። በአሁኑ ጊዜ ግን ክርስቲያን መባልን እንደመመኪያ አድርገው ሊጠሩበት ይፈልጋሉ፤ ክርስቲያን ለሆነ ሁሉ ይህ ስም የሚያስመካ ነው። ዋናው ቁም ነገር ክርስቲያን ተብሎ መጠራቱ ሳይሆን ክርስቲያን ሆኖ መገኘቱ ነው፤ ክርስቲያን በመሆንና ክርስቲያን ተብሎ በመጠራት መካከል ብዙ ልዩነት አለና። አንድ ሰው ክርስቲያን ሳይሆን ክርስቲያን ተብሎ መጠራት ይችላል፤ ይሁን እንጂ ክርስቲያን የሆኑትንና ክርስቲያን ተብለው የሚጠሩትን ለመለየት የሚያስቸግር አይደለም።

በአሁኑ ጊዜ ክርስቲያን ነን የሚሉት ክርስቲያን ለመሆናቸው ቢጠየቁ የሚሰጡት መልስ፡-

- ከክርስቲያን ቤተሰብ ተወልጃለሁ፤
- ተጠምቄአለሁ፤
- ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ በማለት ይሆናል።

ይሁን እንጂ እነዚህን ሥርዓቶች መፈጸሙ አግባብና መልካም ቢሆንም ይህን በመፈጸም ብቻ ማንም ክርስቲያን መሆን አይችልም፤ እነዚህን ሥርዓቶች የፈጸመ ሰው ክርስቲያን መባል ይችል ይሆናል ክርስቲያን መሆን ግን አይችልም። እነዚህ ሥርዓቶች ክርስቲያን ከሆንን በኋላ የምንፈጽማቸው ናቸው እንጂ ክርስቲያን ለመሆን የምንፈጽማቸው አይደሉም።

ታዲያ ክርስቲያን መሆን የሚቻለው ምን በማድረግ ነው? የክርስትና ሕይወት ከየት ይጀምራል? ወይም አንድ ሰው ክርስቲያን መሆን የሚችለው እንዴት ነው? ብሎ መጠየቅ አግባብ ያለው ጥያቄ ነው። የዚህ ጽሁፍ ዋነኛ ዓላማ ከሆኑት አንዱ ክርስቲያን ተብለው በሚጠሩትና ክርስቲያን በሆኑት መካከል ያለውን ልዩነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ገልጾ ማሳየት ነው። ለዚህ ጥያቄ ቀጥተኛና ግልጽ የሆነ መልስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማግኘት ይኖርብናል፤ ምክንያቱም ለክርስትና እምነት መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነውና። አንዳንድ ሰዎች የክርስቲያኖች መጽሐፍ አንድ ሆኖ ሳለ በክርስቲያኖች መካከል የእምነት ልዩነት ለምን ሊፈጠር ቻለ? ብለው ጥያቄ ያቀርባሉ። ጥያቄው አግባብ ያለው ነው፤ አንዳንዶቹ ይህን ጥያቄ የሚያቀርቡት መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ቢሆን ኖሮ በክርስቲያኖች ዘንድ መለያየት አይኖርም ነበር ለማለት አስበው ነው። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስን በሚያነቡት መካከል መለያየት መፈጠሩ መጽሐፍ ቅዱስ ከሰዎች አእምሮ ያልወጣና የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ያረጋግጣል። ለምን ቢባል ከሰዎች አእምሮ ወጥቶስ ቢሆን ኖሮ የሚያነቡ ሁሉ ወደ አንድ ኃሳብ በደረሱ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ እየተነዱ የጻፉት ስለሆነ የሚያነቡትም ደግሞ በእግዚአብሔር መንፈስ እየተረዱ ካላነበቡ በስተቀር ሊገባቸው አይችልም (1ጴጥ.1:20-21፤ 1ቆሮ.2:10-14)።

ነገር ግን ብዙ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ላይ ሳይደገፉ እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስን የአተረጓጎም ሕግ ሳይከተሉ በራሳቸው ጥረት ብቻ አንብበው

ለመረዳት ሲሞክሩ የተለያየ መረዳት ላይ ደረሱ (ማቴ.22:29)። ለሕዝበ ክርስቲያን መለያየት ሌላው ምክንያት የሆነው ሁሉም መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ የእግዚአብሔር ቃል አድርጎ አለመቀበል ነው። ይህ ደግሞ ልጓም እንደሌለው ፈረስ መሆን ነው፤ ልጓም የሌለው ፈረስ መግቻ የለውምና ከድንበር አልፎ መሄዱ አይቀርም። እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ የእግዚአብሔር ቃል አድርጎ የማይቀበል ወገን ከእግዚአብሔር ኃሳብ ርቆ መሄዱ አይቀርም (1ቆሮ.4:6)። ስለዚህ ክርስቲያን ስለመሆን መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? ብለን መጠየቃችን አግባብ ነው። ምክንያቱም ስለክርስትና ሕይወት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ እውነቱን ሊያስጨብጠን የሚችል ሌላ የለም።

ወደ ዋናው ኃሳብ እንምጣና በመጀመሪያ ክርስቲያን ለሚለው ቃል "የክርስቶስ የሆኑ" ወይም "ክርስቶሳውያን" የሚል ትርጉም ማግኘታችንን እናስታውስ። "የክርስቶስ የሆኑ" ወይም "ክርስቶሳውያን" የሚለው ኃሳብ ከዘላለም ሕይወት ጋር መያያዝ ይኖርበታል። ክርስቶሳውያን የሆኑ ሁሉ ወይም የክርስቶስ የሆኑ ሁሉ የዘላለም ሕይወት አላቸው። አንድ ሰው የክርስቶስ የሚሆነው ወይም የዘላለም ሕይወት የሚያገኘው እንዴትና መቼ ነው? መልሱ በዮሐንስ ወንጌል 3:1-16 በግልጽ ተጽፎ ይገኛል።

በዚህ ክፍል ውስጥ የምናየው ኒቆዲሞስ በሌሊት ወደ ጌታ መጥቶ ከጌታ ጋር ያደረገውን ውይይት ነው። ኒቆዲሞስ ማነው? ኒቆዲሞስ ከፈሪሳውያን ወገን የአይሁድ አለቃና መምህር እንደነበረ በዚህ የንባብ ክፍል ውስጥ እናያለን፤ በሁለተኛ ደረጃ ስለ ኒቆዲሞስ ልንጠይቅ የሚገባን ጥያቄ አለ፤ ይኸውም ኒቆዲሞስ ወደ ኢየሱስ በሌሊት ለምን መጣ? የሚል ነው፤ ለዚህ ጥያቄ ቀጥተኛ የሆነ ወይም በግልጽ የተቀመጠ መልስ አናገኝም። ይሁን እንጂ ተገቢ የሆኑ ነጥቦችን በማንሳት ለምን ኒቆዲሞስ ወደ ኢየሱስ እንደመጣ ልንደርስበት እንችላለን። ብዙ ሰዎች ወደ ጌታ ኢየሱስ በተለያየ ምክንያት ይመጡ ነበር፤ አንዳንዶች ከገዢዎች የሚሰሙትን ዛቻ ሊነግሩት ይመጡ ነበር (ሉቃ.13:34)፣ አንዳንዶች ደግሞ የሚከሱበትን ምክንያት ለማግኘት በነገር ሊያጠምዱት ይመጡ ነበር (ማቴ.22:15-18)፣ አንዳንዶች ደግሞ ሊከተሉትና ደቀ መዛሙርት ለመሆን ይመጡ ነበር (ሉቃ.9:57)፣ ሌሎች ደግሞ የዘላለም ሕይወት የሚገኝበትን መንገድ ሊጠይቁት ይመጡ ነበር (ማቴ.19:16)። ኒቆዲሞስ ወደ ኢየሱስ የመጣው ከእነዚህ በአንዱ ሊሆን ይችላል። ታዲያ ወደ ኢየሱስ የመጣበት በየትኛው ምክንያት ይሆን?

ኢየሱስ ከአይሁድ አለቆች ተቃውሞ ስለደረሰበት ተስፋ እንዳይቆርጥ ሊያበረታታው ይሆን? አነጋገሩ ይመስላል፤ ነገር ግን ለዚህ ብሎ አለመምጣቱን ከአነጋገሩ እንረዳለን፤ . . . ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ "እውቄአለሁ" እንደማለት ፈንታ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልከህ እንደመጣህ "እውቀናል" አለው። ይህ እውነት አልነበረም። ምክንያቱም በዚህ ወቅት አይሁድ ስለኢየሱስ በጥያቄ ላይ ነበሩና (ዮሐ.2:18)። እርሱም ቢሆን በሌሊት ወደ ኢየሱስ የመጣው አይሁድን ፈርቶ ነበር፤ ደግሞም ጌታ የሰጠው መልስ ከእርሱ አባባል ጋር አይዛመድም፤ ስለዚህም ኒቆዲሞስ ወደ ኢየሱስ የመጣበት ምክንያት ይህ ሊሆን አይችልም።

እንደ ሌሎች ፈሪሳውያንና ጸሐፍት በነገር ሊፈትነውና ሊያጠምደው ፈልጎ ይሆን? ይህም ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን በእርሱ ላይ ሲያሴሩ ኒቆዲሞስ ሕጋቸውን በመጥቀስ ሊያደርጉበት ያለው ነገር አግባብ አለመሆኑን አንስቶ ሲከራከር እናያለን (ዮሐ.7:50)። እውነተኛ ወዳጅ መሆኑንም አልፎ በተሰጠበት ጊዜ በስውር የጌታ ደቀ መዝሙር ከነበረው የአርማትያሱ ዮሴፍ ጋር የኢየሱስን ሥጋ በመውሰድ የከርቤና የእሬት ቅልቅል ይዞ እንደ አይሁድ አገናነዝ ልማድ በመፈጸም በግልጽ ሲከተሉት የነበሩ ሐዋርያት እንኳን ያላደረጉትን ታላቅ ነገር አድርጓል (ዮሐ.19:39)። ስለዚህ በነገር ሊያጠምደው የመጣ አለመሆኑን እንረዳለን።

ሊከተለውና ደቀ መዝሙር ሊሆን ፈልጎ ይሆን? ምናልባት ሊሆን ይችላል። ታዲያ በግልጽ ሊከተለው ከሆነ ለምን በሌሊት መጣ? አይሁድ ጌታን ይቃወሙት ስለነበር በሌሊት ተደብቆ ወደ ኢየሱስ መምጣቱ በመፍራቱ ነው፤ ስለዚህ ይህ ነጥብ መልስ ሊሆነን አይችልም።

ለራሱ ጉዳይ በልቡ ጥያቄ ይዞ መጥቶ ይሆን? ያለጥርጥር ይህ መልስ ነው፤ ኒቆዲሞስ ስለራሱ ጉዳይ ጥያቄውን በልቡ ይዞ ወደ ጌታ መጥቶ ነበር ማለት እንችላለን። ነገር ግን በልቡ የነበረው ጥያቄ ምን ይሆን? ጌታ የሰጠውን መልስ ወደ ጥያቄ ብንለውጠው የኒቆዲሞስ ጥያቄ ሆኖ እናገኘዋለን።

ቀጥለን እንይ፦ ኒቆዲሞስ ወደ ኢየሱስ መጥቶ "መምህር ሆይ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን

ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን" አለው። ጌታ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ተልኮ የመጣ ነው፤ ኒቆዲሞስ ወደ ኢየሱስ የመጣውም ይህንን በመረዳቱ ነው፤ በዚያ ሌሊት ወደ ኢየሱስ የመጣው ይህን ሊያስረዳውና አይሁድ እንደተቀበሉት ሊገልጽለት አይደለም። ያለጥርጥር ኒቆዲሞስ ወደ ኢየሱስ የመጣው ስለራሱ ጉዳይ ነው።

ስለዚህም የኒቆዲሞስን አባባልና ጌታ የሰጠውን መልስ ልብ ብለን ካስተዋልነው የልቡ ጥያቄ ምን እንደነበር ልንደርስበት እንችላለን። ኢየሱስም መልሶ "እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም" አለው፤ ይህ መልስ ከኒቆዲሞስ ጥያቄ ጋር ምን ግንኙነት አለው? ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ምላሽ ከኒቆዲሞስ ጥያቄ ጋር አይዛመድም ነገር ግን ዮሐ.2:23-25 ብንመለከት ". . . ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር ስለ ሰውም ማንም ሊመሰክር አያስፈልገውም ነበርና፤ አይተማመናቸውም ነበር፤ ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበረና" በማለት ከፈሪሳውያን ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበር ብሎ ይቀጥላል። በምዕራፍ ሁለት መጨረሻ ቁጥርና በምዕራፍ ሦስት መጀመሪያ ቁጥር ላይ ያለው ኃሳብ የተያያዘ መሆኑን በቀላሉ መረዳት እንችላለን። የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎች ከጊዜ በኋላ የተከፋፈሉ ስለሆነ ተመሳሳይነት ያላቸውን ምዕራፎች ብዙ ቦታ ማግኘት እንችላለን። ስለዚህ አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስናጠና በምዕራፎች ሳንገደብ አውደ ንባቡን ማየት ይገባናል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምናገኘው ዋናው ሃሳብ ጌታ ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ በልቡ ውስጥ ለነበረው ጥያቄ የሰጠው መልስ ነው።

ጌታ ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ የሰጠውን መልስ እንደገና እንመልከት፡- "ኢየሱስም መልሶ እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም" አለው። በዚህ መልስ ውስጥ ሁለት ኃሳብ እናገኛለን፤ አንደኛው ዳግም ስለመወለድ ሲሆን ሁለተኛው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለመግባት ነው።

ለኒቆዲሞስ ጥያቄ መልስ የሚሆነው የትኛው ኃሳብ ይሆን? ዳግም ስለመወለዱ ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም ኒቆዲሞስ ስለ ዳግም መወለድ ምንም ዓይነት ኃሳብ እንዳልነበረው ስለ ዳግም መወለድ በመገረም በጠየቀው ጥያቄ እንረዳለን። ስለዚህ ጌታ ለኒቆዲሞስ የሰጠውን

መልስ ወደ ጥያቄ ለውጠን ብናይ "ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት የሚችለው ምን ቢያደርግ ነው?" የሚል ይሆናል ማለት ነው።

ይህ ጥያቄ በኒቆዲሞስ ልብ ውስጥ ባይኖር ኖሮ ጌታ ይህን መልስ ባልሰጠውም ነበር። ይህ ጥያቄ በልቡ ውስጥ ሥር የሰደደና ለብዙ ጊዜ ያብሰለሰለው ሳይሆን አይቀርም። ኒቆዲሞስ ፈሪሳዊና የአይሁድ መምህር ነበር፤ ቅዱሳት መጻሕፍትን በሚገባ የሚያውቅና ሕግጋቱንም ጠንቅቆ የጠበቀ ሰው እንደነበር ይታወቃል። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለ መግባቱ እርግጠኛ አልነበረም። በዚያን ወቅት አይሁዶች የዘላለም ሕይወት የሚገኘው መጽሐፍትን በመመርመር ነው ብለው በማመናቸው መጽሐፍትን ይመረምሩ ነበር፤ ስለዚህም ጌታ ሲናገር "እናንተ በመጽሐፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ" ያለው መጽሐፍትን በመመርመር የዘላለም ሕይወት ይገኛል ብለው ከሚያስቡት ውስጥ አንዱ ኒቆዲሞስ ቢሆንም በውስጡ ዕረፍት አላገኘም (ዮሐ.5:39)። ስለዚህ ጉዳይ ሕግ አዋቂ ከሚባሉትና ከመምህራን ጋር ብዙ ቢወያይም የሚያረካ መልስ ከማናቸውም አላገኘም።

ኒቆዲሞስ ጽድቅን የተጠማ ሰው እንደነበር አያጠራጥርም፤ የአይሁድ መሪና መምህር ቢሆንም ስለ ሕይወት ጉዳይ ጥያቄ ነበረው። የዘላለም ሕይወት የማገኘው ምን ባደርግ ነው የሚል ጥያቄ ልቡን አስጨንቆት ነበር። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ ጌታ ወንጌል እየሰበከ መጣ፤ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስብከት እንደ ፈሪሳውያን ሳይሆን በኃይልና በሥልጣን ሲሆን የሚያደርጋቸውም ድንቅና ተዓምራቶች የብዙ ሰዎችን ልብ ማርኳል፤ ሰዎች ለሚጠይቁት ጥያቄ የሚሰጠው መልስም የማያዳግም ነበር፤ ስለዚህ ኒቆዲሞስ ወደ ጌታችን ኢየሱስ ቢመጣ ለጥያቄው ሁሉ መልስ እንደሚያገኝ ተስፋ አደረገ፤ ነገር ግን በግልጽና በቀን ወደ ኢየሱስ እንዳይመጣ አይሁድን ፈራ፤ ስለዚህ በሌሊት ተሰውሮ ወደ ኢየሱስ መምጣትን መረጠ።

ታዲያ ኒቆዲሞስ ወደ ኢየሱስ እንደመጣ በልቡ የነበረውን ጥያቄ በቀጥታ እንዳይጠይቅ ምን አገደው? ፈሪሳዊነቱ ተጽዕኖ ሳያደርግበት አልቀረም፤ በአይሁድ የታወቀ መምህርና ፈሪሳዊ ሆኖ እንዲህ ያለ ጥያቄ መጠየቅ የሚያስገምተው መስሎ ታይቶት ሊሆን ይችላል፤ ደግሞም በዙሪያ ጥምጥም እንጂ በቀጥታ ኃሳቡን መግለጽ የአይሁዳውያን ባህል

አልነበረም። ነቢያት ብዙውን ጊዜ የሚናገሩት በፈሊጥና በዘይቤ ስለነበር አይሁዳውያን የነቢያት የአነጋገር ፈሊጥ ተጽዕኖ ሳያደርግባቸው አልቀረም። ስለዚህ "መምህር ሆይ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት የምችለው ምን ባደርግ ነው" ብሎ ስለ ራሱ በግልጽ መጠየቅ አልሆነለትም፤ ስለሆነም ስለ ራሱ ስለ ኢየሱስ ገዶት የመጣ ሰው መስሎ ቀረበ፤ ጌታ ኢየሱስ ደግሞ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና የኒቆዲሞስን ንግግር ወደ ጎን ተወና በልቡ ላለው ጥያቄ መልስ ሰጠው። "እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም" አለው። እንግዲህ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መልስ እንደምንረዳው በኒቆዲሞስ ልብ የነበረው ጥያቄ የዘላለም ሕይወት ስለማግኘትና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለመግባት እንደነበረ ግልጽ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ ኒቆዲሞስ ኢየሱስ ከንግግሩ መስመር እንደወጣ በመቁጠር ወደ መጀመሪያው ንግግር ሊመልሰው በቃጣው ነበር። ኒቆዲሞስና ኢየሱስ ልብ ለልብ ተገናኙ። ስለዚህም ኒቆዲሞስ ሁለተኛውን ጥያቄ ለመጠየቅ በቀጥታ ደፈረ።

ኒቆዲሞስ ጌታ ኢየሱስ የልቡን ጥያቄ እንዳገኘለት ካየ በኋላ በመቀጠል ሁለተኛውን ጥያቄ ከአፉ አውጥቶ ጠየቀው "ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማሕጸን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን?" ኒቆዲሞስ የጌታን አባባል የወሰደው ቃል በቃል ነበር፤ ስለዚህ ይህን ጥያቄ ጠየቀው፤ ይህ ጥያቄ ማንም ተራ ሰው ሊጠይቀው የሚገባ ነው ምክንያቱም ዳግም ስለ መወለድ ከዚያን በፊት ተሰምቶ አይታወቅም ነበርና፤ ስለዚህም ኒቆዲሞስን የሚያህል ታላቅ መምህር ይህን ጥያቄ ቢጠይቅ አያስገርምም፤ ሆኖም ይህን አባባል በፌዝ ለማለፍ አልፈለገም።

ኒቆዲሞስ ከፊት ይልቅ ስለ ራሱ ማንነት ሳያስብ አልቀረም፤ ዳግም ስለ መወለድ የሚያውቀው ነገር የለምና የመንግሥተ ሰማያት ሰው አለመሆኑን ሲያውቅ ፍርሃት፣ በሌላም በኩል ደስታና የተስፋ ጭላንጭል ሳይፈራረቁበት አልቀረም። ጌታ ኢየሱስ ወደ መንግሥተ ሰማያት የመግባትን ምስጢር እየነገረው ስለሆነ ከመጽሐፍትም እየጠቀሰ በክርክር አልገጠመውም፤ እንደሌሎች ፈሪሳውያንም በቸልታ ማለፍ አልሆነለትም የዘላለም ሕይወት ማግኘት ትልቁ ጥያቄው ነበርና።

ለዚህ ለሁለተኛው ጥያቄ ጌታ የሰጠው ምላሽ ለኒቆዲሞስ ብቻ ሳይሆን

ለሰው ሁሉ መሠረታዊና ቁልፍ መልስ ስለሆነ ልብ ብለን እንድናየው ያስፈልጋል። ጌታ የሰጠው መልስ:- "እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር የእግዚብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም" አለው። ይሁን እንጂ የተሰጠው መልስ ለኒቆዲሞስ ግልጽ ስላልነበረ ሦስተኛውን ጥያቄ ለመጠየቅ ተገደደ።

የኒቆዲሞስ ሦስተኛው ጥያቄ "ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?"
የሚል ነበር፤ ማለትም "ሰው ከውኃና ከመንፈስ እንዴት ሆኖ ሊወለድ ይችላል?" ማለት ነው። ጥያቄው መሠረታዊ ጥያቄ ነው፤ ይሁን እንጂ ኒቆዲሞስ የእሥራኤል መምህር ሆኖ ይህን ጥያቄ መጠየቁ ጌታን አስገርሞታል። ስለዚህ "አንተ የእሥራኤል መምህር ሳለህ ይህን አታውቅምን" አለው።

ጌታ ኢየሱስ ከውኃና ከመንፈስ ስለ መወለድ ኒቆዲሞስ ማወቅ እንዳለበት መገመቱ እኛንም ያስገርመን ይሆናል። ምክንያቱም በዚህ ጉዳይ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በግልጽ የተቀመጠ ነገር አናይም፤ ይሁን እንጂ ለእኛም በግልጽ ባይታየን፣ ኒቆዲሞስም ባይረዳ ስለ ዳግም መወለድ በብሉይ ኪዳን የተጻፈ ነገር አለ ማለት ነው። አለበለዚያማ ኒቆዲሞስ ይህን ማወቅ እንዳለበት ጌታ አይጠብቅም ነበር።

ለኒቆዲሞስ ሦስተኛ ጥያቄ ጌታ የሰጠው መልስ ለክርስቲያኖች ሁሉ እምነት መሠረት የሚሆን ነው። እርሱም እንዲህ ብሎ መለሰለት "ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው የሰው ልጅ ይሰለቀል ዘንድ ይገባዋል" አለው።

ኒቆዲሞስ ስለ ሙሴ መጽሐፍና ስለ እሥራኤል ታሪክ ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነው። ሙሴ የእሥራኤልን ሕዝብ ከምድረ ግብፅ በባርነት ይኖሩበት በነበረው አገር በእግዚአብሔር ኃይል ነፃ አውጥቷቸዋል። ወደ ተስፋይቱ አገር ለመግባት በምድረ በዳ ሲጓዙ ከመንገዱ ርዝመት የተነሳ በደከሙ ጊዜ በሙሴና በእግዚአብሔር ላይ አጉረመረሙ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ እባቦችን ሰደደ። ስለዚህ ብዙ እሥራኤላውያን በመርዙ ተነድፈው ሞቱ። በዚህ ጊዜ ሕዝቡ ወደ ሙሴ መጥተው በአንተና በእግዚአብሔር ላይ ስለፈጸምነው በደል ይቅር ይለን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸልይልን አሉት። ስለዚህም ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው:- ". . . እባብን ሠርተህ

በዓላማ ላይ ሰቀል፤ የተነደፈውም ሰው ሁሉ ሲያያት በሕይወት ይኖራል አለው"። በዚህም መሠረት ሙሴ እንደታዘዘው አደረገ። በእባብ የተነደፉ ሁሉ ወደ ነሐስ እባብ ሲያዩ ዳኑ (ዘኁ.21:4-9)።

ይህን እውነተኛ ታሪክ ኒቆዲሞስ ጠንቅቆ ያውቃል። ነገር ግን ሙሴ በምድረ በዳ የሰቀለው የነሐስ እባብ የክርስቶስ አምሳያነት እንዳለው አልተረዳም። እርሱ ብቻ ሳይሆን መላው እሥራኤል የተሰቀለው እባብ የክርስቶስ አምሳየነት እንዳለው የተገነዘበ አይመስልም። ጌታ ኢየሱስ ኒቆዲሞስ የሚያውቀውን ታሪክ በመጥቀስ ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ በእባብ መርዝ የተነደፈ ሰው ወደ ተሰቀለው እባብ ሲመለከት እንደሚድን ሁሉ እንዲሁም ክርስቶስ ለዓለም ሕዝብ እንደሚሰቀልና በእምነት ወደ እርሱ የሚመለከቱ ሁሉ ከኃጢአት እንደሚድኑና ለዘላለም ሕይወት እንደሚያገኙ አስረዳው (ዮሐ.3:14)።

እሥራኤላውያን በምድረ በዳ በመርዛማው እባብ ሲነድፉ ወደ ተሰቀለው የነሐስ እባብ ሲያዩ ከእባብ መርዝ እንደሚድኑ አያጠራጥርም፤ ብዙ ሕዝብም እንደተባለው አድርገው ድነዋል። አንዳንዶች ደግሞ ወደ ተሰቀለው የነሐስ እባብ ማየትን ቀልድና ሞኝነት አድርገው በመውሰድ በመርዛሙ እባብ ተነድፈው የሞቱም ሳይኖሩ አይቀሩም። ነገር ግን በመርዛሙ እባብ የተነደፈ ሰው ለመዳን ያለው ምርጫ ወደተሰቀለው እባብ መመልከት ብቻ ነበር። ዛሬም ኃጢአተኛ ሰው ከኃጢአቱ ለመዳን ቢፈልግ ያለው ምርጫ ወደተሰቀለው ኢየሱስ በእምነት መመልከት ብቻ ነው።

በእሥራኤላውያን መካከል በእባብ ያልተነደፈ ሰው ይኖር ይሆናል፤ ስለዚህም ሁሉ ሰው ወደተሰቀለው እባብ መመልከት አያስፈልገውም። ነገር ግን ስለ ሰው ኃጢአት ስናስብ ኃጢአት የሌለበት ሰው በዓለም ላይ ጨርሶ የለም፤ የሰው ዘር ሁሉ ከአዳም የተገኘ ነው። የአዳም ልጆች ሁሉ ኃጢአትን ወርሰዋል። ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ያስረዳልና "ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል" ይላል (ሮሜ.3:23)። ደግሞም "ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው (በአዳም) ወደ ዓለም ሁሉ ገባ። በኃጢአት ሞት፤ እንዲሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ" ይላል (ሮሜ.5:12)። ደግሞም በሌላ ሥፍራ "ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም" ይላል (1ዮሐ.1:8)። እንግዲህ "ሁሉ

ኃጢአትን ሠርተዋል" ሲል የማይመለከተው ሰው የለም ማለት ነው። ኃጢአት የለብኝም የሚል ቢኖር ከአዳም ዘር አልተወለድኩም ማለቱ ነው።

ስለዚህ የአዳም ዘር ሁሉ ከኃጢአት ለመንጻት ያለው አማራጭ አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም ክርስቶስን መቀበል ነው። "ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል" ብሎ አልዘጋም፤ ቀጥሎም "በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነ ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ" ይላል። እንዲሁም "በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከአመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ፃድቅ ነው" ይላል (1ዮሐ.1:9)። ሰው የኃጢአት ይቅርታን ሲያገኝና ሲቤዥ የዘለዓለም ሕይወት አግኝቶ ይጸድቃል። ይህም የሚሆነው ሰው ወዶና ፈቅዶ ክርስቶስን አምኖ ሲቀበል ብቻ ነው፤ ኒቆዲሞስ ለሦስተኛው ጥያቄው ከጌታ ያገኘው መልስ በቀጥታ ይህንኑ ነው።

እንግዲህ ሰው ዳግም ተወልዶ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት የሚችለው እንዴት ነው? ወይም አንድ ሰው የዘላለም ሕይወት የሚያገኘው እንዴት ነው? ቢባል በተሰቀለው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመኑ ብቻ መሆኑን ጌታ ኢየሱስ ከተናገረው ቃል አይተናል። ስለዚህ ክርስቲያን መሆን የሚቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመንና ዳግም በመወለድ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያሳያል።

ከመጀመሪያ ለመግለጽ እንደተሞከረው አንድ ሰው ዳግም ሳይወለድ ክርስቲያን ተብሎ ሊጠራ ይችል ይሆናል። ነገር ግን ክርስቲያን ተብሎ በመጠራትና ክርስቲያን በመሆን መካከል ያለውን ልዩነት ልብ እንድንል ያስፈልጋል። ክርስቲያን ለመባል አንዳንድ ሥርዓቶችን መፈጸም ብቻ በቂ ሲሆን ክርስቲያን ለመሆን ግን ዳግም መወለድ ያስፈልጋል፤ ዳግም ለመወለድ ደግሞ ንስሐ በመግባት ክርስቶስን መቀበል ያስፈልጋል።

እዚህ ላይ ክርስቶስን መቀበል ማለት ምን ማለት ነው? የሚል ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ነው። ክርስቲያን ነን የሚሉ ሁሉ ክርስቶስን ያምናሉ፤ ክርስቶስን አይክዱም። ታዲያ ዳግም ተወልደዋል? ይህ ጥያቄ ተገቢ የሆነ ጥያቄ ነው። ነገር ግን ክርስቲያን ተብሎ በመጠራትና ክርስቲያን በመሆን መካከል ልዩነት እንዳለ ለማየት ሞክረናል። አንድ ሰው በቤተ ክርስቲያን የሚደረጉ ሥርዓቶችን በመፈጸም ክርስቲያን ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

ይሁን እንጂ ሰው ክርስቲያን የሚሆነው ዳግም ሲወለድ ብቻ እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ተረድተናል። ስለዚህ አንድ ሰው ኢየሱስን ተቀብሎ ዳግም ሲወለድ የሚያልፋቸው ሦስት ደረጃዎች ወይም እርምጃዎች አሉ። እነዚህን በሚቀጥለው ምዕራፍ የምንመለከተው ይሆናል።

## I. ክርስቲያን ስለመሆን መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

1. ለክርስትና እምነት መሠረትና መመሪያ ማድረግ ያለብን መጽሐፍ ቅዱስን ነው ያልንበት ምክንያት ምንድን ነው?
2. የክርስትና መጽሐፍ አንድ ሆኖ ሳለ በክርስቲያኑ ዓለም መከፋፈል የተፈጠረው ለምንድን ነው? ከሌሎች ጋር ተወያይበት።
3. ክርስቲያን የሚለው ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተደጋግሞ ያልተጠቀሰው ለምንድን ነው?
4. የክርስትና ሕይወት በውርስ የሚተላለፍ አይደለም የተባለበት ምክንያት ምንድን ነው?
5. ክርስቲያን ተብሎ በመጠራትና ክርስቲያን በመሆን መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ተወያይበት።
6. ክርስቲያን የሚለው ስያሜ ከየት መጣ? ምንስ ማለት ነው?
7. ክርስቲያን ከመሆን በኋላ የምንፈጽማቸው ሥርዓቶች ምንድን ናቸው?
8. ብዙ ሰዎች ወደ ክርስቶስ ይመጡ የነበረው በተለያየ ምክንያት ነበር፤ ኒቆዲሞስስ ወደ ክርስቶስ ያመጣው ጉዳይ ምንድን ነው ብለህ ትገምታለህ?
9. ጌታ ለኒቆዲሞስ የሰጠው መልስ ለክርስትና እምነት መሠረት ነው ያልንበትን ምክንያት ግለጽ።
10. ጌታ የኒቆዲሞስን ንግግር ወደ ጎን ትቶ "ሰው ዳግም ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም" ብሎ የመለሰለት ለምን ይሆን?
11. ጌታ ለኒቆዲሞስ በተናገረው መሠረት አንድ ሰው ክርስቲያን መሆን የሚችለውና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት የሚችለው ምን ሲያደርግ ነው?
12. ሙሴ በምድረ በዳ የሰቀላት የነሃስ እባብ እንደ ጥላ ሆና የምታመለክተው ማንን ነበር?
13. በምድረ በዳ በመርዛማው እባብ የተነደፈ ሰው ለመዳን የነበረው ምርጫ ምን ነበር? ለአዳም ዘር ሁሉ ከኃጢአት ለመንፃት ያለው ምርጫስ ምንድን ነው?
14. እስራኤላውያን በምድረ በዳ ሲጓዙ በመርዛማው እባብ ያልተነደፈ ሰው ይኖር ይሆናል፤ ነገር ግን ከአዳም ልጆች ኃጢአት የሌለበት ሰው ይኖራል ብለህ ታስባለህ?
15. የአዳም ኃጢአት አይመለከተኝም የሚል ሰው ቢገጥምህ ምን ትለዋለህ?
16. እግዚአብሔር የመዳንን መንገድ አዘጋጅቷል፤ የሰውስ ድርሻ ምንድነው?

## II. ክርስቲያን ለመሆን የሚያበቁን እርምጃዎች

አንድን ሰው ክርስቶስን እመን፣ የዘላለም ሕይወት ታገኛለህ ወይም ክርስቶስን እመንና ተቀበል ከዘላለም ሞት ትድናለህ ብትለው እኔ ክርስቶስን አምናለሁ፣ ክርስቶስን አልካድኩም፣ እንዲያውም ክርስቲያን ነኝ ሊልህ ይችላል። ነገር ግን ያ ሰው ዳግም እንዳልተወለደና ከኃጢአት እንዳልተላቀቀ፣ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት አለመሆኑን ታውቃለህና ታዲያ ምን መልስ ትሰጠዋለህ? ስለምትሰጠው መልስ እስቲ ቆም ብለህ አስብ፤ እንደዚህ ያለ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች ልትረዳቸው የምትችልበትን ኃሳብ በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ስለምታገኝ በጥንቃቄ አንብብ።

ብዙ ሰዎች ክርስቲያን ነን የሚሉ በግትርነት አቋም ሳይሆን ከአያት ከቅድመ አያት ጀምሮ "ክርስቲያን ነኝ" ብለው ስለሚያስቡ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የክርስትና ሕይወት እንደ አይሁዳዊነት በዘር ሐረግ የሚተላለፍ ወይም ከእናት አባት የሚወረስ ሳይሆን በግል በምናደርገው ምርጫና ውሳኔ ንስሐ ገብተን ክርስቶስን በመቀበል መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (ዮሐ.3:16-18፣ 8:2-24)። በሥጋ ከአይሁድ የተወለደ ሁሉ አይሁድ ይሆናል፤ ነገር ግን ከክርስቲያን ቤተሰብ የተወለደ ሁሉ የግድ ክርስቲያን ሊሆን አይችልም። የቤተሰቡን አካሄድና አኗኗር በማየት ውሳኔ እምዲያደርግ ይረዳው ይሆናል እንጂ ከቤተሰቡና ከወላጆቹ ክርስትናን መውርስ አይችልም።

ከአያት ከቅድመ አያት ክርስቲያን ነን እያሉ በሕይወታቸውና በአኗኗራቸው ከኃጢአት በታች ታስረው የኃጢአት ባሪያዎች ሆነው የሚኖሩ አሉ። ስለሆነም የማይወዱትን ያደርጋሉ፤ መልካም የሆነውን ለማድረግ ምርጫ ቢኖራቸውም እንኳን የኃጢአት ባሪያዎች ስለሆኑ መልካም ከማድረግ ይልቅ የማይወዱትን ክፉ ነገር ማድረግ ይቀላቸዋል። ስለዚህ ይዋሻሉ፣ ያመነዝራሉ፣ ይሰርቃሉ፣ ርኩሰት የተባለውን ነገር ሁሉ ያደርጋሉ፣ ቁጣ፣ ቅንዓት፣ ምቀኝነት፣ ዘፋኝነት ከሕይወታቸው ጋር ተቆራኝተው ይኖራል። ስለዚህ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ጨካኞች፣ ኃጢአተኞች፣ ከዳተኞች፣ ይህን የመሳሰሉትን ሁሉ ያደርጋሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም ይላል (ገላ.5:19-21, 1ቆሮ.6:9-11 ኤፌ.5:5) ምንም እንኳን እንደዚህ ያሉትን ነገሮች ሲያደርጉ አመፅ መሆኑን ቢያውቁም የኃጢአት

እስረኞች ስለሆኑ ከእነዚህ ድርጊቶች መራቅና ማምለጥ አይችሉም። ስለ ሃይማኖታቸው ቢጠየቁ ክርስቲያን ነን ብለው ይመልሱ ይሆናል። የእግዚአብሔር መንግሥት ደግሞ እንደዚህ ከሚያደርጉት ጋር ምንም ኅብረት የለውም (1ዮሐ.1:7)። ይሁን እንጂ ሰዎች ሁሉ በኃጢአታችሁ ቢናዘዙና ኢየሱስ ክርስቶስን ቢቀበሉ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአታቸው ሁሉ እንደሚያነጻቸውና ዳግም በመወለድ ልጆቹ እንደሚያደርጋቸው መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስረዳል(1ዮሐ.1:9፣ 1:12 -13) ስለዚህ አንድ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን ተቀብሎ ዳግም ለመወለድ ቢፈለግ የሚከተሉትን ሦስት እርምጃዎች መውሰድ አለበት። ወደ ዝርዝር ሁኔታ ውስጥ ከመግባታችን በፊት በዓለም ያሉትን ሰዎች በአራት ቦታ መድበን ማየት ይኖርብናል።

በመጀመሪያ ደረጃ የምንመድባቸው ስለ ጌታ ኢየሱስ ጨርሶ ያልሰሙትን ነው። በዚህ ዘመን በዓለም ስለጌታችን ያልሰሙ ሰዎች መኖራቸው ያስደንቅ ይሆናል። ይሁን እንጂ "ኢየሱስ ክርስቶስ" የሚለውን ስም እንኳን ያልሰሙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ መኖራቸው የተረጋገጠ ነው።




በሁለተኛ ምድብ ያሉት ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም በሥጋ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን፣ መሞቱንና መነሳቱን ከሃይማኖታቸው ጋር በተያያዘ ሁኔታ ወይም በታሪክ ሰምተው ነገር ግን እውነትነቱን ያልተቀበሉ ናቸው። እነዚህ ምናልባት ከፍተኛውን ቁጥር የያዙ ይሆናሉ። ለምሳሌ እስላሞችን ብንወስድ ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም መወለዱን

ያምናሉ ነገር ግን ስለ ስቅለቱ አያምኑም አይቀበሉምም። አይሁድ እንደ እስላሞች ከሃይማኖታቸው ጋር በተያያዘ ሁኔታ ስለ ኢየሱስ መወለድ፣ መሞትና መነሳት ሰምተዋል፤ ነገር ግን ነቢያት የተናገሩለት ክርስቶስ ነው ብለው አይቀበሉም። አይሁድ ኢየሱስን "ክርስቶስ" ነው ብለው እንዳይቀበሉት ያደረጋቸው ነገር የአይሁድ መምህራን ስለ መሲህ ወይም ስለ ክርስቶስ አመጣጥ የነበራቸው የተለያየ አመለካከት ነው።

አንዳንዶች ሁለት ዓይነት መሲሕ አለ ብለው ያምናሉ፤ ስለዚህ መሲሑ የፖለቲካ መሪ ሆኖ ይነሳል ይሉ ነበር። ሌሎች ደግሞ መሲሑ ሙሴ፣ እንደ ኤልያስ፣ ታላላቅ ታምራትንና ድንቆችን በማድረግ በእግዚአብሔር ኃይል ይነሳል ብለው በተስፋ ይጠባበቁ ነበር። ብዙዎቹ ደግሞ የሚመጣው መሲሕ እንደሚሰቃይ የሚያመለክቱትን ጥቅሶች ለምሳሌ እንደ ኢሳ.53 ያሉትን አይቀበሉም። ስለዚህም እስከ አሁን ድረስ እስራኤላውያን ኢየሱስን "ክርስቶስ" ነው ብለው አያምኑም። ይሁን እንጂ በፓለስታይን አገር የተወለደው ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ እስከ አሁን በክርስቲያኖች ስለሚሰበክ ስለ እርሱ በየዘመናቱ ያሉ አይሁድ መልስ መስጠት ነበረባቸውና አይሁድ ሁሉ ስለ ኢየሱስ ማንነት ሰምተዋል ማለት እንችላለን።

ሌላው ቀርቶ ኮሚኒስቶችም ከታሪክ ጋር በተያያዘ መልኩ መስማታቸው አልቀረም፤ እነርሱ በድፍረት የእግዚአብሔርን ሕልውና በመካድ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል እንደተጻፈው አይቀበሉም። የሚያሳዝነው ነገር ለእነዚህ ሁሉ ጥፋት መነሻ የሆኑት ጥቂት ሰዎች ቢሆኑም በቢሊዮን የሚቆጠሩትን ሰዎች ወደ ሲኦልና ወደ ዘላለም ጥፋት ለመምራት ምክንያት ሆነዋል።

ሦስተኛ ምድብ ውስጥ የምናገኛቸው በስም ክርስቲያን ነን የሚሉትን ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው እነዚህ ወንጌል ተሰብኮላቸው በራሳቸው ውሳኔ አድርገው ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው የተቀበሉ ሳይሆን በውርስ ክርስቲያን የሆኑ ናቸው። ከማንኛውም የሃይማኖት ክፍል ልጆች የቤተሰባቸውን ሃይማኖት በመውሰድ ይጠሩበታል። ዛሬም ክርስቲያን ነን ከሚሉ ቤተሰብ ስለ ተወለዱ "ክርስቲያን ነን" የሚሉ ብዙዎች ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ ስለ ክርስቶስ የሚሰብኩ ሊኖሩ ይችላሉ። ይህ አያስደንቅም፤ ክርስቶስን ደጅ አቁሞ በእርሱ ማመን ይቻላል (ራዕ.3:20)። ሰዎች በሕይወታቸው የሌለውን ነገር በአፋቸው መግለጥ

ይቻላቸዋል። "ስለ ክርስቶስ" ማወቅና "ክርስቶስን ማወቅ" ይለያያል። የእግዚአብሔር ፍቅር በሕይወታቸው ሳይኖር ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ሊሰብኩ ይችላሉ፤ ሰላምና ደስታ በሕይወታቸው ሳይኖር ስለ ሰላምና ደስታ ሊሰብኩ ይችላሉ፤ ትሕትና ሳይኖራቸው ስለ ትሕትና ሊሰብኩ ይችላሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ ክርስቶስን በሕይወታቸው ሳይኖር የኃጢአት ባሪያዎች ሆነው በክርስቶስ ያለውን አርነት ሳያገኙ ነፃ ውጡ ብለው ሌሎችን ሊያስተምሩና ሊሰብኩ ይችላሉ (2ጴጥ.2:19)።

ከ1912-1929 ይኖር የነበረ ሱንዳር ሲንግ የተባለ ሕንዳዊ ሰው በአንድ ወቅት ክርስቶስ ተገልጦለት በነበረ ጊዜ፦

"ስለምን ለብዙዎች አትገለጥም?" ብሎ ጌታን ጠየቀው። ጌታም ሲመልስለት ". . . በዚች ዓለም ላይ ስለ እኔ የሚናገሩ ብዙዎች ናቸው፤ ነገር ግን ከእኔ ጋር ስላልተዋሃዱ ምንም አያውቁኝም፤ ስለ እኔ የሚናገሩትና የሚጽፉት በማያውቁት ነገር ብቻ ነው። እንግዲያስ ስለ እኔ ብለው የሚናገሩትን ሁሉ እንደሚገባ አድርገው አያውቁትም፤ እኔንም አላመኑኝም . . . በእውርነት የተወለደ ሰው ስለ ቀለማት ዓይነቶች ቢጠይቁት ጥቁር፣ ነጭ፣ ቀይ፣ ቢጫ፣ ቅጠልያ እያለ በየስማቸው ሊሰይማቸው ይችላል። ነገር ግን በወሬ እየሰማ አጥንቷቸው ነው እንጂ አላያቸውምና ኅብራቸውን አስተካክሎ ሊያስረዳ ከቶ አይችልም፤ ዓይኑ እስኪገለጥለት ድረስም ኅብራቸውን ሊያስተውል አይችልም። እንዲሁም የተማረ ሊቀ ሊቃውንት እንኳን ቢሆን መንፈሳዊ ዓይኑ ካልበራለት ስለ እኔ ሊናገር እንጂ እኔን ሊያውቀኝ አይችልም . . . እነዚያ እኔ በልባቸው ውስጥ መኖሬንና ከእኔ ሕይወትንና ሰላምን ማግኘታቸው የታወቃቸው ሰዎች በዚያ በውጭ ባለው ዓይናቸው ምንም ሊያዩ አይችሉም። ዓይን ብዙውን ነገር ትመለከታለች፤ መድኃኒት ጠብ ቢያደርጉላት ግን ያ መድኃኒት በውስጧ መኖሩ ብቻ ይታወቃታል እንጂ ልታየው ከቶ አትችልም . . . እነዚያ በእኔ ያመኑ ሰዎች በውስጣቸው በመኖሬ በሚያገኙት ሰላም ኃይሌ ተሰምቷቸው በእርሱ ያርፋሉ እንጂ በዓይናቸው ሊያዩት አይሆንላቸውም" የሚል መልስ ሰጥቶት ነበር። (ሱንዳር ሲንግ ሕንዳዊ ሰማዕት ገጽ 7-8)። እንግዲህ ከዚህ እንደምንረዳው ብዙ ሰዎች ስለ ክርስቶስ አብዝተው እየፃፉና እያስተማሩ እርሱን በሕይወታቸው አያውቁት ይሆናል።

በአራተኛ መደብ ያሉት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉና የኃጢአት ሥርየት ማግኘታቸውን ለራሳቸው ያረጋገጡና ዳግም ስለ መወለዳቸው በፍሬያቸው የሚታወቁ ናቸው (ማቴ.7:17)።

አንድ ሰው በጌታ በኢየሱስ አምኖ የኃጢአት ሥርየት ሲያገኝ ደኅንነትን ስለማግኘቱ በራሱ ሊያረጋግጥ ይችላል። እራሱ ክርስቲያን ነኝ በማለቱ ብቻ ሳይሆን ክርስቲያን ስለመሆኑ በሌሎችም ይታወቃል። የኃጢአት ባሪያ የነበረው ከእስራቱ ሲፈታ ራሱም ያውቃል። ማንም ሰው የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻኛል ብሎ ካመነ ከኃጢአቱ ወዲያው ሊነፃ ይችላል (1ዮሐ.1:7)። ከዚህ በመቀጠል የምናየው አንድ ሰው ጌታን ለመቀበልና ዳግም ለመወለድ የሚያስችሉትን ሦስት እርምጃዎች ይሆናል። ማንም ሰው ክርስቶስን ለመቀበል እነዚህን ሦስት ደረጃዎች መራመድ አለበት።

የመጀመሪው እርምጃ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት መስማትና ማወቅ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል" ይላል (ሮሜ.10:14)። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከፍ ብለን ቁጥር 9 ላይ "ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሳው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና" ይላል። እንግዲህ ያላመኑትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ ስለሚል ሰው ለማመንም ሆነ ላለማመን መጀመሪያ መስማት አለበት። ስለሆነም አንድ ሰው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከድንግል ማርያም በሥጋ መወለዱን፤ ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት በመስቀል ላይ ደሙን ማፍሰሱን፤ መሞቱንና በሦስተኛው ቀን ከሙታን ስለመነሳቱ፤ ስለማረጉና ዳግም ለፍርድ ስለ መምጣቱ፤ በእርሱ ብቻ በማመን የኃጢአት ሥርየት እንደሚገኝና የዘላለም ሕይወት ማግኘት እንደሚቻል ሊሰማና ሊያውቅ ይገባል።

ይህን መልእክት ለመጀመሪያ ጊዜ መስማት የሚገባቸው ስለ ኢየሱስ ማንነት ጨርሶ ያልሰሙ ያላወቁ በአራተኛ ምደብ ያሉት ናቸው። ይሁን እንጂ አንድ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን መልእክት ሲሰማ የሚኖረው ምርጫ ሁለት ብቻ ሊሆን ይችላል፤ አንደኛው ይህ ፈጽሞ ውሸት ነው ብሎ መቃወም ሲሆን፤ ሁለተኛው እውነት ነው ብሎ መስማማት ነው።

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌል ሲሰብክ የገጠመው ሁኔታ አለ። በአንድ ወቅት ሐዋርያው ጳውሎስ ለአቴና ሰዎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በሰበከላቸው ጊዜ ለመጀመሪያ ጊዜ መስማታቸው ስለ ነበረ "ይህ የምትናገረው አዲስ ትምህርት ምን እንደሆነ እናውቅ ዘንድ ይቻለናልን? በጆሮአችን እንግዳ ነገር ታስተምረናለህና እንግዲህ ይህ ነገር ምን እንደሆነ እናውቅ ዘንድ እንፈቅዳለን" ብለው አርዮስፋጎስ ወደተባለ ሥፍራ ወሰዱት። ጳውሎስ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ከሰበከላቸው በኋላ አኩሌቶች አፌዙበት፤ ጥቂቶች ሐዋርያው ጳውሎስ በተናገረው የወንጌል ቃል አመኑ (ሐዋ.17:16-34)። በጊዜው የነበሩ የአቴን ሰዎች ወንጌልን ለመጀመሪያ ጊዜ መስማታቸው ቢሆንም ከሰሙ በኋላ የነበራቸውን ምርጫ መቀበል ወይም አለመቀበል ስለነበር አንዳንዶቹ ተቃወሙት፤ አንዳንዶቹ ደግሞ አምነው ቃሉን ተቀበሉ። ቃሉን መስማት የመጀመሪያ እርምጃ ስለሆነም አንዳንዶች ቃሉን ከሰሙ በኋላ ወደ ሁለተኛ እርምጃ ሳይደርሱ በአንደኛው ላይ ቆመው ሊቀሩ ይችላሉ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ቃሉን እንደሰሙ ወደ ሁለተኛው ደረጃ ላይ ወጥተው ሊቆሙ ይችላሉ። ሁለተኛው እርምጃ ምንድነው? ሁለተኛው እርምጃ የሰሙትን የወንጌል ቃል እውነት ነው ብሎ በኃሳብ ደረጃ መስማማት ነው።

የወንጌልን መልእክት ሰዎች በተለያየ ጊዜ ሊሰሙት ይችላሉ፤ አንዳንዶች ከልጅነታቸው ጀምሮ፤ አንዳንዶች ካደጉ በኋላ በተለያየ መንገድ ሰምተው ይሆናል። ስለሰሙትም ቃል እውነት ነው ብለው ፅንሰ ኃሳቡን ተቀብለዋል ማለት ነው። እነዚህ ወደ ሁለተኛ ደረጃ መጡ እንጂ ዳግም ተወለዱ ማለት ሳይሆን በኃሳብ ደረጃ የሰሙት ቃል እውነት ስለመሆኑ መስማታቸው ነው። አንዳንዶቹ በዚህ ቅጽበት ውስጥ አቋም ወስደው ወደ ሦስተኛው ደረጃ በመድረስ ጌታን አምነው በመቀበል ደህንነት ሊያገኙ ይችላሉ። ሦስተኛው እርምጃ ምን እንደሆነ በኋላ እናያለን። ይሁን እንጂ አንዳንዶች ወደ ሁለተኛው እርምጃ መጥተው ሦስተኛውን እርምጃ ሳይራመዱ እዚያው ሊቆሙ ይችላሉ። ይህ ደግሞ ሊሆን የሚችለው በተለያየ ምክንያት ነው።

ከላይ እንደተጠቀሰው አንዳንዶች እዚህ ሁለተኛው ደረጃ ላይ ከልጅነታቸው ጀምረው ይሆናል። ክርስቲያን ስለመሆናቸው ከልጅነታቸው ጀምሮ ስለሰሙና ስለተነገራቸው ስለ ክርስቶስ ማንነት ሊሰሙ ምንም ዓይነት አቋም ላይወሰዱ ይችላሉ። ከቤተሰባቸው የወረሱት ሃይማኖት

ክርስትና በመሆኑ ስለ ክርስቶስ ሲነገራቸው እንደገና አዲስ ነገር አይሆንባቸውም። ከዚህም የተነሳ ክርስቶስን አልካድኩትም፣ አምነዋለሁ ይሉ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ዳግም ሳይወለዱ እራሳቸውን ክርስቲያን አድርገዋል።

ብዙ ሰዎች ዳግም ልደት ሳያገኙ እራሳቸውን እንደ ክርስቲያን የሚቆጥሩትም በዚህ ምክንያት ነው። ሆኖም ክርስቲያን የሆነ ሰው ማድረግ የማይገባውን ከላይ የጠቀስናቸውን እርኩሰት ያደርጋሉ። ይህም ሆኖ በኃጢአት የተሸነፉና የኃጢአት ባሪያዎች መሆናቸውን አያስተዋሉም። ይሁን እንጂ ስለ ሃይማኖታቸው የሚቀኑ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ስለ ሃይኖታቸው በመቅናት የሕይወት ራስ የሆነውን ክርስቶስን አሳልፈው እንደሰጡ እንደ አይሁድ ናቸው። ክርስቶስን በሃይማኖት ቅንዓት አሳልፈው ስለሰጡ አይሁድ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል "በእውነት አይቅኑ እንጂ ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ እመሰክርላቸዋለሁና" (ሮሜ.10:12)።

ክርስቶስ በአይሁድ መካከል ብዙ ድንቅና ተዓምራቶችን አድርጓል። እውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ዓይኖቹን በሰንበት በመክፈቱ የአይሁድ መሪዎች ሰንበትን አያከብርምና ከእግዚአብሔር አይደለም ብለው ተቃወሙት (ዮሐ.9:16)። አራት ቀን በመቃብር የከረመውን አልዓዛርን ከሞት ሲያስነሳ ሸንጎ ሰብስበው "ምን እናድርግ ይህ ሰው ብዙ ምልክቶችን ያደርጋል እንዲሁ ብንተወው ሁሉ በእርሱ ያምናሉ" ብለው ሊያጠፉት ተስማሙ (11:47-48)። ክርስቶስም እንዳልተቀበሉት አውቆ እርሱን ባለመቀበላቸው የሚደርስባቸው ጥፋትና እልቂት ታይቶት አለቀሰላቸው (ሉቃ.19:41-44)። ይህ ሁሉ ሲሆን ቅንዓት ልባቸውን አሳውሮት ነበርና ሊያስተውሉ አልቻሉም። በመጨረሻም ለጲላጦስ አሳልፈው ሰጡት። ጲላጦስ ግን በቅንዓት እንደሰጡት አውቆ በነፃ ሊለቀው በፈለገ ጊዜ የካህናት አለቆችና የሕዝቡ መሪዎች አባብለው በኢየሱስ እንዲፈርድ አብዝተው እንዲጮኹ አነሳሷቸው (ማቴ.27:17-24)። ይህን ሲያደርጉ በእነርሱ አስተሳሰብ እግዚአብሔርን ማገልገላቸው ነው። ጲላጦስ ግን ውኃ አንስቶ "እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ እናንተ ተጠንቀቁ" ሲል ሕዝቡ መልሰው ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን አሉ (ማቴ.27:24-25)። በዚህም ምክንያት በዚያችው ከተማ ከነልጆቻቸው በሮማውያን ተጨፈጨፉ፣ ከተማይቱ ፈራረሰች፣ በሂትለር ጊዜ ስድስት ሚሊዮን ሕዝብ ተጨፈጨፈ፤ እስከ ቅርብ ዓመት አይሁድ

በዓለም ሁሉ ተበትነው ተንከራትተው ኖሩ፤ እነርሱ ባይቀበሉትም እግዚአብሔር ዓለምን ለማዳን ያደረገውን እቅድ ግን ማስቀረት አልተቻላቸውም (ዮሐ.1:11-12)።

የሃይማኖት ቅንዓት መንፈሳዊ ልብን ያሳውራል። አሁን በዚህ ክርስቲያን ነን እያሉ ወንጌልን የሚሰብኩትን በመቃወም ምንም የማያውቁትን ሰዎች በማሳመጽ አይሁድ ካደረጉት ነገር የከፋና የባሰ ነውርን ሲያደርጉ አይታወቃቸውም። ክርስቶስ ግን እርሱ ጌታ ሆኖ የዓለም ሰዎች እርሱን እንዳሳደዱት የእርሱ የሆኑትን የበለጠ እንደሚያሳድዷቸው እንዲህ በማለት ተናግሯል፦"ባሪያ ከጌታው አይበልጥም እኔን አሳደውኝ እንደሆነ እናንተን ደግሞ ያሳድዷችኋል" (ዮሐ.15:20)።

በተጨማሪም "ሲነቅፏችሁና ሲያሳድዷችሁ በእኔ ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብጹዓን ናችሁ፤ ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ ሐሴትም አድርጉ" አለ (ማቴ.5:11)። ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ እንዲህ ብሏል "በአንድም ነገር በተቃዋሚዎች አትደንግጡ ይህ ለእነርሱ የጥፋት ለእናንተ ግን የመዳን ምልክት ነው፤ ይህ ከእግዚአብሔር ነው ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቷአችኋልና ስለ እርሱ መከራ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም" ፊል.1:28-29። በሌላ ሥፍራም "ስለ እርሱ ደግሞ መከራ ለምትቀበሉለት ለእግዚአብሔር መንግሥት የምትበቁ ሆናችሁ ትቆጠሩ ዘንድ ይህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ ምልክት ነው። ጌታ ኢየሱስ በሥልጣኑ ከመላእክት ጋር ከሰማይ በእሳት ነበልባል ሲገለጥ መከራን ለሚያሳዩአችሁ መከራን፣ መከራንም ለምትቀበሉ ከእኛ ጋር ዕረፍት ብድራት አድርጎ እንዲመልስ በእግዚአብሔር ፊት በእርግጥ ጽድቅ ነውና" ይላል (2ተሰ.1:57)።

እንዲህ ዓይነት መከራና ስደት ወንጌልን በሚሰብኩት ላይ እየፈጸሙ በሌላ መልኩ አይሁድ በኢየሱስ ክርስቶስ የፈጸሙትን ያወግዛሉ። እነዚህ ራሳቸው በዚያን ጊዜ ቢኖሩ ስቀለው፣ ስቀለው እያሉ አብዝተው ከሚጮኹት ወገን ይሆኑ ነበር። ነገር ግን አሁን እያደረጉ ያሉትን አመፅ ቢያስተውሉት አይሁድ ከፈጸሙት ስህተት ይልቅ የከፋ መሆኑን ተረድተው በተመለሱ ነበር። በዚያን ጊዜ ይቃወሙት የነበሩትን አይሁድ ጌታ እንዲህ ብሏቸው ነበር፤ "እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን የነቢያትን መቃብር የምትሰሩ የጻድቃንን መቃብር ስለምታስጌጡና በአባቶቻችን ዘመን ኖረን በሆነስ በነቢያት ደም ባልተባበርናቸውም ነበር

ስለምትሉ ወዮላችሁ"አላቸው (ማቴ.23:29-30)። በዘመኑ የነበሩ አይሁድ አባቶቻችን ተሳስተው ነበር፤ እኛ ብንሆን እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት አንፈጽምም ማለታቸው የሚያስገርም ነው። ምክንያቱም አባቶቻቸው ያልፈጸሙትን የከፋ ነገር ሊፈጽሙ ተዘጋጅተዋል። ያም የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ለሞት አሳልፎ ለመስጠት መዘጋጀታቸው ነው። ከእነርሱም በፊት የነበሩ አባቶቻቸው እንዲህ እያሉ በዘመናቸው ክፉ ነገር እየፈጸሙ አልፈዋል።

ነቢያት ሲነሱ ስለ አመፃቸውና ስለ ክፋታቸው ሲገስጹአቸው ይነሱባቸውና ይገድሏቸዋል። ከእነርሱ በኋላ የሚነሳው ትውልድ እነዚያ ነቢያት የተናገሯቸው ትንቢቶች ሁሉ እውነት መሆናቸውን ሲያረጋግጡ ተነስተው የእነዚያን ነቢያት መቃብር ሸላልመው ያስጌጡና "አባቶቻችን ተሳስተዋል፤ እኛ በዚያን ጊዜ ብንኖር ኖሮ ከእነርሱ ክፋት ጋር አንተባበርም ነበር።" በማለት በራሳቸው ዘመን የሚነሱትን ነቢያት ግን ያሰቃዩአቸውና ይገድሏቸው ነበር። እራሳቸው የሚፈጽሙት ክፋት ግን አይታያቸውም፤ እነርሱ ካለፉ በኋላ ሌላ ትውልድ ይመጣና አባቶቻቸው ሲሉት እንደነበር "እኛስ ብንኖር ኖሮ በአባቶቻችን በደል ባልተካፈልን ነበር" ይላሉ። እንዲህ እያሉ ኢየሱስ ክርስቶስም በነበረበት ጊዜ የነበሩ አይሁድ ያንኑ ቢሉም የከፋ ስህተት ከመፈጸም አልታቀቡም። በአሁኑም ዘመን ያሉ የሃይማኖት አባቶች ነን የሚሉ በክፉ የሃይማኖት ቅንዓት ወንጌል የሚሰብኩትን ያሳድዳሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ እንደጻፈው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሥልጣኑ መላእክት ጋር ከሰማይ በእሣት ነበልባል ሲገለጥ ያን ጊዜ ለእርሱ መልስ ይሰጣሉ (2ተሰ.1:6-8)።




ሦስተኛው እርምጃ ለደህንነት በክርስቶስ መታመን ነው። ይህን የእምነት እርምጃ የሚወስዱ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስን ቤዛቸው፤ አዳኛቸው፤ ጽድቃቸው፤ አድርገው ተቀበሉት ማለት ነው (1ኛ ቆሮ.1፡30-31)። በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ሰላምና ፍቅር ከታላቅ ደስታ ጋር በመንፈስ

ቅዱስ በልባቸው መፍሰስ ይጀምራል። የዓይን ጠብታ የተደረገለት ሰው ጠብታውን በዓይኑ ባያየውም ጠብታው በውስጡ መኖሩን እንደሚታወቀው ሁሉ በክርስቶስ አምኖ የዳነ ሰው ክርስቶስን በዓይኑ ባያየውም ክርስቶስ በሕይወቱ መኖሩን ያውቃል (2ቆሮ.13:5 ዮሐ.14:20 ሮሜ.8:9)።

የክርስቶስ ፍቅር ሲገባቸው አንዳንዶች በታላቅ ጩኸት እግዚአብሔርን ማመስገን ይጀምራሉ፣ አንዳንዶች ደግሞ የራሳቸው ኃጢአተኝነትና የእግዚአብሔር ፍቅርና ምህረት ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ይታያቸውና በታላቅ ድምጽ በማልቀስ ስሜታቸውን ይገልጻሉ። ከኃጢአታቸው ስለ መንጻታቸውና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ስለማግኘታቸው ማንም ሳይነግራቸው በራሳቸው ያውቃሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ እውነትም ጌታ ነው ማለት ይጀምራሉ (1ቆሮ.12:1-3)። የውስጥ መንፈሳዊ ዓይናቸው ስለሚበራ ኢየሱስ የጌቶች ሁሉ ጌታ፣ የነገሥታት ሁሉ ንጉሥ የዓለም ሁሉ አዳኝ እርሱ ብቻ መሆኑን ይገነዘቡታል። ከዚያም በኋላ በሚጸልዩበት ጊዜ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ኅብረት ማድረግን ይለማመዳሉ።

ስለዚህ የትም ቦታ ከመሄድና ከማንም ጋር ከመሆን ይልቅ በጸሎት ሥፍራ ከእግዚአብሔር ጋር መሆንን ይመርጣሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ሲያነቡ እንደ ድሮው ማስጠላቱ ቀርቶ በሕይወታቸው ውስጥ እንደ ፈሳሽ ዘይት፣ ልዩ ጣዕም እንዳለው ምግብ ይሆንላቸዋል። ቃሉን ባነበቡ ቁጥር እግዚአብሔር አእምሮአቸውን ስለሚከፍትላቸው ልባቸው በእግዚአብሔር ፍቅር ይቃጠላል። በሕይወታቸው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም በማያቋርጥ ሁኔታ መፍሰስ ይጀምራል።

ሰው በዚህ ዓለም ነገር ለጥቂት ጊዜ ደስታን ሊያገኝ ይችላል፤ ሆኖም በዚህ ዓለም ያለው ነገር ሁሉም ጊዜያዊ ስለሆነ ያ ደስታ ቶሎ ይጠፋል። በመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ ደስታ አለማቋረጡ ብቻ ሳይሆን ሰማያዊ ስለሆነ በሰዎች ቋንቋ መግለጽ ያስቸግራል። ሌላውም ሁሉ እንደዚህ ነው፣ ፍቅር ቢሆን ቋንቋ የለውም። ከእግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ወደ ልባችን የሚፈሰው ፍቅር የተለየ ነው። እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ በመንፈስ ቅዱስ ወደ ልባችን የሚያፈሰው ፍቅር የራሱ የእግዚአብሔር ፍቅር ነው (ሮሜ.5:5)። የእግዚአብሔር ፍቅር ደግሞ በዚህ ዓለም እንዳለው ፍቅር ዓይነት አይደለም። ይህ ፍቅር ሰዎችን ሁሉ እንዲሁ እንድንወዳቸው

ያስችለናል። የሚጠሉንን ሁሉ እንኳን እንድንወዳቸው ይረዳናል። በአጭሩ አዲስ ፍጥረት ሆነን ራሳችንን እናገኘዋለን (2ቆሮ.5:17)። አንድ ሰው ኃጢአቱን ተናዝዞ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ሲቀበል ክርስቶስ በሕይወቱ ማደሩን ያውቃል።

ስለ እግዚአብሔር ሕልውና ድንግዝግዝ ብሎበት የነበረው ተለውጦ አሁን ከእርሱ ጋር ኅብረት ማድረግ ይጀምራል። "ኅብረታችን ከአባት ጋር ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው" ይላል (1ዮሐ.1:3)። ይህንን ቃል ማንም ሰው ሊሰብከው፣ ሊያስተምረውም ይችል ይሆናል። ነገር ግን ከአብ ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ኅብረት አድርጎ መኖር የተለየ ነገር ነው። ዕውር ሆኖ የተወለደ የቀለማትን ዓይነቶች በየስማቸው ሲጠራቸው ኖሮ ዐይኑ ሲበራ ኅብረ-ቀለማትን ሁሉ በዓይኑ ሲያይ በወሬ መሆኑ ቀርቶ በዓይኑ እያየ አስተካክሎ ማስረዳት ይጀምራል፤ ልክ እንደዚሁ መንፈሳዊ ዓይኑ የበራለት ለእግዚአብሔር አብ ክብር እየሰጠ ኢየሱስ ጌታ መሆኑን ይመሰክራል።

በአጠቃላይ አንድ ሰው ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ሲቀበል የመንፈስ ቅዱስ ባሕርይ በውስጡ ያድራል፤ ይህ የመንፈስ ቅዱስ ባሕርይ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዋኃት፣ ራስን መግዛት ነው (ገላ.5:22)። እነዚህ ሁሉ ባሕርያት በሰው ቋንቋ ይነገሩና ይጻፉ እንጂ በልምምድ በሕይወታችን ስናያቸው ግን ፈጽሞ ሰማያዊ ቋንቋ የሚያስፈልጋቸው ሆነው እናገኛቸዋለን። ማንም ሰው በሕይወቱ እነዚህን ባሕርያት ሲላበስና ሲለማመድ በምድራዊ ቋንቋ ለመግለጽ ከቶ እንደሚያስቸግረው ያያል። ምነው? ቢባል ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን ነገር ለመግለጽ ምድራዊ ቋንቋ ውስን ነውና።

እነዚህን ሰማያዊ ጸጋዎች በክርስቶስ ካልሆነ ማንም ሰው በሌላ መንገድ ሊቀበላቸው አይችልም። በኃጢአት የረከሰና የተበከለ የሰው ልብ ያለ ክርስቶስ ደም ሊታጠብና ሊነፃ አይችልም። ባልተቀደሰና ባልነጻ የሰው ልብ ውስጥ ዳግም መንፈስ ቅዱስ ሊገለጽ አይችልም። አንድ ሰው ጌታን አምኖ ሳይቀበል መንፈስ ቅዱስ ሊቀበል አይችልምና።

ከሁለተኛው ደረጃ ወደ ሦስተኛው ደረጃ አንድ ሰው ሲራመድ ወዲያውኑ በሕይወቱ የሚለማመደው መንፈሳዊ ልምምድ በአጭሩ ይህን ይመስላል። ብዙዎች በሁለተኛ ደረጃ ደርሰው ወደ ሦስተኛ ደረጃ እንዳይራመዱ

የሚያግዳቸው ነገር ምን ይሆን? በሁለተኛ ደረጃ ላይ እንደቆሙ የሚያስቀሯቸው ብዙ የተለያዩ ችግሮች ቢኖሩም ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋና ሦስት የሆኑ ነገሮችን ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን።

ሰዎች የወንጌልን ትክክለኛ መልእክት በሚረዱበት ጊዜ ከሁለተኛ ደረጃ ወደ ሦስተኛ ደረጃ በመምጣት ጌታን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው በመቀበል ዳግም ተወልደው የዘላለም ሕይወት በማግኘት እውነተኛ ክርስቲያን ሊሆኑ ይችላሉ። በስም ክርስቲያን ተብሎ ከመጠራት ወደ እውነተኛ የክርስትና ሕይወት የሚመጡት በዚህ ሁኔታ ነው። አንዳንዶች ደግሞ ትክክለኛውን የወንጌል ቃል ቢሰሙም እዚያው ሊቀሩ ይችላሉ። በሁለተኛ ደረጃ ላይ እንዳሉ ወደ ሦስተኛ ደረጃ እንዳይራመዱ ከሚያግዷቸው ሁኔታዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ሦስቱ ናቸው።

## 1ኛ. ሰዎችን መፍራት:-

ብዙ ሰዎች እውነቱ ቢገባቸውም "ሰው ምን ይለኛል" በማለት ለጊዜያዊ ስምና ክብር የዘላለም ሕይወትን ይጥላሉ፣ ይህን ማድረግ ከእግዚብሔር ከሚገኘው ክብር ይልቅ ከሰው የሚገኘውን ክብር መምረጥ ነው። ለዚህ ጥሩ ማስረጃ የሚሆነን በዮሐንስ ወንጌል 12:42 ላይ የተጠቀሰው ቃል ነው። "ከዚህ ጋር ከአለቆች ደግሞ ብዙዎች በእርሱ አመኑ። ነገር ግን ከምኩራብ እንዳያወጧቸው በፈሪሳውያን ምክንያት አልመሰከሩለትም ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ የሰውን ክብር ወደዋልና" ይላል።
እነዚህ የሕዝብ አለቆች ኢየሱስ ሲያስተምር፣ ድንቅና ተዓምራትን ሲያደርግ ቢያዩም ነቢያት የተናገሩለት መሲሕ እርሱ ነው ብለው አመኑ። ነገር ግን በእርሱም ምክንያት መነቀፍን ስላልፈለጉ ሊከተሉት አልወደዱም። ከእግዚአብሔር ከሚገኝ ክብር ይልቅ ከሰው የሚገኘውን ክብር መርጠዋልና።

ይህን የሚመስል የንጉሥ አግሪጳ ታሪክ አለ። ሐዋርያው ጳውሎስ በወንጌል ምክንያት ታስሮ በንጉሥ ፊንጦስና በንጉሥ አግሪጳ ፊት ሲቀርብ ከሳሾቹ እግዚአብሔርን እናገለግላለን የሚሉ ካህናት ነበሩ (ሐዋ.25:13-15)። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ እራሱ እንዲናገር በተፈቀደለት ጊዜ እርሱም ኢየሱስ ማን እንደሆነ፣ እርሱንም እንዴት እንደጠራው ሲመሰክር ንጉሥ ፊንጦስ በታላቅ ድምጽ "ጳውሎስ አብደሃል እኮ" አለው ጳውሎስ ግን ትክክለኛውን ነገር ተናገርኩ እንጂ አላበድኩም፤ ንጉሥ አግሪጳ ይህ ነገር

እውነት መሆኑን ያውቃል አለና ወደ ንጉሥ አግሪጳ ዞወር ብሎ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ ነቢያትን ታምን የለምን እንደምታምናቸው አውቃለሁ አለው። ንጉሡ አግሪጳ ምንም እንኳን ሮማዊ ቢሆንም በእግዚአብሔር ቃል እንደሚያምን ጳውሎስ ያውቅ ነበር። ምናልባት ንጉሥ አግሪጳ ክርስቲያን መሆን ብቻ ነው የቀረው እውነቱን ተረድቷል። ክርስቲያን መሆን ባይጠላም ክርስቲያን ቢሆን የሚደርስበትን ነገር ያውቃል። በዘመኑ ክርስቲያን ተብሎ መጠራት በአሁኑ ጊዜ ጴንጤ ተብሎ እንደመጠራት ያህል ነው። ስለዚህ ጳውሎስን በጥቂት ክርስቲያን ልታደርገኝ ትወዳለህን? አለው። ጳውሎስም "በጥቂት ቢሆንም ወይም በብዙ አንተ ብቻ አይደለህም ነገር ግን ዛሬ የሚሰሙኝ ሁሉ ደግሞ ከእዚህ እስራት በቀር እንደ እኔ ይሆኑ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር እለምናለሁ" አለው። ዛሬም ብዙ ሰዎች እውነቱን ቢረዱም ነቀፋን በመፍራት ጌታን መከተል አይፈልጉም፤ ስማቸው የሚጠፋ ክብርና ዝናቸው የሚነካ ይመስላቸዋልና። "ሰው ዓለሙን ሁሉ አትርፎ ራሱን ቢያጠፋ ወይም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል? በእኔና በቃሉ የሚያፍር ሁሉ፣ የሰው ልጅ በክብሩ በአባቱና በቅዱሳን መላእክቱ ክብርም ሲመጣ በእርሱ ያፍርበታል።" ብሎ ጌታ ተናግሯል (ሉቃ.9:25-26)።

ክብርና ዝናን የሚወድ ሰው የአሁኑን እንጂ የሩቁን አያይም። በዚህ ዓለም ያለው ነገር ጊዜያዊ ነው። የዚህ ዓለም ጊዜያዊ ነገር ሰውን ሲገዛው ማየት እጅግ ያሳዝናል። "ሥጋ ለባሽ ሁሉ ሣር ነው፣ ክብሩም ሁሉ እንደ ምድረ በዳ አበባ ነው። የእግዚአብሔር እስትንፋስ ይነፍስበታልና ሣሩ ይደርቃል አበባውም ይረግፋል በእውነት ሕዝቡ ሣር ነው" ይላል የእግዚአብሔር ቃል (ኢሳ.40:6)። እነዚህ ለዚህ ዓለም ከንቱ ውዳሴ ብለው ጌታን ያልተቀበሉ የሕዝብ አለቆች ከእግዚአብሔር ተለይተው በዘላለም ጉስቁልና ይኖራሉ። ዛሬም ቢሆን እውነት እየገባቸው ለዚህ ዓለም አላፊና ጊዜያዊ ክብር ብለው ጌታን የማይቀበሉ ጸጸታቸው ምን ያህል የከፋ ይሆን!!

### 2ኛ. ለሥጋ ፈቃድ መገዛት:-

በሁለተኛ ደረጃ ላይ ሆነው ወደ ሦስተኛ ደረጃ እንዳይመጡ የሚከለክላቸው ሁለተኛ ምክንያት ዓለምን መውደድ ነው። በዓለማዊ ስያሜ የተያዘ ሰው ጌታ ኢየሱስ አዳኝ መሆኑን ቢረዳም ወስኖ ጌታን መከተል ይቸገራል። ክርስቶስን መቀበል ነፃነትን የሚያሳጣ ይመስለዋል። ክርስቶስ በነፃነት እንድንኖር ነፃ አወጣን እንጂ ነፃነት አያሳጣንም፤ እነዚህ የነፃነት ትርጉም የጠፋባቸው ናቸው (ገላ.5:1)። ነፃነት ማለት ያለግዳጅ

መሆን ወይም የፈለግነውን ማድረግ መቻል ነው። በወንጌል የምናገኘው ነፃነት ያለግዳጅ እንድንኖር ያስችለናል።

ዓለምን ወደው ኃጢአትን የሚያደርጉ ሁሉ እውነተኛውን ነፃነት አግኝተው አይደለም። ኃጢአትን የሚያደርጉ ሁሉ ወደው አይደለም፤ የኃጢአት ኃይል ስለሚገዛቸው እየጠሉት እንኳን ያደርጉታል። መልካም ለማድረግ ፈቃደኛ ቢሆኑም መልካም ማድረግ ስለማይችሉ የሚጠሉትን ኃጢአት ይፈጽማሉ። የሚያስገድዳቸው በውስጣቸው ያለው የኃጢአት ኃይል ነው። ከግዳጅ ወጥተው ነፃነት በማግኘት ለመኖር ቢፈልጉም የሚቻላቸው አይመስላቸውም። ስለዚህ ለተሸነፉበት ለዚያ ባሪያ ሆነው መኖርን ይመርጣሉ። ነፃ መውጣት ቢያምራቸውም በራሳቸው ነፃ መውጣት እንደማይችሉ ስለሚያውቁ ምናልባት አሁን ላሸነፋቸው ኃጢአት ተገዝተው በሽምግልናቸው ጊዜ ነፃ ሊሆኑ የሚችሉ ይመስላቸውና ያን ጊዜ ሃይማኖተኛ እሆናለሁ ብለው ያስባሉ። ስለዚህ አሁን እንደ ልባቸው መሆንን ይመርጣሉ። ሃይማኖተኛ መሆን የሚቻለው ስሜት ሲዝል፣ ሲሸመግል ይመስላቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንዲህ ይላል "አንተ ጎበዝ፥ በጉብዝናህ ደስ ይበልህ፥ በጉብዝናህም ወራት ልብህን ደስ ይበለው በልብህም መንገድ ዓይኖችህም በሚያዩት ሂድ፤ ዳሩ ግን ስለዚህ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ወደ ፍርድ እንዲያመጣህ እወቅ" (መክ.11:9)። ሰው በልቡ የተመኘውን አድርጎ ቢጸጸተውም ለጊዜው ደስ ይለው ይሆናል። ሰው ጌታን ለመከተል ሲያስብ ደስ ያሰኘውን ሁሉ እንዳያደርግ ነፃነት የሚያጣ ስለሚመስለው ደስ ያሰኘውን ለማድረግ በመምረጥ ክርስቶስን በኋለኛ ዘመኑ ለመከተል ሲያስብም ሟች መሆኑን በመዘንጋት ነው።

የሥጋ ፈቃድ መፈጸም ለጊዜው ደስታ አለው፤ ይሁን እንጂ በማግሥቱ ብርቱ ጸጸትን ያስከትላል። በጌታ የሚገኘው ሰላምና ደስታ ግን በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም የማያቋርጥ ነው። በሥጋ ስንሆንና በእግዚአብሔር መንፈስ ስንሆን ያለውን ልዩነት በማነጻጸር ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሎ ጽፏል:- "የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኩሰት፥ መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኝነት፥ መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም" ይልና ". . . የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣

ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው" ይላል (ገላ.5:19-22)።

በሥጋ የዘሩት ኋላ ይከተላልና ከዘላለም ፍርድ ማምለጥ አይቻልም። ክርስቶስ ከዚህ ሁሉ ነፃ ሊያወጣን መጣ። በሥጋችን ያለውን የኃጢአት ኃይል ማሸነፍ አንችልም። ክርስቶስ ከእኛ ጋር ሲኖር ግን የጽድቅ ፍሬ ይሞላብናል። የኃጢአት ኃይል ሲሸነፍ፣ የቀድሞ ሕይወት ይለወጥና አዲስ ፍጥረት እንሆናለን።

ክርስቶስን መከተል በሃይማኖት ሕግ መታሰር የሚመስላቸው ብዙዎች ናቸው። ክርስቶስ ግን ከሕግ እሥራትና ከኃጢአት ኃይል ነፃ ሊያወጣን መጣ። ሕግን ሊሰጠን ከሆነማ የብሉይ ኪዳን መቼ አነሰ! "ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና ጸጋና እውነት በክርስቶስ ሆነ" (ዮሐ.1:17)።

ሕግን በመፈጸም ማንም ሰው እንደማይጸድቅ እግዚአብሔር ስላወቀ ጸጋን እናገኝ ዘንድ ክርስቶስን ላከው (ገላ.2:16)። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው በክርስቶስ ኢየሱስ ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ቅዱስ ከኃጢአት ሕግና ከሞት ነፃ ያወጣልና (ሮሜ.8:1-2)። እንደዚሁም "ኃጢአት አይገዛችሁምና ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና" ይላል (ሮሜ.6:14)።

"ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁም" ሲል ከሕግ በታች አይደለንም፣ ያሰኘንን ነገር ሁሉ ለመፈጸም ተፈቅዷል ማለት አይደለም። ለዚህ የሚሆነን የውርንጫዋ ታሪክ ነው። ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ተቀምጦባት የነበረችው ውርንጫ ታስራ የነበረው ለምንድን ነው? እንዳትጠፋ ለአውሬ መብል እንዳትሆን ወይም በአካባቢው ያለው ሰብል እንዳይጠፋ ነው። በጌታ ስትመረጥ ግን ከእስራቷ ተፈታች፤ የራሱ የክብር መቀመጫ ስለሆነችም ክርስቶስ መራት። ወደ ገመዷ ትመለስ ይሆን? ያን ገመድ ለጊዜው በሕግ እንመስለው፥ ክርስቶስ የሌለው ሰው እንዲሁ በሕግ የታሰረ ነው። ሕግ ለአመጸኞች እንጂ ለጻድቃን እንዳልተሰራ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል (1ጢሞ.1:8-11)።

የአህያ ውርንጫ አውቃ ወደ ጋጣዋ በጊዜው የምትገባ ከሆነ መታሰር አያስፈልጋትም። በክርስቶስ ስንሆን በተመሳሳይ ሁኔታ በጸጋ የምንቀበለው መንፈስ ቅዱስ እንደ እግዚአብሔር ኃሳብ እንድንኖር ይመራናል፣

ያግዘናል (ዮሐ.16:13)። "በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና" ይላል የእግዚአብሔር ቃል (ሮሜ.8:14) እንደዚሁም "የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ሰው የእርሱ ወገን አይደለም" ይላል (ሮሜ.8:9)። ስለዚህ ክርስቶስ በእኛ በሚኖርበት ጊዜ ሕግ ከሚለው በላይ መኖር ያስችለናል። ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁም ማለት ይህ ነው።

ለምሳሌ የብሉይ ኪዳን ሕግ "ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ" ይላል (ዘሌ.19:18)። ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ትእዛዝ "እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ እንደ ወደድኳችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ" የሚል ነው (ዮሐ.13:34)። ክርስቶስ እንዴት ነው የወደደን? ብንል ነፍሱን አሳልፎ እስኪሰጥ ድረስ ወዶናል (ዮሐ.15:13)። ዮሐንስ ደግሞ "እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቷልና፤ በዚህ ፍቅርን አውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል" ይላል (1ዮሐ.3:16)።

እንግዲህ ከብሉይ ኪዳን ሕግና ከጌታ ትእዛዝ የትኛው የከበደ ነው? ያለጥርጥር ጌታ የሰጠው ትእዛዝ ከባድ ነው። ታዲያ የብሉይ ኪዳን ሰዎች ሊፈጽሙ ያልቻሉትን ትእዛዝ እኛ የበለጠውን ትእዛዝ እንዴት ልንፈጽመው እንችላለን? ነገሩ እንደዚህ ነው፡- የብሉይ ኪዳን ሰዎች የተሰጣቸው የተጻፈ ሕግ ነው፤ ሕጉ ደግሞ መፈጸም ያለባቸውን ይነግራቸዋል እንጂ የሚረዳቸው አይደለም፤ ለእኛ ግን የተሰጠን ጸጋ ነው፤ ክርስቶስ እኛን እንደወደደን እርስ በርሳችን እንድንዋደድ በመንፈስ ቅዱስ ፍቅርን ሰጠን። ያ የተሰጠን ፍቅር በጸጋ ነው። ስለዚህ ሳንቸገር እርስ በርሳችን ለመዋደድ እንችላለን። ስለዚህ ነገር በዝርዝር ወደ ፊት እናየዋለን፤ አሁን ግን ጌታን መከተል እሥራት ለሚመስላቸው ሰዎች የክርስትናን ሕይወት የምንኖረው በሚሰጠን ጸጋ እንደሆነ ለማመልከት ምሳሌ መጠቀሚ ነው።

ስለዚህ ወዳጄ ሆይ ክርስቶስን ያልተቀበልክ ከሆንክ እርሱን መከተል የሃይማኖት እሥረኛ ያደርገኛል ብለህ አታስብ፤ ክርስቶስ ከእሥራት ይፈታሃል እንጂ አያስርህም። "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔ አሳርፋችኋለሁ" ይላል ጌታ (ማቴ.11:28)። ክርስቶስን ብትቀበል ከአመድ ፈንታ አክሊልን፣ በልቅሶ ፈንታ የደስታን ዘይት፣ በሃዘን ፈንታ የምስጋናን መጎናጸፊያ ትለብሳለህ፤ በጨለማ ፈንታ ብርሃን

ይበራልሃል (ኢሳ.61:3፤ ዮሐ.8:12፤ 12:44) የቱን ትመርጣለህ? ከአክሊል ይልቅ አመድን፤ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን፤ ከደስታ ዘይት ይልቅ ለቅሶን፤ ከምስጋና መጎናጸፊያ ይልቅ ኃዘንን መልበስ ትፈልጋለህን? ዓለምን ብትመርጥ ዓለም የምትሰጥህ ይህንን ነው። አንተ ግን ንቃ ፍጠን ወደ ክርስቶስ ዛሬውኑ ና፤ እርሱም ያበራልሃል። አንተም በወንዝ ዳር እንደተተከለች ፍሬዋንም በየጊዜው እንደምትሰጥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ትሆናለህ፤ የምትሠራው ሁሉ ይከናወንልሃል" (መዝ.1:3፤ ኤር.17:7-8)።

## 3ኛ. በክርስቶስ ብቻ ሳይሆን በሌሎች መንገዶችም ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይቻላሉ ብሎ ማመን:-

ብዙ ሰዎች በሁለተኛ ደረጃ ላይ እንዳሉ የሚቀሩበት ሦስተኛ ምክንያት ወደ እግዚአብሔር መምጫው መንገድ ክርስቶስ ብቻ ሳይሆን ጻድቃን፤ ሰማዕታትና ቅዱሳን መላእክትም ያቀርቡናል ብለው በማመናቸው ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ግን "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም" ብሏል (ዮሐ.14:6)። ለራስ ምታት ብዙ ፍቱን መድኃኒት ማማረጥ ይቻላል፤ ለምሳሌ አስፕሪን፤ ካፌኖል፤ ፓናዶል፤ አልጎን የመረጥነውን ወይም በቅርባችን የምናገኘውን መውሰድ እንችላለን። አንዱ ካላሻለን ሌላውን መቀየር እንችላለን። ለነፍሳችን ደኅንነት ግን አማራጭ የለንም፤ ያለን ምርጫ አንድ ነው፤ እርሱም ሰው የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ጻድቃንና መላእክት ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርቡን የማይችሉ ከሆነ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ ማለት ነው፤ ደግሞ ቅዱሳን መላእክት ጻድቃንና ሰማዕታት ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርቡን የሚችሉ ከሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ከእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም ለምን አለ? እንግዲህስ ክርስቶስ ዋሽቶናል ማለት ነውን? ወይም ይህን የሚያስተምሩን ተሳስተዋልን? በዚህ ነገር ከሁለት አንዳቸው ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ ብለን እንኳ ልናስብ አይገባንም። ምክንያቱም ጌታችንን ከሰዎች ጋር ማነጻጸር ይሆናልና፤ ነገር ግን ሰው ሁሉ ሃሰተኛ ቢሆን እግዚአብሔር እውነተኛ ነው ተብሎ ተጽፏል (ሮሜ.3:4)።

ስለ ቅዱሳን ሰዎች ከሆነ ደግሞ ከሞቱ በኋላ በሕይወት ለሚኖሩት ሰዎች ሊማልዱም ሆነ ሊያገለግሉ እንደማይችሉ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በግልጽ ተጽፎ እናገኛለን። በእርግጥ በሥጋ ያሉ ቅዱሳን በሥጋ ላሉ ለሌሎች ወገኖቻቸው ሊጸልዩና ሊማልዱ ይችላሉ(ዮሐ.5:16፤

2ቆሮ.5:18-20፤ ሮሜ.8:26-27)። ነገር ግን ሙታን ለሕያዋን ሊማልዱ ይችላሉ ማለት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር መጋጨት ይሆናል። በሕይወት ሳሉ የክህነት አገልግሎት የነበራቸው እንኳ ከሞቱ በኋላ ይህ አገልግሎታቸው አይሠራም። የብሉይ ኪዳን ካህናት አንዱ አገልግሎታቸው ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ ነበር። ከሞቱ በኋላ ግን ይህ አገልግሎታቸው ይቋረጣል። አሁን ግን በአዲስ ኪዳን ክህነቱ የማይለወጥ ለዘላለም የሚኖር ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ አለን፤ እርሱም እግዚአብሔር የላከው ስለሆነ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ያድናቸዋል። "እነርሱ እንዳይኖሩ ሞት ስለከለከላቸው ካህናት የሆኑ ብዙ ናቸው። እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ፥ የማይለወጥ ክህነት አለው። ስለ እነርሱ (ስለ ሰዎች) ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና፤ ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል" ይላል (ዕብ.7:23-25)።

ቅዱሳን ሰዎች ከሞቱ በኋላ በሥጋ ላሉ የሚማልዱ ቢሆን ኖሮ የክርስቶስ ክህነት ባላስፈለገ ነበር፤ እነርሱም ከሞቱ በኋላ አገልግሎታቸውን መቀጠል በተቻላቸው ነበር። ነገር ግን እኛ በአጸደ-ሥጋ ያለነው በአጸደ-ነፍስ ያሉት እንዴት እንደሚኖሩ እንደማናውቅ ሁሉ እግዚአብሔር ፈቅዶና ወዶ ካልገለጸላቸው በስተቀር እነርሱም በራሳቸው ብቃት በሥጋ ስላለን ሰዎች ሁኔታ ምንም የሚያውቁት ነገር የለም፤ በዘመናት ውስጥ በምድር የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ የሚያውቁ ከሆነ እንደ እግዚአብሔር ሆኑ ማለት ነው። በምድር ላይ ያሉትን ሰዎች ሁሉ የማያውቁ ከሆነ ደግሞ አማልዱን ብለው የሚማጸኑአቸው ሰዎች በከንቱ ደከመዋል ማለት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ደም ሳይፈስ ሥርየት የለም ይላል (ዕብ.9:22)። የለም ማለት የለም ነው፤ ታዲያ ከመላእክት ለሰው ልጆች ደህንነት ደማቸውን ያፈሰሱ እነማን ናቸው? የእግዚአብሔር ቃል ያለ ደም ሥርየት የለም ካለ መላእክት ወይም ጻድቃን ሰማዕታት የማንን ደም ይዘው ነው የኃጢአት ሥርየት የሚያስገኙልን? ወይስ ፍጹምና ጻድቅ የሆነውን አምላክ ቃሉን ማስቀየር ይችላሉን? ነገር ግን ክርስቶስ በደሙ የኃጢአት ሥርየት እናገኝ ዘንድ በመስቀል ላይ ደሙን አፈሰሰ። የኃጢአት ስርየት አግኝተን የዘላለም ሕይወት ለመቀበል ብንፈልግ ያለን አማራጭ ይህ ብቻ ነው። ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርበን ሌላ አቋራጭ መንገድ የለም። ይህንን አንቀበልም ብንል የሚጠብቀን የእግዚአብሔር ፍርድ ነው። ለጌታችንም ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል (2ተሰ.1:8)። ባሳቱን

ሰዎች ላይ ብናመካኝ የሚያሻሽልልን ነገር አይኖርም። ቃሉ ተሰጥቶናልና፣ ቃሉን ባንቀበል የሰዎችን ሥርዓትና ትምህርት ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ አስበልጠን በማየታችን የባሰ ፍርድ ይጠብቀናል።

ደግሞም ጻድቃን ሰማዕታትና መላእክት ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡን ከሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ መስቀል ላይ መከራን መቀበል ለምን አስፈለገው? እንዲህ ከሆነ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ ማለት ነው። ስለ መላእክትም ብናስብ እንደዚሁ ነው። መላእክት ሊድኑ ስላላቸው ሰዎች ለማገዝ ከእግዚአብሔር የሚላኩ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ናቸው (ዕብ.1:14)። ሌላው ቀርቶ እግዚአብሔር ካልላካቸው በስተቀር ጸሎታችንን ሰምተው በራሳቸው ፈቃድ ሊያግዙንና ሊረዱን ወደ እኛ ሊመጡ አይችሉም።

መላእክት እንዲያውም በበቀል የተሞሉ ናቸው፣ ኃጢአተኞችን መበቀል እንጂ ስለ ኃጢአተኞች መማለድ አይችሉም። ለምሳሌ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ "ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ፣ መላእክቶቻቸው በሰማያት ዘወትር ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ እላችኋለሁ" አለ (ማቴ.18:10)። ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ ሲጠቃ መላእክቶቻቸው የእግዚአብሔርን ፊት የሚያዩት ለምንድ ነው? መልሱ አጭር ነው፣ የእርሱ ከሆኑት ቅዱሳን አንዱ ሲጠቃ ሲያዩ ለመበቀል እግዚአብሔርን ፈቃድ መጠየቃቸው ነው እንጂ ምህረት ለመለመን አይደለም። ያማልዱናል ብለው የሚያምኑትን እንኳን ሳይቀር በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያመጹትን ለመቅጣት እግዚአብሔር ወደ እዚህ ዓለም እነርሱን የሚልክበት ጊዜ አለ። እግዚአብሔር በፍርድ ቀን አመጸኞችን ለመበቀል ወደዚህ ዓለም የሚልካቸው መላእክትን ነው። "በዓለም መጨረሻ እንዲህ ይሆናል። መላእክት መጥተው ኃጢአተኞችን ከጻድቃን መካከል ይለዩአቸዋል፣ ወደ እቶን እሳትም ይጥሏቸዋል ከዚያም ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል" (ማቴ.13:49)።

በተጨማሪም "ስለሚያስቷችሁ ሰዎች ይህን ጽፌላችኋለሁ። እናንተስ በእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል። ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፣ ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንዲያስተምራችሁ እውነተኛም እንደሆነ ውሸትም እንዳልሆነ እናንተም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ" ይላል (ዮሐ.2:26-27)።

እንግዲህ ይህን ስለማንው የሚናገረው? በመላእክትና በጻድቃን ሰማዕታት ስለሚታመኑ ነው? አይደለም በኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚታመኑት ነው እንጂ "ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በሚታመን ሁሉ እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራል" ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ (1ዮሐ.2:15)።

እግዚአብሔር በእኔ መኖሩን አላውቅም የሚል ሰው ቢኖር ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ያልታረቀ ሊሆን ይችላል። በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የማይታመን ገና በኃጢአት አለ ማለት ነው። ስለሆነም እግዚአብሔር ባልታቀደስ ሕይወት ውስጥ አይገለጽምና እግዚአብሔር በእርሱ ሊኖርበት አይችልም።

ሐዋርያው ጳውሎስ "ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን" ይላል (ገላ.1:8)። ሐዋርያት የሰበኩት ወንጌል ምን ዓይነት ነው? በመጀመሪያ "ወንጌል" የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? ብንል:- ወንጌል ማለት የምሥራች ማለት ነው። ይህ የምሥራች ምንድን ነው? ይህ የምሥራች ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት ከድንግል ማርያም ስለመወለዱ፣ ለዓለም ሁሉ ኃጢአት በቀራኒዮ መስቀል ላይ ደሙን ማፍሰሱ፣ መሞቱና በሦስተኛው ቀን መነሳቱን በእርሱ የሚያምን ሁሉ የኃጢአት ሥርየት ማግኘት መቻሉን ማብሰር ነው። ስለዚህ ኃጢአተኞችን ለማዳን ወደዚህ ዓለም የመጣውን ኢየሱስ ክርስቶስን ትቶ የተለየ ወንጌል የሚሰብክ ሐዋርያው ጳውሎስ "የተረገመ ይሁን" እንዳለ የተረገመ ይሆናል።

ክርስቶስ ኢየሱስም ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ብሎ በሐዋርያት እጅ የላከው የዘላለም ወንጌል ይህ ነው (ማር.16:5)። ሐዋርያትም ከጌታ ተቀብለው የሰበኩት ወንጌል "መዳን በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለም" ብለው ነው (ሐዋ.4:12)። በተጨማሪም "እናንተ ደግሞ የእውነትን ቃል ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ፣ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ" ይላል (ኤፌ.1:13)። ሐዋርያት ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበሉትና የሰበኩት ወንጌል "ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ ሊቀበሉት የተገባ ነው" የሚል ነው (1ጢሞ.1:15)።

አንዳንዶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ተነስተው ይህን የመዳን ወንጌል ቢያጣምሙና ቢያስተምሩም የዘላለም ፍርድ እንደሚጠብቃቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። "ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ሆነው ይመላለሳሉና ብዙ ጊዜ ስለ እነርሱ አልኋችሁ አሁንም እንኳን እያለቀስኩ እላለሁ። መጨረሻው ጥፋት ነው፤ ሆዳቸው አምላካቸው ነው፤ ክብራቸው በነውራቸው ነው፤ ኃሳባቸው ምድራዊ ነው" ይላል (ፊልጵ.5:18-19)። በሌላ ሥፍራ ደግሞ ". . . እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሰቡ የሚያጠፋ ኑፋቄን አሹልከው ያገባሉ። ብዙዎችም በመዳራታቸው ይከተሏቸዋል በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል። ገንዘብንም በመመኘት በተፈጠረ ነገር ይረቡባችኋል፤ ፍርዳቸው ከጥንት ጀምሮ አይዘገይም ጥፋታቸውም አያንቀላፋም" ይላል (2ጴጥ. 2:1-3)። እንደገናም በሮሜ.1:18 "እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሰማይ ይገለጣልና" ይላል።

ይህ ጥፋት ለእነርሱ ብቻ ሳይሆን ለመዳን የሚያበቃቸውን የእውነት ቃል እየሰሙ የማይቀበሉትንም ይመለከታል። እውነትን አናምንም ብለው በውሸት ቃል የሚደሰቱትን ሁሉ ወደ ፍርድ እንዲያመጣቸው እግዚአብሔር የስህተትን መንፈስ እንደሚልክባቸው በግልጽ ተጽፏል። "ስለዚህ ምክንያት በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፃ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፤ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስህተትን አሠራር ይልክባቸዋል" (2ተሰ.2:11-12)።

ስለዚህ አንባቢ ሆይ! እስቲ ለአንድ አፍታ ቆም ብለህ አስብ፤ ወደ ክርስቶስ ያልመጣህ ከሆነ እንዳትመጣ የያዘህ የቱ ነው? እንደጥላ የሚያልፈው የዚህ ዓለም ክብርና ዝና ነውን? ወይስ የጥቂት ቀን ደስታ ይሆን? ወይስ ከክርስቶስ ሌላ መንገድ አለ ብለህ አስበሃል? ክርስቶስ ሞቶልሃል። ወደ እርሱ ና፤ በክርስቶስ ብትታመንና ኃጢአትህን ብትናዘዝ ኃጢአትህን ሁሉ ይቅር ሊልህ እግዚአብሔር የታመነ አምላክ ነው። ይህን ልታደርግ ብትፈልግ መንፈስ ቅዱስ ያግዝሃል። የማንንም እርዳታ ሳትጠይቅ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር ጸጋ ዙፋን በእምነት ቅረብና ኃጢአትህን ተናዘዝ፤ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአትህ መንጻትህን ሳትጠራጠር በፍጹም ልብህ አምነህ ተቀበል፤ ከዚያም ድምጽህን ከፍ አድርግና እግዚአብሔርን አመስግነው፤ ሸክምህ ቀልሎ ታገኘዋለህ።

## II. ክርስቲያን ለመሆን የሚያበቁን እርምጃዎች

1. በሥጋ ከአይሁድ የተወለደ ሁሉ አይሁዳዊ ነው፤ ከክርስቲያን የተወለደ ሁሉ ክርስቲያን ሊሆን የማይችልበት ምክንያት ምንድን ነው? ከሌሎችም ጋር ተወያይበት።
2. ዓለማዊ ኑሮ እየኖሩ ክርስቲያን ነን ለሚሉ ምን መልስ ትሰጣለህ?
3. እግዚአብሔር ያዘጋጀውን የመዳን መንገድ አለመቀበል ምን ያስከትላል? (ዮሐ.3:36)
4. ከክርስትና ሕይወት ጋር በተያያዘ ሁኔታ በዓለም ያሉትን ሰዎች በአራት ከፍለናቸዋል፤ እነርሱ እነማን ናቸው።
5. እስላሞችና አይሁድ ስለ ክርስቶስ ያላቸው አመለካከት ምንድን ነው?
6. ከክርስቲያን ቤተሰብ ስለተወለዱ ብቻ ክርስቲያን ነን ስለሚሉ ሰዎች ምን ትላለህ? ከሌሎችም ጋር ተወያይበት።
7. ሰው የእግዚአብሔር ፍቅር በሕይወቱ ሳያድር እግዚአብሔር ፍቅር ስለመሆኑ አስተካክሎ ማስተማር የሚችል ይመስልሃልን?
8. ዳግም ለመወለድ የሚያስፈልጉ ሦስት እርምጃዎች ምን ምን ናቸው?
9. ስለ ክርስቶስ ሰምቶ የማያውቅ ሰው በመጀመሪያ የሚያስፈልገው መልእክት ምንድን ነው?
10. ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ክርስቶስ አዳኝነት የሰማ ሰው ምርጫ ምንና ምን ሊሆን ይችላል?
11. አንድ ሰው ስለ ክርስቶስ አዳኝነት በጽንሰ ኃሳብ ደረጃ እውነቱን ተቀብሎ ቢያቆም ይህ ሰው ከተገለጹት ደረጃዎች ስንተኛው ላይ ይሆናል?
12. በሁለተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ወደ ሦስተኛ ደረጃ እንዳይመጡ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ሦስት ሁኔታዎችን ጥቀስ።
13. ስለ ክርስቶስ አዳኝነት ለመጀመሪያ ጊዜ ስትሰማ ቶሎ እርምጃ እንዳትወስድ አንተን ያገደህ ነገር ምን ነበር?
14. ብዙ ሰዎች ዳግም ልደት ሳያገኙ እራሳቸውን እንደ ክርስቲያን ይቆጥራሉ፤ ምክንያቱ ምንድን ነው? ተወያይበት።
15. ክርስቶስ አዳኝ መሆኑን ከማወቅ አልፎ ዳግም ለመወለድና ክርስቲያን ለመሆን የሚያበቃ ምስጢር ምንድን ነው? ተወያይበት።
16. አንድ ሰው ክርስቶስ አዳኝ መሆኑን አውቆ ለራሱ ደህንነት ላይታመንበት ይችላል ብለህ ታስባለህ? ተወያይበት።
17. ብዙ ሰዎች ክርስቶስ ስለ ኃጢአተኞች በመስቀል ላይ ደሙን ማፍሰሱንና በደሙ የኃጢአት ሥርየት እንደሚገኝ እያወቁ የመላእክትንና የፃድቃን ሰማዕታትን አማላጅነት ለምን ይፈልጋሉ? ተወያይበት።
18. ለርኩሰትና ለኃጢአት ባሪያ ሆነው እየኖሩ ለሃይማኖታቸው ስለሚቀኑ ሰዎች ምን ትላለህ?
19. የነቢያትን መቃብር ይሰሩ የነበሩትን አይሁድ ክርስቶስ ለምን ነቀፋቸው?
20. ክርስቲያን ነን እያሉ ወንጌል የሚሰብኩትን የሚያሳድዱ ወገኖች ከአይሁድ ይልቅ የከፋ ነገር እየፈጸሙ ነው ያልንበት ምክንያት ምንድን ነው?

21. ክርስቶስ በሁሉ ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ ብሏል (ማቴ.10:23) ክርስቶስን በመስበካቸው በአሁኑ ዘመን የሚጠፉ ወገኖች አሉ ብለህ ታስባለህ? አሉ ካልህ በምን ይታወቃሉ?
22. አንድ ሰው ክርስቲያን ከመባል አልፎ ክርስቲያን መሆኑ በምን ይታወቃል? (ማቴ.7:17-18) ተወያይበት።
23. አንድ ሰው ንስሐ ገብቶ ክርስቶስን ቤዛና አዳኝ አድርጎ ሲቀበል በሕይወቱ ምን ሊሰማው ይችላል? ከራስህ ሕይወት ጋር በማነጻጸር ግለጽ።
24. ንጉሥ አግሪጳ ክርስቲያን እንዳይሆን ያገደው ነገር ምን ሊሆን ይችላል ብለህ ታስባለህ? (ሐዋ.26:28)
25. ብዙ ወጣቶች ክርስቲያን መሆን ነፃነት ያሳጣል ብለው ያስባሉ፤ ከወንጌል ያልተረዱት ነገር ምንድን ነው? (ገላ.5:1)
እውነተኛውን ነፃነት እንዴት ትገልጸዋለህ? እንዴትስ ሊገኝ ይችላል?
26. በሮሜ.6:14 ላይ "ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና" ሲል ምን ማለቱ ነው?
27. ለራስ ምታት ብዙ አማራጭ መድኃኒት ሊኖር ይችላል፤ ለነፍስ ደህንነት ክርስቶስ ብቻ ነው ያልንበት ምክንያት ምንድን ነው?
28. በጻድቃንና በመላእክት አማላጅነት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ቢቻል ኖሮ ክርስቶስ ከእኔ በስተቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም ማለቱን እንዴት ታየዋለህ?
29. መላእክትና ጻድቃን ከእግዚአብሔር ጋር ሊያማልዱን የሚችሉ ቢሆን ኖሮ የክርስቶስ በመስቀል መሞት ምን ትርጉም ይኖረዋል?
30. የክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት ምስጢሩ ምንድን ነው?
31. መጽሐፍ ቅዱስ ደም ሳይፈስ ሥርየት የለም ይላል (ዕብ.9:22)። በክርስቶስ ደም የኃጢአት ሥርየት ከተገኘ የጻድቃንና የመላእክት አማላጅነት ለምን አስፈለገ?
32. እግዚአብሔር በፍርድ ቀን ወደዚህ ዓለም የሚልካቸው መላእክትን ነው፤ መላእክት ያማልዱናል የሚሉትን ሰዎች የሚያልፏቸው ይመስልሃል? ለምን?

## III. ክርስቲያን ስንሆን በእግዚአብሔር ፊት የምናገኘው ሥፍራ

ክርስቲያን የምንሆነው ንስሀ ገብተን፣ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደግል አዳኛችን አድርገን ስንቀበልና ዳግም ስንወለድ መሆኑን ቀደም ብለን አይተናል። በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ከቀድሞ የተለየ መልክ ይኖረናል። በእግዚአብሔር ፊት የምናገኘውን ሥፍራ ለማየት የሚያስችሉን መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ የእምነት መመሪያችን ሲሆን መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ስላመነው ቃል ውስጣችን የሚመሰክርልንና ወደ እውነት የሚመራን ነው (ዮሐ.14:25-26, ዮሐ.16:12-15 1ዮሐ.2:20-26)። በእግዚአብሔር ፊት የምናገኘውን አቋም ማወቃችን በፈተናና በችግር ውስጥ ፀንተን ለመቆም ያስችለናል። ስለዚህ ዳግም ስንወለድ በእግዚአብሔር ፊት የምናገኘው አቋም ከዚህ በመቀጠል በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመስርተን ከሕይወታችን ጋር እያመሳከርን እናያለን።

### 1. <u>በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅን መቆም</u>

ከቃሉ ትርጉም ብንነሳ <u>መጽደቅ</u> ማለት ቅዱስና ጻድቅ በሆነ አምላክ ፊት ተቀባይነት ማግኘት ማለት ነው። ኃጢአተኛ የሆነ የሰው ልጅ ፍጹም ጻድቅና ቅዱስ በሆነ አምላክ ፊት እንዴት ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል? ይህን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት ሰውን በእግዚአብሔር ፊት እንዳይቆም ስለሚከለክለው ኃጢአት ግንዛቤ እንዲኖረን ማየት ያስፈልጋል።

ሰው ኃጢአትን በሁለት መንገድ ይለማመዳል፤ አንደኛው መንገድ ኃጢአትንና ድካምን ከአዳም በመውረስ ነው። "ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንዲሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ" (ሮሜ 5:12)። ሁለተኛው መንገድ ሰው ከተወለደ ጀምሮ ዝንባሌው ሁሉ ክፉ ማድረግ ስለሆነ ኃጢአትን በልምምድ ያገኘዋል። "የሰው ልብ ኃሳብ ከታናሽነቱ ጀምሮ ክፉ ነውና፤" (ዘፍ.8:21) ስለዚህ ልዩነት ሳይኖር የአዳም ዘር ሁሉ ኃጢአተኛ ነው፤ የኃጢአት ደመወዝ ደግሞ ሞት ነው። ስለዚህ ማንም ሰው ከኃጢአት ነፃ ነኝ ብሎ ራሱን ገለልተኛ ማድረግ አይችልም (ሮሜ.6:23)፤ ስለሆነም የሰውን ልጅ ሁሉ የእግዚአብሔር ቁጣ ይጠብቀዋል።

ከእግዚአብሔር ቁጣ ድነን የዘላለምን ሕይወት እንዲያው እናገኝ ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ላከልን፤ ምንም እንኳን ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ብንሆን እግዚአብሔር ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሳ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሁሉ ይጸድቅ ዘንድ ክርስቶስን ቤዛ አድርጎ ሰጠን። ስለዚህ ከእርሱ የተነሳ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን እናገኛለን ማለት ነው።

ይህ ሲሆን ሁለት ነገሮች እንድናስብ ያስፈልጋል፤ አንደኛ ሰው ከእግዚአብሔር ቁጣ የዳነው እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በእኛ ቦታ በመቅጣቱ እንደሆነ ልናውቅ ይገባናል። እግዚአብሔር ጻድቅ ነው ስንል ፍርዱ ትክክል እንደሆነ ያመለክታል። ኃጢአተኛን ያለ ቅጣት አይተውም፣ ትእዛዙን ለሚጠብቁ ዋጋን ይከፍላል። ስለዚህ ኃጢአተኛን ባይቀጣ ወይም ትእዛዙን ለጠበቀ ዋጋ ባይከፍል የእግዚአብሔር ጽድቅ ይዛነፋል። ስለዚህ እኛ ልንቀበለው የነበረውን ቅጣት ክርስቶስ ተቀብሎ እኛ ነጻ ወጣን፤ በሮሜ 5:18 ላይ "ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና" (ኤፌ.4:32) ይላል። ስለሆነም እግዚአብሔር ስለ ክርስቶስ ሲል ይቅር አለን።

ይህንን ሁኔታ ግልጽ የሚያደርግልን አጭር ታሪክ እንመልከት፡- በአንድ አገር ይኖር የነበረ ቅንና የማያዳላ ዳኛ ነበር፤ ከዕለታት አንድ ቀን ልጁ ወንጀል ሠራና ፍርድ ይቀበል ዘንድ የራሱ አባት ወደሚፈርድበት ፍርድ ቤት ተወሰደ፤ ዳኛውም ወንጀሉን የሰራው የራሱ ልጅ እንደሆነ ከመረመረ በኋላ እንደ ሕጉ መሠረት የሞት ፍርድ ይፈርድበታል በማለት የፍርዱን ሃተታ አዘጋጀ። ከዚያም በሕዝብ ፊት ቆሞ የፍርዱን ቃል ካነበበ በኋላ የዚህ ወንጀለኛ ልጅ አባት እኔ ስለሆንኩ በልጄ ፈንታ የወንጀሉን ቅጣት እኔ እቀበላለሁ፣ ወንጀለኛ የሆነው ልጄም ነፃ ይወጣል ብሎ በልጁ ፈንታ ሞተ።

ክርስቶስም እንዲሁ ነው ያደረገው፤ በኃጢአታችን ምክንያት ሊፈረድብን የሚገባንን እኛን ነፃ ለማውጣት ሲል ስለ ኃጢአታችን ሞተ። "ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ አመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና" (1ጴጥ.3:18)፤ ስለሆነም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሁሉ አይፈረድበትም፤ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምን አሁንም ቢሆን የእግዚአብሔር ቁጣ ይጠብቀዋል (ዮሐ.3:36)። ከዚህ በኋላ ሰዎች የሚፈረድባቸው

በኃጢአታቸው ምክንያት ሳይሆን የእግዚአብሔርን ምህረት ባለመቀበላቸው እንደሆነ ከዚህ በታች ያለው ታሪክ ጥሩ ምሳሌ ይሆነናል።

በአንድ ቀበሌ የሚኖር ጥሩ ምግባር ያለው ወጣት ልጅ ነበር፤ በአንድ ወቅት ከጓደኛው ጋር ሲጫወት በድንገት ጓደኛውን ገደለው። በዚህ ምክንያት ፍርድ ቤት ቀርቦ የሞት ፍርድ በስቅላት እንዲቀጣ ተፈረደበት። የአካባቢው ሕዝብ ይህን ወጣት በጥሩ ምግባሩ ያውቁት ስለ ነበር ለአገረ-ገዢው ይህ ወጣት ልጅ ምህረት እንዲያገኝ በየአቅጣጫው ደብዳቤ ጻፉለት፤ የአገረ ገዥውም ጠረጴዛ በደብዳቤ ተሞልቶ ነበር። በዚህ ምክንያት አገረ ገዥው ለዚህ ወጣት ልጅ ምህረት ሊያደርግለት ወደ የምህረት ደብዳቤ ጻፈና ወደ ወህኒ ቤት ሄደ። አገረ ገዥውም ወህኒ ቤት ሲሄድ የቄስ ልብስ ለብሶ ነበር የሄደው፤ እንደደረሰም ይህን ወጣት ልጅ ለማነጋገር ዘበኛውን ላከበት፤ ወጣቱ ልጅ ግን አገረ ገዥውን ሲያየው ቄስ መሰለውና ሊያነጋግረው አልፈቀደም። አገረ ገዥውም የሚጠቅምህን ነገር ይዤ መጥቻለሁና አንድ ጊዜ አነጋግረኝ ይለዋል፤ ደጋግሞ ቢልክበት ወጣቱ ልጅ እኔ ሃይማኖቴን እቤት ትቻለሁ ስለዚህ ላነጋግርህ አልፈልግም ይለዋል። በዚህም ምክንያት አገረ ገዥው እያዘነ ተመልሶ ሄደ። ነገር ግን ዘበኛው ወደዚህ ወጣት መጥቶ ዛሬ አገረ ገዥው ሊያነጋግርህ ሲፈልግ ለምን እምቢ አልከው ይለዋል፤ ወጣቱም ልጅ ይደነግጥና አገረ ገዥው ነው እንዴ! አለ፤ ዘበኛውም አዎን አገረ ገዥው እርሱ ነው እንዲያውም የምህረት ደብዳቤ ይዞልህ ነበር የመጣው አለው። ወጣቱም ልጅ በዚህን ጊዜ እጅግ ምርር ብሎ አለቀሰ፤ በኋላም እስክሪብቶና ወረቀት ዘበኛውን ለምኖ ለአገረ ገዥው "ክቡር አገረ ገዥ ሆይ አገረ ገዥ መሆንዎን ባለማወቄ ነውና እባክዎን ምህረት አድርጉልኝ" ብሎ ጻፈ። አገረ ገዥውም ደብዳቤውን ካነበበ በኋላ በስተጀርባው ስለዚህ ጉዳይ ሁለተኛ አይመለከተኝም ብሎ ጽፎ ተወው። ያም ወጣት የሚሰቀልበት ቀን ደረሰና ወደ ስቅላት ቦታ ተወሰደ፤ እንደደረሰ ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ ስለነበር ከመሰቀሉ በፊት ለሕዝቡ እንዲህ አለ፦ "እናንተ ዛሬ የእኔን መሰቀል ለማየት የመጣችሁ ሁሉ ስሙኝ፤ ዛሬ የምሰቀለው በፈጸምኩት ወንጀል አይደለም፤ አገረ ገዥው ምህረት አድርጎልኝ ሳለ ምህረቱን አልቀበል ስላልኩ ነው" አለ።

የእግዚአብሔርን ምህረት የማይቀበሉ ሁሉ የሚፈረድባቸው በተመሳሳይ መንገድ ነው። "በእርሱ የሚያምን አይፈረድበትም በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል (ዮሐ.3:17)።

ስለ መጽደቃችን ስናስብ አንደኛ፦ከእግዚአብሔር ቁጣና ፍርድ መዳናችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ መከራን በመቀበሉ እንደሆነ ልናውቅ ይገባናል። ሁለተኛ ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት አግኝተን በፊቱ መቆም የምንችለው የክርስቶስን ጽድቅ በመልበሳችን እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል። ይህ ባይሆን ኖሮ በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ አንችልም።

ክርስቶስ ወደ እርሱ በመጣን ጊዜ የእርሱን ጽድቅ አልብሶን ወደ አባቱ አቅርቦናል፤ እርሱ ደግሞ የእኛን ኃጢአት ለብሶ በመስቀል ላይ ውሏል። "እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለእኛ ኃጢአት አደረገው" (2ቆሮ.5:21) ይላል። እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ "ክርስቶስን ለብሳችሁታል" ይላል (ገላ.3:27፤ ሮሜ 13:14)። ስለዚህ ሁላችን ወደ እግዚአብሔር መቅረብና በፊቱ መቆም የቻልነው በክርስቶስ ኢየሱስ የጽድቅ ሥራ እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል (ኤፌ.2:18)።

ማንም ሰው በራሱ መልካም ሥራ ጻድቅና ቅዱስ በሆነ በእግዚአብሔር ፊት መቆም እንደማይችል ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል፡- "ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን አውቀን፥ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል" (ገላ.2:16)። በሌላ ሥፍራ ደግሞ ". . . ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ስለማይጸድቅ ነው ይላል (ሮሜ.3:20)።

ስለሆነም አንድ ሰው ጌታን ጽድቄም፤ ቅድስናዬም፤ ቤዛዬም ነው ብሎ ሲታመንበት ቀስ በቀስ ሳይሆን ወዲያውኑ ኃጢአተኛነቱ ይቀርና ከእግዚአብሔር ጋር ታርቆ ጻድቅ ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት መቆም ይችላል። "እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበረና በደላቸውን አይቆጥርባቸውም" (2ቆሮ.5:18)። "በደላቸውን አይቆጥርባቸውም" ሲል ጨርሶ ኃጢአት ሰርተው እንደማያውቁ አድርጎ ያያቸዋል ማለት ነው። በዚህም ምክንያት በዕብ.8:12 ላይ እንደምናየው "ዓመፃቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም ደግሜ አላስብም" ይላል።

ለእኛ ለኃጢአተኞች ከእግዚአብሔር ምህረት የበለጠ የሚያስፈልገን ምን

ሌላ ነገር ሊኖር ይችላል? እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር በማለት ብቻ አላበቃም፤ የልጁን የኢየሱስ ክርስቶስን ጽድቅ አልብሶን በፊቱ ሊያቆመን ወደደ፤ ክብርና ምስጋና ከዘላለም እስከ ዘላለም ለእርሱ ይሁን!!

## 2. <u>የልጅነት ሥልጣን መቀበል</u>

"የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ እንዲሁም ነን" (1ዮሐ.3:1)። የሚያስገርም ነው፤ ኃጢአተኞች የነበርነውን የሰው ልጆች እግዚአብሔር የራሱ ልጆች እንድንሆን ማድረጉ!

"ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑ ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም" (ዮሐ.1:12-13)። ይህ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን የዝምድና ሥፍራ የሚያሳየን ነው። እግዚአብሔር ልጆቹ ያደረገን በሕግ ሳይሆን ከመንፈስ ቅዱስ ዳግም በመወለዳችን ነው።

አንድ ሰው የልጅነት መብት በሁለት መንገድ ሊያገኝ ይችላል፤ አንደኛው መንገድ በሥጋ በመወለድ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ማደጎ (Adopt) ተደርጎ በመወሰድ በሕግ የሚደረግ ልጅነት ነው። በማደጎነት የልጅነት መብት ያገኘ ሰው በእርሱና በአባቱ መካከል በሕግ የተከናወነ የአባትና የልጅ ዝምድና ይፈጠራል። እንደ ሕጉም ማደጎ ተደርጎ የተወሰደው ልጅ ማደጎ አድርጎ በወሰደው ሰው ስም የመጠራትና የወራሽነት መብት ይኖረዋል።

በጥንት ዘመን የግሪኮችን ባህል ስንመለከት አንድ ሰው የሌላውን ልጅ ማደጎ አድርጎ ከወሰደ የዕድሜ ልክ ልጁ ይሆነዋል፤ ማደጎ ያደረገው ሰው ከሞተና ሴት ልጆች ካሉት አንደኛዋን ያገባና ወራሹ ይሆናል። ማደጎ ተደርጎ ከተወሰደ በኋላ ወንድ ልጅ ቢወለድ ግን ኃብቱን እኩል የመውረስ መብት ይኖረዋል።

የጥንት ሮማውያንን ሥርዓት ብንመለከት ደግሞ ሁለት ዓይነት ማደጎ የማድረግ ሕግ አላቸው። አንደኛው ለማደጎነት የተወሰደው ልጅ ጥገኛ ሳይሆን ራሱን ችሎ የሚኖር ነው። በዚህ ዓይነት ማደጎ የተደረገው ልጅ

በሕግ የተደረገ የአባትና የልጅ ዝምድና ቢኖረውም ማደጎ ባደረገው ሰው ስም የመጠራት ግዴታ የለበትም። ሁለተኛው ደግሞ ማደጎ ተደርጎ የተወሰደው ልጅ በቤተሰብ ውስጥ አዲስ ልጅ ሆኖ እንደ ተወለደ ይቆጠራል፤ የሚጠራውም ማደጎ አድርጎ በወሰደው ሰው ስም ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ምሳሌ (Analogy) አድርጎ የተጠቀመው ሁለተኛውን የማደጎ (Adoption) ዓይነት ነው (ሮሜ 8:15-23፤ ኤፌ.1:4)። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ማደጎ (Adopt) አደረገን ሲል በግሪኮቹ ወይም በሮማውያን መንገድ ማለቱ አይደለም። ከእግዚአብሔር መወለዳችንን በሰብአዊ መንገድ ልንወስደውም አይገባም፤ ከእግዚአብሔር ስለ መወለዳችን ስናስብ እጅግ ጥልቀት ያለውና ከአእምሮአችን በላይ ስለሆነ ከተጻፈልን አልፈን እንዳንሄድ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል።

ጌታም ለኒቆዲሞስ ዳግም ልትወለድ ይገባሃል ሲለው ኒቆዲሞስ በሰብአዊ መንገድ መስሎት ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? ብሎ ሲጠይቀው ጌታ በሰጠው መልስ ሰው ዳግም የሚወለደው ከመንፈስ ቅዱስ እንጂ ከሥጋና ከደም አለመሆኑን አስረዳው። ይህንን የመንፈስ ቅዱስ አሰራር ማንም ሰው ሊመረምረውና ሊረዳው ስለማይችል ጌታ ለኒቆዲሞስ በምሳሌ ሲያስረዳው እንመለከታለን። "ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፥ ድምፁንም ትሰማለህ፥ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው" (ዮሐ.3:8) አለው። እውነት ነው ነፋስ መንፈሱን እንጂ ከወዴት እንደመጣና ወዴት እንደሚሄድ ማየት አይቻልም። እንዲሁ አንድ ሰው ዳግም መወለዱን እንጂ እንዴት ዳግም እንደተወለደ ሊያውቅ አይችልም። በእናታችን ማህፀን ተፀንሰን እንደተወለድን በሰብአዊ ሁኔታ ከእግዚአብሔር አልተወለድንም። "እነርሱ ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም" (ዮሐ.1:13) ይላል የእግዚአብሔር ቃል።

የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን በምን እናውቃለን የሚሉ ይኖራሉ። ዳግም በተወለድን ጊዜ ማንም ሳያስተምረን መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር አባታችን መሆኑን በውስጣችን ይነግረናል። "አባ አባት ብለን የምንጮህበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና" (ሮሜ 8:15-16)። እንደገናም በሌላ ሥፍራ እንዲህ ይላል "ልጆችም ስለሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ

የሚጮህ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ" (ገላ.4:6)። ከእግዚአብሔር ቃልና ከእግዚአብሔር መንፈስ የበለጠ እውነቱን የሚያረጋግጥልን የለም። የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችን ሲኖር እናውቃለን፤ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚነግረንን ደግሞ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እናመሳክራለን።

የእግዚአብሔር ልጆች ተብሎ ስለመጠራት ስናስብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን የተጠራን ክርስቲያኖች ብቻ አይደለንም። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ተብሏል (ዮሐ.1:4-18፡ 3:16)፤ መላእክትም የእግዚአብሔር ልጆች ተብለዋል (ኢዮ.1:6፡ 2:1፡ 38:7)፤ እስራኤላውያንም እንዲሁ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለዋል (ሆሴ.2:1፤ ኤር.31:9፡ ኢሳ.63:16)። ዳግም ተወልደን ከእግዚአብሔር የልጅነትን ሥልጣን ከተቀበልነው ከእኛ ጋር ያለው ልዩነት ምንድነው? በእርግጥ ትልቅ ልዩነት አለ፤ መላእክትም ሆኑ እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው የተጠቀሱት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም ጥቂት ሥፍራ ብቻ ነው። ከኢዮብ መጽሐፍ በስተቀር መላእክት በቀጥተኛ አነጋገር የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆኑ የተጠቀሰበት ሥፍራ የለም።

መላእክት የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት በፍጥረት የእግዚአብሔር ስለሆኑና ወላጅ አባት እንደሌላቸው ለመግለጽ ሲሆን፤ በሰማያዊ አገር በእግዚአብሔር ዘንድ ሲኖሩ ያላቸውን ነፃነትና የሚኖሩትን የደስታ ኑሮ ለማሳየት ነው። "ከዕለታት አንድ ቀን እንዲህ ሆነ <u>የአምላክ ልጆች</u> በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም መጡ" (ኢዮ.1:16፤ 2:1)ይላል። በመቀጠልም "የአጥቢያ ኮከቦች በአንድነት ሲዘምሩና የእግዚአብሔርም ልጆች ሁሉ እልል ሲሉ" (ኢዮ.38:7) ይላል። ይህ የሚያሳየው ልጆች በአባታቸው ቤት ነፃና ደስተኞች ሆነው እንደሚኖሩ ሁሉ መላእክትም በእግዚአብሔር ዘንድ ያላቸውን ደስታና ነፃነት በማነጻጸር ለመግለጽ ነው።

ስለ እስራኤላውያን ብንመለከት ደግሞ:- እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ሕዝብ ስለሆኑና የመጀመሪያውን ኪዳን የተቀበሉ በመሆናቸው እግዚአብሔር እንደ አባት ሆኖ እንደሚያዝንላቸው የሚገልጹ ጥቂት ጥቅሶች አሉ። እነርሱም "እናንተ ሕዝቤ አይደላችሁም ተብሎ በተነገረበት በዚያ ሥፍራ የሕያው አምላክ ልጆች ይባላሉ" (ሆሴ.2:1)። በተጨማሪም "አብርሃም ባያውቀን እስራኤል ባይገነዘበን አንተ አባታችን ነህ፤ አቤቱ

አንተ አባታችን ነህ፥ (ኢሳ.63:16) ይላል። ከዚህ በኋላ ሁኔታ ለእስራኤላውያን እግዚአብሔር እንደ አባት ተደርጎ የተጠቀሰበት ቦታ የለም። እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ልጆች መባላቸው ዳግም ተወልደው አይደለም። እንዲያውም እስራኤላውያን እግዚአብሔርን አባታችን ብሎ መጥራትን እግዚአብሔርን እንደመሳደብ ይቆጥሩታል። ጌታ ኢየሱስ እግዚአብሔርን አባቴ በማለቱ እግዚአብሔርን እንደመሳደብ ቆጥረው ሊውግሩት የነበረው በዚሁ ምክንያት ነው (ዮሐ.5:18)።

ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናየው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ ዘላለማዊነት ያለው ነው። እንደ መላእክትም በመፈጠር ወይም እንደ ክርስቲያን ዳግም በመወለድ አይደለም። እርሱ ከዘላለም የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ! ይህንን ማንም ሰው በስሌት ሊደርስበት አይችልም። እግዚአብሔር በክርስቶስ ያመነውን ልጆቹ ከአደረገን በኋላ ልጅ ከአባቱ የሚያገኘውን የልጅነት መብት እንድናገኝ አድርጓል። ልንገነዘበው የሚገባን ነገር ቢኖር የልጅነት መብት አገኘን ስንል የግድ ሊደረግልን የተገባን ሆነን ተገኝተናል ማለት አይደለም። ደኅንነትን ያገኘነው የሚገባን ሆኖ ሳይሆን እግዚአብሔር እንዲሁ በፀጋው የሰጠን ነው። የልጅነት መብትም የተሰጠን በተመሳሳይ ሁኔታ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባናል።

## 3. የኢየሱስ ክርስቶስን መልክ መምሰል

ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመስለው አባቱን በመሆኑ እኛም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን በመምሰላችን እግዚአብሔርን እንደምንመስል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታ ተጽፏል (2ጴጥ.1:6፤ 3:11፤ 1ጢሞ.6:11)። እግዚአብሔርን ወይንም ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰላችን በአኗኗራችን ወይም በሞራል ረገድ ብቻ አይደለም። በአኗኗርና በሞራል ረገድ እግዚአብሔርን መምሰል እንዳለብን ብዙ ቦታ ተጽፎ እናገኛለን (1ጴጥ.1:7፤ 1ጢሞ.4:3)። በዚህ ረገድ ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር መልክ ተፈጥረዋል በያዕ.3:9 ላይና በዘፍ.1:26 ላይ ያሉት ኃሳቦች ተመሳሳይ ናቸው። ዳግም ልደት ያገኘን እኛ ግን ክርስቶስን መምሰል የተሰጠን በተለየ መንገድ ነው። "ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወስኗልና" ይላል (ሮሜ 8:29)።

"የልጁን መልክ እንዲመስሉ" የሚለው አባባል ሰው በፍጥረቱ በእግዚአብሔር መልክ ተፈጥሯል ከሚለው አባባል ፈጽሞ የተለየ ነው። ክርስቶስን መምሰል የምናገኘው ቀድሞ ከነበረን ሁኔታ በመለወጥ ነው እንጂ ካፈጣጠራችን አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ "የፈጠረውን ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል" ይላል (ቆላ.3:10)። ይህ "የፈጠረውን እንዲመስል" የሚለው ስለ ማነው? ብንል ክርስቶስን ማለቱ ነው፤ 'አዲሱን ሰው' ማለት ደግሞ አዲሱን መልካችንን ነው። ስለዚህ 'የፈጠረውን አዲሱን ሰው' ጌታን እንዲመስል ተደርጎ ተፈጥሯል ማለት ነው። እንደገናም በኤፌ.4:24 ". . . እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ" ይላል። ይሁን እንጂ አዲሱ መልካችን ምን እንደሚመስል ወይም ምን ዓይነት እንደሆነ አሁን ባናውቅም አሁን የክርስቶስን መልክ አግኝተናል። አዲስ ሰው ሆነንም ተፈጥረናል (2ቆሮ.5:17)። ቢሆንም የክርስቶስን የከበረ አካል ገና አላየንም፤ አሁን ልናየውም አንችልም፤ ምክንያቱም ይህ የሚጠፋው የማይጠፋውን ማየት ስለማይችል ነው።

ከለበስነው ሥጋችን ተለይተን የማይበሰብሰውን አካል ስንለብስና ወደ ክብር ስንለወጥ ያን ጊዜ የከበረውን ጌታ በማይጠፋ ዐይን ፊት ለፊት ስናየው እርሱን መምሰላችንን እናውቃለን። "የእግዚአብሔር ልጆች ነን፥ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም፤ ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን" (1ዮሐ.3:2)። አዲሱ የውስጥ ሰውነታችን አዲስ የተፈጠረ ሰው ቢሆንም ገና በዚህ ዓለም ስላለን የከበረውን የጌታችንን መልክ መምሰላችንን የምናየው ይህ ድንኳንና ጊዜያዊ መኖሪያ የሆነው ሥጋችን ሲፈርስና ከክብር ወደ ክብር ሲለወጥ ነው (2ቆሮ.5:1-5)። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ሲያረጋግጥልን በ2ቆሮ.3:18 እንዲህ ይላል "እኛ ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደመስታወት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግልን ያን መልክ እንመስል ዘንድ <u>ከክብር ወደ ክብር</u> እንለወጣለን።"

ጌታ ይህን የሚያደርገው አሁን ያለውን ሰውነታችንን በመለወጥና የእርሱን የከበረ ሰውነት እንዲመስል በማድረግ ነው። "እርሱ ሁሉን እንኳ ለራሱ ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሰራር ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል" "ክቡር ሥጋውን" የሚለውን ቃል የ1980 ዓ.ም. ትርጉም እንደሚከተለው ያቀርበዋል፡-"እርሱ ይህንን የተዋረደ ሰውነታችንን በመለወጥ የእርሱን ክቡር ሰውነት እንዲመስል

ያደርገዋል" ይላል (ፊልጵ.3:21)። በተጨማሪ ሌሎች የእንግሊዝኛ ትርጎሞችን ማየት ጥሩ ግንዛቤ ይሰጣል።

ይህን የከበረ ሰውነት ለመልበስ የማይናፍቅ ክርስቲያን የለም፤ ተስፋ የሰጠን የታመነ ስለሆነ እኛም ታምነን ከጠበቅነው አሁን የለበስነው ሟች ሥጋችን ተለውጦ የማይሞትና የማይበሰብስን መንፈሳዊ ሰውነት አልብሶን ይወስደናል (1ቆሮ.15:51-54)። ክብርና ምሥጋና ከዘላለም እስከ ዘላለም ለስሙ ይሁን።

## 4. <u>የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ መሆን</u>

"ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ . . . ሰጠን" (2ጴጥ.1:4)።
የመለኮት ባሕርይ የእግዚአብሔር፣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስና የመንፈስ ቅዱስ መለያ ባሕርይ ነው። ይህ ሲባል የተለያየ ሦስት መለኮታዊ ባሕርይ አለ ማለት አይደለም። በክርስትና 'ትምህርተ መለኮት' አንድ እንደሆነ ይታመናል። እንግዲህ መለኮት አንድ ሆኖ ሳለ ሰው ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ ሲሆን ምን ሆነ ማለት ነው? ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ ስለሆነ መለኮት ሆነ ማለት ነውን? እግዚአብሔርን ስለመምሰልና የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ ስለመሆናችን ትምህርት ሲሰጥ በየጊዜው ተደጋጋሚ ስህተቶች ተደርገዋል።

ይህም የእግዚአብሔርን ማንነትና የእግዚአብሔርን ባሕርይ ለይቶ ባለማወቅ የሚደረግ ስህተት ነው። አንዳንዶቹ በስሜት ግለትና ጉጉ ከመሆን የተነሳ ይህንን ትምህርት አጋኖ በማቅረብ ከመጠኑ ባለፈ መልኩ ሰውን ትናንሽ አማልእክት አድርገው ለማቅረብ ይቃጣቸዋል። እነዚህ ተደጋጋሚ ስህተቶች እንዳይፈጠሩና ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ተገፋፍተው ከመስመር የወጡ ትምህርት ያገኙ ዘንድ ስለ እግዚአብሔር ማንነትና ስለ ባህርያቱ ለይቶ ማወቅ እንዲቻል መጠነኛ ትንተና ከተደረገ በኋላ የመለኮት ተካፋይ መሆን ምን ማለት እንደሆነ ግልጽ ለማድረግ እሞክራለሁ።

**በመጀመሪያ ስለእግዚአብሔር ማንነት እንመለከታለን:-**

**ሀ. የእግዚአብሔር ማንነት:**

የእግዚአብሔርን "ማንነት" ለማየት በቅድሚያ መታወቂያ ባሕርያቱን ሳንነካ ስለ እሱነቱ እናያለን። የእግዚአብሔር ማንነት ከዚህ በታች የሚከተሉትን አራት ዋና ዋና ነጥቦች ይይዛል።

1) እግዚአብሔር በማንነቱ መንፈስ ነው:-
እግዚአብሔር መንፈስ ነው ስንል በአካልና በቅርጽ የማይወሰን መሆኑን ማወቅ አለብን፤ ይሁን እንጂ መንፈስ በማናቸውም አካል ሊገለጽ ይችላል፤ በአንዱም አይወሰንም።

2) እግዚአብሔር በማንነቱ የሕይወት ምንጭ ነው:-
እግዚአብሔር የሕይወት ምንጭ ነው፤ ሕይወትን ከየትም አላገኘውም፤ ሕይወት ያለው ሁሉ ከእርሱ ተገኘ። "የሕይወት ምንጭ ከአንተ ዘንድ ነውና" (መዝ.36:9)።

3) እግዚአብሔር በማንነቱ ወሰን የለሽ ነው:-
እግዚአብሔር በሥፍራ አይወሰንም፣ በአንድ ጊዜ ሁሉ ቦታ ሊገኝ ይችላል (መዝ.(139):7-10)።

4) እግዚአብሔር በማንነቱ መነሻና መድረሻ የለውም:-
እግዚአብሔር ዘላለማዊ ስለሆነ በዓመታትና በዘመናት አይወሰንም፣ ወጣት አልነበረም፣ አያረጅም፤ በማንነቱ የሚመስለው የለም።

ለ. የእግዚአብሔር ባሕርያት:-

1) በፍጥረት ሥራ የተገለጡ የእግዚአብሔር ባሕርያት:-
በፍጥረት ሥራ ከተገለጡትን የእግዚአብሔር ባሕርያት አራት ዋና ዋና የሆኑትን እናያለን።

1ኛ. በሥፍራ የማይወሰን ነው (ዮሐ.4:24፤ 2ቆሮ.3:17)።
እግዚአብሔር በሥፍራ የማይወሰን ስለሆነ ማንም ከእርሱ ሊሸሽና ሊደበቅ አይችልም። "እኔ የቅርብ አምላክ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም።" "ሰው በስውር ቢሸሽግ እኔ አላየውምን? ሰማይና ምድርን የሞላሁ እኔ አይደለሁምን? ይላል እግዚአብሔር" (ኤር.23:23፤ መዝ.139:7-12)። ፍጥረት ባይኖር ኖሮ 'በሥፍራ አይወሰንም' የሚለው አባባል ትርጉም አይሰጥም ነበር።

2ኛ. ሁሉን አዋቂ ነው (ሳሙ.2:3፤ ማቴ.6:8፤ 10:30፤ 1ዮሐ.3:20)።
እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ስለሆነ አይዘበትበትም፤ ማንም ሊያታልለው አይችልም፤ በራሱ ሁሉን ስለሚያውቅ ማስረጃ አያስፈልገውም። ስለዚህ የእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት በፍጥረት ሥራ ውስጥ የተገለጠ ሆነ።

3ኛ. ሁሉን ቻይ ነው (ኢዮ.42:2፤ ማቴ.19:26)።
እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ስለሆነም ከእርሱ በላይ ወይም ከእርሱ ፈቃድ ውጭ ሆኖ መከናወን የሚችል ምንም ነገር የለም፤ ስለሆነም የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት የተገለጠው በፍጥረት ሥራ ውስጥ ነው።

4ኛ. የማይለወጥ አምላክ ነው (ሚል.3:6)።
ለውጥ የሚመጣው በውጭ ካለው ግፊት የተነሳ ስለሆነ እግዚአብሔር ለውጥ ሊኖረው አይችልም። ፍጥረት ባይኖር ኖሮ እግዚአብሔር የማይለወጥ አምላክ ነው ለማለት መነሻ የሚሆነን ነገር አይኖረንም ነበር።

2) **በደኅንነት የተገለጹ የእግዚአብሔር ባሕርያት**

1ኛ. **ቅድስና፦**

እግዚአብሔር በደኅንነት ሥራ ውስጥ ከተገለጹት ባሕርያት አንዱ ቅድስናው ነው። እግዚአብሔር ቅዱስ አምላክ ስለሆነ ከማይመስለው ፍፁም የተለየ ነው። እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ርቆና ተገልሎ የሚኖርና የማይቀርብ ነው ማለት አይደለም። እግዚአብሔር በደኅንነት ሥራ ውስጥ እንደታየው በእግዚአብሔርና በኃጢአተኛው ሰው መካከል ርቀት አለ (ኢሳ.59:1-2)። በዚህ ምክንያት በእግዚአብሔርና በኃጢአተኛው ሰው መካከል የሚቆምና የሚያቀራርብ አስፈለገ፤ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

"አንድ እግዚአብሔር አለና በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛ ደግሞ አንድ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ" (1ጢሞ.2:5-6፤ ኤፌ.2:18፤ ዕብ.10:19-20)። ስለዚህ ቅድስና በደህንነት የተገለጠ የእግዚአብሔር ባሕርይ ሆኖ እናገኘዋለን።

2ኛ. **ጽድቅና ፍትህ፦** ጽድቅንና ፍትህን ልናለያያቸው አንችልም። ጽድቅ ስንል የዕቅዱን ትክክለኛነት የሚጠቁም ሲሆን ፍትህ ደግሞ አሠራሩ ትክክል መሆኑን የሚያሳይ ነው። እግዚአብሔር ጻድቅ አምላክ

ስለሆነ በተናገረው ቃል መሠረት ይሠራል (ነህ.9:33፣ ዕዝ.9:15)። ፍትህ በባህላዊ ሳይሆኑ መለኮታዊ ሥራዎች መሆናቸውን መገንዘብ ይኖርብናል። ስለሆነም ጽድቅና ፍትህ በማዳን ሥራ ውስጥ የተገለጡ የእግዚአብሔር ባሕርያት ናቸው።

3ኛ. **ጥሩነት፡-** ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ሁኔታ "ጥሩ" የሚለው ቃል በገላጭነት የቀረበ ቃል ሳይሆን ከዚህ በላይ የለም በሚል አስተሳሰብ ውስጥ ሆነን እንድናይ ያስፈልጋል፤ ስለሆነም ለመልካምነቱ ገደብ የለውም። የእግዚአብሔርን ጥሩነት በተመለከተ ጥቂት ነጥቦችን አንስተን እናያለን።

ሀ) **ፍቅር፡-** ፍቅር የሥራውን ዓላማ ያመለክታል፤ ፍቅር ምን ጊዜም መልካም የሆነውን ብቻ ያስባል (1ቆሮ.13:1-11)።

ለ) **ቸርነት፡-** ቸርነት ከተጠበቀው በላይ መታገሱንና ማፍቀሩን ያሳያል።

ሐ) **ምህረት፡-** ምህረት ማለት ሲበድል በመበቀል ፈንታ ሊያድን መፈለጉን ያሳያል (ኤፌ.2:4፣ ሮሜ 11:30)።

መ) **ፀጋ፡-** ፀጋ ነጻ ስጦታ ማለት ነው። ፀጋ ለኃጢአተኛ ሰው የሚያቀርበው መልስ ነው። ላጠፋና ሕግጋቱን ለተላለፉት ቅጣትን ለመስጠት መዘግየቱና የደኅንነት መንገድ በማዘጋጀት የሚያሳየው ፊት ነው። እነዚህን ሁሉ የምናየውና ልንረዳ የምንችለው በደኅንነት ሥራ በተገለጹ የእዚአብሔር ባሕርያት ነው።

4ኛ. **እውነት፡-** ከእግዚአብሔር ጋር በተያያዘ ሁኔታ እውነት አንጻራዊነት የለውም፤ ምን ጊዜም እንደተናገረው ሆኖ ይገኛል (ዮሐ.17:3፣ 1ዮሐ.5:20)። ስለዚህ እውነት ከእግዚአብሔር ባሕርይ ጋር ተያይዞ የተገለጸ ባይሆን ኖሮ ትርጉሙ በጠፋብን ነበር፤ እንግዲህ ስለ እግዚአብሔር ማንነትና ስለ ባሕርያቱ በመጠኑም ቢሆን አይተናል። በመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች እንድንሆን አድርጎናል የሚለውን ኃሳብ አሁን ማገናዘብ እንችላለን።

የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ አድርጎናል ስንል ከማንነቱ ባሕርይ ተካፋይ አድርጎናል ማለት ነውን? ስለ እግዚአብሔር "ማንነት" አይተናል፤ የእግዚአብሔር ማንነቱ መንፈስ ነው፣ የሕይወት ምንጭ ነው፣ ወሰን የለሽ

ነው፤ መነሻና መድረሻ የለሽ ነው፤ ስለዚህ ከመለኮት በስተቀር ይህ ማንነት ለማንም ሊኖረው አይችልም።

ከእግዚአብሔር ማንነት ተካፋይ ካልሆንን ከየትኛው ባሕርይ ነው ተካፋይ መሆን የምንችለው? ስለ እግዚአብሔር ባሕርያት ስንመለከት በሁለት ከፍለን አይተን ነበር። አንደኛው በፍጥረት ሥራ የተገለጠ የእግዚአብሔር ባሕርይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በደኅንነት ሥራ የተገለጠ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው። በፍጥረት ሥራ የተገለጡት የእግዚአብሔር ባሕርያት፡- የማይወሰን፣ ሁሉን አዋቂ፣ ሁሉን ቻይ፣ የማይለወጥ፣ መሆኑን አይተናል። ስለዚህ በፍጥረት ሥራ የተገለጠ የእግዚአብሔር ባሕርይ ሊኖረን አይችልም፤ በዚህ የሚመስለው ማንም የለም።

ሁለተኛውን ኃሳብ ይዘን በደኅንነት ሥራ ስለ ተገለጠው የእግዚአብሔር ባሕርይ ስንመለከት እኛ የተካፈልነው ባሕርይ ይህ መሆኑን እንረዳለን። ለማገናዘብ እንዲያመቸን ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ ከመሆናችን ጋር ተያይዞ የተጻፈውን ኃሳብ ማየት ይኖርብናል። በደኅንነት ሥራ የተገለጡ የእግዚአብሔር ባሕርያት ቅድስና፣ ጽድቅ፣ ፍትህ፣ ጥሩነትና እውነት ናቸው። ይህንን ኃሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ለመረዳት ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ መሆናችንን የሚያመለክቱትን ጥቅሶች እንመልከት።

2ጴጥ.1:4 ላይ "ስለክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ፣ በእነዚያ ክብርና ምስጋና፣ በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን" ይላል። በዚህ ቃል ውስጥ "የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ" የሚለው ኃሳብ "ከዓለም ጥፋት አምልጣችሁ" ከሚለው ሃሳብ ጋር በማያያዝና በማነጻጸር የቀረበ ነው። በዓለም ያለው ጥፋት ደግሞ ርኩሰት ነው፤ ከዚህ ርኩሰት አምልጣችሁ ወደ ጽድቅና ወደ ቅድስና መጣችሁ ማለት ነው። ይህ ደግሞ ከላይ እንዳየነው መለኮታዊ ባሕርይ ነው።

በተጨማሪም "ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም ዘሩ በእርሱ ይኖራልና፣ ከእግዚአብሔር ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም" ይላል (1ዮሐ.3:9)። "ዘሩ" በእርሱ ይኖራል ሲለ ባሕርይው በእርሱ ይኖራል ለማለት ነው። ይህም ዘር ወይም ባሕርይ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው (1ጴጥ.1:23)። ስለዚህ የእግዚአብሔር ዘር ወይም ባሕርይ በልጆቹ ይኖራል ማለት ነው።

"ዘሩ" በእርሱ ይኖርበታልና ከእግዚአብሔር ተወልዶአልና የሚለው ኃሳብ ከኃጢአት ጋር በማነጻጸር የተጻፈ ነው (1ዮሐ.3:4-10)። ኃጢአት ምንድነው? ኃጢአት ርኩሰት ነው፤ ስለዚህ ርኩሰትና ቅድስና በአንድነት ሊኖሩ አይችሉም። ሐዋርያው ዮሐንስ ሊያስረዳን የፈለገውም ይህንን ነው። ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ ስለ መሆን በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠው በዚህ መልኩ ነው።

እንግዲህ በመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ መሆናችን በደኅንነት ሥራ ከተገለጠው ባሕርይ ተካፋይ ስለመሆናችን እንጂ ከእግዚአብሔር የማንነት ባሕርይ ተካፋይ አለመሆናችንን መገንዘብ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪ ማገናዘቢያ ለማግኘት እነዚህን ጥቅሶች መመርመር ይቻላል። (1ዮሐ.3:7፣ 1ጴጥ1:15፣ ዕብ.12:10፣ ኤፌ.4:32፣ ገላ.5:22፣ ኤፌ.5:9፣ ፊል.1:11፣ 1ጢሞ.6:11፣ 2ጢሞ.2:22)

## 5. ከክርስቶስ ጋር ወራሾች መሆን

እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ሁሉን ወራሽ አድርጎታል (ዕብ.1:2)። እኛን በዳግም ልደት ልጆቹ የሆነውን ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ደግሞ አደረገን። "ልጆች ከሆንን ደግሞ ወራሾች ነን፣ ማለትም የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፣ አብረንም ደግሞ እንድንከብር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን" (ሮሜ 8:16-17)ይላል በሌላ ሥፍራ ደግሞ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ ባሪያ አይደለህም። ልጅም ከሆንክ ደግሞ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሽ ነህ" ይላል (ገላ.4:7)።

አባት ለልጆቹ የሚያወርሳቸው እንዳለው መጠን ነው፤ የእግዚአብሔር ያልሆነ ነገር የለምና ሁሉም የእግዚአብሔር ስለሆነ እንደ ክብሩ ባለጠግነት መጠን ያወርሰናል። እግዚአብሔር የሚያወርሰን ርስት የተረገመችውን፣ እሾህና አሜከላ የምታበቅለውን በመጨረሻም የምትጠፋውን ይህችን ምድር አይደለም፤ እግዚአብሔር ሊያወርሰን ያለው ሰማያዊውን ዓለም የመላእክትን አገር ነው።

"እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም"(ኤፌ.2:19) እግዚአብሔር ሰማያዊውን አገር አውርሶን ብቻችንን እንድንኖር አላደረገም፤ እርሱ ባለበት ለዘላለም ከእርሱ ጋር እንድንኖር ጠራን።

እግዚአብሔር ሁሉን ካወረሰን ለእርሱ ምን ይቀርለታል? የሚል ሰብአዊ አስተሳሰብ ሊኖረን ይችላል። እግዚአብሔር ሁሉን ካወረሰን በኋላ እኛም ሆንን የወረስነው ነገር ሁሉ ለእርሱ ይሆናል፤ የእግዚአብሔር ያልሆነ ነገር አይኖርም፤ እግዚአብሔር ግን ከሁሉም በላይ ሆኖ በሁሉም ይኖራል፤ ሁሉም በእርሱ ይኖራል። "ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ" (ኤፌ.4:6)።

እግዚአብሔር ሊያወርሰን ላለው ሰማያዊ ርስት ተስፋ በመስጠት ብቻ አላቆመም፤ የገባልንን ተስፋ እስኪያወርሰን ድረስ መንፈስ ቅዱስን እንደ መያዣ አድርጎ ሰጠን። "እርሱም (መንፈስ ቅዱስ) የርስታችን መያዣ ነው፤ ለእግዚአብሔር ያለውን እስኪዋጅ ድረስ ይህ ለክብሩ ምስጋና ይሆናል" (ኤፌ.1:14)። የእግዚአብሔር የሆኑት በሙሉ አልተዋጁም፤ ገና ወደ ፊት የሚዋጁ ይኖራሉ፤ አሁን የዋጀንን የእርሱ ስለመሆናችን ማስረጃ የሚሆን ማህተም በእኛ ላይ ካኖረ በኋላ እንደማይተወን ማረጋገጫና ዋስትና ይሆነን ዘንድ መንፈስ ቅዱስን እንደ መያዣ አድርጎ ሰጠን። መንፈስ ቅዱስ የተሰጠን ለዚህ ብቻ አይደለም፤ ጌታ እስኪመጣ ወይም እኛ ወደ እርሱ እስክንወሰድ ድረስ ሊያጽናናን፣ ሊያስተምረን፣ ሊመክረን፣ ሊገስጸን፣ የፀጋ ተውህቦ ሊሰጠን፣ ወደ እውነት ሁሉ ሊመራንና የሚመጣውን ሊነግረን ተሰጥቶናል (ዮሐ.15:25፣ 16:12-15፣ 1ቆሮ.12:4-8)።

እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የከንዓንን ምድር ማውረስ ለእኛ ለአዲስ ኪዳን ሕዝብ ሰማያዊውን አገር የማውረስ ምሳሌነት አለው። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የከንዓንን ምድር ያወረሳቸው አስቀድሞ በአብረሃም በኩል በሰጣቸው የተስፋ ቃል መሠረት ነው (ዘፍ.13:14-15)። በብሉይ ኪዳን የተፈፀሙ ሁሉ እንደ ጥላ ሆነው በምሳሌነት ይናገሩናል፤ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ የከንዓንን ምድር መውረስ ነው (ገላ.4:24-26)፤ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው የተስፋ ቃል በሥጋ ከእርሱ ለተወለዱ የከንዓንን ምድር ለመውረስ ብቻ አይደለም፤ በእምነት አባት ለሆናቸው መንፈሳዊ እስራኤላውያን ጭምር ነው እንጂ (ገላ.3:29፣ ሮሜ 4:11-17)። የእስራኤላውያንን የከንዓንን ምድር መውረስ ከእኛ ሰማያዊውን አገር መውረስ ጋር ብናነጻጽር ይህን ይመስላል:-

1ኛ. እስራኤላውያን የከንዓንን ምድር የወረሱት ከሰዎች ጋር ተዋግተው ሲሆን እኛ ግን መጋደላችን ከሰዎች ጋር ሳይሆን ከሰይጣንና ርኩሳን

መናፍስት ጋር ነው (ኤፌ.6:12፣ 2ቆሮ.12:3)።

2ኛ. እስራኤላውያን የከንዓንን ምድር ከወረሱም በኋላ ዕድሜ ልካቸውን እየተዋጉ ኖረዋል፤ እኛ ግን በሰማያዊ አገር ውጊያ አይገጥመንም።

3ኛ. እስራኤላውያን የከንዓንን ምድር የወረሱት ዳርና ድንበር ከልለው ነው፤ ለእኛ ግን እግዚአብሔር ሰማያዊውን አገር ሲያወርሰን ለእያንዳንዳችን ዳርና ድንበር እየከለለልን አይደለም። በሰማያዊ አገር ስሜታችንና ፈቃዳችን ሁሉ በሁሉ በሆነ አምላክ ይሞላል፤ ስለዚህ ችግር፣ ብቸኝነት፣ ጉድለት የሚባል ነገር አይሰማንም። ይሁን እንጂ የመቀናናት ስሜት ባይኖርም የደረጃ ልዩነት መኖሩ የማይቀር ነው። ስለዚህ ጉዳይ 'የታማኝ ክርስቲያን' ዋጋ በሚለው በመጨረሻው ምዕራፍ ወደ ፊት በዝርዝር የምናውቀው ይሆናል። ያም ሆነ ይህ ከክርስቶስ ጋር ወራሽ ሆነን መቆጠራችን እጅግ ታላቅ ነገር ነው፤ ይህም ወደፊት ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ከታተምንበት ጊዜ አንስቶ ይህ መብት ተሰጥቶናል።

## 6. ሰማያዊ ዜግነትን ማግኘት

"እኛ አገራችን በሰማይ ነውና ከዚያ ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እንጠባበቃለን (ፊልጵ.3:20)።

"እኛ አገራችን በሰማይ ነውና" የሚለውን ቃል አዲሱ የ1980 ዓ.ም. የአማርኛ ትርጉምና ኤን አይ ቪ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ "እኛ የመንግሥተ ሰማያት ዜጎች ነን" ይለዋል። "ዜጋ" ማለት የአንድ አገር ነዋሪ ወይም የአንድ ኅብረተሰብ አባል ማለት ነው። የአንድ አገር ዜጋ የሆነ ሰው ከሌላው ኅብረተሰብ ጋር እኩል መብት ያለው ይሆናል። የዜግነት መብት የሌለው ሰው እንግዳ ወይም መጻተኛ ይባላል፤ እንግዳ ወይም መጻተኛ የሆነ ሰው ነዋሪነቱ ጊዜያዊ ነው። እኛ የሰማያዊ ዜግነት ያገኘን ሰዎች በዚህ ዓለም ነዋሪነታችን ጊዜያዊ ስለሆነ የዚህን ዓለምን ኑሮ እንዳንመኝ መጽሐፍ ቅዱስ ያስጠነቅቀናል። "ወዳጆች ሆይ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት ትርቁ ዘንድ እንግዶችና መጻተኞች እንደመሆናችሁ እለምናችኋለሁ" ይላል (1ጴጥ.2:11)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣበት ምክንያት ሰማያዊ ዜግነት እንድናገኝ ጥሪ ሊያደርግልን ነው። "ስለዚህ ከሰማያዊ ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይየሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ" ይላል (ዕብ.3:1)።

ጥሪውን ሰምተው የተቀበሉት ሰማያዊ ዜጋ ስለመሆናቸው በመንፈስ ቅዱስ ይታተማሉ። "እናንተ ደግሞ የእውነት ቃል ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው" (ኤፌ.1:13)። በሌላ ሥፍራ "በክርስቶስ ስም ከእናንተ ጋር የሚያፀናን፣ የቀባን እግዚ.አብሔር ነው። ደግሞም ያተመን የመንፈሱንም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው" ይላል (2ቆሮ.1:21-22)። የታተምነው በምንድን ነው? የታተምነውስ ምን ተብሎ ነው? ብሎ የሚጠይቅ ሰው ይኖራል። ያተመን የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ የሆነው ልዑል እግዚአብሔር ነው። እርሱ ያተመን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው፤ እግዚአብሔር ያተመን የእኔ ናቸው ብሎ ነው (2ቆሮ.1:22)። አዲሱ የ1980 የአማርኛ ትርጉም እንዲህ ተጽፏል:-"የእርሱ ለመሆናችን ማስረጃ የሚሆን ማህተሙን በእኛ ላይ ያደረገና ወደ ፊት ለእኛ ስለሚሰጠን ሃብት በልባችን መንፈስ ቅዱስን እንደዋስትና አድርጎ የሰጠን እርሱ ነው"።

እናስተውል! የሰማይ አገር ዜጎች ነን፤ ጠባቂያችን ከሁሉም በላይ ነው። "በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፣ እኔም አውቃቸዋለሁ፣ ይከተሉኝማል፣ እኔም የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ ለዘላለም አይጠፉም፣ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፣ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም እኔና አብ አንድ ነን" ይላል (ዮሐ.10:28-29)።

በአንድ ወቅት ጌታ ደቀመዛሙርቱን ሁለት ሁለት አድርጎ ድውያንን እንዲፈውሱና አጋንንትን በስሙ እንዲያወጡ ስልጣን ሰጣቸውና "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ብላችሁ ስበኩ" ብሎ ላካቸው፤ የላካቸውም ተመልሰው ስለ አገልግሎታቸው ሪፖርት አቀረቡለት፤ ከሁሉም ይልቅ ያስደሰታቸው በስሙ አጋንንት ማውጣታቸው ነበርና "ጌታ ሆይ አጋንንት እንኳ በስምህ ተገዝተውልናል" አሉት። ጌታ በዚህ ሁሉ ደስ ቢለውም ደቀ መዛሙርቱ አጋንንት በስሙ ስለተገዛላቸው የተሰማቸውን ደስታ ሲያገናዘብ ስሞቻቸው በሰማያት በመጻፉ ከተሰማቸው ደስታ በልጦ አገኘው። ስለዚህ እንዲህ አላቸው:- "እነሆ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፣ የሚጎዳችሁም ምንም የለም፤ ነገር ግን መናፍስት ስለተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፣ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለተጻፈ ደስ ይበላችሁ" (ሉቃስ 10:19-20፣ ራዕ.21:27)። ይህን ሁሉ ካስተዋልን ፀንተን ለመቆም ምክንያት ይሆንልናል። ሰማያዊ ዜግነትን ከማግኘትና በሕይወት መጽሐፍ ከመጻፍ

በላይ ሊያስደስተን የሚችል ነገር የለምና።
ክብርና ምስጋና ለእርሱ ይሁን።

## 7. <u>**የእግዚአብሔር ካህናት መሆን፡-**</u>1ጴጥ.2:9

"ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ፥ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን አሜን" (ራዕ. 1:6)።

"መጽሐፍትን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፤ ታርደሃልና በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ፤ ከቋንቋም ሁሉ፤ ከወገንም ሁሉ፤ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አድርገሃቸዋል፤ በምድርም ላይ ይነግሳሉ" (ራዕ.6:9-10)።

በዚህ ባነበብነው ክፍል ሁለት ዓይነት ሥልጣንና ደረጃ በእግዚአብሔር ፊት እንደሚኖረን እናያለን፤ አንደኛው የክህነት ሥልጣን ሲሆን ሁለተኛው በምድር ላይ መንገሣችን ነው። በምድር ላይ መንገሥን ወደ ፊት እንደሚፈጽም ሲያመለክት "በምድርም ላይ <u>ይነግሣሉ</u>" ይላል። የክህነት ሥልጣን ወደ ፊት የምንደርስበት የተሰጠን ተስፋ ሳይሆን በምድር እያለን የተሰጠን ሥልጣን ስለመሆኑ ሲያመለክት "ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው" ይላል። ይህ "<u>አደረግሃቸው</u>" የሚለው ቃል የወደፊት ጊዜ ሳይሆን የአሁን ጊዜን የሚያመለክት ቃል ነው።

ለቅዱሳን የተሰጠን ብዙ የተስፋ ቃል ቢኖርም በዚህ ክፍል መጀመሪያ እንደተገለጸው ክርስቶስን አዳኛችንና ቤዛችን አድርገን ስንቀበል በእግዚአብሔር ፊት ስለምናገኘው አቋም ለመግለጽ ስለሆነ በምድር ላይ ይነግሣሉ" የሚለውን ኃሳብ ለጊዜው አልፈን ካህናት ስለመሆናችን በሚለው ላይ እናተኩራለን።

ካህን ወደ እግዚአብሔር ቀርቦ ማገልገል የሚችል ነው። በብሉይ ኪዳን ካህናት ይሆኑ ዘንድ መብትና ሥልጣን የተሰጣቸው ለአሮን ልጆች ነበር። በአዲስ ኪዳን ግን ከየነገዱ፤ ከየቋንቋው፤ ከየሕዝቡ ሁሉ በክርስቶስ ደም የተዋጁ ሰዎች ካህናት መሆናቸውን እናያለን። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ

የአገልግሎት ሥልጣንና ደረጃ ቢኖርም የክህነትን ሥልጣን በተመለከተ ግን ፆታና ነገድ ሳይለይ በክርስቶስ ለተዋጁት ሁሉ እኩል የተሰጣቸው ሥልጣንና መብት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ የእግዚአብሔር ቃል አድርጎ የሚቀበል ወገን አይክድም።

የአዲስ ኪዳን የክህነት ሥርዓትና የአገልግሎት ሥፍራ ከብሉይ ኪዳን ሲነፃጸር የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን። በመጀመሪያ ካህን ስንሆን እንደ አሮን ልጆች እንስሳት ደም በመርጨት ሳይሆን በክርስቶስ ደም መርጨት ነው። ". . . ይታዘዙና በኢየሱስ ደም ይረጩ ዘንድ ለተመረጡ" (1ጴጥ.1:2) " . . . በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋ ሁሉ ከወገን ሁሉ ከሕዝብ ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው" ይላል (ራዕ.5:10)። ይህ ደግሞ በሰዎች የሚደረግ ሥርዓት ሳይሆን በራሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የሚሰጥ ሥልጣን ነው። ". . . ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ <u>አደረግሃቸው</u>" የሚለው ቃል አድራጊው ጌታ መሆኑን ያረጋግጣል። ስለዚህ የአዲስ ኪዳን ክህነት በሰው የሚሰጥ አለመሆኑን የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ያሳየናልና።

በሁለተኛ ደረጃ የአዲስ ኪዳን ክህነት በውኃ መታጠብ የሚደረግ መንጻት ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ የሚደረግ መንጻት ነው (ቲቶ.3:5)። የብሉይ ኪዳን ሰዎች በእንስሳት ደም በመረጨትና በውኃ በመታጠብ ሥጋን በማንጻት በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ለማገልገል የሚያበቃ እንደ ጥላ ወይም እንደ ሞግዚት ሆኖ የተሰጣቸው ሥርዓት ቢሆንም አሁን ግን አካሉ መጥቷልና ጥላው አያስፈልግም። ሕጉ ሞግዚት ሆኖ ለአንድ ሺ አራት መቶ ዓመታት አገልግሏል። ክርስቶስ ከመጣ ወዲህ ግን ሞግዚት አላስፈለገም (ገላ. 3:23፣ 4:1-7)።

በሦስተኛ ደረጃ የብሉይ ኪዳን ካህናት ለክህነት የሚቀቡት በወይራ ዘይት የተቀመመ የተፈጥሮ ዘይት በመቀባት ነበር፣ እኛ ግን የተቀባነው በሰው እጅ በሚደረግ የተፈጥሮ ዘይት በመቀባት ሳይሆን ከእግዚአብሔር በሆነ ሰማያዊ ዘይት ነው፤ "በክርስቶስም ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው" ይላል (2ቆሮ.1:21)። ይህም በመንፈስ ቅዱስ ከሆነ ሰማያዊ ቅባት እውቀትንና ማስተዋልን የሚሰጠን ከእግዚአብሔር የሆነውንና ያልሆነውን ለይተን ለማወቅ የሚያስችለን ቅባት ነው (1ዮሐ.2:20-27)።

የብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚገባው በዓመት አንድ ጊዜ ሲሆን በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ታቦቱ የሚቀመጥበት ሥፍራ ስለ ነበር ሊቀካህኑ ስለ ራሱ ኃጢአት የእንስሳት ደም ሳይዝ መግባት አይችልም ነበር። ነገር ግን በሰው እጅ ባልተሠራች ወደ ሰማያዊ መቅደስ ለሰዎች ኃጢአት የገዛ ደሙን ይዞ የገባው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው (ዕብ.11:10-12)። ስለዚህ ሊቀካህናችን ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ ስለሚል በዓመት አንድ ጊዜ ሳይሆን ዘወትር ወደ እግዚአብሔር ዙፋን መቅረብ እንችላለን (ዕብ.4:14-16)።

ክርስቶስ ሊቀ ካህናችን ሆኖ አገልግሎቱን በዚህ መልኩ የሚፈጽም ሲሆን እኛስ የክህነት አገልግሎታችንን የምንፈጽመው በምን መልኩ ነው? ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖረን አሁንም የብሉይ ኪዳንን የካህናት አገልግሎት በማነጻጸር ማየት ይኖርብናል። ለእነርሱ አገልግሎታቸውን መፈጸም የሚያስችላቸው ልዩ ልዩ ሥርዓት ተሰጥቷቸው ነበር። ሊቀ ካህኑ በሕዝቡና በእግዚአብሔር መካከል በመሆን የእንስሳት ደም ይዞ የሕዝቡን ኃጢአት ያስተሰርይ ነበር (ዘሌ.16:3-6)። ስለዚህ አንድ ሰው ያለ ካህኑ የእንስሳት ደም ይዞ ሊቀርብና ኃጢአቱን ሊያስተሰርይ አይችልም።

ከላይ እንዳየነው የአዲስ ኪዳን የክህነት አገልግሎት ከዚህ የተለየ ነው። በሕዝቡና በእግዚአብሔር መካከል የሚቆም ክርስቶስ ብቻ ነው። "አንድ እግዚአብሔር አለና፤ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ" (1ጢሞ.2:5)። ስለዚህ ማንም ሰው በክርስቶስ በመታመን ወደ እግዚአብሔር ፊት በእምነት በመቅረብ ምህረትን መቀበል ይችላል (ዕብ.4:14፤ 16፤ 10:19-22፤ ዮሐ.14:6)።

በክርስቶስ ደም የተዋጀ ሁሉ የክህነት አገልግሎትና ሥልጣን እንዳለው አይተናል፤ የእኛ የክህነት አገልግሎት የሚካሄደው በምን መልኩ ነው? የአዲስ ኪዳን የካህናት አገልግሎት እንደ ብሉይ ኪዳን የካህናት አገልግሎት እንድንመራበት የተሰጠን ሕግ የለም። የእግዚአብሔርን ኃሳብ ለማገልገል እንዲመራን የተሰጠን መንፈስ ቅዱስ ነው። "እርሱ ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን" (2ቆሮ.3:6)። ስለሆነም በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናየው የክህነት አገልግሎቶታችንን እንድንፈጽም መንፈስ ቅዱስ ይመራናል።

እርሱም አንደኛ በክርስቶስ ላለን ሁሉ፥ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር የማስታረቅ አገልግሎት ሰጠን። "ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ጋር ነው" (2ቆሮ.5:18)። የካህናት አገልግሎት አንዱ ሕዝብን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቅ ነው። ይህን የማስታረቅን አገልግሎት የምንፈጽመው በዓለም ላሉ ሰዎች ወንጌልን በመስበክ ነው። እግዚአብሔርም የማስታረቅ አገልግሎት ስለ ሰጠን መልዕክታችንን የማይቀበሉትን እርሱን እንዳልተቀበሉት አድርጎ እንደሚቆጥር ጌታ የተናገረውም ለዚህ ነው። "የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል፤ እናንተንም የጠላ እኔን ይጠላል፤ እኔንም የጠላ የላከኝን ይጠላል" (ሉቃ.10:16) "እውነት እውነት እላችኋለሁ ማናቸውንም የምልከውን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል" (ዮሐ.13:20)።

ሁለተኛ እግዚአብሔር የማስታረቅን ቃል በእኛ ያኖራል፡-"እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅን ቃል አኖረ" (2ቆሮ.5:19)። እግዚአብሔር የማስታረቅን አገልግሎት ብቻ ሰጥቶን አልተወም፤ ለሰዎች የምንናገረውን መልእክት በውስጣችን ያኖራል። "ዳሩ ግን በዚያች ሰዓት የሚሰጣችሁን ተናገሩ የሚናገረው መንፈስ ቅዱስ እንጂ እናንተ አይደላችሁም" ማር.13:11። በሰዎች ፊት ስንቆም መንፈስ ቅዱስ ጥበብንና ድፍረትን የሚሰጠን ስለ ራሳችን መከራከር እንድንችል ሳይሆን ክርስቶስ አዳኝና ጌታ መሆኑን መመስከር እንድንችል ነው። ይህንን የማዳኑን ምስጢር ላልዳኑ ሰዎች እንድንናገር ካህናት አድርጎ ጠራን። "እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፥ <u>የንጉሥ ካህናት</u>፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ" (1ጴጥ.2:9)።

በሦስተኛ ደረጃ የማስታረቅ መልእክት ለሰዎች ሳንታክት ለማድረስ የሚያስችለንን ጸጋ ሰጠን፤ "እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን" (2ቆሮ.5:20)። ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ ለመንገር የሚገፋፋን እግዚአብሔር በውስጣችን ያኖረው ጸጋ መሆኑን የዓለም ሰዎች ባይረዱትና ባያውቁትም እኛ ግን የተቀበልነውን እናውቃለን። ስለዚህ ይህን እንድናደርግ የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና (2ቆሮ.5:13)። ስለሆነም ማንም ሰው ጌታን ከተቀበለ በኋላ ይህ ጸጋ ይኖረዋል።

በአራተኛ ደረጃ በኃጢአት ለወደቁ ቅዱሳንና ለሌሎችም እንድንማልድ የምልጃ አገልግሎት ይሰጠናል። "ማንም ወንድሙን ሞት የማይገባው ኃጢአት ሲያደርግ ቢያየው ይለምን፤ ሞትም የማይገባውን ላደረጉት ሕይወት ይሰጣቸዋል" ይላል (1ዮሐ.5:16)።
ቁጥር 14 ላይ ስናነብ "በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው እንደፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል" ይላል፤ ከዚያም በመቀጠል "ማንም ወንድሙን ሞት የማይገባው ኃጢአት ሲያደርግ ቢያይ ይለምን (ይጸልይ) ሞትም የማይገባው ኃጢአት ላደረገ ሕይወት ይሰጥለታል፤ ሞት የሚገባው ኃጢአት አለ ስለዚያ እንዲጠይቅ (እንዲጸልይ) አልልም" ይላል። ይሁን እንጂ ሐዋርያው ዮሐንስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መጸለይ የምንችለው በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሆነ አልተነተነልንም። ስለዚህ ለሞት የሚያደርስ ኃጢአትና ለሞት የማያደርስ ኃጢአትን ለይቶ ለማወቅ ያስቸግራል ብለን ልናስብ እንችላለን። ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ፈቃዱ መጸለይ የሚያስችለን መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ሲገልጽ እንዲህ ይላል። "እንዲሁ ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥ <u>እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ</u> ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና"

(ሮሜ.8:26-27)። ስለሆነም ልንጸልይላቸው የሚገባንን የሚያመለክተንና በውስጣችን በመቃተት እንድንጸልይ የሚረዳን መንፈስ ቅዱስ ነው። የክህነት አገልግሎታችንን የምንፈጽመው በዚህ መንገድ ስለ ሆነ ይህንን ድንቅና የከበረ አገልግሎት ለመፈጸም እንደተሰጠን አውቀን ለመንፈስ ቅዱስ በመታዘዝ በአገልግሎታችን ልንተጋ ይገባናል።

## 8. <u>ቅዱስ ሕዝብ መሆን</u>

"በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል" (ዕብ.10:10)። "እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ" (1ጴጥ.2:9)። የንጉሥ ካህናት ስለመሆናችን ቀደም ሲል አይተናል፤ በዚህ ክፍል የምናየው ደግሞ ቅዱስ ሕዝብ ስለመሆናችን ነው። ብዙ ክርስቲያኖች ጽድቅንና ቅድስናን ለይቶ ለማወቅ ይቸግራቸዋል። በመሠረቱ ጽድቅና

ቅድስና የማይነጣጠሉ ቢሆኑም የሚለያዩበት ነገር አለ። መጽደቅ የሚለው ቃል ቀደም ሲል እንዳየነው በአንድ ወገን ከእግዚአብሔር ቁጣና ፍርድ መዳን ማለት ሲሆን በሌላ ወገን ደግሞ ጻድቅና ቅዱስ በሆነ አምላክ ፊት ተቀባይነትን ማግኘት ማለት ነው።

መቀደስ ማለት ቀጥተኛ ትርጉሙ መለየት ማለት ሲሆን፣ ይህም ከዓለምና ከኃጢአት ተለይቶ ለእግዚአብሔር ሆኖ መቅረብ ማለት ነው። ስለዚህ የአዲስ ኪዳን ሕዝብ ለእግዚአብሔር የተለየ ወገን ነው። ይህ ሲባል ከሌላው ሕዝብ ተገልሎ መኖር ይኖርበታል ማለት አይደለም።

በዚህ ዓለም እስካለን ድረስ በማናቸውም ማኅበራዊ ኑሮ መሳተፍ እንችላለን። "ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልልም" ብሎ ጌታ ወደ አባቱ የጸለየውን ጸሎት ልናስብ ይገባናል። ከዓለም የተለየን ነንና በዓለም ካለው ጋር ሕዝብ በክፉ ሥራ አንተባበርም። "እንዲሁም እግዚአብሔር ተናገረ እንዲህ ሲል፣ በእነርሱ እኖራለሁ፣ በመካከላቸውም እሆናለሁ፣ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ። ስለዚህም ጌታ ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ፣ ርኩሱንም አትንኩ፣ ይላል ሁሉን የሚገዛ ጌታ" (2ቆሮ.6:16-17፣ 1ቆሮ.5:9-13)።

ምንም እንኳን የቅድስና ሕይወት ደረጃ ቢኖረውም መጽደቅ ግን አንድ ጊዜ የሚፈጸም ነው፤ ይሁን እንጂ የመጀመሪያውን የመቀደስ ሕይወትና ጽድቅን የምናገኘው በተለያየ ጊዜ ሳይሆን ጌታን በተቀበልንበት ቅጽበት በእግዚአብሔር ፊት የምናገኘው ሥፍራ ነው። በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ እኩል በእግዚአብሔር ፊት ጽድቅን እንደሚያገኙ ሁሉ እንዲሁ ደግሞ በክርስቶስ ያመኑ ሁሉም እኩል ለእግዚአብሔር የተቀደሱ ይሆናሉ። አማኞች ሁሉም በእግዚአብሔር ፊት ቅዱሳን ናቸው። ሌላው ቀርቶ በቆሮንቶስ የነበሩ አማኞች እንኳን ቅዱሳን ተብለዋል (1ቆሮ 1:2፣ 2ቆሮ 9:1)። በቆሮንቶስ የነበሩ ክርስቲያኖች በክርስቶስ ከማመን በስተቀር በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያልበረቱና ሥጋውያን እንደነበሩ ከተጻፈላቸው መልእክት እንረዳለን (1ቆሮ.3:1)። ይሁን እንጂ ከጣዖት አምልኮና ከነበራቸው ልዩ ልዩ ልምዶች ተመልሰው በጌታ በማመናቸው ብቻ ቅዱሳን ተብለዋል (1ቆሮ.1:2)። ስለዚህም የቆሮንቶስ ሰዎች በራሳቸው እንዳይመኩ ያስጠነቅቃቸዋል፤ ምክንያቱም ጽድቃቸውም ሆነ ቅድስናቸው በክርስቶስ ነውና። "የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ ተብሎ እንደተጻፈ ይሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም

ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው" (1ቆሮ.1:30-31) የ1980 የአማርኛ ትርጉም እንዲህ ያቀርበዋል:-"እናንተን ግን እግዚአብሔር ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ አደረገ፤ ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስን ጥበባችን፥ ጽድቃችን፥ ቅድስናችን፥ ቤዛችን እንዲሆን አደረገው። እንግዲህ መጽሐፍ እንደሚለው የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ" ይላል።

## ሀ. ቅድስና የመጀመሪያው ደረጃ

ከላይ እንደተመለከተው የመጀመሪያውን የመቀደስ ሕይወት ጌታን ባመንበት ቅጽበት ብናገኝም ደረጃ አለው። የመጀመሪያው ደረጃ ጌታን እንደግል አዳኛችን አድርገን በተቀበልንበት ቅጽበት እንቀደሳለን። "በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል" ይላል (ዕብ.10:10)።

በዚህ ምክንያት የመጀመሪያውን መቀደስ በተመለከተ በአማኞች መካከል ምንም ልዩነት አይኖርም። በ1ቆሮ.1:30 ላይ እንዳየነው ቤዛችንና ጽድቃችን ክርስቶስ ነው እንደተባልን ሁሉ ቅድስናችንም ክርስቶስ ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተቀድሰው የሚለዩት በእንስሳት ደም በመረጨትና በውኃ በመታጠብ የመንጻት ሥርዓት ከተደረገ በኋላ ነው።

መንጻት የቅድስና መለስተኛ ትርጉም ሲሆን አለነቀፋ ሆኖ መገኘት ነው። በእንስሳት ደም መረጨትና በውኃ መታጠብ የሚደረግ ሥርዓት ሥጋን የሚያነፃ እንጂ ውስጣዊ ሕይወትን ሊያነፃ የሚችል አልነበረም። "እንደዚህማ ባይሆን፥ የሚያመልኩት አንድ ጊዜ ነጽተው ከዚያ በኋላ በሕሊናቸው ኃጢአትን ስላላወቁ ማቅረብን በተው አልነበረምን? ነገር ግን በዚያ መስዋዕት በየዓመቱ የኃጢአት መታሰቢያ አለ፤ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይችል ነውና" (ዕብ.10:2-4)። ስለዚህ ያ የእንስሳት ደም ሕሊናቸውን ሊያነጻቸው ስላልቻለ የኃጢአተኝነት ክስ ዘወትር በውስጣቸው ይኖር ነበር።

በአዲስ ኪዳን የተደረገልን መቀደስ በክርስቶስ ደም በመረጨትና በመንፈስ ቅዱስ በመታጠብ የሚከናወን ፍጹም የሆነ የውስጥ ሕይወት መንጻትና መቀደስ ነው። "ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም

መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፤ ጸድቃችኋል" ይላል (1ቆሮ.6:11)። በሌላ ሥፍራ ደግሞ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም በረከሱትም ላይ የተረጨ የጊደር አመድ ሥጋን ለማንጻት የሚቀድሱ ከሆነ፤ ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞት ሥራ ሕሊናችሁን ያነፃ ይሆን? (ዕብ.9:13-14) ይላል። ይህም የክርስቶስ ደም በሥጋችን ላይ የሚረጭ ሳይሆን በውስጣዊ ማንነታችን ማለትም በመንፈሳዊ ክፍላችን ላይ የሚረጭ ስለሆነ ኃጢአታችንን ከውስጣችን ደምስሶ በእግዚአብሔር ፊት ሊያቀርበን የሚችል ነው (1ዮሐ.1:7፤ 1ጴጥ.1:1-2)። በክርስቶስ ደም የምናገኘው የኃጢአት ሥርየት ብቻ ሳይሆን መቀደስንም ጭምር ነው። በዚህ መሠረት አማኞች ሁሉ እኩል ቅዱሳን ሆነው በእግዚአብሔር ፊት የመቅረብ ጸጋን አግኝተዋል።

## ለ. ቅድስና በሂደት

ሁለተኛው የቅድስና ደረጃ በሕይወታችን ዘመን በሂደት እየተለማመድን እያደግንበት የምናገኘው ሕይወት ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው ቅድስናን እንደ ጽድቅ አንድ ጊዜ ካገኘን በኋላ በዚያው የሚያቆም አይደለም። በቅድስና ሕይወት ለማደግ በመጀመሪያ ደረጃ በክርስቶስ ቅድስናን ማግኘት ይኖርብናል፤ ያለበለዚያ ቅድስናን መለማመድ አንችልም። አንዳንድ ሰዎች ጽድቅን ከመጠማት የተነሳ ለመቀደስ ብለው ቤት ዘግተው ወይም በዋሻ ውስጥ ተሰውረው ሊኖሩ ይችላሉ። ይሁን እንጂ መጀመሪያውኑ ውስጣቸው አልነጻምና ቅድስናን ሊለማመዱና ሊያገኙ አይችሉም።

አንዳንድ ክርስቲያኖች በክርስቶስ አምነው ደህንነታቸውን ካረጋገጡ በኋላ በቅድስና ሕይወት ማደግን እምብዛም አይናፍቁም። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆኑን ለማየት ከፈለግን ቅድስናን መለማመድ ይኖርብናል። ያለቅድስና እግዚአብሔርን ማየት አይቻልምና፤ (ዕብ.12:14)። መቀደስ መለየት ነው ብለናል፤ መለየትም ከዓለምና ከኃጢአት ነው። የእግዚአብሔር ቃል "ትቀደሱ ዘንድ ፈልጉ" ማለቱ በቅድስና ሕይወት ማደግ እንዳለብን ሊያሳየን ነው (ዕብ.12:14)።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው ኃሳብ ቅድስና ነው፤ መቀደስ ከአንድ ነገር ተገልሎ ወይም ተለይቶ በመቆም አያበቃም። ከአንድ ወገን በመራቅ ወደ

ሌላው ወገን መቅረብ ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ 'ቅድስና ለእግዚአብሔር' የሚለው ትርጉም የለውም፤ ከዓለማዊ ልማዳችን ቀስ በቀስ እየራቅን ወደ እግዚአብሔር ልንቀርብ ይገባናል። "እንግዲህ ወዳጆች ሆይ የዚህ ተስፋ ቃል ካለን በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም እያደረግን ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክሱ ሁሉ እራሳችንን እናንጻ" (1ቆሮ.7:1)።

"በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም እያደረግን" የሚለውን አባባል በኃላፊ ጊዜ የተደረገውን ወይም ወደ ፊት ስለሚደረገው ቅድስና ሳይሆን ስላለንበት ጊዜ ይናገራል። ስለሆነም ባለንበት ዘመን ሁሉ ቅድስናን እየተለማመድን ልናድግ ይገባናል። እንደገናም በዚህ ክፍል ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ነገር በመጠበቅ መቀደስ እንዳለብን ይናገራል። ይህ በሕይወታችን እንዴት እንደሚፈጸም እንመልከት።

1) ቅድስና በውስጥ ሕይወት:-

ወፍ በራስህ ላይ ጎጆ እንዳትሠራ መከልከል ትችላለህ እንጂ ከራስህ በላይ እንዳትበር መከልከል አትችልም የሚለው አባባል በብዙ ክርስቲያኖች ዘንድ ይጠቀሳል። ዘይቤውም ኃጢአትን በሕይወትህ አትለማመድ እንጂ በአእምሮህ እንዳይመጣ መከልከል አትችልም ለማለት ነው። ነገሩ እውነት ይመስላል ይሁን እንጂ በአእምሮአችን ለሚመላለሰው ከንቱ ነገር ሁሉ ለራሳችን ይቅርታን ለማድረግ ይህንን ኃሳብ መውሰድ የለብንም። ከዓለም የምንለየው በድርጊት ብቻ ሳይሆን በአስተሳሰባችንም ነው። "የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነውን ነገር ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ" ይላል (ሮሚ.12:2)። ምክንያቱም ዓለማዊነት የሚኖረው በልብ ውስጥ ነው፤ ኃጢአት በኃሳብ ተጸንሶ በተግባር ይገለፃል።

ቅድስና የውስጥ ሕይወት ከሆነ የውስጥ ሕይወታችን በዚህ ዓለም ግብስብስ ነገር እንዳይሞላ ልባችንን መጠበቅ አለብን። "ቅጥር እንደሌላት እንደፈረሰች ከተማ መንፈሱን የማይከለክል ሰው እንዲሁ ነው" (ምሳ.25:28)። ቅጥር የሌላት ከተማ ሽቀጣ ሽቀጡን ይዞ ማንም ይገባባታል። አእምሮውን የማይጠብቅ ሰው አእምሮው ውስጥ ብዙ የማያስፈልጉ ነገሮች ይከማቻሉ፤ ስለዚህ ቅድስናን መለማመድ ያቅተውና መንፈሳዊ ሕይወቱ መደብዘዝ ይጀምራል። ቀስ በቀስ የቅድስና ነገር ይጠፋበትና በኃጢአት ሊወሰድ ይችላል። "ከዚህ በኋላ ምኞት ጸንሳ

ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች" (ያዕ.1:15)። ስለዚህ ክርስቶስን የተቀበልን ሁላችን ከዚህ ዓለም ምኞት መጠበቅ እንዳለብን የእግዚአብሔር ቃል ያስጠነቅቀናል(1ዮሐ.2፡15-17፤ ቆላ.1:3)።

2) ቅድስና በኑሮአችን:-

ቅድስናን በኑሮአችን ልንለማመድ ያስፈልገናል፤ ቅድስና የሚያስፈልገው በውስጥ ሕይወት ነውና በሥጋችን የምንፈጽመው አያረክሰንም ብሎ የወደዱትን ማድረግ የድሮ የግሪኮች ፈሊጥ ነው። እነርሱም ሥጋ ርኩስ ነው፤ እግዚአብሔር አይፈልገውም በሥጋችን የምናደርገው ምንም አይደለም በማለት ያሻቸውን ያደርጉ ነበር። ከክርስቲያኖችም በዚህ ከንቱ ፍልስፍናቸው በመታለል የተወሰዱ ነበሩ። እግዚአብሔር ግን ሥጋችንም ነፍሳችንም በቅድስና ይጠበቁ ዘንድ አዟል። "እንግዲህ፥ ወዳጆች ሆይ የዚህ ተስፋ ቃል ካለን፥ በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድስናን ፍጹም እያደረግን <u>ሥጋንና</u> <u>መንፈስን</u> ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እናንጻ"። በተጨማሪም "ዳሩ ግን እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ" ይላል (1ጴጥ.1:15)። ስለዚህ እጆቻችን ከጥፋት ሥራ ተመልሰው መልካምን ሥራ በመሥራት ሌሎችን በመርዳት መቀደስ ይኖርብናል።

"የሰረቀ ከእንግዲህ ወዲህ አይስረቅ፤ ነገር ግን በዚያ ፈንታ ለጎደለው የሚያካፍለው እንዲኖርለት በገዛ እጆቹ መልካምን እየሠራ ይድከም" (ኤፌ.4:28)። በሌላ ሥፍራም "እንግዲህ ወዳጆች በየሥፍራው ሁሉ አለቁጣና አለክፉ ኃሳብ የተቀደሱትን እጆች እያነሱ እንዲጸልዩ እፈቅዳለሁ" ይላል (1ጢሞ.2:8)። እጆቻችን ለእግዚአብሔር የተቀደሱ መሆን እንዳለባቸው ሁሉ እንዲሁም እግሮቻችን ለእግዚአብሔር ተለይተው የተቀደሱ መሆን ይኖርባቸዋል። በዚያን ጊዜ ነው መልካሙን የምሥራች ይዘን መጓዝ የምንችለው። "መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮች እንዴት ያማሩ ናቸው (ሮሜ.10:15፤ ኢሳ.52:7)። ስለዚህ ሁለንተናው የተቀደሰ ሰው ወንጌልን በአፉ ብቻ ሳይሆን በእጁም በእግሩም ይሰብካል።

3) ቅድስና በአንደበታችን:-

ቅድስናን በአንደበታችን የምንለማመደው ከክፉ ንግግር በመጠበቅ ነው። በአንደበታችን ክፉ ስንናገር የምንጎዳው ሁለተኛውን ወገን ብቻ ሳይሆን

እራሳችንንም ጭምር ነው። "አንደበት እሳት ነው አንደበት በብልቶቻችን መካከል ዓመጸኛ ዓለም ሆኗል፤ ሥጋን ሁሉ ያሳድፋል" (ያዕ.3:6)። "ስሙ አስተውሉም ሰውን የሚያረክሰው ወደ አፍ የሚገባ አይደለም ከአፍ የሚወጣው ግን ሰውን የሚያረክሰው ይህ ነው አላቸው" (ማቴ.15:10)።

ኢሳይያስ አንደበቱ በረከሰ ሕዝብ መካከል ይኖር ነበርና አንደበቱ የረከሰ ሆነ፤ አንደበቱ እንዲቀደስ የእግዚአብሔር መልአክ አንደበቱን በእሳት ዳሰሰው
(ኢሳ.6:5-7)። ከዚያም በኋላ ኢሳይያስ ከንፈሮቹ ስለተቀደሱ እግዚአብሔርን ለመላክ ደስተኛ ሆነ (ኢሳ.6:8)። አንደበቱን በማይጠብቅ ሕዝብ መካከል ስለምንኖር አንደበታችንን ከመጥፎ ንግግር መቆጠብ መቻል ይኖርብናል (መዝ.34:12፤ 39:1)። አንደበቱን የማይጠብቅ በመጀመሪያ ደረጃ:-

ሀ) ይዋሻል (መዝ.5:9)።
ለ) ሌላውን ያስታል (መዝ.5:9)።
ሐ) ፌዘኛ ነው (ምሳ.21:23-24)።
መ) ሌላውን በነገር ይወጋል (ምሳ.12:18፤ 26:28)።
ሠ) ሐሜተኛ ይሆናል (ያዕ.4:11)።

በሌላ አንጻር ደግሞ አንደበቱን የሚጠብቅ:-
ሀ) እውነትን ብቻ ይናገራል (መዝ.37:30፤ 71:24)።
ለ) ሌላውን ከጉዳት ያድናል (ምሳ.25:15)።
ሐ) ጸጋን ይሞላል (ቆላ.4:6)።
መ) ለብዙዎች ፈውስ ይሆናል (ምሳ.10:21፤ 12:18፤ 15:4)።

ከዚህም ሁሉ በላይ ቅዱስ የሆነውን ጌታ የምንጠራበት ስለሆነ አንደበታችን የተቀደሰ መሆን አለበት (ያዕ.3:9)፤ አንደበታችን ሲቀደስ ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ዝማሬና ምሥጋና ያማረ ይሆናል (መዝ.119:14)፤ እግዚአብሔር አንደበታችንን በመልካም ቃል ይሞላል (ኢሳ.50:4፤ መዝ.126:2)። እስካለን ድረስ ሁለንተናችን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ መሆን አለበት። እራሳችንን ከፋፍለን ለእግዚአብሔር መስጠት አይኖርብንም፤ እግዚአብሔር የቀደሰልን ሁለተናችንን ነውና፤ እኛም በሁለንተናችን ተቀድሰን መሰጠት አለብን።

ቅድስና ከእግዚአብሔር አገልግሎት ጋር የተያያዘ ስለሆነ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል "እንግዲህ ወዳጆች ሆይ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው" (ሮሜ.12:1)። በቅድስና ሕይወት ማደግ እንዳለብን ከተረዳን በቅድስና ሕይወት ለማደግ የሚያግዙን ምን እንደሆኑ ቀጥለን እንመለከታለን።

4) ቅድስና በመንፈስ ቅዱስ፡-

የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የጸጋ ስጦታዎችን በማከፋፈል ብቻ የሚወሰን አይደለም፤ ውስጣዊ ሕይወታችንን ያጥባል፣ ይቀድሳል። ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፣ ተቀድሳችኋልም፣ ጸድቃችኋልም ይላል (1ቆሮ.6:11) እንዲሁም በቲቶ.3:3-7 እንዲህ ተጽፎል። "ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደድ በተገለጠ ጊዜ እንደ ምህረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ አዳነን እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም፤ ያ መንፈስ በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው" ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እኛን ለማንጻት ከፍተኛ ድርሻ ስላለው ዘወትር ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የምንሆንበትን ጊዜ ማመቻቸት የእኛ ድርሻ ነው (ይሁዳ 20)። መንፈስ ቅዱስ በእሳት ይመሰላል፣ እሳት ያነጥራል ያነጻል። መንፈስ ቅዱስም ልክ እንደ እሳት ያደፈውን ውስጣዊ ሕይወታችንን ያነጥራል፣ ያነጻልም (ሮሜ.12:11)።

ክርስቶስ ኢየሱስ እንደ አንጠረኛ የሚያነጥረው መንፈስ ቅዱስን በመጠቀም ነው (ሚል.3:2-3፣ ማቴ.3:11)። ስለዚህ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚኖረን ልምምድ በአንድ ወቅት ብቻ መቆም የለበትም (ኤፌ.5:18)።

5) ቅድስና በእግዚአብሔር ቃል፡-

"በእግዚአብሔር <u>ቃልና</u> በጸሎት . . . የተቀደሱ ናቸው" 1ጢሞ.4:5 የእግዚአብሔርን ቃል ዘወትር ማንበብ ወይም መስማት ለመቀደስ ይረዳናል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደማናቸውም መጽሐፍ የሚነበብ ቢሆንም እንደማናቸው መጽሐፍ አይደለም፤ አእምሮአችን በእግዚአብሔር ቃል ሲሞላ እውቀት ብቻ ሆኖ የሚቀመጥ አይሆንም፣ ውስጣችንን የመሥራት ኃይል አለው። ሌሎችን መጽሐፍት በማንበብ እውቀትን ሁሉ ብናከማች

ሕይወታችንን የመቀየርና የመለወጥ ኃይል አይኖራቸውም። የእግዚአብሔር ቃል ውስጣችን ሲከማችና ሲሞላ በውስጣችን ያለውን ከንቱ ነገር ሁሉ የማጽዳት እና የመለወጥ ኃይል አለው። "በውኑ ቃሌ እንደ እሳት፣ ድንጋይንም እንደሚያደቅቅ መዶሻ አይደለምን? ይላል እግዚአብሔር" (ኤር.23:29)።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ "እኔ የነገርኳችሁ ቃል መንፈስ ነው፣ ሕይወትም ነው" አለ (ዮሐ.6:63)፤ እንደገናም (በዕብ.4:12) ላይ "የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና የሚሠራም ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነውና ነፍስንና መንፈስንም፣ ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፣ የልብንምስሜትና ኃሳብ ይመረምራል" ይላል። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል በውስጣችን ሲኖር ዝም ብሎ የሚቀመጥ አይሆንም፤ ሕያው ስለሆነ የሚሠራው ሥራ አለው፤ ከሚሠራውቸውም ሥራዎች ውስጥ አንዱ ውስጣችንን ማንጻት ነው። ስለሆነም የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ሊኖረን ይገባል (ቆላ.3:16)። ይሁን እንጂ ቃሉ በውስጣችን መሥራት የሚጀምረው ስናነብና የምንሰማውን ቃል በእምነት ስንቀበል ነው። "ለእነዚያ ደግሞ እንደተነገረ ለእኛ የምሥራች ተሰብኮልናልና፤ ዳሩ ግን የሰሙት ቃል ከሰሚዎች ጋር በእምነት ስላልተዋሃደ አልጠቀማቸውም" (ዕብ.4:2)። ከዚህ በተጨማሪ ስለ እግዚአብሔር ቃል ወደ ፊት በሌላ ክፍል በዝርዝር የምናየው ይሆናል።

6) ቅድስና በጾምና በጸሎት ውስጥ:-

". . . . በጸሎት የተቀደሱ ናቸው" (1ጢሞ.4:5)። እግዚአብሔር ለእኛ ካለው መልካም ኃሳብ ወደ እርሱ ቀርበን ከቅድስናው እንድንካፈል ነው (ዕብ.12:10)። ጾምና ጸሎት ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ ሁኔታ ነው። ስለሆነም ጾምና ጸሎትን ስናዘወትር ከአዘቦቱ ቀን ይልቅ ቅድስና ይሰማናል። የእግዚአብሔር መገኘትም ከምን ጊዜውም ይልቅ ይታወቀናል።

ጾም ወይም ጸሎት በራሱ ይቀድሰናል ማለት ሳይሆን ሕይወታችንን ለመንፈስ ቅዱስ ያመቻቻል፣ የእግዚአብሔርንም ቃል በእምነት እንድንቀበል ይረዳናል፤ ዝንባሌያችንም መንፈሳዊ ይሆናል። መንፈሳዊነትም በተፈጥሮ እንደምንታደለው ዓይነት አይደለም። ስለሆነም ልንለማመደው ይገባናል። (ጾምና ጸሎትን በተመለከተ በተናጠል ወደፊት የምናተኩርበት ጉዳይ ይሆናል)።

እነዚህ የተመለከትናቸው በሁለተኛ ደረጃ ያሉት የቅድስና ሕይወት ደረጃዎች ናቸው። ይህም የመጀመሪያውን ደረጃ በክርስቶስ ካገኘን በኋላ በሁለተኛው ደረጃ እያደግንበት መሄድ ስለሚገባን የቅድስና ልምምድ ነው። ከዚህ በመቀጠል በአጭሩ ሦስተኛውንና የመጨረሻውን የቅድስና ደረጃ እናያለን።

**ሐ. ፍጹም ቅድስና፦**

ፍጹም የሆነ ቅድስና የሚኖረን መቼ ነው? በዚህ ዓለም ስንኖር ቅድስናን እየተለማመድን ማደግ ቢኖርብንም ወደ ፍጹም ቅድስና መድረስ አንችልም። ሌላው ቀርቶ በአንድ ወቅት የደረስንበትንና የተለማመድነውን የቅድስና ሕይወት የምንቀንስበት ሁኔታ ይኖራል። በዚህ ዓለም ስንኖር በሕይወታችን መውጣትና መውረድ ይገጥመናል። ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ የምንናፍቀው ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ ያቆማል። ያን ጊዜ ቅድስናችንም ፍጹም ይሆናል። ከዚያ በኋላ ዳግም ኃጢአት የመሥራት ሁኔታ አይኖርም። በዚህ ዓለም እስካለን ኃጢአት የማድረግና ከቅድስና ሕይወት የመውደቅ ሁኔታ ሊገጥመን ይችላል። ስለዚህም ዘወትር በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ደኅንነታችንን መፈጸም እንዳለብን የእግዚአብሔር ቃል ይመክረናል (ፊልጵ.2:12፤ 2ቆሮ.11፡1-13፤ ዕብ.6:4-8፤ ማቴ.10:22)።

አሁን የጸደቅንና የተቀደስን ብንሆንም ሁለተኛ ተመልሰን ኃጢአት ለመሥራት እንደማንችል ሆነን አልተለወጥንም። ይህ ወደፊት በተስፋ የምንጠብቀው ነው (ሮሜ.8:22-23፤ 2ቆሮ 5:1-5)። መዋቅራችን አሁን የተፈጸመ ቢሆንም አዳማዊ ባህርያችን እንዳለ ነው። ስለዚህ በብዙ ሁኔታ የተያዝንና የተወሰንን ነን፤ ኃጢአት ባይገዛንም ኃጢአት የማድረግ ዝንባሌና ክጃሎት ሊኖረን ይችላል፤ ፍጹም የሆነ ቅድስና ላይ ስንደርስ ተፈጥሮአችን እንዳለ ሙሉ በሙሉ ይለወጣል። አሁን የሚበሰብሰው ሰውነታችን የማይበሰብስና የማያረጅ አካል ሆኖ ይለወጣል (ፊልጵ.3:21)። ያንን ፍጹም አካል ስንለብስ ቅድስናችንም ፍጹም ስለሚሆን እርሱን እያየን ከእርሱ ጋር እንኖራለን። በዚህ ዓለም ስንኖር በቅድስና ሕይወት ማደግና መበላለጥ ቢኖርም ከተወሰድን በኋላ በሰማይ የሚኖረን የቅድስና ደረጃ የሚበላለጥ አይሆንም፤ የሁሉም ቅድስና ፍጹም ይሆናል። በቅድስና ሕይወት ለመኖርና ለእግዚአብሔር ክብር ለመቆም በምናደርገው ተጋድሎ ምክንያት በሰማያዊ አገር የሚኖረን ክብር መበላለጡ የማይቀር ነው። ስለዚህ ጉዳይ በመጨረሻው ምዕራፍ የምናየው ይሆናል።

## III. ክርስቲያን ስንሆን በእግዚአብሔር ፊት የምናገኘው ሥፍራ

1. ዳግም ስንወለድና ክርስቲያን ስንሆን በእግዚአብሔር ፊት የምናገኘው አቋም ምን እንደሆነ ግለጽ።
2. ኃጢአተኛ የሆነ ሰው ከእግዚአብሔር ቁጣ ድኖ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን ማግኘት የሚችለው እንዴት እንደሆነ አብራራ።
3. እግዚአብሔር ጻድቅ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው?
4. ሥጋ የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ በእግዚአብሔር ፊት መጽደቅ እንደማይችል በእግዚአብሔር ቃል ላይ በመመርኮዝ ትንታኔ ስጥ።
5. ኃጢአተኛ ሰው ከእግዚአብሔር ምህረት እንዴት ሊቀበል ይችላል?
6. ከእግዚአብሔር የልጅነትን ሥልጣን ልናገኝ የምንችለው ምን በማድረግ ነው?
7. የእግዚአብሔር ልጆች ስለ መሆናችን በምን ማረጋገጥ እንችላለን? (ሮሜ.8:16)
8. የእግዚአብሔር ልጆች ስለመሆን በእስራኤላውያን፣ በመላእክትና በክርስቲያኖች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
9. በያዕ.3:9 እና በዘፍ.1:26 ላይ ያለው ኃሳብ ተመሳሳይ ነው፤ ከሮሜ.8:29 ጋር ያለውን ልዩነት አብራራ።
10. ከቆላ.3:10 ላይ "የፈጠረውን" የሚለው ቃል ማንን ሲያመለክት ነው? 'አዲሱን ሰው' የሚለውስ ማንን ያመለክታል?
11. ጌታ ክርስቶስን እንደምንመስል በፍጹም የምናውቀው መቼና እንዴት ነው?
12. በ1ቆሮ.5:1 ላይ 'ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን' የሚለው ቃል ምንን ያመለክታል?
13. የእግዚአብሔርን ማንነትና የእግዚአብሔርን ባሕርይ ለይተህ አስረዳ።
14. እግዚአብሔር መንፈስ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው?
15. እግዚአብሔር የሕይወት ምንጭ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው?
16. እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ ሁሉ ቦታ ሊገኝ የሚችለው እንዴት ነው?
17. እግዚአብሔር መነሻና መድረሻ የለውም ስንል ምን ማለታችን ነው?
18. በፍጥረት ሥራና በደህንነት ሥራ የተገለጡትን የእግዚአብሔር ባህርያት ለይተህ ግለጽ።
19. እግዚአብሔር በሥፍራ አይወሰንም የሚለው አባባል ፍጥረት ባይኖር ኖሮ ምን ትርጉም ሊሰጥ ይችላል?
20. የእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት በምን ሥራ ውስጥ የተገለጠ ነው?
21. የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት እንዴት ታወቀ?
22. ከፍጥረት ጋር በተያያዘ ሁኔታ የእግዚአብሔር ቅድስና ምን ትርጉም አለው?
23. እግዚአብሔር በተናገረው መሠረት መሥራቱ የትኛውን ባሕርይውን ይገልጣል?
24. ጽድቅና ፍትህ ልዩነታቸው ምንድን ነው?
25. 'እውነት' አንጻራዊነት የለውም ስንል ምን ማለታችን ነው?
26. ከመለኮት ባሕርይ ተካፋይ እንድንሆን ተሰጠን ስንል ከማንነቱ ተካፋይ ሆንን ማለት ነውን?
27. የእግዚአብሔር ባህርያት 'በፍጥረት ሥራ'፣ 'በደህንነት ሥራ' የተገለጡ ናቸው ብለን አይተናል፤ እኛ እንድንካፈል የተሰጠን መለኮታዊ ባሕርይ የትኛው ነው?
28. በ2ጴጥ.1:4 ላይ "ከመለኮት ባሕርይ ተካፋይ" የሚለውንና በ1ዮሐ.3:10 "ዘሩ

በእነርሱ ይኖራል" የሚለው አባባል ከምን ጋር በማነፃፀር እንደቀረበ አስረዳ።

29. እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ሁሉን ካወረሰን ለእርሱ ምን ይቀርለታል?
30. እግዚአብሔር ሊያወርሰን ስላለው ርስት እርግጠኛ እንድንሆን የሰጠን መያዣ ምንድን ነው?
31. የእስራኤላውያን ከነዓንን መውረስ ከእኛ ሰማያዊውን ርስት መውረስ ጋር ያለውን ምሳሌነት በማነጻጸር አስረዳ።
32. በብሉይ ኪዳን የነበረውንና በአዲስ ኪዳን ያለውን የክህነት አፈጻጸም ሥርዓት በማነጻጸር አስረዳ።
33. በብሉይ ኪዳን የነበረው የሊቀ ካህናት አገልግሎት በአዲስ ኪዳን በማን ተተካ?
34. በብሉይ ኪዳን የነበረውንና በአዲስ ኪዳን ያለውን የሊቀ ካህናት አገልግሎት በማነጻጸር ልዩነቱን አስረዳ።
35. የክህነት አገልግሎቱን በተመለከተ እንደ ብሉይ ኪዳን ካህናት ሕግና ሥርዓት በዝርዝር አልተሰጠንምና የክህነት አገልግሎታችንን የምንፈጽመው በምን መልኩ ነው?
36. በቆሮንቶስ የነበሩ ክርስቲያኖች 'ቅዱሳን' ተብለው መጠራታቸው በክርስቶስ በማመናቸው ምክንያት ከሆነ እኛ በዚህ ዘመን ያለን በክርስቶስ ያመንን ቅዱሳን ተብለን ለመጠራት ያስችለናልን?
37. የመጀመሪያውን የቅድስና ደረጃ በክርስቶስ ካገኘን በዚህ ዓለም ሳለን በቅድስና ሕይወት ለማደግ እኛ ያለን ድርሻ ምንድን ነው?
38. ዓለማዊነት የሚገኘው በልባችን ውስጥ ከሆነ ከሰዎች ተሰውረን በመኖር ከዓለማዊነት ባሕርይ ማምለጥ የምንችል ይመስልሃል? ተወያይበት።
39. ቅድስናን በኑሮአችን መለማመድ ያለብን እንዴት ነው?
40. በአንደበታችን ቅድስና እንዲኖር ምን ማድረግ አለብን?
41. በቅድስና ሕይወት ለማደግ የሚረዱን ነገሮች ምን እንደሆኑ ግለጽ።
42. የቅድስና ሕይወታችንን በተመለከተ መንፈስ ቅዱስ ያለው ድርሻ ምንድን ነው?
43. የእግዚአብሔር ቃል ቅድስናን በተመለከተ በሕይወታችን ያለው ሥራ ምን እንደሆነ አስረዳ።
44. ጾምና ጸሎት በራሱ ሊቀድሰን ይችላልን? ካልቻለ ጾምና ጸሎት ማዘውተሩ በቅድስና ሕይወት ለማደግ እንዴት ሊረዳን ይችላል?
45. ፍጹም ቅድስና ላይ የምንደርሰው መቼ ነው?
46. በዚህ ዓለም እያለን ወደ ፍጹም ቅድስና መድረስ እንችላለን ብለህ ታስባለህ? የማንደርስ ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው?
47. በሰማያዊ አገር ስንኖር የቅድስና ደረጃ ያለ ይመስለሃል?
48. በዚህ ዓለም ስንኖር በቅድስና ሕይወት ለመኖር የምናደርገው ጥረት በዚያኛው ዓለም ምን ልዩነት ያመጣል? ተወያይበት።
49. እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ እኛን ማተሙ ምን ያሳያል?
50. በደኅንነት ሥራ ከተገለጡት የእግዚአብሔር ባሕርያት አንዱ ጥሩነት ነው ስንል ከዚህ በላይ ሊሆን አይችልም ለማለት ካልሆነ ምን ማለት ነው?
51. እግዚአብሔር በአካልና በቅርጽ የማይወሰንበት ምክንያት ምንድን ነው?
52. ድንኳን የሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ሲፈርስ ምትኩ ምን ይሆናል?

## IV. በክርስትና ሕይወት የምናድግበት አቅጣጫ

የክርስትና ሕይወት ዳግም ለመወለድ የሚያበቃ አይደለም፤ ዳግም ከመወለድ በኋላ ማደግ ይኖራል። ዳግም መወለድ በተፈጥሮ መንገድ እንዳይደለ ሁሉ እንዲሁ መንፈሳዊ ዕድገት የተፈጥሮን ሕግ የሚከተል አይሆንም።

ሕይወት ያለው ሁሉ እስከተወሰነ ደረጃ በመጠን ያድጋል፤ መንፈሳዊ እድገት ግን የማያቋርጥና መጨረሻ የሌለው እድገት ሲሆን የተፈጥሮ ሕግን የሚከተል አይደለም። ስለሆነም መንፈሳዊ ዕድገት በመጠን የመጨመር ጉዳይ ሳይሆን በመንፈሳዊ ሕይወት ማደግ በውስጥ ሰውነት መጠንከርና መጎልመስን የሚመለከት ነው። "በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነከሩ ክርስቶስ በልባችሁ በእምነት እንዲኖር እንደ ክብሩ መጠን ይስጣችሁ" ይላል (ኤፌ.3:16)። ይሁን እንጂ መንፈሳዊ ዕድገት በዓይን የማይታይ ወይም በመጠን የማይለካ ባሆንም ዕድገት ይኖራል፤ በዚህ ምክንያት የየክርስቲያኑ መንፈሳዊ ሕይወት የተለያየ ነው። በክርስትና ሕይወት የምናድግበት አቅጣጫ ብዙ ቢሆንም ዋና ዋና የሆኑትን ከዚህ በመቀጠል እንመለከታለን።

### 1. <u>**እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግ**</u>

በ1929 ዓ.ም. ወደ ሂማሊያ ተራራ ወጥቶ ወዴት እንደደረሰ ያልታወቀ ሱንደር ሲንግ የሚባል እግዚአብሔር ያስነሳው ሐዋርያ ነበር። በአንድ ወቅት ሱንዳር ሲንግ ወደ ዱር ሄዶ ሲጸልይ ጌታ ተገልጾለት በእግሩ ሥር ቁጭ ብሎ ብዙ መንፈሳዊ ነገሮች ሲጠይቀውና ሲረዳ እርሱን ስለ ማወቅ ጌታ እንዲህ አለው:-

> "በዕውርነት የተወለደ ሰው ስለ ቀለማት ዓይነቶች ቢጠይቁት ጥቁር፤ ነጭ፤ ቀይ፤ ቢጫ፤ ቅጠልያ እያለ በየስማቸው ሊሰይማቸው ይችላል። ነገር ግን በወሬ እየሰማ አጥንቷቸው ነው እንጂ አላያቸውምና ኅብራቸውን አስተካክሎ ሊያስረዳ ከቶ አይቻለውም፤ ዓይኑ እስኪገለጽ ድረስም ኅብራቸውን ሊያስተውል አይችልም። እንዲሁም ሰው የተማረና ሊቀ ሊቃውንት እንኳን ቢሆን መንፈሳዊ ዓይኑ ካልበራለት ስለ እኔ ቢናገር ብቻ እንጂ እኔን ሊያውቀኝ አይችልም" አለው።

ኢዮብ እግዚአብሔርን በዝና ያውቀው ነበር፤ እንደዚያም ሆኖ

እግዚአብሔርን የሚፈራና ጻድቅ ሰው ነበር። ይሁን እንጂ ስለ ደረሰበት መከራ እግዚአብሔርን መሞገት ፈልጎ ነበር፤ ስለዚህም በክርክሩ እንደሚረታው እንኳን አስቦ እንዲህ አለ:-

> "እንድመልስለት አብረን ወደ ፍርድ እንገባ ዘንድ፣ እርሱ እንደ እኔ ሰው አይደለም። እጁን በሁለታችን ላይ የሚያኖር ዳኛ በመካከላችን ምነው በተገኘ! በትሩን ከእኔ ላይ ያርቅ፣ ግርማውም አያስፈራኝ እናገርም ነበር፣ አልፈራውምም ነበር፣ በራሴ እንዲህ አይደለሁምና" (ኢዮ.9:32-35)።
>
> ነገር ግን ሁሉን ለሚችል አምላክ መናገር እፈልጋለሁ። ከእግዚአብሔር ጋር ለመዋቀስ እሻለሁ" (ኢዮ.13:3)።
>
> "የሰው ልጅ ከባልንጀራው ጋር እንደሚሟገት ሰው በእግዚአብሔር ፊት ለመሟገት ምነው በቻለ!" (ኢዮ.16:21)። እርሱን ወዴት እንዳገኘው ምነው ባወቅሁ! ወደተቀመጠበት ሥፍራ ምነው በሄድኩ! በፊቱ ሙግቴን አዘጋጅ ነበር፣ አፌንም በማስረጃ እሞላው ነበር" አለ (ኢዮ.23:3)።

ኢዮብን ከንግግሩ እንደምንረዳው እግዚአብሔርን እንደሚገባ የሚያውቀው ይመስላል። ስለሆነም እግዚአብሔርን ሁሉን የሚችል አምላክ ይለዋል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ መሆኑን ሰምቷልና፤ በኋላ ግን እግዚአብሔር ራሱ ተገለጠለት፣ እንዲህም ብሎ ተናገረው:-

> "ያለ እውቀት በሚነገር ቃል ምክርን የሚያጨልም ይህ ማነው? እንግዲህ እንደ ሰው ወገብህን ታጠቅ እጠይቅሃለሁ፣ አንተም ተናገረኝ" (ኢዮ. 38:1-3) አዲሱ የ1980 ዓ.ም. ትርጉም እንዲህ ያቀርበዋል:- "ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር በአውሎ ንፋስ ውስጥ ሆኖ ኢዮብን እንዲህ አለው:- ማስተዋል በጎደለው ከንቱ ንግግር የእኔን ምክር የምታቃልል ለመሆኑ አንተ ማነህ? እስቲ ጎበዝ ከሆንክ ቀጥ ብለህ ቁምና እኔ የማቀርብልህን ጥያቄ መልስ"።

ኢዮብ እግዚአብሔርን ካየ በኋላ የመለሰው መልስ እንዲህ የሚል ነበር:-

> "እግዚአብሔር ሆይ! አንተ ሁሉን ነገር ማድረግ እንደምትችል አውቃለሁ። የአንተን ዕቅድ ማሰናከል የሚችል የለም፣ እውቀት ሳይኖረው ምክሬን የሚያቃልል ይህ ማነው? ብለህ ጠይቀኸኛል። እኔ ምንም የማላውቅ ስሆን ላስተውላቸው ስለማይቻለኝ ድንቅ

ነገሮች ተናግሬአለሁ። እኔ ስናገር አድምጠኝ። ጥያቄም ሳቀርብልህ መልስ ስጠኝ ብለኸኛል፤ እኔ እስካሁን ስለ አንተ የማውቀው ሰዎች የነገሩኝን በመስማት ብቻ ነበር፤ አሁን ግን በዓይኖቼ አየሁህ ስለዚህ የተናገርኩት ነገር ሁሉ እኔን እራሴን አሳፍሮኛል፤ ከዚህም የተነሳ በአመድና በትቢያ ላይ ተቀምጬ ንስሐ እገባለሁ" አለ (ኢዮ.42:1-6)።

ስለ እግዚአብሔር ማንነት ብዙ መጻፍና ብዙ መናገር ይቻል ይሆናል፤ እግዚአብሔርን በግል ሕይወት ማወቅ ግን ከዚህ ይለያል። ስለ እግዚአብሔር ለማወቅ ከተፈለገ የሥነ መለኮት ትምህርት ቤት ገብቶ የዶክትሬት ዲግሪ ማግኘት ይቻላል። እግዚአብሔርን ለማወቅ ከተፈለገ ግን ሁለት መንገዶች አሉ፤ እነርሱን አብዝቶ መለማመድ ያስፈልጋል፤ እነርሱም በክርስቶስ ኢየሱስ <u>**የቅድስናና የጸሎት ሕይወት**</u> ናቸው። እግዚአብሔርን ለማየት ከተፈለገ ቀደም ብለን እንዳየነው የቅድስና ሕይወት ያስፈልጋል፤ ያለ ቅድስና እግዚአብሔርን ማየት አይቻልምና (ዕብ.12:14)። እግዚአብሔር ባልተቀደሰ ሕይወት ውስጥ አይገለጥም፤ በተቀደሰ ሕይወት ግን ይገለጣል።

አንድን ሰው በውል ለማወቅ ከተፈለገ በየጊዜው ኅብረት ማድረግ ያስፈልጋል። ስለ አንድ ዝነኛ ሰው ሳናየው ብዙ መናገር እንችላለን፤ በደንብ የሚያውቁት ግን አብረውት የሚውሉት ናቸው። በቅርብ ከሚያውቁት እኩል አስተካክለን መናገር እንችል ይሆናል፤ ነገር ግን አብረውት ከሚውሉት እኩል አወቅነው ማለት አይደለም። ከላይ እንዳየነው ብዙ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር በሰሙት መሠረት በትክክል ይናገሩ ይሆናል፤ እነርሱ ግን በሕይወታቸው አያውቁትም። ስለዚህ እግዚአብሔርን በቅርብ ለማወቅ ከተፈለገ በመንፈስ ቅዱስ በመታገዝ ከእርሱ ጋር የማያቋርጥ ኅብረት ማድረግ ያስፈልጋል (2ቆሮ.12:1-3፤ 1ዮሐ.1:3፤ 3:24፤ 4:13፤ ዮሐ.15:26፤ 16:14)።

የእግዚአብሔር ቃል "ኅብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው" ይላል (1ዮሐ.1:3)። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ አስፈላጊ ነው፤ ያም የኅብረት ጊዜ ጸሎት ነው። በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የረጅም ጊዜ ኅብረት በየቀኑ ካደረግን እግዚአብሔርን በማወቅ እናድጋለን። ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዲህ አለ "ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ" (2ጴጥ.3:8)።

በጸጋ እደጉ የሚለውን አባባል ኋላ እንመጣበታለን፤ አሁን ግን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት እደጉ በሚለው ላይ እናተኩራለን። ይህ ክፍል በ1980 ዓ.ም. አዲሱ የአማርኛ ትርጉም እንዲህ ተጽፏል፦ "ይልቅስ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እርሱንም በማወቅ እደጉ"።

ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ "በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ በእግዚአብሔር እውቀት እያደረጋችሁ በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ በጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን" ይላል (ቆላ.1:10-12)። በአዲሱ የአማርኛ ትርጉም እንደገና ብናይ "የመልካም ሥራ ፍሬ ቢገኝባችሁ እግዚአብሔርንም በማወቅ ልታድጉ ትችላላችሁ"። በሁለቱም ሥፍራ የምናገኘው ኃሳብ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስንና እግዚአብሔርን በማወቅ እደጉ የሚል ነው።

እግዚአብሔር በዓይን አይታይም፤ መጠንም የለውም፤ በምን ሁኔታ ነው እርሱን በማወቅ ማደግ የሚቻለው? የሚል ኃሳብ ሊመጣ ይችላል። ምን ጊዜም እግዚአብሔርን በሥጋዊ ዓይን ማየት አይቻልም፤ መጠን የለውምና በአእምሮአችን ቀርጸን ወይንም ስለን ማየት አንችልም።

እግዚአብሔር ስለ እራሱ እንዲህ ይላል፦ "ውኆችን በእፍኙ የሰፈረ፣ ሰማይንም በስንዝሩ የለካ፣ የምድርንም አፈር በመስፈሪያ ሰብስቦ የያዘ፣ ተራሮችን በሚዛን ኮረብቶችንም በሚዛኖች የመዘነ ማነው?" (ኢሳ.40:12)። ሌላውን እንተውና እግዚአብሔር ቢፈልግ በምድር ላይ ያለውን ውኃ በእፍኙ መያዝ ይችላል ማለት ነው። እንደምናውቀው የምድር ሁለት ሦስተኛው እጅ ውኃ ነው፤ ስለዚህ የእጁ እፍኝ ይህን ያህል ስፋት ካለው እርሱን በአእምሮአችን እንዴት መሳል እንችላለን? ለነገሩ የእጁ እፍኝ በምድር ያለውን ውኃ ይይዛል ብንል እንኳን ወሰነው ማለት ነው። እርሱ ግን በምንም አይወሰንም፤ ቀደም ሲል እንዳየነው እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ መንፈስ ደግሞ በቅርጽና በአካል አይወሰንም።

በዚህ ቃል ውስጥ እንደምናየው እግዚአብሔር ቢፈልግ ሰማይን በስንዝሩ መለካት እንደሚችል ነው። የሰማይ መነሻና መድረሻ ማለትም ጫፍና ጫፍ የለውም፤ ስለሆነም በቢሊዮን የሚቆጠሩ ከዋክብት ሰማይን አልሞሉትም። ሳይንቲስቶች እንደሚነግሩን ፀሐይ እራሷ ምድርን አንድ ሚሊዮን እጥፍ ትበልጣለች ይላሉ። ፀሐይን ደግሞ አንድ ሚሊዮን ጊዜ የሚበልጡ

በቢሊዮን የሚቆጠሩ ከዋክብት አሉ፤ እነርሱም ሰማይን አልሞሉም። እግዚአብሔር ግን ከፈለገ ሰማይን በስንዝሩ ይለካል። ስለዚህ ማንም ሰው የእግዚአብሔርን ታላቅነት በአእምሮው መሳል አይችልም።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግ እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ይህ የሚሆነው በቅድስና ሕይወት እየኖርን በጸሎት ሕይወት ውስጥ ስንገባ ከእግዚአብሔር ጋር የማያቋርጥ ኅብረት ማድረግ ስንጀምር ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ የእግዚአብሔር ክብር፣ ታላቅነት፣ ሁሉን ቻይነት እየበራልንና እየተገለጸልን ይሄዳል። ከዚያ በኋላ እኛው ራሳችን እግዚአብሔር ታላቅ መሆኑን መናገር እንጀምራለን፤ እግዚአብሔርንም ባወቅነው ልክ እንመካበታለን፣ እናከብረዋለን፤ ከዚያም እግዚአብሔርን ልናገለግለው እንናፍቃለን። ማንም ሰው የእግዚአብሔርን ክብር ሲያይ የሚናፍቀው ነገር ቢኖር እርሱን ማገልገል ነው። ስለዚህ እግዚአብሔርን በማወቅ የምናድገው በዚህ መልኩ ነው እንጂ ትልቅነቱን በአእምሮአችን እየሳልን አይደለም።

2. <u>**በጸጋ ስጦታዎች ማደግ**</u>

"ነገር ግን በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ" (2ጴጥ.3:18)። ቀደም ሲል እግዚአብሔርንና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ስለ ማደግ አይተናል፤ በመቀጠል ደግሞ በጸጋ ስለ ማደግ በሚለው ኃሳብ ላይ እናተኩራለን። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ማደግ እንዳለብን ሁሉ በጸጋም ማደግ እንደሚኖርብን ይናገራል። ጸጋ ማለት ነፃ የሆነ የእግዚአብሔር ስጦታ ማለት ነው። ወደ ዋናው ነጥብ ከመሄዳችን በፊት ጸጋን በሦስት ከፍለን እናያለን።

አንደኛው አጠቃላይ ጸጋ የምንለው ሲሆን፡-ይህም ለፍጥረት ሁሉ የተሰጠ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። አየር፣ የፀሐይ ብርሃን፣ የፀሐይ የሙቀት፣ ዝናብ የመሳሰሉት ሁሉ ነፃ የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው (ማቴ.5:45፤ 6:25-30)። ፍጥረት ሁሉ የእነዚህ ነፃ ስጦታ ተጠቃሚ ነው። ስለ እነዚህ ነፃ ስጦታዎች እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ ሰዎች በጣም ጥቂቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ብዙ ሰዎች ተፈጥሮ ያስገኘው ነው ብለው ለእግዚአብሔር አድናቆት የላቸውም። ነገር ግን ተፈጥሮን በራሱ ያስገኘው ምንም ነገር የለም፤ ተፈጥሮን ያስገኘው የሚቆጣጠረውም እግዚአብሔር ነው። ይሁን እንጂ ሰው ሁሉ ከተፈጥሮ ለሚያገኘው ጥቅም ዋጋ መክፈል ቢኖርበት እንዴት መኖር ይችል ይሆን?

ሁለተኛው አዳኝ ጸጋ ወይም ልዩ ጸጋ የምንለው ነው። ይህም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኝ ደኅንነት ነው (ሮሜ.3:24)። ጸጋ የሚለው ቃል ከደህንነት ጋር በተያያዘ ሁኔታ በክርስትና ሃይማኖት ብቻ የታወቀ ነው። ቢሆንም በሕዝበ ክርስቲያኑ ዘንድ የተለመደ ቃል ሆኖ ሳለ የጸጋ ተጠቃሚዎች ግን በጣም ጥቂቶች ናቸው። እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ለመዋጀት ጸጋን እንዳዘጋጀ እያወቁ ሕግን በመጠበቅ በሥራችን እንድናለን ብለው የእግዚአብሔርን ጸጋ እየጣሉ ክርስቲያኖች ነን የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም። ሐዋርያው ጳውሎስ "ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን አውቀን ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ አምነን እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል" ይላል (ገላ.2:16)። እግዚአብሔር ያዘጋጀው ጸጋ ለሁሉም የሚበቃ ስለሆነ የጸጋው ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስፈልገው እራስን ዝቅ አድርጎ ወደ እግዚአብሔር የጸጋ ዙፋን በእምነት በመቅረብ ነው (ዕብ.4:16)።

ሦስተኛው የጸጋ ስጦታ ዓይነት **በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጠን የእግዚአብሔር ጸጋ** ነው (ሮሜ.12:6)። በዚህ ክፍል የምናተኩረው በጸጋ ስጦታዎች አጠቃቀም ላይ ሳይሆን በጸጋ ማደግ በሚለው ኃሳብ ላይ ብቻ ይሆናል። በ2ጴጥ.3:18 ላይ "በጸጋ እደጉ" ሲል በመንፈስ ቅዱስ በሚሰጠን ጸጋ ስለ ማደግ ያሳስበናል። በዚህ በሦስተኛ የጸጋ ስጦታ የሚካኑት በክርስቶስ ኢየሱስ ደም የተዋጁና ዳግም ተወልደው ክርስቲያን የሆኑ ብቻ መሆናቸውን ማወቅ ይኖርብናል። ስለሆነም ቅዱሳን ሁሉ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታ አላቸው። "ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደመሆናችሁ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ" (1ጴጥ.4:10)።

እግዚአብሔር ለቅዱሳን ሁሉ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎችን የሰጠበት ምክንያት በመጀመሪያ እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማክበር ያስችለን ዘንድ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ እርስ በርሳችን ለመተናነጽ እንድንችል ነው (ዮሐ.4:24፤ 1ቆሮ.14:26)። ስለሆነም የጸጋ ስጦታን የተቀበለ ለግል ጥቅሙ እንደተሰጠው አድርጎ ማንም ሊያስብ አይገባውም። በመንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎችን መስጠቱ ለጋራ ጥቅም እንጂ ለግል ጥቅም አይደለምና።

"ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ መገለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል" ይላል

(1ቆሮ.12:7)። በዚህ ጥቅስ ውስጥ "ለእያንዳንዱ" በሚለው ቃልና "ለጥቅም" በሚለው ቃል መካከል በታዋቂነት የቀረ ቃል አለ፣ ይህም "ለጋራ" የሚል ቃል ነው። አስተውለን ካላየን ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል የሚለውን ቃል "ለጥቅሙ" ይሰጠዋል ብለን በቀላሉ ልናልፈው እንችላለን። የ1980 ዓ.ም. በአዲሱ አማርኛ ትርጉም እንደዚህ ተጽፏል "ለእያንዳንዱ መንፈስ ቅዱስ የመገለጥ ስጦታ የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው"። በተጨማሪም ሌሎች የእንግሊዝኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞችን ማመሳከር ይቻላል።

ስለ ጸጋ ስጦታዎች ሲነሳ ብዙ ክርስቲያኖች ቶሎ የሚያስታውሱት በ1ቆሮ.12:8-11 ላይ ስለተጻፉት ዘጠኙ የጸጋ ስጦታዎች ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ.12:8-11 ላይ ሲጽፍ ለምሳሌ ያህል ብሎ ባይጽፍም እነዚህ ለምሳሌ የጠቀሳቸው የጸጋ ስጦታዎች ናቸው። በዚህ ክፍል ውስጥ ያልጠቀሳቸው ነገር ግን በሌላ መልእክቱ "የጸጋ ስጦታ" ብሎ የጠቀሳቸው ሌሎችም የጸጋ ስጦታዎች መኖራቸውን በግልጽ መረዳት እንችላለን። በሮሜ.12:6-8 ላይ የተጠቀሱትን የጸጋ ስጦታዎች ብናይ አገልግሎት፣ ማስተማር፣ መምከር፣ መስጠት፣ ማስተዳደር፣ በ1ቆሮ.12:8-11 ላይ አልተጠቀሱም። ይህ ለማስረጃ ያህል ነው እንጂ በሌሎች መልእክቶች ውስጥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የተገለጹ ብዙ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች መኖራቸውን እንረዳለን።

ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህን የጸጋ ስጦታዎች የጠቀሰው አዘውትረው በቤተ ክርስቲያን የሚገለጹ በመሆናቸው እንጂ ዓላማው የጸጋ ስጦታዎችን በቁጥር ማቅረቡ አልነበረም። የጸጋ ስጦታዎች የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ስለሆኑ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በቁጥር ሊወሰን እንደማይቻል ልንገነዘብ ይገባናል።

የቃላት አጠቃቀም ጉዳይ ሆነና ነው እንጂ በገላ.5:22 የመንፈስ ፍሬ ተብለው የተዘረዘሩትም ቢሆኑ የጸጋ ስጦታዎች ናቸው። ጸጋ ነፃ ስጦታ ነው ካልን ዘንዳ እነዚያም የመንፈስ ፍሬዎች እንዲሁ በጸጋ የተሰጡን እንጂ እኛ ስላደረግነው በጎ ሥራ የተሰጡን አይደሉም፤ ወይም ለአንዳንዶች እንደሚመስላቸው መንፈሳዊ ከመሆናችን የተነሳ የምናፈራቸው ባሕርያት አይደሉም። ምክንያቱም ከእኛ የተገኙ ፍሬዎች ሳይሆኑ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ናቸውና። መንፈስ የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰውን መንፈስ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስን ነው።

የመንፈስ ፍሬ ብሎ በመጀመሪያ ደረጃ የጠቀሰው ፍቅርን ነው(ገላ.5:22)። በ1ቆሮ.12:31 ላይ ደግሞ ከሁሉ የሚበልጥ የጸጋ ስጦታን በብርቱ ፈልጉ ብሎ እርሱም ፍቅር መሆኑን በማያያዝ በምዕራፍ 13:1 ላይ ይገልጻል። ስለዚህ የመንፈስ ፍሬ ተብሎ የተጠቀሰው "ፍቅር" የጸጋ ስጦታ ከሆነ ሌሎች ከፍቅር ጋር ተያይዘው የተጠቀሱትም የመንፈስ ፍሬዎች ናቸው ማለት እንችላለን። በተጨማሪም "እምነት" የሚለውን ቃል የመንፈስ ፍሬ ከሚለው ጋር በገላ.5:22 ላይ የተጠቀሰ ሲሆን በ1ቆሮ.12:8-11 ላይ ደግሞ የጸጋ ስጦታ በማለት ተጠቅሶ እናገኘዋለን።

እነዚህ የመንፈስ ፍሬዎች በግል ሕይወታችን እንድንታነጽበት የተሰጡን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ወይም በውስጣችን የሚኖሩ የመንፈስ ቅዱስ ባሕርያት ሲሆኑ የጸጋ ስጦታዎች የምንላቸው ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ለጋራ ጥቅም የተሰጡን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ወይንም የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ናቸው። ለጋራ ጥቅም መባሉ እነዚህ የጸጋ ስጦታዎች ሌሎችን ለማነጽ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ሲሠራ እኛም በጋራ እንደምንታነጽበት ለማመልከት ነው። መንፈስ ቅዱስ በማናቸውም ሁኔታ በውስጣችን ሲያልፍ ሳያንጸንና ሳይባርከን አያልፍምና።

የመንፈስ ፍሬ የምንለውም ሆነ የጸጋ ስጦታዎች እያደጉ መሄድ እንዳለባቸው ልንገነዘብ ይገባናል። ስለሆነም እንዴት ማደግ እንደሚችሉ "በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ አስፈላጊ ነገሮች" በሚለው ክፍል ውስጥ ወደፊት በዝርዝር የምናየው ይሆናል። ከዚህ ቀጥለን የጸጋ ስጦታዎችን ከአገልግሎት ጋር በተያያዘ መልኩ በአራት ክፍለን ለማየት እንሞክራለን።

1ኛ. በመድረክ አገልግሎት ጊዜ የሚገለጡ የጸጋ ስጦታዎች ሲሆኑ እነዚህም ከማስተማርና ከመስበክ ጋር የተያያዙ ናቸው።

2ኛ. ከአስተዳደር ወይም ከአገዛዝ ጋር ተያይዘው የሚገለጡ የጸጋ ስጦታዎች ናቸው። የጥበብና የእውቀት ጸጋዎች በሁሉም የአገልግሎት ክፍል ውስጥ አስፈላጊ ቢሆኑም በይበልጥ ግን በእነዚህ በሁለቱ የአገልግሎት ክፍሎች ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ናቸው። እውቀት የተሰውረውን ነገር በመንፈስ ቅዱስ መረዳት ሲሆን ጥበብ ደግሞ የተገለጠውን እውቀት በሥራ ላይ የማዋል ዘዴ ነው። ስለሆነም በመድረክ አገልግሎትና በአስተዳደር ሥራ ላይ ያለ ሰው እነዚህ የጸጋ ስጦታዎች ፍሬ ሊኖረው አይችልም።

3ኛ. የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በቀጥታ የሚያልፍበት የአገልግሎት ጸጋ ነው። ይህም ትንቢት መናገር፣ መገለጥ፣ ታምራትን ማድረግ የመሳሰሉትን የጸጋ ስጦታዎችን የሚይዝ ነው። 'የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚያልፍበት አገልግሎት' ሲባል በሌሎች የአገልግሎት ክፍሎች ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አይኖርም ለማለት አይደለም። ነገር ግን በሦስተኛ የአገልግሎት ክፍል ውስጥ በቀጥታ መንፈስ ቅዱስ ካላለፈበት በስተቀር ማንም ሰው ጸጋው አለኝ ብሎ ተዘጋጅቶ ሊፈጽማቸው አይችልም።

ትንቢት ለመናገር፣ ታምራትንም ለማድረግ ትልቅ እምነት ከሰዎች ይጠበቃል ብለን እናስብ ይሆናል። ይሁን እንጂ የእምነትን ኃይል በሚጠቀምባቸው ሰዎች ውስጥ የሚያሳልፈው መንፈስ ቅዱስ ነው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በራሱ ጊዜ ድንቅና ታምራትን ማድረግ ሲፈልግ ወይንም ከእግዚአብሔር ዘንድ መልእክት ለማስተላለፍ ሲፈልግ የሚጠቀምባቸውን ሰዎች በእምነት ይሞላና በማነሳሳት ማድረግ የፈለገውን ይፈጽማል እንጂ ማንም ሰው በራሱ ጊዜ ተዘጋጅቶ ከእግዚአብሔር የሆነውን ትንቢት ሊናገር ወይም መገለጥን ሊያመጣ ወይንም ድንቅና ታምራትን ማድረግ አይችልም። የመድረክ አገልግሎትና የአስተዳደር አገልግሎት ጸጋ ያለው አገልጋይ በራሱ ጊዜ ተዘጋጅቶ በመንፈስ ቅዱስ ላይ በመታመን አገልግሎቱን መፈጸም ይችላል።

4ኛ. ቅዱሳንን በገንዘብና በጉልበት በማገልገል የሚገለጥ ስጦታ ነው። በሮሜ.12:7-8 ላይ "አገልግሎት ከሆነ በአገልግሎታችን እንትጋ . . . የሚሰጥም በልግስና ይስጥ" የሚል ቃል እናገኛለን። ሁሉንም ዓይነት የእግዚአብሔር ሥራ አገልግሎት ብለን እንጠራዋለን። መስበክ፣ ማስተማርና ማስተዳደርም ቢሆን አገልግሎት ነው። ነገር ግን በሮሜ.12:7-8 ላይ አገልግሎት ተብሎ የተጠቀሰው የጉልበት አገልግሎት ወይም የልግስና አገልግሎትን ነው። ከመጀመሪያው ሲጠቀስ "እንደተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ አለን" ብሎ ስለጀመረ አገልግሎትና መስጠት የጸጋ ስጦታዎች ናቸው ማለት እንችላለን። ምንም እንኳን መስጠት ሁሉንም የሚመለከት ቢሆንም በልግስና ለመስጠት በዚህ ጸጋ የተዋቡ ክርስቲያኖች መኖራቸውን ያመለክታል።

ስለሆነም እነዚህ የጸጋ ስጦታዎች ሁሉም ባለማቋረጥ ማደግ ይኖርባቸዋል። ወደ አገልግሎት ከመሰማራት በፊት በጸጋ ማደግ ያስፈልጋል። በጸጋ የሚያድጉ ክርስቲያኖች አገልግሎታቸው ሊሸፈን አይችልም፤ በጸጋ

ያደጉ ክርስቲያኖች አገልግሎታቸው አይሰለችም፤ በጸጋ ስጦታ ባደጉ አገልጋዮች የምትጠቀም ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ድርቀት አይይዛትም። ጸጋን በምትለማመድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ ጸጋው ገብቶ የሚያገለግል አገልጋይ ይታወቃል።

ስለዚህም በአገልግሎት ከመጠመድ በፊት በጸጋ ማደግ አስፈላጊ ነው፤ ሁሉም በተሰጠው ጸጋ ቢያድግ የአገልግሎቱን ሥፍራ ያውቃል፤ የአገልግሎቱን ሥፍራ ያወቀ ከሆነ ደግሞ በአገልግሎት ሥፍራ መቆም ይችላል፤ ሁሉም የአገልግሎታቸውን ሥፍራ አውቀው በሚያገለግሉበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትርምስ አይኖርም። ቤተ ክርስቲያንም አገልግሎቷን እየፈጸመች ወደ ክርስቶስ ሙላት መድረስ ትችላለች።

3. <u>**በእግዚአብሔር ፍቅር ማደግ**</u>

"ጌታ እርስ በእርሳችሁ ያላችሁን ለሁሉም የሚሆን ፍቅራችሁን ያብዛ ይጨምር" (1ተሰ.3:13)። ". . . ፍቅራችሁ በእውቀትና በማስተዋል ሁሉ ከፊት ይልቅ እያደገ እንዲበዛ ይህን እጸልያለሁ" የክርስትና ሕይወት የተመሠረተው በፍቅር ላይ ነው፤ ጌታ ነፍሱን አሳልፎ መስጠቱ ስለ ፍቅር እንደሆነ ተናግሯል። "ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለም" (1ዮሐ.15:13)። "እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቷልና በዚህ ፍቅርን እናውቃለን" (1ዮሐ.3:16)።

ፍቅር በመልካም ስጦታ ይገለጣል፤ ይሁን እንጂ መልካም ስጦታ ሁል ጊዜ የፍቅር መግለጫ ላይሆን ይችላል። የእግዚአብሔር ስጦታ ግን ሁልጊዜ ከፍቅር የተነሳ ነው፤ ስጦታው ቀርቶ ቁጣው እንኳን በፍቅር ነው። እግዚአብሔር ፍቅሩን ለዓለም የገለጠው በመልካም ስጦታ ብቻ ሳይሆን አንድ ልጁን መስዋዕት አድርጎ በመስጠት ነበር፤ እርሱም ከመልካም ስጦታ ሁሉ በላይ ነው። እንዲህም ሆኖ የዓለም ሕዝብ የእግዚአብሔርን ፍቅር አላወቀም። "በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኳልና" (1ዮሐ.4:9)። እግዚአብሔር ልጁን በመስጠት ብቻ አላቆመም፤ ፍቅሩን የገለጠበትን ስጦታ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ለተቀበሉት ደግሞ ፍቅሩን ሰጠ። ሰው ፍቅሩን በተለያየ መንገድ መግለጥ ይችላል፤ ፍቅርን ግን መስጠት አይችልም። እግዚአብሔር ግን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በአማኞች ሕይወት ውስጥ ፍቅሩን ያፈሳል። "በተሰጠን በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋው አያሳፍርም" (ሮሜ.5:5)።

ከራሱ ልብ ፍቅርን አውጥቶ በሚወደው ሰው ልብ ውስጥ ፍቅርን ማፍሰስ ማን ይችላል? እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር በልባችን አፈሰሰና አቀመሰን፤ ስለዚህ እግዚአብሔር እንደሚወደን በስጦታው ብቻ ሳይሆን ፍቅሩን ተቀብለን አየን። "የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ" (1ዮሐ.3:1)። ይህም ፍቅር በአንድ ወቅት በልባችን ፈስሶ የሚያቆም ሳይሆን ዘወትር ወደ እርሱ በቀረብን ቁጥር አብዝቶ የሚፈስስ ነው።

የጌታ ፍቅር ስፋቱና ርዝመቱ ቁመቱና ጥልቀቱ ምን ያህል እንደሆነ አይታወቅም እጅግ ሰፊ ነው፣ እጅግም ጥልቅ ነው። (ኤፌ.3:18)። የእግዚአብሔር ፍቅር በሚሊዮን በሚቆጠሩ አማኞች ልብ ውስጥ ፈሷል፤ አሁንም ይህ ፍቅር ሳያቋርጥ በልባችን ሲፈስ ቢውል እርሱ አይቀንስም፣ እርሱ ፍቅር ነውና እኛ በፍቅር ውስጥ፣ ፍቅሩም በእኛ ውስጥ እንዲኖር ይሻል (ዮሐ.15:9)።

የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን እየፈሰሰና እየጨመረ ሲሄድ በሦስት አቅጣጫ የምንለማመዳቸው ነገሮች አሉ፤ እነዚህን በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን።

ሀ. አንዱና የመጀመሪያው ነገር በእግዚአብሔር መወደዳችንን የበለጠ ማረጋገጥ ነው። እግዚአብሔር አንድ ልጁን ለዓለም በመስጠት ፍቅሩን ገለጠ፤ ይህም በስጦታ የተገለጠ ነው። አንዳንድ ሰዎች እነርሱ እግዚአብሔርን የሚወዱትን ያህል እግዚአብሔር ቢወደን ብለው የሚመኙ አሉ። ምክንያቱም ፍቅሩ በልባቸው ስላልፈሰሰ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ለሚታዘዙት ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጋር ፍቅሩን በልባቸው በማስፍሰስ እንደሚወዳቸው ያረጋግጣል (ሐዋ.5:32)። ታዲያ በእግዚአብሔር መወደድን ከማረጋገጥ የበለጠ ለሰው የሚያስፈልገው ነገር ምን አለ?

እስራኤላውያን በዚህ መልኩ የእግዚአብሔርን ፍቅር ስላልተለማመዱ ችግር በገጠማቸው ቁጥር የእግዚአብሔርን ፍቅር ይጠራጠሩ ነበር። እነርሱ የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚለኩት በዘዳ.28:1-14 በተዘረዘሩት ምድራዊ በረከቶች ነበር።

በአንድ ወቅት ከምርኮ የተመለሱት እስራኤላውያን ሕይወታቸው ፣

በማጉረምረም ተሞልቶ ነበር፤ በቤታቸውም በረከት አልነበረምና በእርሻቸውም በረከት ጠፋ፤ የሚያቀርቡት መስዋዕት ተቀባይነት አጣ። ስለዚህ እግዚአብሔር ክፉዎችን እንጂ እኛን አይወድም አሉ፣ እንዲያውም እግዚአብሔር በአመጸኞች ደስ ይለዋል ብለው አሙት፤ እግዚአብሔርንም ማገልገል ጥቅም የለውም፣ ትእዛዙንም መጠበቅ ኃዘንተኛ መሆን ነው ብለው አሰቡ (ሚል.2:17፣ 3:14)።

በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በነብዩ ሚልክያስ በኩል "እወዳችኋለሁ፣ እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም፣ እናንተ የያዕቆብ ልጆች ሆይ ስለዚህ የጠፋችሁ አይደላችሁም" ብሎ ተናገራቸው (ሚል.1:2፣ 3:6)። እነርሱ ግን እንደምትወደን በምን እናውቃለን? አሉ፤ ምክንያቱም በእግዚአብሔር መወደዳቸውን የሚለኩት በምድራዊ በረከት ነበርና፤ ስለዚህ ምድራዊ ኑሮ አልሳካ ሲላቸው እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው መቀበል አቃታቸው። ምድራዊውን በረከት ያጡትም ትእዛዙን ባለመጠበቃቸው ነበር (ሚል.1:6-8፣ 2:13፣ 3:7-9)። እርሱ በኪዳኑ የታመነ ቢሆንም እነርሱ በኪዳኑ አልጸኑም ነበርና በዘዳግም 28:15-68 ላይ የተፃፈው መርገም ተከተላቸው።

እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን የጠራን በሰማያዊ በረከት ሁሉ ሊባርከን ነው፤ "በክርስቶስ በሰማያዊ ሥፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ" (ኤፌ.1:3)። አሁንም ቢሆን ዝንጉ የሆኑ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ፍቅር በዚህ በምድራዊ ስጦታ ሊያረጋግጡ ይፈልጋሉ፤ ስለሆነም አንድ ቀን የፈለጉትን ሲያጡ በእግዚአብሔር ላይ ማጉረምረማቸው አይቀርም። እግዚአብሔር ልጁን እንኳን ሳይራራ አሳልፎ የሰጠን ስለሆነ ሌላውን ነገር ሁሉ አብሮ እንደሚሰጠን የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ይናገራል "ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለራሳችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም" (ሮሜ.8:32)።

ክርስቶስ ባለጠጋ ሆኖ በእርሱ ድኅነት እኛ ባለጠጎች እንሆን ዘንድ ስለ እኛ ብሎ ድኃ እንደሆነ ተጽፎልናል (2ቆሮ.8:9)። ይሁን እንጂ በዚህ ዓለም ባለጠጋ እሆናለሁ ብሎ ክርስትናን የሚቀበል ቢኖር ተሳስቷል። "በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን" (1ቆሮ.15:19)።

የእግዚአብሔርንም ፍቅር በምድራዊ ነገር ለማየት የሚሹ ሰዎች የተመኙትን ሲያጡ የእግዚአብሔርን ፍቅር መጠራጠር ይጀመራሉ፤ እግዚአብሔር ግን አብዝተው ለሚጠጉት ልጆቹ የሚሞላቸው ፍቅሩን ነው። እነርሱ በፈተና ሁሉ ውስጥ ቢገቡ፣ የችግር ማዕበል ቢከባቸው፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር አይጠራጠሩም፤ ያ በልባቸው የፈሰሰ የእግዚአብሔር ፍቅር እንደ እሳት ስለሚነድ ለአንድ አፍታ እንኳን የእግዚአብሔርን ፍቅር ሊጠራጠሩ አይችሉም።

ለ. በመንፈስ ቅዱስ በልባችን የፈሰሰ ፍቅር እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችን እንድንወደው ያደርጋል።

በብሉይ ኪዳን ሰዎች "እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ኃይልህ ውደድ" የሚል ሕግ ተሰጥቷቸው ነበር (ዘዳ.6:5)። ይህም ፊተኛውና ከሁሉም የሚበልጥ ትዕዛዝ ነው፤ እግዚአብሔር ፍቅር ሆኖ ፍቅርን ይፈልጋል። እስራኤላውያን ግን ይህንን ትእዛዝ መፈጸም አልተቻላቸውም። ምክንያቱም ትእዛዙ እግዚአብሔር አምላካቸውን መውደድ እንዳለባቸው ያሳስባቸዋል እንጂ አያግዛቸውም። ለአዲስ ኪዳን ሕዝብ ትዕዛዙ እንዳለ ሆኖ ፍቅሩን ጨምሮ ሰጠን፤ በልባችን የፈሰሰው የእርሱ ፍቅር መልሰን እርሱን እንድንወደው አስቻለን። "እርሱንም ሳታዩት ትወዱታላችሁ" (1ጴጥ.1:8)።

ለመውደድ ማየት ያስፈልጋል፤ እርሱን ግን ሳናየው እንዴት ልንወደው ቻልን? ምስጢሩም ይህ ነው እግዚአብሔር ልጁን ከሁሉ አብልጦ ይወደዋል (ማር.9:7)። ስለዚህ በልባችን ያፈሰሰው ፍቅር ልጁን የሚወድበት ፍቅር ስለሆነ ያ በልባችን የፈሰሰ የእግዚአብሔር ፍቅር እርሱን ባናየውም እንድንወደው ያደርገናል። ስለዚህ ነው ጌታ "ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባም፤ ከእኔ ይልቅ ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ አይገባም" ያለው (ማቴ.10:37)። የእግዚአብሔርን ፍቅር ተቀብሎ ከእርሱ ይልቅ ሌላውን አብልጦ የሚወድ ቢኖር የእርሱ ሊሆን አይችልም፤ ለምን ቢባል ከእርሱ የተቀበልነውና በውስጣችን የፈሰሰው የእግዚአብሔር ፍቅር ልጁን ከሁሉ አብልጦ የሚወድበት ፍቅር ስለሆነ ነው።

ይሁን እንጂ ፍቅር በአንድ ወገን ምርጫም ስለሆነ ከእርሱ ይልቅ ሌላውን የሚወድ አይጠፋም፤ በኤፌሶን የነበረ መጋቢ ቀደም ሲል ይህን ፍቅር

ተለማምዶ ነበር፤ ኋላ ግን ቀስ በቀስ ለጌታ ያለው ፍቅር መቀነስ ጀመረ። ሆኖም በአገልግሎቱ ይተጋ ስለነበር ለጌታ ያለውን ፍቅር በአገልግሎት ማካካስ እንደጀመረ አልታወቀውም። ጌታ ግን "የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና ንስሐ ግባ፤ አለበለዚያ መቅረዝህን እወስድብሃለሁ" አለው (ራዕ.2:1-2)።

በዚህ ዘመን ያሉ ብዙ አገልጋዮች ለጌታ ያላቸውን ፍቅር በአገልግሎት ብዛት ማረጋገጥ ይፈልጋሉ፤ እርሱ ግን በልባችን ውስጥ ያለውን ፍቅር ይመዝናል። ስለሆነም መቅረዙ እንዳይወሰድበት የሚሻ ታማኝና ልባም ባሪያ ከሁሉም አስቀድሞ ለጌታው ያለውን ፍቅር ይጠብቃል። ፍቅር ሳይኖር ሁሉ ቦታ በአንድ ጊዜ መገኘት ቢቻልስ ምን ይጠቅማል?

"በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮህ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ። ትንቢትም ቢኖረኝ ምስጢርንም ሁሉና እውቀትንም ሁሉ ባውቅ፣ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ። ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፣ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም። . . ." (1ቆሮ.13:1-13)።

እነዚህን ቃላት መተንተን አያስፈልግም፤ ሁሉም በግልጽ ተቀምጠዋል። በእግዚአብሔር ፍቅር ተሞልተን ስንትረፈረፍ ብቻ ነው ለእነዚህ የፍቅር መግለጫዎች እውነተኛ መልስ መስጠት የምንችለው። የፍቅርን ምንነት በቃላት መግር አይቻልም፤ በመንፈስ ቅዱስ ስንሞላ ያን ጊዜ የእግዚአብሔርን ፍቅር እንማራለን።

የእግዚአብሔር ፍቅር መለኪያ የለውም፤ እርሱም ሰፍሮ አይሰጥም። አእምሮን አያስትም እንጂ የእግዚአብሔር ፍቅር ሲበዛ እንደ እብድ ያደርጋል። እብድ ካለው ባህርይ ይሉኝታን አያውቅም፣ ክብሩን አይጠብቅም፣ ዝናንም አይሻም፣ ቢያዋርዱትም ቅር አይለውም፣ ተስፋ አይቆርጥም፣ ከፍ ከፍ ቢያደርጉትም ትእቢት አይሰማውም፣ በገንዘብ ብዛት አይታለልም። ስለዚህ እብድን የሚያከብረው የለምና ያገኘው ሁሉ ይወግረዋል፤ ቢሆንም ዝም ማሰኘት አይቻልም፤ ቢገርፉት፣ ቢወግሩት፣ ቢያስሩት፣ ቢጠፍሩት መለፍለፉን አይተውም፤ እንዲሁም ሆኖ የሚሰማው አያጣም።

የእግዚአብሔር ፍቅር ሲበዛ እንዲህ ያደርጋል፤ የፍቅር ዋጋ ከሁሉ ይበልጣል ብሎ የጻፈልን ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ እብድ የተቆጠረበት ጊዜ ነበር። እርሱም እንደ እብድ ለሚቆጥሩት መልስ ሲሰጥ "እብዶች ብንሆን ለእግዚአብሔር ነው" አለ (2ቆሮ.5:13)። እንደ እብድ ያስቆጠረው ምንድን ነው? ቢባል ስለ ክርስቶስ በየገበያውና በየአደባባዩ መስበኩ ነው። ታዲያ ሰዎች እንደ ለፍላፊና እንደ እብድ አድርገው ቆጠሩት (ሐዋ.17:18)። እርሱ ግን ይህንን የማደርገው የክርስቶስ ፍቅር ግድ ብሎኝ ነው ይላል (2ቆሮ.5:14)።

በቆሮንቶስ የነበሩ አንዳንድ ክርስቲያኖች ይልቁንም አገልጋዮች የነበሩ ይንቁት ነበር። የሚሰጡት ምክንያት አይታወቅም፣ እርሱ ከሚሰጠው መልስ እንደምንረዳው ግን የሐዋርያነት ሥልጣን የለውም ብለው ሳይሆን አይቀርም (1ቆሮ.9:1)። ወንጌልን በመጀመሪያ የሰበከላቸውና ያደራጃቸው እርሱ ስለነበር ሐዋርያነቱን መካድ አይችሉም፤ ስለዚህ የሐዋርያነቴ ማረጋገጫ እናንተው ናችሁ ይላቸዋል (1ቆሮ.9:2)። ማንም ትምክህቴን ከንቱ ከሚያደርግብኝ ሞት ይሻለኛል ያለበትም ጊዜ ነበር (1ቆሮ.9:15)። እራሱን እያዋረደ በመኖሩ ንቀውታል፤ እንደሌሎች ሐዋርያትም መብቱን ባለመጠቀሙ የሐዋርያነት ሥልጣን ባይኖረው ነው ብለው አስበው ይሆናል። እርሱ ግን "ከእነዚህ ከዋነኞቹ ሐዋርያት በአንድ ነገር እንኳን እንደ ጎደልሁ ራሴን አልቆጥርም። . . . ወይስ የእግዚአብሔርን ወንጌል ያለ ደመወዝ ስለ ሰበክሁላችሁ፣ እናንተ ከፍ እንድትሉ ራሴን እያዋረድሁ ኃጢአት አድርጌ ይሆንን? እኔ ራሴ ካልበደልኋችሁ ከዚህ በቀር ከሌላ ቤተ ክርስቲያን ያነሳችሁበት በምን እኮ ነው? ይህን በደሌን ይቅር በሉኝ" በማለት ልብ በሚሰብር ሁኔታ ይወቅሳቸዋል (2ቆሮ.11:5-9)።

ሐዋርያው ጳውሎስ ሥልጣን እንዳለው ሰው ሆኖ ራሱን ጠብቆ አልኖረም፤ በሄደበት እንደ እብድ በድንጋይ ይወገራል፣ በበትር ይደበደባል፣ በጅራፍ ይገረፋል፣ ይህ ሁሉ ሲደርስበት የክርስቶስ ፍቅር ግድ ብሎት እንደሆነ ይናገራል፤ ሰዎች ግን ናቁት፤ ፍቅር ያስንቃልና (መኃ.ዘ.8:7)።

ፍቅር ሌላውን ሁሉ እስኪረሳ ድረስ የሚያስበውና የሚያወራው ስለሚያፈቅረው ብቻ ነው። ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ ሥፍራ ሳይመርጥ፣ ልዩነት ሳያደርግ፣ የሚያፈቅረውን ክርስቶስን ለሁሉ ሰበከ። መቼም እብድ ባለበት ብዙ ሁከት ይሆናልና ሐዋርያው ጳውሎስ ባለበት

ከተማ ሁሉ ሁከትና መናወጥ ይሆን ነበር (ሐዋ.16:20፤ 17:5, 13፤ 18:29፤ 21:30፤ 23:9)።

ጳውሎስ ወንጌልን በመስበኩ በደረሰበት መከራ ተማር አያውቅም፤ እንዲያውም ስለሚያፈቅረው ክርስቶስ የበለጠ መከራን ለመቀበል እድል ቢያጋጥመውም በሞቱ እንኳን እርሱን እንዲመስል ይመኝ ነበር (ፊል.3:11)። ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ወይስ ጭንቀት፤ ወይስ ስደት፤ ወይስ ረሃብ፤ ወይስ ራቁትነት፤ ወይስ ፍርሃት፤ ወይስ ሰይፍ ነውን ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደተጻፈ ነው። በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን ሞት ቢሆን፤ ሕይወት ቢሆን፤ መላእክትም ቢሆኑ፤ ከፍታም ቢሆን፤ ዝቅታም ቢሆን ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ ጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቻለሁ" ይላል (ሮሜ.8:35-39)።

ሐዋርያው ጳውሎስ መግለጽ የፈለገው የክርስቲያኖችን ብርቱነት ሳይሆን የክርስቶስን ፍቅር ነው። በክርስቶስ ፍቅር የተሞላ ደካማ ሰው እንኳን ቢሆን ከአሸናፊዎች ይበልጣል። መከራና ችግር ቢበዛበት የማይረታ ሰው የለም። በዓለም ብርቱ የተባለ ሰው እንኳን ይህ ሁሉ ቀርቶ ከእነዚህ በአንዱ ምክንያት ከሚወደው ሰው ሊለይ ይችላል። የጌታ ፍቅር የበዛለት ግን ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሁሉ በየተራ ቢገጥሙት ከክርስቶስ ሊለዩት አይችሉም፤ እነዚህን ሁሉ ተረማምዶ ወደ ጌታው ይደርሳል፤ ያ የክርስቶስ ፍቅር ብርቱ ሰንሰለት ስለሆነ ከእነዚህ በአንዱም ሊበጠስ አይችልም። ይህንን ለማረጋገጥ ግን በእግዚአብሔር ፍቅር መሞላት ያስፈልጋል፤ ያ የፍቅር ምንጭ አሁንም ይፈልቃል። የብዙዎች ፍቅር ምንጭ በቀዘቀዘበት በዚህ በመጨረሻው ትውልድ እንኳን አላቋረጠም፤ የተጠማም ይምጣ አሁንም እግዚአብሔር ፍቅር ነው።

ሐ. የእግዚአብሔር ፍቅር እርስ በርስ እንድንዋደድ ያስችለናል፡- ሁለተኛው የአሪት ሕግ ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የሚል ነው (ማቴ.22:39)። ይሁን እንጂ ለእስራኤላውያን ይህንንም መፈጸም አልተቻላቸውም። በአዲስ ኪዳን ጌታ "እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ እኔ እንደወደድኳችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ" አለ (ዮሐ.13:34)። የትኛው ትእዛዝ ነው የሚከብደው? ያለ ጥርጥር የአዲስ ኪዳኑ ትእዛዝ ይበልጣል፤ ምክንያቱም

እርሱ በወደደን ልክ እንድንዋደድ ያዝዛልና፤ እርሱ እንዴት ነው የወደደን ብንል፣ "እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቷልና በዚህ ፍቅርን አወቅን" ይላል። ስለዚህ እኛ ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን እንድንሰጥ ይገባናል ይላል (1ዮሐ.3:16)።

ለብሉይ ኪዳን ሰዎች የተሰጣቸው ሕግ ነው፤ ለእኛ የተሰጠን ግን መንፈስ ቅዱስ ነው፤ ከላይ እንዳየነው በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር ፍቅር አለ፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በመንፈስ ቅዱስ በልባችን ሲፈስ እርስ በርሳችን ያፋቅረናል። ይህ እንደሚሆን ስለሚያውቅ ነው "እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ" ያለው (ዮሐ.13:35)። ምክንያቱም የእርሱ የሆኑት ሁሉ እርስ በርሳቸው ፍቅር እንደሚኖራቸው እርግጠኛ ነው። ከዚህ ተነስቶ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ "ጌታ እርስ በርሳችሁ ያለውን ለሁሉም የሚሆን ፍቅራችሁን ያብዛ ይጨምር" ያለው (1ተሰ.3:13)።

ታዲያ ፍቅርን የሚጨምርና የሚያበዛ እርሱ እስከሆነ ድረስ ፍቅር ቢያንሰኝ እኔ ለምን እጠየቃለሁ የሚል ይኖር ይሆናል። ፍቅር ሰጭ እግዚአብሔር ነው፤ ነገር ግን ቀደም ሲል እንዳየነው በአንድ በኩል ፍቅር ምርጫ እንደሆነ ማሰብ ይኖርብናል። ስለዚህ አንድ ሰው ከፈለገ ሰው ሁሉ የጠላውን መውደድ ይችላል፤ ደግሞም ሰው ሁሉ የወደደውን መጥላት ይችላል። ሐዋርያው ጳውሎስ ፍቅርን ተከታተሉት ያለው ለዚህ ነው (1ቆሮ.14:1)። ስለዚህ ምርጫችንን ፍቅር ስናደርግ ያን ጊዜ ለሁሉ የሚሆን ፍቅርን በመንፈስ ቅዱስ በልባችን ያፈሳል። የሚጠሉንን እንኳን ለመውደድ ምርጫ ብናደርግ የሚጠሉንን ለመውደድ የሚያስችለንን ፍቅር ከእርሱ እናገኛለን። እግዚአብሔር የሚጠሉትን ይወዳቸው የለምን? (ሮሜ.5:10)። ለፍጥረታዊ ሰው የሚጠሉትን መውደድ የማይቻል ነገር ነው፤ ነገር ግን ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ይሆናል (2ቆሮ.5:17)። ስለዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ሲፈስስ አሮጌውን ባህርያችንን ይለውጥና ፍቅር ይሞላናል፤ ከዚያም የሚጠሉንን እንኳን መውደድ አንቸገርም፤ የብዙዎች ፍቅር በቀዘቀዘበት በዚህ በመጨረሻው ትውልድ እንኳ ፍቅርን ምርጫ ማድረግ ይቻላል። "ከአመፃም ብዛት የተነሳ የብዙዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች" ተብሎ የተነገረን ይህ ያለንበት ትውልድ ነው (ማቴ.24:12)። ቢሆንም የብዙዎች ተባለ እንጂ የሁሉም አልተባለምና ከጥቂቶቹ ውስጥ ለመሆን ምርጫ ማድረግ ይቻላል።

ሰዎችን ገለል አድርገው እግዚአብሔርን ብቻውን ማገልገል የሚሹ ሰዎች ይኖራሉ። አገልጋይ ማለት የእግዚአብሔር ተላላኪ ማለት ነው፤ የእግዚአብሔር መልእክት ፍቅሩ ነው፤ ስለዚህ ያለ ፍቅር ወደ ሰዎች ቢኬድ የእግዚአብሔርን መልእክት ማበላሸት ይሆናል። የፍቅር ቃል በአፍ ብቻ ቢከማች ምን ዋጋ አለው? "ልጆች ሆይ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ" (1ዮሐ.3:18)። ስለዚህ ፍቅራችን ሁል ጊዜ ትኩስ እንዲሆን ከፈለግን የፍቅር አባት ወደ ሆነው ጌታ መቅረብ አለብን። እርሱ ግብዝነት የሌለበትን ለሁሉ የሚሆን ፍቅር ያበዛልናል።(1ተሰ.3:13)። ለሰዎች የሚኖረን ፍቅር በሦስት ዋና ዋና ነገሮች ላይ ተደግፎ ማደግ እንዳለበት ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

1ኛ. **በእውቀትና በማስተዋል ላይ መመሥረት አለበት፤**

"ፍቅራችሁ በእውቀትና በማስተዋል ሁሉ ከፊት ይልቅ እያደገ እንዲበዛ ይህንን እጸልያለሁ" (ፊልጵ.1:11)። ማናቸውንም ነገር ለማወቅና ለመረዳት ረጋ ብሎ ማየትና ማስተዋል ያስፈልጋል። ማስተዋል ማለት በስሜት ከመነዳት ይልቅ አርቆ ማየት ወይም ጠለቅ አድርጎ ማሰብ ነው። ስለዚህ ማስተዋል የጎደለው ሰው ለማፍቀርም ሆነ ለመጥላት የፈጠነ ይሆናል። ፍቅር እሳት ነው፤ ስለሆነም በውስጣችን ግልብልብ እሳት እንዳይሆን ማስተዋል ያስፈልገናል። እውቀትና ማስተዋል የጎደለው ፍቅር ዘለቄታ አይኖረውም፤ እንደ ገለባ እሳት ቶሎ ተያይዞ ቶሎ ሊጠፋ ይችላል። በማስተዋል የተያዘ ፍቅር ግን እንደ በረሃ ግንድ ነው፤ ቀስ ብሎ ይያያዝና መሃል ላይ ሳይጠፋ እስከ መጨረሻው ይዘልቃል።

2ኛ. **በንጹሕ ልብና በንጹሕ ሕሊና ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፤**

"የትእዛዝ ፍጻሜ ግን ከንጹሕ ልብና ከበጎ ሕሊና . . . የሚወጣ ፍቅር ነው" (1ጢሞ.1:5)። ፍቅር በአንድ መልኩ ስሜት ነው፤ ፍቅር ቃሉ አንድ ቢሆንም የስሜት ዓይነቱ ብዙ ነው፤ ፍቅር ነው ብለን ሁሉንም ዓይነት ስሜት በውስጣችን ማስተናገድ የለብንም፤ ሰውን ሁሉ መውደዳችን ከንጹሕ ልብ የመነጨ መሆኑን ማረጋገጥ አለብን። የራሳችንን ሕሊና ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ሕሊና መጠንቀቅ ደግሞ ይገባናል። ሰዎች ፍቅራችንን በበጎ ሕሊና እንዲቀበሉት ማድረግ የእኛ ፈንታ ነው። ያለማስተዋል የሚገለጥ ፍቅር በጎ ሕሊና ሊያሳጣ ይችላል፤ በሰዎች ዘንድ በጎ ሕሊና ማጣት ሰዎችን ያሳጣናል። ያለንበት ጊዜ ከላይ እንዳየነው አብዛኛው ሰው ሕሊናው የቆሸሸበት ዘመን ነው፤ ሕሊናው የቆሸሸበት ሰው ደግሞ ንጹህ ፍቅርን አያስብም።

3ኛ. **በግብዝነት ላይ ያልተመሠረተ መሆን አለበት፤**

"የትእዛዝ ፍጻሜ ግን . . . ግብዝነት ከሌለበት የሚወጣ ፍቅር ነው" (1ጢሞ.1:5)። ግብዝነት ያልሆኑትን መሆን ማለት ነው (ስለ ግብዝነት ወደ ፊት የምናይበት ክፍል ይኖራል)። እውነተኛ ፍቅር ባለበት ግብዝነት እንደ እድፍ ነው። እውነተኛ ፍቅር ባለበት የግብዝነት ፍቅር ይታወቃልና የሌለውን ፍቅር ከመግለጽ መቆጠብ ማስተዋል ነው።

የግብዞች ፍቅር ያለ ምርኩዝ አይቆምም፤ እግዚአብሔር ግን እንዲሁ ያለ ምርኩዝ እንደወደደን እኛም እርስ በርሳችን እንዲሁ እንድንዋደድ አዝዞናል። ፍቅር ለሚወዱት ብቻ ከሆነ ከግብዝነት የነፃ አይሆንም። የትእዛዝ ፍጻሜ ግን ግብዝነት ከሌለበት ፍቅር የሚወጣ ነው። በጥቂቶች ላይ የተመሠረተ ፍቅር ግብዝነት ያለበት ነው። ይሁን እንጂ እውነተኛውን ፍቅር ራሳችን መፍጠር አንችልም፤ እውነተኛውን ፍቅር የምናገኘው ከጌታ ብቻ ነው። ስለዚህ ጌታ በወደደን ፍቅር እርስ በርሳችን መዋደድ ብንመርጥ ለሁሉም የሚሆን ፍቅር እርሱ ሊሰጠን እንደሚችል ልንገነዘብ ይገባናል።




4ኛ. **የእግዚአብሔርን ድምጽ መለየት፤**

"በጎቼ ድምጼን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል" (ዮሐ.10:26)። በመጀመሪያ እንደተመለከትነው መንፈሳዊ ዕድገት የማያቋርጥና መጨረሻ የሌለው ዕድገት ነው። ስለሆነም በሁሉም አቅጣጫ እንደሚገባ ለማደግ ረጅም ዓመታት ሊወስድ እንደሚችል መዘንጋት የለብንም። ጊዜ ለሁሉም ነገር አስፈላጊ ቢሆንም በመንፈሳዊ ዕድገት ግን ለሁሉም እኩል አይሠራም፤ ለምን ቢባል ጊዜን የበለጠ የሚጠቀምበት ቀድሞ ሊያድግ ስለሚችል ነው። ኤሊሁም ለኢዮብና ለጓደኞቹ ዕድሜን በተመለከተ እንዲህ አለ "እኔ በዕድሜ ታናሽ ነኝ እናንተ ግን ሽማግሌዎች ናችሁ፤ ስለዚህ ሰጋሁ የዓመታትም ብዛት ጥበብን ባስተማረች ነበር፤ ነገር

ግን በሰው ውስጥ መንፈስ አለ ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ማስተዋልን ይሰጣል በዕድሜ ያረጁ ጠቢባን አይደሉም፤ ሽማግሌዎች ፍርዱን አያስተውሉም ስለዚህ ስሙኝ" አለ (ኢዮ.32:6-10)።

ስለ እግዚአብሔር ድምጽ ስናስብ የሰውን ድምጽ በጆሮአችን እንደምንሰማው የሰው ድምጽ ዓይነት አድርገን ገምተን ይሆናል። የምንሰማው ድምጽ አየሩን እየገፋ ወይም እያርገበገበ የሚመጣ አይደለም። የእግዚአብሔር ድምጽ ወደ ሰው ሲመጣ ምንም ዓይነት ድምጽ ማስተላለፊያ አያስፈልገውም፤ አየር በሌለበት ሕዋ ውስጥም እንኳን ያልፋል።

የእግዚአብሔር ድምጽ ወደ እኛ ሕይወት የሚመጣባቸው ብዙ መንገዶች አሉት። በየትኛውም መንገድ ይምጣ ነገር ግን ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ድምጽ መለየት መቻል አለበት፤ በጎቼ ድምጼን ይሰማሉ ይላልና። ደግሞም በሌላ ሥፍራ "እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውንም ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና፤ የሚመጣውንም ይነግራችኋል" ይላል (ዮሐ.16:13)። ስለዚህ ክርስቲያን የእውነትን ቃል ከእግዚአብሔር መቀበል የሚችለው የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማት ከቻለ ነው።

የእግዚአብሔርን ድምጽ መለየት የማይችል ክርስቲያን ተመሳስለው በሚመጡ ድምጾች መወሰዱ አይቀርም። የእግዚአብሔርን ድምጽ አስመስሎ ሰይጣን በመሸንገል ብዙዎችን ያስታልና (2ቆሮ.11:3፤ ራዕ.12:9)። ስለዚህ የእግዚአብሔር ድምጽ ወደ እኛ እንዴት እንደሚመጣና አስመስሎ የሚመጣውንም ድምጽ እንዴት መለየት እንደምንችል በጥንቃቄ ማጤን ይኖርብናል። የእግዚአብሔር ድምጽ ወደ እኛ የሚመጣበት ብዙ መንገድ ቢኖርም ዋና ዋና የሆኑትን ሦስት መንገዶች እናያለን።

አንደኛው መንገድ በቋንቋችን የምንሰማው የእግዚአብሔር ድምጽ ነው። በዚህ ጊዜ የምንሰማውን የእግዚአብሔር ድምጽ በአጠገባችን ያሉ ሌሎች ሰዎች ላይሰሙት ይችላሉ። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የብላቴናው ሳሙኤል ልምምድ ነው። ሳሙኤል ብላቴና በነበረበት ጊዜ የእግዚአብሔር ታቦት ባለበት ተኝቶ ሳለ እግዚአብሔር ደጋግሞ ጠራው። ሳሙኤል ዔሊ የጠራው መስሎት ደጋግሞ ወደ ዔሊ ይሮጥ ነበር። ዔሊ በወቅቱ

ከእርጅናው የተነሳ ዓይኖቹ ፈዝዘው ነበር፡ ቢሆንም ጆሮው በደንብ ይሰማ ነበር። ምክንያቱም ሳሙኤል ዔሊ የጠራው መስሎት ዔሊን እነሆ አለሁ ሲለው አልጠራሁህም ይለው ነበር። ለሳሙኤል ይሰማው የነበረው የእግዚአብሔር ድምጽ ለዔሊ ግን አይሰማውም ነበር። ዔሊ የእግዚአብሔርን ድምጽ ያልሰማበት ምክንያት ከላይ እንደተጠቀሰው የእግዚአብሔር ድምጽ አየሩን እየሰነጠቀ የሚመጣ አልነበረም።
እግዚአብሔር ድምጹን ማሰማት የፈለገው ለሳሙኤል ብቻ ነው። እግዚአብሔር ድምጹን ማሰማት ከፈለገ እንደ መብረቅ ለሕዝቡ ሁሉ ማሰማት ይችላል፤ በዚህም መልኩ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ድምጹን ያሰማበት ብዙ ጊዜ መኖሩን እናስተውላለን (ዘጸ.19:16-23፤ ዮሐ.12:28-29)። በጉባዔው ውስጥ ለአንድ ሰው ብቻ የሚሰማ የእግዚአብሔር ድምጽ ለሌሎች ላይሰማ እንደሚችል መገንዘብ አለብን። በዚህ ሁኔታ የምንሰማው የእግዚአብሔር ድምጽ ከምንችላቸው ቋንቋዎች ውስጥ በአንደኛው ሊሆን ይችላል፤ ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ላይ "ሳውል ሳውል ስለምን ታሳድደኛለህ?" ብሎ ተናገረው፤ ጳውሎስ የእብራይስጥ ቋንቋ ይችል ስለነበር በዚህ ወቅት ጌታ የተናገረው በእብራይስጥ ቋንቋ እንደነበር እናስተውላለን። የብሉይ ኪዳን ነብያት ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔርን ድምጽ በዚህ ሁኔታ ሰምተው ይጽፉ እንደነበር እንገነዘባለን። (ኤር.1:4፤ 11፤ 13፤ 2:1፤ ሕዝ.2:1፤ 3:1፤ 16፤ 6፡1፤ ዘካ.1:7፤ 4:8)። ጳውሎስ በዚያን ጊዜ ከአንድ በላይ ቋንቋዎችን ይችል ነበር፤ በዚህ ወቅት ግን ጌታ የተናገረው በእብራይስጥ ቋንቋ ነበር።

ሁለተኛው የእግዚአብሔር ድምጽ ወደ እኛ የሚመጣበት መንገድ በፍንደቃ መልክ ነው። እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ኃሳቡን ወደ እኛ ይልካል (ዮሐ.16:12-15)። በዚህን ጊዜ በታላቅ ፍንደቃ ወይም በታላቅ ደስታ ይሞላናል። በዚህ መልኩ ወደ እኛ የሚመጣው የእግዚአብሔር ድምጽ ወይም መልእክት በሰዎች ቋንቋ ሳይሆን ኃሳቡ ብቻ ነው በውስጣችን የሚፈስሰው፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ኃሳብ ወደ እኛ ሲመጣ በምናውቀው ቋንቋ ላይሆን ስለሚችል እግዚአብሔር በውስጣችን ያፈሰሰውን ኃሳብ በመረጥነው ቋንቋ መግለጽና ማብራራት የእኛ ፈንታ ይሆናል።

በሌላ አንፃር ደግሞ የእግዚአብሔር ድምጽ በውስጣችን ከሚወለደው ከራሳችን ኃሳብ መለየት መቻል አለብን። ብዙውን ጊዜ በመንፈሳዊ ግለት

ውስጥ ስንሆን የራሳችንን ኃሳብና ወደ እኛ የሚመጣውን የእግዚአብሔርን ኃሳብ መለየት ያስቸግረን ይሆናል፤ ምክንያቱም ከላይ እንደተገለጸው የእግዚአብሔር ኃሳብ በውስጣችን መፍሰስ ሲጀምር ታላቅ ፍንደቃ ይሰማናል፤ እኛም ደግሞ አእምሮ ያለን ስለሆንን ኃሳቦችን በውስጣችን ማፍለቅ እንችላለን። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነን በውስጣችን የሚፈጠረው ኃሳብ ከእግዚአብሔር የመጣ ኃሳብ ሊመስለን ይችላል። እንግዲህ እዚህ ላይ ነው የእግዚአብሔርን ድምጽ ለመለየት ብስለትና ልምምድ የሚያስፈልገው።

ይሁን እንጂ ከእኛ ውጭ የሆነ ኃሳብ በውስጣችን ሲፈስ በማስተዋል ሆነን መለየት መቻል አለብን። የእግዚአብሔር ኃሳብ ወደ ውስጣችን ሲፈስ በትዝታ መልክ አይደለም፤ ከእኛ ውጭ የሚመጣው ኃሳብ ውስጣችንን ሰንጥቆ ይገባል፤ ቀስ በቀስ እያሰላሰልን የምንደርስበት ኃሳብ አይሆንም። የራሳችን ኃሳብ ከሆነ አእምሮአችን ምክንያት ሲፈጥር ይታወቀናል፤ ቀደም ሲል ከሰማነው ነገር ጋር ወይም በውስጣችን ከቆየ ጉዳይ ጋር የምናገናዝበው ነገር ይኖራል። የእግዚአብሔርን ኃሳብ ከምንም ነገር ጋር ሳናገናዝብ ከታላቅ ፍንደቃ ጋር እንደተከማቸ ኃይል ድንገት በውስጣችን ሲፈስስ ይታወቀናል። ያ በውስጣችን የመጣው የእግዚአብሔር ኃሳብ በዓመታት ውስጥ ሊረሳን አይችልም።

የእግዚአብሔር ድምጽ ወደ እኛ የሚመጣበት ሦስተኛው መንገድ በሰዎች በኩል ነው። ብዙውን ጊዜ በሰዎች የሚመጣ የእግዚአብሔር ድምጽ በትንቢት መልክ፣ በስብከት ውስጥ ወይንም ምክር በምንቀበልበት ጊዜ ሊሆን ይችላል። በእነዚህ ሁኔታዎች ወደ እኛ የሚመጣ የእግዚአብሔር መልእክት የመጀመሪያ ሳይሆን ቀደም ሲል ለሰማነው ማረጋገጫ ሊሆን ይችላል፤ ወይንም አጥብቀን እንድንረዳ ሊቀሰቅሰን የመጣ መልእክት ይሆናል። የሐዋርያው ጳውሎስን ልምምድ ብናይ ጥሩ ግንዛቤ ይሰጠናል። ሐዋርያው ጳውሎስ ከሦስተኛው የሚሲዮናዊነት ጉዞው በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ቆረጠ፤ በጉዞው ላይ እያለ ነቢያት በኢየሩሳሌም መከራ እንደሚጠብቀው ይናገሩት ነበር (ሐዋ.21:4-11)። ሐዋርያው ጳውሎስ ግን አስቀድሞ ይህ እንደሚደርስበት ያውቅ ስለነበር ማገናዘብ ችሏል (ሐዋ.20:23)።

በሰዎች በኩል የሚመጣውን ድምጽ የእግዚአብሔር ኃሳብ ነው ብሎ ለመቀበል እጅግ ጥንቃቄና ማስተዋል በተሞላበት ሁኔታ ማሰብ

ያስፈልጋል። ምክንያቱም የእግዚአብሔርን በጎች ለማባበል ሰይጣን በሰዎች ሊጠቀም ስለሚችል ነው። ብዙ ክርስቲያኖች የሚያባብልና የሚያሞካሽ ቃል መስማት ይፈልጋሉ። መልእክቱ ተግሳጽ ከሆነባቸው የእግዚአብሔር ኃሳብ ነው ብለው ባለማስተዋል ላይቀበሉ ይችላሉ። የእግዚአብሔርን ድምጽ የተለማመደ ብስለት ያለው ክርስቲያን ከሆነ ግን መልእክቱ ምንም ዓይነት ይዘት ይኑረው፣ ከእግዚአብሔር የሆነውንና ከእግዚአብሔር ያልሆነውን ኃሳብ ይለያል።

ንጉሥ አክአብ ጉጉ ሰው ነበር፤ ስለዚህም እግዚአብሔር በሚክያስ የነገረውን ማስጠንቀቂያ ከመቀበል ይልቅ ያደነቁትን ነቢያት ድምጽ ሰምቶ ጠፋ (2ዜና.18:4-22)። የእስራኤል ነገሥታትና የሕዝብ አለቆች ብዙ ጊዜ እውነተኛ ነቢያቶችን አይቀበሉም ነበር። ኤርምያስ ስለ ኢየሩሳሌም መፍረስና መጥፋት ትንቢት ሲናገር ይቃወሙት ነበር። ከእግዚአብሔር ያልሆነውን ባዶ ተስፋ የሚተነብዩትን ነቢያት ይሰሙና ይከተሉ ነበር። ነገር ግን ከእግዚአብሔር የሆነውን መልእክት ለመለየት በማስተዋል ቢመረምሩ ኖሮ እነርሱም ሆኑ ልጆቻቸው ባልጠፉም ነበር።

ታላላቅ በሚመስሉ ሰዎች በኩል የሚመጣውን መልእክት ከእግዚአብሔር ነው ብሎ ለመቀበል ብዙ ሰዎች አይቸገሩም፤ የእግዚአብሔርን ነገር ዝቅ ብለን እንድንቀበል አንዳንድ ጊዜ ባልታወቁና በተናቁ ሰዎች በኩል ሊመጣልን ይችላል። አስተዋይ ሰው ግን የዕቃውን ዓይነት ብቻ ሳይሆን በዕቃው ውስጥ ያለውን ነገር ይመረምራል።

"ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለ" (2ቆሮ.4:7)። የከበረን ገንዘብ ማን በሸክላ ዕቃ ውስጥ ያኖራል? በሸክላ ዕቃ ውስጥስ የከበረ ነገር አለ ብሎ ማን ያስባል? እግዚአብሔር ግን ታላቅ ኃይሉን ለመግለጽ የከበረውን ነገር በሸክላ ዕቃ ውስጥ ሊያኖር ወደደ፤ ስለሆነም ወደ እነዚህ ሸክላዎች መምጣት ምናልባት ራስን ዝቅ ማድረግ ይጠይቅ ይሆናል።

ከእግዚአብሔር ድምጽ ጋር ተመሳስለው ከሚመጡ ሌሎች ድምጾች እንዴት መጠበቅ እንችላለን? መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣንን ሸንጋይ ወይንም አስመሳይ ነው ይለዋል (ኤፌ.6:11፣ 2ቆሮ.11:3። ሰይጣን የእግዚአብሔርን በጎች ከመንጋው ነጥሎ የሚወስደው በኃይል ሳይሆን በማባበልና በመሸንገል ነው። ስለዚህም የራሱን ኃሳብ ወደ ሰዎች

የሚያደርሰው ብዙ የተለያዩ መንገዶች ቢኖሩትም ዋና ዋናዎቹ መንገዶች ድምጽን ቀጥታ በመላክ፣ የራሱን ኃሳብ በማስተላለፍና በሰዎችም በመጠቀም ነው።

የእግዚአብሔርን ድምጽ በቀጥታ ሰማን የሚሉ ብዙ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ የሰይጣንንም ድምጽ ሰማን የሚሉ ብዙ ሰዎች መኖራቸውን እናያለን። ሰይጣን ድምጽንም ሆነ ኃሳብን ያለምንም መሣሪያ ወደ ሰው መላክ ይችላል፤ ራሱ መንፈስ ስለሆነ በፈለገው መልክና ቅርጽ መገለጥ ይችላል።

ሱንደር ሲንግ ሰይጣን ሊያታልለውና ሊሸነግለው እንዴት ወደ እርሱ መጥቶ እንደነበር እንዲህ ሲል መስክሯል፦

> ". . . ሌላ ማታ ደግሞ ከሥራዬ በኋላ ወደ ጫካ ገብቼ በድንጋይ ላይ ተቀምጬ ስለ ምን እንደምጸልይ ላስብ ጀመርኩ። ይህን እያሰብኩ በተመስጦ ሆኜ ሳለሁም አንድ ሰው መጣብኝ፤ በአስተያየቱና በአነጋገሩ በልብሱ ባለ ግርማ አምላክን <u>በተለምዶ</u> የሚያገለግል መስሎ ታየኝ። ነገር ግን የዓይኑ አገላለጥ የማታለልና የተንኮል የእስትንፋሱን የጢስ እቶን የሚመስል <u>ዝናማዊ</u> ሆኖ ይታይ ነበር። እንዲህም ብሎ ተናገረኝ፡ "ቅዱስ ክቡር ጌታ ሆይ በጸሎትዎ መካከል በመግባቴ ይቅርታዎትን። ነገር ግን ስለ ፍቅር በስመ አብ ይቅር ይባላልና ወደ እርስዎ አምጥቶ ያለ ኃሳብ ይስሙኝ። ይህቺ ራስዎን መንና ለብዙ ሰዎች ጥቅም የተሰዋች ሕይወትዎ <u>ለእኔ ለብቻዬ ሳይሆን</u> እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ብዙዎች አስደንቃለች።
>
> ነገር ግን ምንም ሥጋዎና ነፍስዎ ለአምላክ ክብርና ለሌሎችም ጥቅም ቢሰዋት እነዚያ የሚበዙትስ በእምነት እንኳን አያዩዋትም። በሞቀ ክርስትናዎ በሺዎች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖችን እንዳነቃቁ እርግጥ ነው። ከእነርሱ የሚበዙት ግን ምንም አላመኑዎትም። እንዲያስ እንደ ኃሳቤ በሕንዳውያን ወይም በመሐመዳውያን ዘንድ መሪ ቢሆኑ አይሻልዎትምን? አሁንም ምክሬን ቢሰሙ እነርሱ እንደ እርስዎ የመሰለ መንፈሳዊ መሪ ይፈልጋሉና ሺዎች ሰዎች በትህትና እያከበሩዎ በኋላዎ ሲከተሉዎ እናይ ነበር።" ይህንን በሰማሁ ጊዜ ድምጼን ከፍ አድርጌ ጮኼ አንተ ሰይጣን በጎችን የምትነጥቅ ተኩላ መሆንህን ፈጥኜ አውቄያለሁ ወደ ሕይወት ከምታስገባው ቀጭንዋ መንገድ አውጥተህ ወደ ሞት

በምታስገባው ሰፊ መንገድ ልታስገባኝ ፈልገሃል። እኔ ግን ለዚያ ሕይወቱን ስለ እኔ ላሳለፈልኝ ሕይወቴን ያለኝንም ሁሉ ለእርሱ ላስገዛው እወዳለሁ። አሁንም ሂድ ከእኔ ራቅ ከአንተ ጋር ምንም ጉዳይ የለኝም አልኩት ይህንንም በሰማ ጊዜ ከንፈሩን እየነከሰና በቁጣ እያጉረመረመ ሄደ" (ሱንደር ሲንግ መግቢያ ውስጥ ሁለተኛ ራዕይ)።

ሱንደር ሲንግ የገጠመው ሁኔታ ሐዋርያው ጳውሎስ "ሰይጣን የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና" ያለውን ያስታውሰናል (2ቆሮ.11:14)።

ሰይጣን በድምጽ ብቻ ሳይሆን ኃሳብን ወደ ሰው መላክ ይችላል፤ ጌታ በፋሲካ ምሽት ከሐዋርያቱ ጋር እራት እየበላ ሳለ ዲያብሎስ በአስቆሮቱ ይሁዳ ልብ አሳልፎ እንዲሰጠው ኃሳብ አገባበት ይላል (ዮሐ.13:2)። በዚህን ጊዜ ሰይጣን ራሱ ገባበት ማለት አይደለም፤ የገባበት ከዚያ በኋላ ነው (ዮሐ.13:27)። በዚህ መልኩ ሰይጣን ብዙውን ጊዜ ክርስቲያኖችን ሁሉ መፈተኑ አይቀርም፤ ይሁን እንጂ የዚያን የአፍቃሪ ድምጽ የተለማመዱ ክርስቲያኖች የሰይጣን ኃሳብ መልካም መስሎ እንኳን ወደ እነርሱ ቢመጣም እንግዳ ነገር ስለሚሰማቸው 'በኢየሱስ ስም!' ብለው መገሰጻቸው አይቀርም። ጌታ "በጎቼ ድምጼን ያውቃሉ ከሌላው ግን ይሸሻሉ" ያለው ለዚህ ነው (ዮሐ.10:4-5)። ሰይጣንን ተቃወሙት ከእናንተ ይሸሻል ተብሎ የተጻፈልንም ለዚህ ነው (ያዕ.4:7)።

ሰይጣን ብዙ ክርስቲያኖችን የሚያስትበት ሌላው መንገድ ሰዎችን የጽድቅ አገልጋዮች አስመስሎ በመላክ ነው። "ይህ ድንቅ አይደለም ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ለውጧልና። እንግዲህ አገልጋዮች ደግሞ የጽድቅ አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም ፍጻሜያቸውም እንደሥራቸው ይሆናል (2ቆሮ.11:14-15)። እንዲህ ዓይነት ሰዎች በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበሩ (ራዕ.2:1-2)። ነገር ግን በዚያ የነበረው መጋቢ በጥንቃቄ ይከታተላቸው ስለነበር ኋላ ሐሰተኞች መሆናቸውን ደረሰባቸው። ምናልባት ለብዙ ጊዜ በጌታ ስም ሰብከው ይሆናል፤ እንደነዚህ ዓይነቶቹ ኢየሱስ በሕይወታቸው ሳይከብር በአፋቸው 'ጌታ፣ ጌታ' ሲሉ ይታወቅባቸዋል። በመንፈስ ቅዱስ ሆነው በውስጣቸው እያከበሩት የጌታን ስም የጠሩት ደግሞ እንዲሁ ይታወቃሉ (1ቆሮ.12:1-3)።

ብዙውን ጊዜ ሰይጣን ያልበሰሉ ክርስቲያኖችን የሚያስተው የእግዚአብሔር አገልጋይ በሚመስሉ ሰዎች ነው። እነዚህ የእግዚአብሔርን ቃልና የክርስቲያኖችን ቋንቋ እየተናገሩ ስለሚመላለሱ ቶሎ ላይታወቅባቸው ይችላል። በተለይ ጉጉ የሆነ ክርስቲያንን በእጃቸው ለማስገባት ጊዜ አይወስድባቸውም (ቲቶ 1:11፣ 2ጴጥ.2:14፣ 2ጢሞ.3:6-7)። በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ ይላል (ሮሜ.16:18፣ ይሁዳ 16)። ሰይጣን ክርስቲያኖችን በወጥመዱ ለመያዝ ሁልጊዜ ውሸት እየተናገረ ሳይሆን አብዛኛውን ጊዜ እውነተኛ የሆኑትን መልእክቶች እያስተላለፈ የእግዚአብሔርን እውነተኛነት በሰዎች መልእክት ማረጋገጥ የሚፈልጉ ሰዎችን በቀላሉ በማታለል ነው። የእውነተኛ ትንቢቶች መልእክተኛ ከእግዚአብሔር መሆኑን ያረጋግጡልናል እንጂ የእግዚአብሔርን እውነተኛነት አያረጋግጡልንም፤ እግዚአብሔር ለዘለዓለም እውነተኛ ነውና (ዘዳ.18:20-27)። ስለሆነም የእግዚአብሔርን እውነተኛነት ለማረጋገጥ የሚፈልግ ሰው በቀላሉ ሊስት ይችላል። ሰይጣንም እውነተኛ መልእክት ማስተላለፍ ከቻለ የሰይጣን መሆኑን እንዴት መለየት ይቻላል? የሚል ሰው ይኖራል። እግዚአብሔር መናፍስት የመለየት ጸጋን ሰጥቶናል። በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ክርስቲያኖች ሁሉም በጉጉነት ካልተወሰዱ በስተቀር የሰይጣንን ድምጽ ሊለዩ ይችላሉ ብዬ አምናለሁ። መንፈስ ቅዱስ የጌታን ድምጽ ሰምተን እንድናከብረው እንደሚያስችለን ሁሉ እንዲሁም ደግሞ የሰይጣን ድምጽ በየትኛውም አቅጣጫ ቢመጣ እንድንቃወመው ይገፋፋናል። በእርግጥ የረቀቀውን የሰይጣንን አሠራር ለመለየት በመንፈሳዊ ሕይወት ማደግ ያስፈልጋል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በፊልጵስዩስ የገጠመውን እንደ ምሳሌ ወስደን ብናይ የምዋርተኝነት መንፈስ የነበረባት ያች ገረድ ባሪያ እነ ጳውሎስን ባየች ጊዜ "የመዳንን መንገድ የሚነግሩዋችሁ እነዚህ ሰዎች የልዑል አምላክ ባሪያዎች ናቸው" እያለች ለብዙ ቀናት ትጮህ ነበር፤ ንግግርዋ እውነት ነው እነ ጳውሎስ የመዳንን መንገድ የሚያስተምሩ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ናቸው፤ ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቱን አልተቀበለውም፤ ለምን ቢባል መልእክት አስተላላፊው ማን መሆኑን አውቆ ነበርና፣ ስለዚህ ለቋት እንዲሄድ አዘዘው(ሐዋ.16:16-18)።

የሰይጣን ድምጽ በየትኛውም መንገድ ይምጣ ይቀፋል፣ በቆዳችን ላይ የሚኮሰኩስ ነገር ሲሄድ እንደሚቀፈን ሁሉ የሰይጣን ድምጽ ሲመጣ

ውስጣችንን ይቀፈናል፡ መንፈሳችን ይቆጣል፤ በዚያን ጊዜ ሳናመነታና ሳናብሰለስል በጌታ ስም መገሰጽ ይኖርብናል (ያዕ.4:7)።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እግዚአብሔርም ሳይልካቸው ሰይጣንም ሳይልካቸው ከእግዚአብሔር መልእክት አለን ብለው የሚመጡብን ወገኖች ይገጥሙናል፤ እንዴት መለየት እንችላለን? በዚህ ዓይነት ወደ እኛ የሚመጡ ወገኖች ምናልባት ጤናማ ክርስቲያኖች ሊሆኑ ይችላሉ። በጸሎት ጊዜ በፍንደቃ ውስጥ ሆነው ስለ እኛ በሚያስቡበት ጊዜ ከእግዚአብሔር መልእክት ያገኙ መስሏቸው ይሆናል። ይሁን እንጂ መልእክታቸው ከእግዚአብሔር እንደምንሰማው ድምጽ ልባችንን ሰነጣጥቆ የሚገባ ላይሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ ከሰይጣን እንደሚመጣው ደምጽ የሚያውከንና የሚቀፈን ላይሆን ይችላል። ስለዚህ ዝም ብለን ብንሰማቸው እንደማናቸውም ጊዜ ዓይነት የሰው ንግግር ብቻ ይሆንብናል። ይሁን እንጂ ሳናስደነግጣቸው በእርጋታ ቀስ ብለን ልናስረዳቸው ይገባል እንጂ መልእክቱን እንደተቀበልን መሰለን መሽኘት አይገባም። ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ሕይወት ልንጠነቀቅ ይገባል፤ ዝም ብለን መተው በስህተታቸው እንዲቀጥሉ ማበረታታት ይሆናል። ራሳችንንም ልዩ መንፈሳዊ ብቃት እንዳለን በመቁጠር ሌሎችን ተስፋ ማስቆረጥም አይጠበቅብንም።

## IV. በክርስትና ሕይወት የምናድግበት አቅጣጫ

1. በክርስትና ሕይወት የዕድገት መጠን እስከ ምን ድረስ ነው?
2. በክርስትና ሕይወት የምናድግባቸው አራት አቅጣጫዎች ምንድን ናቸው?
3. ስለ እግዚአብሔር በማወቅ እና እግዚአብሔርን በማወቅ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ከሌሎችም ጋር ተወያይበት።
4. እግዚአብሔርን ለማወቅ የሚያስችሉን ሁለት ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?
5. እግዚአብሔርን በሰብዓዊ ዓይን ማየት ካልተቻለ እርሱን በማወቅ ማደግ የሚቻለው በምን ሁኔታ ነው?
6. ሦስቱ የጸጋ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?
7. መንፈስ ቅዱስ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎችን ለቅዱሳኑ የሰጠበት ምክንያት ምንድን ነው? ተወያይበት።
8. የጸጋ ስጦታዎችን በቁጥር መወሰን አንችልም ያልንበት ምክንያት ምንድን ነው?
9. በገላ.5:22 ላይ የተጠቀሱት የመንፈስ ፍሬ የጸጋ ስጦታዎች ናቸው ያልንበት ምክንያት አስረዳ።
10. የጸጋ ስጦታዎችም ሆኑ የመንፈስ ፍሬ የምንላቸው ጌታን ከተቀበልክበት ጊዜ ይልቅ አሁን ምን ያህል በሕይወትህ አድገዋል? ተወያይበት።
11. ለጋስነት የጸጋ ስጦታ ሊሆን ይችላል ብለህ ታስባለህ? ሮሜ.12:8 ተመልከት።
12. ጸጋን በምትለማመድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለሥፍራቸው ቆመው የሚያገለግሉትን አገልጋዮች በቀላሉ መለየት የሚቻለው እንዴት ነው? ተወያይበት።
13. በሰው አንፃር መልካም ስጦታ ሁል ጊዜ የፍቅር መግለጫ ላይሆን የሚችልበት ምክንያት ምንድን ነው? ተወያይበት።
14. 'ፍቅርን በመስጠት' እና 'ፍቅርን በመግለጽ' መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
15. እግዚአብሔር አንድያ ልጁን በመስጠት ለዓለም ፍቅሩን ገልጿል፤ በግል ደረጃ እግዚአብሔር እንደሚወደን እንዴት ማረጋገጥ እንችላለን? ተወያይበት።
16. በመንፈስ ቅዱስ በልባችን የፈሰሰ የእግዚአብሔር ፍቅር እየበዛ ሲሄድ በሦስት አቅጣጫ በሕይወታችን የሚከሰቱ ነገሮች አሉ፤ ምንድን ናቸው?
17. ፍቅር የሚሰጠው ከእግዚአብሔር እስከሆነ ድረስ ፍቅር ሲጎድለን ተጠያቂ የምንሆነው ለምንድን ነው? ተወያይበት።
18. "እርሱን ሳታዩት ትወዱታላችሁ" ይላል (1ጴጥ.1:8)። ክርስቶስን ሳናየው እንዴት ልንወደው ቻልን?
19. ፍቅራችን በሦስት ዋና ነገሮች ላይ መመሥረት እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፤ ከጥቅሶቹ ጋር እያገናዘብክ አስረዳ።
20. የእግዚአብሔር ድምፅ ወደ እኛ ሊመጣ የሚችልበት መንገድ ብዙ ቢሆንም ሦስቱ ዋና ዋና መንገዶች ምንድን ናቸው?
21. የእግዚአብሔር ድምፅ በጉባዔ ውስጥ ለአንድ ሰው ሲመጣ ሌሎች ሊሰሙ የማይችሉበት ምክንያት ምንድን ነው?
22. የጠላትን ድምፅና የእግዚአብሔርን እንዴት መለየት እንችላለን? ተወያይበት።

## V. በክርስትና ሕይወት ለማደግ አስፈላጊ ነገሮች

ባለፈው ምዕራፍ በመንፈሳዊ ሕይወት የምናድግበትን አቅጣጫ በተመለከተ አራት መሠረታዊ የሆኑ ነገሮችን አይተናል። እነርሱም እግዚአብሔርንና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ማደግ፣ በጸጋ ማደግ፣ በፍቅር ማደግና የእግዚአብሔርን ድምፅ በመስማት ማደግ የሚሉ ናቸው።

እነዚህ አቅጣጫዎች በሚገባ ለማደግ ዘወትር ልንለማመዳቸው የሚገባን ስለሆነ በዚህ ምዕራፍ ትኩረት የምንሰጥባቸው ይሆናሉ። የመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት ዳግም በመወለድ ይጀምራል፤ ዳግም ልደት ሳይኖር በመንፈሳዊ ሕይወት ማደግ አይኖርም። ለዳግም ልደት ከመጀመሪያው በቂ ትንታኔ ስለተሰጠ በዚህ ክፍል ለመነሻ ያህል መጥቀሱ በቂ ነው።

በክርስትና ሕይወት በአገልግሎት ለማደግ የማይናፍቅ ክርስትያን የለም፤ በሐዋርያትና በነቢያት የተገለጠው አገልግሎት ዛሬም በእኛ ሕይወት እንዲታይ እንመኛለን፣ ክርስቶስን የመምሰል ሕይወት እንዲኖረን እንናፍቃለን፣ በክርስትና ሕይወት በድል ለመጓዝ እንፈልጋለን፤ ይሁን እንጂ ከፊት ይልቅ ሸክማችን ከብዶ፣ መንፈሳዊ ነገራችን ደብዝዞ፣ የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማት ተስኖን፣ ፍቅራችን ቀንሶ ስናይ ጥልቅ የሆነ ሃዘን ይሰማን ይሆናል። ምንም የማይሰማን ከሆነ ግን መንፈሳዊ ደዌ ይዞን ይሆናል ማለት ይቻላል። በደዌ የተያዘ ሰው ምንም ዓይነት ምግብ አይጥመውም፤ በደህናው ጊዜ የሚወደውን ምግብ እንኳን ሲሰጡት ያስጠላዋል። መንፈሳዊ ደዌ የያዘውም ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ እንደዚሁ ነው፤ መንፈሳዊ ምግብ ያስጠላዋል። ይህ ዓይነቱ አዝማሚያ አደገኛ ስለሆነ ወደ ሞት ያደርሰዋል።

በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ አገልጋዮች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሳያድጉና ሳይጠነክሩ አገልግሎታቸውን ማሳደግ ይፈልጋሉ። እንደዚህ ያሉ አገልጋዮች ሥሩን ወደ ታች እንዳልሰደደ ዛፍ ይመስላሉ፤ ሥሩን ወደ ታች ያልሰደደ ዛፍ ጎርፍ ሲመጣ ወይም የዝናብ ውሽንፍር ሲገፋው መቋቋም ያቅተውና ይወድቃል። እንደዚሁም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሳያድጉ አገልግሎታቸውን በማሳደግ ላይ ጊዜያቸውን የሚያጠፉ ክርስቲያኖች ትንሽ ተቃውሞ ወይም ነቀፋ ሲደርስባቸው መጽናናትና መቆም ያቅታቸውና ከወገኖቻቸው መሸሽ ይጀምራሉ። ስለዚህ አገልግሎትን ለማሳደግ ከመሮጥ ይልቅ በመንፈሳዊ ሕይወት ማደግን መነሻ

ያደረገ ክርስቲያን መድረሻው ያማረ ስለሚሆን አገልግሎቱም አይናድም። በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያደገ ክርስቲያን ሥሩን በወንዝ ዳር እንደሰደደ ዛፍ ይመስላል፤ በወንዝ ዳር ሥሩን የሰደደ ዛፍ ወደ ላይ ያድጋል፣ ከሩቅ ሳይቀር ይታያል፣ ቅጠሎቹም አይረግፉም፣ ፍሬውም አይቋረጥም (ኤር.17:5፣ ሕዝ.47:1-12፣ መዝ.1:3)። ስለሆነም በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ለማደግ ስለሚያስችሉ መንፈሳዊ ልምምዶች ቀጥለን እናያለን።

1. **የቃሉ ሙላት**

በቅድስና ሕይወት ስለ ማደግና የእግዚአብሔር ቃል በሕይወታችን ውስጥ ስለሚኖረው ድርሻ ቀደም ሲል አይተን ነበር። በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ የእግዚአብሔር ቃል ስለሚኖረው ድርሻ በዚህ ክፍል ለየት ባለ መልኩ እናያለን። የእግዚአብሔር ቃል በብዙ ነገሮች ተመስሏል፤ ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹን ወስደን እናያለን።

ሀ. የእግዚአብሔር ቃል የሕይወት እንጀራ ነው፡

ዲያብሎስ ጌታ ኢየሱስን ሲፈትነው "እነዚህን ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል" ባለው ጊዜ ጌታም "ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም" ብሎ መለሰለት ማቴ.4:3-4። እርሱም የእግዚአብሔርን ቃል ከእንጀራ ጋር በማነጻጸር "ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም" አለ። ለሰው ከእንጀራ ሌላ የሚያስፈልገው ምግብ ምን እንደሆነ ሲጠቅስ "ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ" ሲል ሰው እንደ እንጀራ የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ አለበት ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው።

ኤርምያስ "ቃልህ ተገኘቷል እኔም በልቼዋለሁ፤" በማለቱ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ምግብ እንደሆነ ይናገራል (ኤር.15:16)። ዳዊት "ቃልህ ለጉሮሮዬ ጣፋጭ ነው፣ ከማርና ከወለላ ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ" ይላል መዝ. (119:103)። በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ ሆነን የእግዚአብሔርን ቃል ስናነብ ተርበን ከምንበላው ጥሩ ምግብ ይልቅ ይጥመናል፤ መንፈሳዊ ሕይወታችን ልዩ ምግብ ማግኘቱ ይሰማናል፤ ከዚያም ተስፋችን ሲታደስ እምነታችን ሲሞላ ይታወቀናል። የመንፈሳዊ ሕይወት ጥንካሬ መለኪያው አንዱ እምነት ነው፤ እምነት የሚገኘው ደግሞ ከእግዚአብሔር ቃል ነው (ሮሜ.10:17)። በመንፈሳዊ ሕይወታችን አድገን ጠንካራ እምነት እንዲኖረን የእግዚአብሔርን ቃል ዘወትር መመገብ ይኖርብናል።

ለ. የእግዚአብሔር ቃል እንደ መብራት፡

በመንፈሳዊ አነጋገር ይህች ዓለም ጨለማ ናት (ፊልጵ.2:14-16፣ ማቴ.5:14፣ 1ዮሐ.1:6፣ 2:11)። ጨለማ በዋጣት ዓለም ውስጥ በሕይወት መንገድ ለመራመድ እንደ ብርሃን ሊመራን የሚችል የእግዚአብሔር ቃል ነው። ዳዊት "ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው" ይላል መዝ. (119:105)። መብራት የሌለው በጨለማ የሚጓዝ መንገደኛ ከመስመር መውጣቱ አይቀርምና ወደማይፍልግበት ሥፍራ ይደርሳል። በመንፈሳዊ ሕይወትም እንደዚሁ ነው፤ ዲያብሎስ ከእግዚአብሔር መንገድ ሊያወጣን የጽድቅ መንገድ አስመስሎ የሚቀይሰው መንገድ አለ፤ ያም መንገድ የእውነትና የሕይወት መንገድ አለመሆኑን ያለ እግዚአብሔር ቃል መለየት ያዳግታል።

በሌላ አንፃር ስናይ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ይዘው መመሪያችን የእግዚአብሔር ቃል ነው እያሉ እውነተኛ መንገድ የጠፋባቸውም አይጠፉም። እነርሱም ኮምፓስ (አቅጣጫ መጠቆሚያ) ይዞ አቅጣጫ የጠፋበት መርከበኛን ይመስላሉ። አነባበቡን አውቆ ካልተጠቀመበት ኮምፓስ መያዙ ምንም አይጠቅምም። በተመሳሳይ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስን በትክክለኛው መንገድ ካልተረዱት ከእውነት መንገድ ወጥተው በተሳሳተ አቅጣጫ መጓዛቸው አይቀርም።

መጽሐፍ ቅዱስን በትክክለኛ መንገድ ለመረዳት ጥረት ማድረግ እንዳለብን ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ታሪክ ነው፤ እርሱም በሰረገላ ተቀምጦ በምድረ በዳ መጽሐፍ ቅዱስ እያነበበ ሲጓዝ ፊልጶስ ቀርቦ "በእውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህን?" አለው እርሱም "የሚመራኝ ሳይኖር ይህእንዴት ይቻለኛል?"ብሎ መለሰለት (ሐዋ.8:30)። ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የጠፋበት ቋንቋው ሳይሆን ትርጉሙ ነው። ለዚህም ነው መልሶ ፊልጶስን "እባክህ ነቢዩ ይህን ስለማን ይናገራል? ስለ ራሱ ነውን ወይስ ስለሌላ?" ሊል የቻለው (ሐዋ.8:34)። ቋንቋውን ባያውቅ ኖሮ እንደዚህ ብሎ መጠየቅ ባልቻለም ነበር። ጃንደረባው የሚያነበውን ክፍል በመሰለው መንገድ ሊረዳው አልፈለገም፤ ከዚህ ይልቅ ትክክለኛውን ትርጉም ለማግኘት በመፈለጉ እግዚአብሔር ቃሉን በትክክል ሊያስረዳው የሚችልን ሰው አዘጋጀለት። የእግዚአብሔርን ቃል በትክክለኛ መንገድ ከተረዳን ከራሳችን አልፈን የእውነት መንገድ ለጠፋባቸው ሰዎች እንደ ፊልጶስ የእውነትን ቃል ልናስረዳቸው እንችላለን (ፊል.2:15)።

ሐ. የእግዚአብሔር ቃል እንደ መልካም ዘር፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል በዘር ሲመሰል ቃሉን የሚሰሙት ደግሞ በእርሻ ይመሰላሉ (ሕዝ.36:9-10፣ ማቴ.13:3-9፣ 1ቆሮ.3:6-9)። የእግዚአብሔር ሕዝብ በእርሻ፣ ቃሉ ደግሞ በዘር የተመሰሉበት ዋናው ምክንያት የእግዚአብሔርን ቃል በመቀበል ብዙ ፍሬ ማፍራት እንዳለብን ለማመልከት ነው። "በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከብራል ይላል" (ዮሐ.15:7-8)። በዚህ ሥፍራ የሚናገረው ፍሬ በገላ.5:22 ላይ እንደተጠቀሰው ዓይነት የመንፈስ ፍሬ ሳይሆን የአገልግሎት ፍሬ ነው። ምክንያቱም "ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ" የሚለው ቃል ደቀ መዛሙርትን ማፍራት እንዳለብን ሲያመለክት ነው። ደቀ መዝሙር ማለት የቃሉ ተማሪ ማለት ነው፤ ደቀ መዝሙር መምህር ሆኖ ብዙ ደቀ መዛሙርትን ማፍራት የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ሲኖረው ነው።

"እነሆ እኔ ለእናንተ ነኝና ወደ እናንተም እመለከታለሁ፣ እናንተም ትታረሳላችሁ ይዘራባችሁማል፣ እኔም የእስራኤልን ቤት ሰዎች ሁሉ ሁሉንም አበዛችኋለሁ" ይላል (ሕዝ.36:9-10)። ጌታ ኢየሱስ ስለ ዘሪው ምሳሌ ሲናገር፡- "በመልካም መሬት የተዘራውም ይህን ቃል ሰምቶ የሚያስተውል ነው፤ እርሱም ፍሬ ያፈራል አንዱም መቶ፣ አንዱም ስድሳ፣ አንዱም ሰላሳ ያድጋል" ብሏል (ማቴ.13:23)። በዚህ ሥፍራ እንደምናየው አንድ ክርስቲያን በሕይወቱ ፍሬ የማፍራቱ ሁኔታ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የተያያዘ መሆኑን ያረጋግጥልናል።

መ. የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሰይፍ፡

በመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሰይፍ ተደርጎ ተጠቅሷል (ኤፌ.6:17)። ይህም የሚያሳየን ጠላታችንን ዲያብሎስን የምንዋጋበት የጦር ዕቃ መሆኑንና የልባችንን ሽለፈት የሚገርዝ መሆኑን ለመግለጽ ነው (ዕብ.4:12)።

ከግብጽ የወጡ ሰልፈኞች በምድረ በዳ ባለቁ ጊዜ እነርሱን መተካት የነበረባቸው አዲሱ ትውልድ ከነሸለፈታቸው ወደ ሰልፍ ከመውጣታቸው በፊት እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲገርዛቸው ስላዘዘው እርሱም በጌልጌላ ገረዛቸው፤ ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር "ዛሬ የግብጽን ነውር ከእናንተ ላይ አንከባልያለሁ" አለው (ኢያሱ 5:2-9)። በእስራኤላውያን ዘንድ የሥጋ

ሸለፈት እንደ ነውርና እንደ ትልቅ ነቀፋ ስለሚቆጠር እስራኤላውያን የሆኑ ሁሉ የግድ መገረዝ ነበረባቸው። በአዲስ ኪዳን ትልቁ ነውር የልብ ሸለፈት ነው፤ የአዲስ ኪዳን የግርዘት አገልጋይ ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። "ክርስቶስ ስለ እግዚአብሔር እውነት የመገረዝ አገልጋይ ሆነ እላለሁ" (ሮሜ.15:9)። እርሱም የልባችንን ሸለፈት የሚገርዘው የመንፈስ ሰይፍ በሆነው በቃሉ ነው። "በክርስቶስ መገረዝ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ" (ቆላ.2:11፣ ኤፌ.6:17)።

የመንፈሳዊ ጥንካሬ ዕድገት ከውጊያ አንፃር ሊታይ ግድ ነው። ይሁን እንጂ ውጊያችን ከደምና ከሥጋ ጋር አለመሆኑንና የጦር ዕቃችንም ሥጋዊ እንዳልሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይነግረናል(ቆሮ.10:3-6፣ ኤፌ.6:12-18) ለውጊያ መሰለፍ ብቻ በቂ አይደለም፤ ውጤት ማምጣት ያስፈልጋል፤ ይህም ውጤት ነፍሳትን ማጥፋት ሳይሆን ነፍሳትን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መማረክ ነው። "የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔር እውቀት ላይ የሚነሳውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን፤ ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን" ይላል (2ቆሮ.10:5)። ስለሆነም አእምሮን ሁሉ የምንማርክበት የጦር ዕቃችን የእግዚአብሔር ቃል ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እራሱን እንደ ክርስቶስ ወታደር አድርጎ ይቆጥራል። ይህም ወንጌልን ለዓለም ለማዳረስ የሚያደርገውን ተጋድሎና ጥረት ለማሳየት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከዲያብሎስና ከሠራዊቱ ጋር የሚያካሂደውን መንፈሳዊ ውጊያ ሲገልጽ ነው። በሁለቱም መንገድ ለመሰለፍና ውጤት ለማግኘት የእግዚአብሔር ቃል በሙላት እንደሚያስፈልግ ይናገራል (ቆላ.3:16)።

ሠ. የእግዚአብሔር ቃል እንደ እሳት:

በኤርምያስ 23:29 ላይ የእግዚአብሔር ቃል በእሳት ተመስሏል። እሳት ደግሞ ለማቃጠል ለማንጠርና ለማጥራት ይጠቅማል፤ የእግዚአብሔር ቃል በሰው ሕይወት ውስጥ እንዲሁ ይሠራል። በሰው ውስጥ ፍሬ የሌለው ገለባ የሆነ ብዙ ከንቱ ነገር ይከማቻል። "ገለባ ከስንዴ ጋር ምን አለው?" ይላል፤ በዚህ ስፍራ ንፋስ ስለሚወስደው ገለባ ሳይሆን በሰው ውስጥ ስለሚከማቸው ከንቱ ኃሳብ ነው የሚናገረው። ይቀጥልና "በውኑ ቃሌ እንደ እሳት . . . አይደለችምን?" ይላል። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል በሕይወታችን በሙላት ሲኖር ከንቱ የሆነ ኃሳብ ልባችንን ሞልቶ ሊያውከን አይችልም። ምክንያቱም እሳት ገለባን እንደሚበላ የእግዚአብሔር ቃል ልባችንን የሞላውን ገለባ የሆነ ኃሳብ ይበላዋልና።

ረ. የእግዚአብሔር ቃል እንደ መዶሻ:
"በውኑ ቃሌ እንደ እሳት፣ ድንጋይንም እንደሚያደቅቅ መዶሻ አይደለምን?" (ኤር.23:29)። በዚህ ሥፍራ ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል በመዶሻ ተመስሏል። ኤርምያስ በነበረበት ጊዜ ብዙ ሕልም አላሚዎችና ትንቢት ተናጋሪዎች ነበሩ። ሕልማቸውም ሆነ ትንቢታቸው ከራሳቸው አመንጭተው የሚናገሩት እንጂ ከእግዚአብሔር አልነበረም (ኤር.14:14፣ 23:26)። ስለዚህ ቃላቸው እንደ ገለባ ከንቱና እርባና ቢስ እንደሆነ በመገለጽ "የሚያልም ነብይ ሕልምን ይናገራል፤ ቃሉም ያለበት በእውነት ቃሉን ይናገራል። ገለባ ከስንዴ ጋር ምን አለው? በውኑ ቃሌ እንደ እሳት ድንጋይንም እንደሚያደቅቅ መዶሻ አይደለምን?" ይላል። ድንጋይን ለማድቀቅም ሆነ ቅርጽ ለመስጠት መዶሻ አስፈላጊ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰው ልብ እንደ ድንጋይ ጠንካራ እንደሆነ ተጽፎ እናገኛለን። (ሕዝ.11:19፣ 36:26)። ስለዚህ የሰውን ድንጋይ ልብ ማቃናት የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው (2ጢሞ.3:16)።

ሰ. የእግዚአብሔርን ቃል በሥርዓት ለማንበብ ያሚያስችል መመሪያ:
ብዙ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን ዘወትር ለማንበብ ልባቸው ይነሳሳና እንዴትና ከየት መጀመር እንዳለባቸው ሲያስቡ መመሪያ የሚሆናቸው ያጣሉ። የሚከተሉት ነጥቦች እንደ መመሪያ ሊያገለግሉ ይችላሉ።

መጽሐፍ ቅዱሳችንን የምናነብበትን የቀኑን ጊዜያችንን መመደብ ይኖርብናል። ለዚህ ጥሩ መነሻ የሚሆነን የመመገቢያ ጊዜያችን ነው። በቀን ውስጥ የቁርስ፣ የምሳና የእራት ጊዜ እንዳለን ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳችንንም የምናነብበት ጊዜ በተመሳሳይ ሁኔታ ይኑረን። ለቁርስ፥ ለምሳና ለእራት ጊዜ ካገኘን ለእግዚአብሔር ቃልም ጊዜ ሊያጥረን አይገባም። በዚህ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ከወሰንን መጽሐፍ ቅዱስን ደግሞ በሦስት ክፍለን መጀመር እንችላለን።

* የመጀመሪያውን ክፍል ከዘፍጥረት እስከ አስቴር፣
* ሁለተኛውን ከኢዮብ እስከ ትንቢተ ሚልክያስ፣
* ሦስተኛውን ደግሞ ከማቴዎስ ወንጌል እስከ ዮሐንስ ራዕይ በማድረግ መክፈል እንችላለን።

ስለዚህ የጠዋቱን የንባብ ጊዜ ከማቴዎስ ብንጀምር የቀኑን የንባብ ጊዜ ከኢዮብ በመጀመር የማታውን የንባብ ጊዜ ደግሞ ከዘፍጥረት በመጀመር እንቀጥላለን፤ የምናነበው የንባብ ክፍል እንዳለን የጊዜ መጠን በማድረግ

የአምስት ደቂቃም ጊዜ ቢሆን መጽሐፍ ቅዱስን የማንበብ ልምድ ሊኖረን ይገባል። ዋናው ቁም ነገር ያነበብነውን ቃል በልባችን ማኖር ነው። "ትእዛዝህን አሰላስላለሁ መንገድህንም እፈልጋለሁ" ይላልና (መዝ.119:15)። ስለዚህ ቁም ነገሩ ብዙ ማንበባችን ሳይሆን ያነበብነውን በማስተዋላችን ነው ብዙ ፍሬ የሚኖረን፤ "ይህ ቃሌን ሰምቶ የሚያስተወለው እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል" (ማቴ.13:23)።

በሥርዓት እየተመራን በዚህ መንገድ ማንበብ ብንጀምር በአጭር ጊዜ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱሳችንን ከዳር እስከ ዳር መወጣት እንችላለን። ይሁን እንጂ ደጋግመን ማንበባችንን ማቆም የለብንም።

ዕድሜ ልካችንን እንጀራ እንደምንበላ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ዕድሜ ልካችንን ልንመገብ ይገባናል። "ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም" ብሎ የተናገረውን የጌታን ቃል መዘንጋት የለብንም።

**የንባብ ሂደት:-**

| ጠዋት ጠዋት | ቀን ቀን | ማታ ማታ |
|---|---|---|
| ከማቴዎስ - ራዕይ | ከኢዮብ - ትን. ሚልክያስ | ከዘፍ. - መጽ.አስቴር |

2. **የጸሎት ሕይወት ውስጥ መግባት**

በየዘመናቱ የሚነሱ ሰዎች ስለ ጸሎት ብዙ ትምህርት ለመስጠት ሞክረዋል፤ ይሁን እንጂ ጸሎት በጽሑፍ ወይም በቃል የምንማረው ሳይሆን ጸሎትን መማር የሚቻለው በመጸለይ ብቻ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ስለሆነም በዚህም ክፍል ስለ ጸሎት ለማስተማር ሳይሆን የእግዚአብሔር ልጆች በጸሎት ዓለም ገብተው መንፈሳዊ በረከት እንዲቀበሉ ለጸሎት ለመቀስቀስ ነው። አዲስ የተወለደ ሕፃን የእናቱን ጡት እንዲጠባ መቀስቀስ እንጂ ማስተማር አያስፈልገውም። ጸሎትም እንዲሁ ከመንፈስ ቅዱስ የተወለዱ ክርስትያኖች እንዲጸልዩ መቀስቀስ እንጂ እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው ማስተማር የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ ነው። ". . . እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፣ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል።"(ሮሜ.8:26-27) ተግተው የማይጸልዩ ክርስቲያኖች እንቅልፍ ውስጥ እንዳሉ ይቆጠራሉ፤

ስለዚህም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ደካማና የአሁኑን ዓለም ፈተና መቋቋም የሚያቅታቸው፤ የሥጋ ምኞትና የሰይጣን ፈተና የማይቋቋሙ ስለሚሆኑ በቀላሉ ሊሸነፉ ይችላሉ። በዚህ ዘመን ውስጥ ያሉትን ክርስቲያኖች ለጸሎት መቀስቀስ እጅግ ከባድ ነው ምክንያቱም ጸሎት ቸል የተባለበት ጊዜ ስለሆነ ነው።

ጸሎትን ምክንያታዊ የሚያደርገው ደግሞ መንፈሳዊነት ነው፤ ሰባኪ ወይም አስተማሪ ለመሆን የግድ የጸሎት ሰው መሆን ላያስፈልግ ይችላል፤ ጥሩ ሰባኪ ወይም ጥሩ አስተማሪ ለመሆን፡-

- ወቅታዊ ርዕስ መምረጥ፣
- ስለ ርዕሱ የሚያወሱ መጽሐፍትን ማንበብ፣
- የአዳማጮቹን ስሜት የሚስብ መግቢያ መጠቀም፣
- ሐተታን አዋህዶና አጣጥሞ ማቅረብ፣
- ምሳሌዎችን ከርዕሱ ጋር ማገናኘት ነው።

ይህን ማድረግ ከተቻለ ብዙ የእሁድ አድማጮችን ማግኘት ይቻል ይሆናል። ይህ ዓይነቱ አቀራረብ አያስፈልግም ለማለት ሳይሆን በዚህ መልኩ ጥሩ ሰባኪ ለመሆን ይቻላል ለማለት ነው። መንፈሳዊ ለመሆን ግን የግድ የጸሎት ሰው መሆን ያስፈልጋል። በአሰባበክ ዘዴ ብቻ ተክነው በሚሰብኩ አገልጋዮችና በጸሎት ሕይወት ውስጥ ገብተው በሚሰብኩ አገልጋዮች መካከል ትልቅና የጎላ የአገልግሎት ልዩነት ይታያል። እነዚህ በስብከት ዘዴ የተካኑ ሰባኪዎች ስብከታቸው እንደ ጥሩ ሙዚቃ ለጊዜው ስሜት ይማርካል እንጂ ትምህርታቸው በሰው ልብ ውስጥ አይቀመጥም፤ እንደ እንፋሎት ፈጥኖ ስለሚጠፋ የሰዎችን ልብ የመለወጥ ኃይል አይኖረውም። ስለዚህ የሚያገለግሏቸው ሰዎች አብዛኞቹ መንፈሳዊ ሕይወታቸው ያልተነካና ያልተለወጠ ይሆናል።

በእንጨት፣ በሳር፣ ወይም በአገዳ የተሰራ ቤት በእሳት ውስጥ ማለፍ እንደማይችል ሁሉ አንድ ቀን የሚፈትናቸው ነገር ሲመጣ መጽናት አይችሉም። በጸሎት የሚተጉ ሰባኪዎች ግን ከውስጣቸው የሚወጣው ቃል በሰው ልብ ውስጥ ይኖራል እንጂ አይጠፋም፤ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንደታሰሩ መጥተው እንዲሁ የሚመለሱ ሰዎች አይኖሩም። በጸሎት የሚተጋ አገልጋይ በመንፈስ ቅዱስ እሳት የቀለጠ ልብ ይኖረዋል (ሮሜ.12:11)። ከቀለጠ ልብ እሳት ይወጣና የሰዎችን ልብ ያቀልጣል፤ (ኤር.1:9)። በዚያም የእግዚአብሔርን ቤት በወርቅና በከበረ ድንጋይ

እንደ መሥራት ይሆናል። ያንን ቤት እሳት ቢፈትነው አይቃጠልም፥ ያነጻውም ሙሉ ደመወዙን ይቀበላል (1ቆሮ.3:12-15፤ 2ኛ ዮሐ.ቁ.8)። ያለ ጸሎት ትልቅ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ መሥራት ቢቻልም ያለ ጸሎት ግን የክርስቶስን አካል ማነጽ አይቻልም። ዘመናዊ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ለመሥራት እውቅ መሐንዲስ ያስፈልግ ይሆናል። የክርስቶስን አካልና የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሆናችውን ቤተ ክርስቲያን ለማነጽ የሚያስፈልገው በጸሎት የተጋ አገልጋይ ነው።

መንፈሳዊ ሰዎችን ለማፍራት በትምህርት መርቀቅና ሊቀ ሊቃውንት መሆን አያስፈልግም። የሚያስፈልገው አንድ ነገር ነው፤ እርሱም በጸሎት ሕይወት ውስጥ መግባት ነው። ለዚህ ነው ቀደም ሲል እንዳየነው አገልግሎትን ለማሳደግ ከመሮጥ ይልቅ መንፈሳዊ ሕይወትን ማሳደግ መቅደም አለበት ያልነው። በመንፈሳዊ ሕይወቱ ያላደገ አገልጋይ የሚያገለግላቸውን ምዕመናን ቁጥር ማብዛት ይችል ይሆናል፤ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ማሳደግ ግን አይችልም። ያላየውን መንፈሳዊ ሕይወት ማሳየትና ያልደረሰበትን መንፈሳዊ ደረጃ ማድረስ አይችልምና።

የወርልድ ቪዥን ኢንተርናሽናል ፕሬዝዳንት የነበሩ፣ ቴዲ ደብሊው ኢንግስትሮም "ዘ ፐርስዩት ኦፍ ኤክሰለንስ" በተባለው መጽሐፋቸው የአሜሪካ ሕንዶች ስለ አንድ ንስር የሚተርኩትን ታሪክ እንዲህ ብለው ጽፈዋል፦

> "አንድ ጊዜ አንድ ገበሬ የንስርን እንቁላል ከዶሮ እንቁላል ጋር አብሮ በማስታቀፍ እንዲቀፈቅፍ አደረገ። የተፈለፈለውም ንስር ከዶሮ ጫጩቶች ጋር አብሮ አደገ፤ ንስሩም እራሱን ከዶሮዎች ለይቶ ማየት ስላቃተው እንደ ዶሮዎቹ ጥራጊ እየጫጫረና ጥራጥሬ እየለቀመ መኖር ጀመረ። ዶሮዎቹ ከአጥር በላይ ሲበሩ ስላላየ እርሱም ከዚያ በላይ ከፍ ብሎ መብረር የሚችል ስላልመሰለው ከአጥር በላይ ለመብረር ሙከራ አድርጎ አያውቅም፤ በዚህ ሁኔታ ብዙ ዓመታት ኖረ። አንድ ቀን ንስር ሰማይ ተጠግቶ ሲበር አየና ጓደኞቹ ለሆኑት ዶሮዎች ይህ ከደመናት በላይ ሆኖ ሰማይን ተጠግቶ የሚበር ባለ ግርማ አሞራ ምንኛ የታደለ ነው አላቸው። እነርሱም እርሱማ የአሞራዎች ሁሉ ንጉሥ ይባላል አሉት። ነገር ግን አንተ እንደ እርሱ እሆናለሁ ብለህ አታስብ በማለት አስጠነቀቁት። ንስሩም ዶሮ ነኝ ብሎ ስላመነ ጥራጥሬ እየለቀመ እድሜውን ጨረሰ"።

እውነት ቢሆን እጅግ በጣም የሚያሳዝን ይሆን ነበር። ከዚህ ይልቅ እውነተኛ የሆነና እጅግ የሚያሳዝን ነገር አለ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ልጆች በጸሎት ሕይወት ውስጥ ገብተው ሰማያዊውን ብርሃን ተላብሰው በድል ሕይወት መንገዝ ሲችሉ እንደ ጥራጊ የሆነውን የዚህን ዓለም ክብርና ተድላ በመፈለግ ዘወትር ሃዘንተኞች ሆነው ሲቆዝሙ መኖራቸው ነው።

የጸሎት ሕይወት ውስጥ መግባት ለብዙ ሰዎች አዳጋች ቢሆንም እንደ ሐዋርያትና ነቢያት ለማገልገል የግድ የጸሎት ሕይወት ውስጥ መግባት ያስፈልጋል፤ እንደ እነርሱ ሆኖ ማገልገል አይቻልም የሚል የዶሮዎችን ምክር ባንሰማ እንደ ንስር በመንፈሳዊ ክንፍ እየበረሩ የዓለምን ጥራጊ ወደ ታች ማየት በተቻለን ነበር።

ዳሩ ግን አንድ የተለመደ አባባል አለ፤ "ከማን ጋር እንደምትውል ንገረኝና ማን እንደሆንክ ልነግርህ እችላለሁ" የሚል ነው። ነገሩ እውነት ነው፤ ሰው አብሮት የሚውለውን ይመስላል። ከፌዘኛ ጋር የሚውል ፌዘኛ ይሆናል፤ ከሰነፍ ጋር የሚውል ስንፍናን ሲማር ከብርቱ ጋር የሚውል ብርቱ ይሆናል ከጸሎተኛ ሰው ጋር የሚውል ደግሞ ጸሎተኛ ይሆናል።

ጸሎት ልመና ብቻ ሳይሆን ከጌታ ጋር ኅብረት የምናደርግበት ሁኔታ ነው። የጸሎት ሰው የጌታ ልብ ይኖረዋል፤ የረጅም ጊዜ ኅብረት ከእርሱ ጋር ከፈለግን ረጅም የጸሎት ጊዜ እንዲኖረን ያስፈልጋል። ረጅም ጊዜ በጸሎት ማሳለፍ ለአንዳንዶች ጊዜን በከንቱ ማጥፋት ይመስላቸው ይሆናል። እርግጥ ነው ሁሉም ሰው ቀኑን ሙሉ በጸሎት ለማሳለፍ ይቸገር ይሆናል። ይሁን እንጂ ሙሉ ጊዜያቸውን ለእግዚአብሔር ሥራ የሰጡ ከቀኑ ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ በጸሎት ማሳለፍ አለባቸው። ምክንያቱም ትልቅ መንፈሳዊ ሥራ የሚሠራው በጸሎት ነውና። በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በነበሩ አገልጋዮችና በዚህ ዘመን ባሉ አገልጋዮች መካከል ትልቅ መንፈሳዊ ልዩነት የሚታየው በጸሎት ምክንያት ነው። የመጀመሪያዎቹን የቤተ ክርስትያን አገልጋዮች ሕይወት መኖር የማይናፍቅ ማንም የለም፤ እነርሱን ለዚያ ታላቅ አገልግሎት ያበቃቸው ጌታ ነው እንጂ በራሳቸው የበቁ አልነበሩም። ለዚያ ታላቅ አገልግሎት ያበቃቸው ጌታ ዛሬም ያው ነው (ዕብ.13:8)።

በእነርሱና በእኛ መካከል ያለው ልዩነት ጸሎት ነው። እነርሱ በጸሎት ተጉ (ሐዋ.2:42፤ 6:4) እኛ ጸሎትን ቸል አልን፤ እነርሱ አብዛኛውን

ጊዜያቸውን ያሳለፉት ቃሉን በማስተማርና በጸሎት ነው፤ እኛ የአምስት ደቂቃ ጸሎት፥ የአምስት ሰዓት ስብሰባ እናደርጋለን። (ያን ያህል ጊዜ ተወስዶም አብዛኛውን ጊዜ ያለ ውሳኔ ስብሰባዎች ያልቃሉ።) እነርሱ ግን አብዛኛውን ጊዜ ችግሮችን ለመፍታት ለጸሎት ይሰበሰባሉ። እኛ ግን ብዙውን ጊዜ ችግሮቻችንን በጠረጴዛ ዙሪያ ለመፍታት እንጥራለን። የውይይት ውጤት ብዙውን ጊዜ የኃሳብ ልዩነት ሲፈጥር፤ ጸሎት ግን ምንጊዜም የልብ አንድነት ይፈጥራል። ስለዚህ ከላይ እንደተጠቀሰው ትልቁን መንፈሳዊውን ሥራ መሥራት የምንችለው በጸሎት መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ሳታቋርጡ ጸልዩ ያለው (1ተሰ.5:16-17)። ጳውሎስ አገልግሎቱን እንዴት እንደሚፈጽም ሲናገር "በእምነታችሁም የጎደለውን ልንሞላበት ሌሊትና ቀን ከመጠን ይልቅ እየጸለይን . . ." 1ተሰ.3:9። "ሌሊትና ቀን ከመጠን ይልቅ" የሚለውን አባባል ልብ እንበል! በዚህ ዘመን ሌሊትና ቀን የሚጸልይ ቀርቶ የቀኑን እኩሌታ እንኳን በጸሎት የሚያሳልፍ አገልጋይ ቢፈለግ ምናልባት ጥቂት ብቻ ይገኝ ይሆናል።

ጸሎት የሃይማኖት ሥርዓት ማድረስ አይደለም፤ የጸሎት ጊዜ የነገሥታት ንጉሥ ከሆነው ጌታ ጋር የምናሳልፈው ጊዜ ነው። ለጸሎት ሰው ከጸሎት ጊዜው የበለጠ የተወደደ ጊዜ አይኖረውም። ጊዜ ክቡር ነው ካልን በጸሎት የምናሳልፈው ጊዜ የበለጠና የከበረ ይሆናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አብረውት የሚውሉትን ያከብራል፤ እርሱን እንዲመስሉ አድርጎ ይለውጣቸዋል፤ በጸሎት እውነተኛ መንፈሳዊ ድል ይገኛል። መንፈሳዊ ድል ክርስቶስን መምሰል ነው፤ ለብዙ ክርስቲያኖች ክርስቶስ ከአድማስ ባሻገር ሆኖ ይታያቸዋል። የጸሎት ሰው ግን ክርስቶስ ከእስትንፋሱ ይልቅ ቅርቡ እንደሆነ ያውቃል። ከብዙ ሰዎች ጋር ጊዜውን የሚያጠፋ ችግር ሰው ይበዛበታል። የጸሎት ሰው ከጥቂቶች ጋር ወይም ለብቻው ይገኛል ቢሆንም ብቸኝነት አይሰማውም፤ በሰዎች ከሚታጀብ ይልቅ መረጋጋትና ምቾት ይሰማዋል። ምክንያቱም ሕይወቱ የሚሞላው በጌታ ክብር ነው። ስለሆነም ለጸሎት ሰው ጊዜ በጣም ውድ ስለሆነ ከማን ጋር እንደሚያሳልፍ ስለሚያውቅ ጊዜውን በጥንቃቄ ይጠቀምበታል። ለዚህ ዓለም ልዩ ልዩ ተድላና ምቾት ባሪያ ለሆኑ ሰዎች የጸሎት ጊዜ አይኖራቸውም። ስለዚህ ዘወትር በመንፈሳዊው ነገር ተሸናፊዎች ይሆናል። የጸሎት ሰው ግን ከራሱ አልፎ የሌሎችን ችግር ይፈታል። በድል ሕይወት ለመመላለስና የዲያብሎስን ሥራ ለማፍረስ ጸሎትን የሚተካ ነገር የለም።

በጸሎት መንፈሳዊ ውጊያ ስላለበት ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ እንዳለን ሲያመለከት "በሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ ብንሆን እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም፤ የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና ፥ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ብርቱ ነው" ይላል (2ቆሮ.10:3-4)። የጠላትን ምሽግ ለማፍረስ ብርቱ መሆን ያስፈልጋል፤ እርሱም እንዴት እንደሆነ በጸሎት ሕይወት ውስጥ የገባ ክርስቲያን ያውቀዋል፤ የጸሎት ሰው ባለበት ዙሪያ የዲያብሎስ ዙፋን አይኖርም። በጸሎት ጊዜ የገሃነም ደጆች ይናወጣሉ፤ ዲያብሎስ ይታሰራል፤ እስረኞች ይፈታሉ (ሐዋ.12:5-11፤ 16:24-34)። ስለዚህ በድል ሕይወት ለመኖር በመንፈሳዊ ሕይወታችንና በአገልግሎታችን ታላቅ ለውጥ ለማየት ከፈለግን ለጸሎት እንነሳ፤ ነገ ሳይሆን ዛሬውኑ እንጀምር።

## 3. ጾምን መለማመድ

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ጾም ከፍተኛ መንፈሳዊ ልምምድ ነው። በብሉይ ኪዳን ረጅም ጊዜ የጾመ ሙሴ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ጾም ራስን በማዋረድ እግዚአብሔርን የምናከብርበት ሁኔታ ነው። ጾም ከፍተኛ መንፈሳዊ ድልና በረከት የምናገኝበት በመንፈሳዊ ሕይወትና በአገልግሎት ለማደግ የሚያግዘን መንፈሳዊ ልምምድ ነው። ጾምን ለምን አዘውትረን መለማመድ እንዳለብን ቀጥለን እንመለከታለን።

### ሀ. ጾም አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት:-

#### 1ኛ. ጾም አምልኮ ነው:-

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን የነበሩ ቅዱሳን እግዚአብሔርን በጾም ያመልኩ እንደነበር ተጽፏል። እስራኤላውያን በየዓመቱ ከሚያከብሯቸው ሦስት ታላላቅ በዓላት አንዱ የሥርየት ቀን ነው። በዚህ ቀን ሕዝቡ ሁሉ ይጾማሉ (ዘሌ.16:29፤ 23:27-29፤ ሐዋ.27:9)። በተጨማሪም በየግላቸው በጾም እግዚአብሔርን በማምለክ የሚተጉ መኖራቸው የታወቀ ነው። ጌታም በምድር በነበረበት ጊዜ አይሁድ በየሳምንቱ ሁለት ቀን የመጾም ልምድ ነበራቸው (ሉቃ.18:12፤ ማቴ.9:14)። አንዳንዶች ግን መንፈሳዊ ለመምሰል ይጾሙ ስለነበረ ከእንደዚህ ያለ የግብዝነት አምልኮ እንዲጠበቁ ጌታ አስተምሯቸዋል (ማቴ.6:6-18)።

በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስትያን የጾም ፕሮግራም ምን ይመስል እንደነበር በዝርዝር የተጻፈልን ነገር ባይኖርም በአንጾኪያ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን

መሪዎች በአንድ ላይ ተሰባስበው እየጾሙ ጌታን ያመልኩ እንደነበር ተጽፏል (ሐዋ.13:1)። በየጊዜው የተደረገው ክስተት ሁሉ ባይጻፍልንም በአንጾኪያና በየቤተ ክርስቲያናቱ በጋራም ሆነ በግል በጾም ሆኖ እግዚአብሔርን ማምለክ የተለመደ ሁኔታ መሆኑን መገመት አያስቸግረንም።

2ኛ. **ጾም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሲሾሙ አስፈላጊ ነው:-**
በአንጾኪያ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጾምና በጸሎት ሆነው ጌታን ሲያመልኩ መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስንና በርናባስን ለአገልግሎት ለዩልኝ አለ። እንዲሁም የጾም ጊዜ ወስደው እጃቸውን ጭነው እንደጸለዩ እናያለን (ሐዋ.13:1-3)። አገልጋዮቹም በየሥፍራው ወንጌልን እየሰበኩ ብዙ ምዕመናንን ካፈሩ በኋላ መሪ የሚሆኑትን ሽማግሌዎች ሲሾሙላቸው በጌታ ፊት በጾም ቆይተው ነበር (ሐዋ.14:23)። በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት መሪዎች ሲሾሙ በጾምና በጸሎት እንደነበር እናያለን።

በዚያን ዘመን በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ሲሾሙ በጾምና በጸሎት መቆየትና መሾም የተለመደ አሠራር ነበር። በዚያን ዘመን የነበረች ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አቋሟ እጅግ ጠንካራ የነበረው በዚህ ምክንያት ነበር ማለት ይቻላል። በአሁኑ ጊዜ ይህንን መንፈሳዊ አሠራር የሚከተሉ ብዙዎች አይደሉም። በአሁኑ ዘመን ያሉ ብዙ መንፈሳዊ መሪዎች ትኩረት የሚሰጡት ለከፍተኛ ትምህርትና ዘመኑን የተከተለ ድርጅታዊ አሠራር ላይ ነው። ይህ አስፈላጊ ቢሆንም መንፈሳዊውን ሥልጣን ለመቀዳጀት ጾምና ጸሎትን ሊተካ አይችልም። መንፈሳዊ ሥልጣን የማይገለጥበት ከሆነ በምንም ሊታወቅ አይችልም። መንፈሳዊ ሥልጣን ከእግዚአብሔር ለመቀዳጀት እንደ እግዚአብሔር ቃል መንፈሳዊውን ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል። የእግዚአብሔር ነገር የሚገኘው ብዙውን ጊዜ ለሰዎች ሞኝነት በሚመስላቸው አሠራር ውስጥ ነው።

3ኛ. **ጾም እራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት የምናዋርድበት ሁኔታ ነው:-**
ሰው እግዚአብሔርን ለማስደሰት የሚችለው ራሱን በማዋረድ ነው። ሰው በትክክል እራሱን ማዋረድ የሚችልበት ሁኔታ ደግሞ ጾምን ሲለማመድ ነው። ስለዚህም "ጾምን አውጁ" ይላል እግዚአብሔር (ኢዩኤል 1:14፣ 2:15-16)። በጾም እራሳቸውን አዋርደው ወደ ፊቱ የሚቀርቡትን እግዚአብሔር ፈጥኖ ያነሳቸዋል (1ጴጥ.5:6፣ ያዕ.4:10)። በእግዚአብሔር ፊት ክፋትን ለማድረግ ሁለንተናውን ለኃጢአት አሳልፎ የሸጠ አክአብን

የሚመስል ማንም አልነበረም የተባለለት ንጉሥ ነብዩ ኤልያስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለሚደርስበት ጥፋት በነገረው ጊዜ ልብሱን በመቅደድ ማቅን ለብሶ በመጾም ወደ እግዚአብሔር ቀረበ፤ እግዚአብሔርም በፊቱ እራሱን በማዋረዱ ሊያመጣበት የነበረውን ክፉ ነገር እንደተወ እናያለን (1ነገ.20:27-29)።

የነነዌ ሰዎች እጅግ ኃጢአትን ባበዙ ጊዜ እግዚአብሔር ሊያጠፋቸው እንዳቀደ በነብዩ ዮናስ መልእክት ላከላቸው። እነርሱም የሚመጣባቸውን ጥፋት በሰሙ ጊዜ ከንጉሡ አንስቶ ሕፃናት እንኳን ሳይቀሩ በጾም ሆነው እራሳቸውን በማዋረድ ወደ እግዚአብሔር ቀረቡ። የነነዌ ሰዎች አሕዛቦችና አመጸኞች ቢሆኑም ዮናስ ወደ እነርሱ ተልኮ ሲመጣ አላላገጡበትም፤ ስለዚህም እግዚአብሔር ሊያመጣባቸው ከነበረው ታላቅ ጥፋት አዳናቸው (ዮናስ 3:5-10)።

4ኛ. **ከአቅም በላይ ችግር ሲገጥመን:-**
ንጉሥ ኢዮሳፍጥ ሦስት ኃያላን ነገሥታት ሊወጉት በከበቡት ጊዜ በጦርነት ቢገጥማቸው ሊቋቋማቸው እንደማይችል አውቆ ስለነበረ ከእግዚአብሔር ዘንድ ረድኤትን ለማግኘት ጾምን አወጀ፤ ከዚያም በሠራዊቱ ፊት መዘምራንን ሲያሰልፋቸው እግዚአብሔር ጠላቶቹን አሸበራቸው፤ እርስ በርሳቸውም ተጠፋፉ (2ዜና.20:1-30)።

በአንድ ወቅት እስራኤላውያን የብንያምን ነገድ ለመውጋት አራት መቶ ሺህ ሠራዊት ሆነው ለጦርነት ወጡ፤ ይሁን እንጂ በተደጋጋሚ በመሸነፍ ብዙ ሺህ ሠራዊት አለቁባቸው። ከዚህ በኋላ ጦርነት መግጠሙ እንደማያዋጣቸው በመረዳት በእግዚአብሔር ፊት ፆምን አወጁ፤ በሚቀጥለው ቀን ለውጊያ በመውጣት የብንያምን ሰልፈኞች መቱ፤ ጥቂት ብቻ እስኪተርፉ ድረስ ደመሰሷቸው። የእስራኤል ሠራዊት ጾምን በማወጅ ድል አገኙ። (መሳ.20:16-48)።

እስራኤላውያን በምርኮ አገር ሳሉ የፋርስ ንጉሥ አርጤክስስ ንጉሥ በነበረበት ጊዜ ሐማ በመርዶክዮስ ምክንያት አይሁድን ለማጥፋት በተንኮል ከንጉሡ ሥልጣን ተቀብሎ አዋጅ አስነግሮ ነበር። መርዶክዮስ ይህን ነገር በሰማ ጊዜ በጊዜው የንጉሡ ሚስት አይሁዳዊ ስለነበረች ሕዝቡን እንድታድን ላከባት፤ በዘመኑ ንጉሡ ሳይጠራ ማንም ሰው ወደ ንጉሡ ገብቶ ቢገኝ ይገደላል። ቢሆንም ንግስቲቱ አስቴር እስራኤላውያን

ሁሉ ጾምን እንዲወስዱ ለመርዶክዮስ ላከችበት፤ ንግስቲቱም ከደንገጡሮችዋ ጋር በመሆን የፆምን ጊዜ ወሰደች። ከሦስት ቀን በኋላ በቀጥታ ወደ ንጉሡ ገባች፤ እግዚአብሔርም በንጉሡ ፊት ሞገስን ሰጣት፤ በፆሙ ምክንያት አዋጁ ተገለበጠ፣ ሐማ ለመርዶክዮስ ባዘጋጀው ኃምሳ ክንድ ርዝመት ባለው ግንድ ላይ ተሰቀለ፤ እስራኤላውያንም ሊያጠፏቸው የተነሱባቸውን ጠላቶቻቸውን አጠፉ (አስቴር 4:15:17)።

5ኛ. ጾም በአገልግሎታችን ፍሬ እንድናፈራ ያደርገናል፦

ጌታ በአገልግሎታችን ብዙ ፍሬ ብናፈራ አብ በዚህ እንደሚከብርና የእርሱም ደስታ እንደሚበዛ ተናግሯል (ዮሐ.15:8-11)። እግዚአብሔር ምንም የሚጎድለው ነገር ሳይኖር በእኛ አገልግሎት መደሰቱ እጅግ የሚያስደንቅ ነው። በአገልግሎታችን ብዙ ፍሬ እንድናፈራ ለመንፈስ ቅዱስ አሰራር ምቹ ልብ እንዲኖረን ጾምን መለማመድ እጅግ አስፈላጊ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ቀንና ሌሊት በጸሎት የሚተጋውና ጾምን የሚያዘወትረው በአገልግሎቱ ፍሬ እንዲያገኝ ነበር (ኤፌ.1:16-18፣ 1ተሰ.3:7-8) ጾም ከመጀመሪያው እንዳየነው የራስን መሻትና ፍላጎት መስዋዕት ማድረግ ነው። የስንዴ ቅንጣት ብዙ ፍሬ ለማፍራት በእርሻ ውስጥ ወድቃ መሞት እንዳለባት ሁሉ ብዙ ፍሬ ለማፍራት ከፈለግን የራሳችን ምኞትና ፍቃድ መሞት አለበት (ዮሐ.12:24)። ይህም እንዲሆን ፆምንና ጸሎትን ማዘውተር ይጠቅማል።

6ኛ. ጾም የአገልግሎት በር እንዲከፈትልን ያደርጋል፦

አንዳንድ ጊዜ በማናውቀው መንገድ የአገልግሎት በር ይዘጋብናል፤ ስለዚህ ባልተጠራንበት አገልግሎት ውስጥ ገብተን ለማገልገል እንገደድ ይሆናል። ይህም የሚሆነው ምናልባት በሰዎች ወይም በሰይጣን አሰራር ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ጌታ የአገልግሎት በር እንዲሰጠን በጾም ልንተጋ ይገባናል። ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ተሰሎንቄ ሄዶ ለማገልገል ቢፈልግም አንዴና ሁለቴ ሰይጣን እንዳዘገየው ይናገራል (1ተሰ.2:18)። እንዲሁም ወደ ቆሮንቶስ ለመሄድና ለማገልገል እየተዘጋጀ ሳለ በአንድ ሰው ምክንያት ጉዞውን መሰረዙን በሃዘን ጻፈላቸው (2ቆሮ.1:15፣ 2:11)። በዚህ ዓይነት አገልግሎቱ እንዳይበላሽ ብዙ ጊዜ እንደፈራ ጽፏል። (2ቆሮ.11:26)። በትንሿ ኤሽያ ውስጥ በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ዲዮድራጢስ የሚባል ሰው ለራሱም ሆነ ለሌሎች ወንድሞች ትልቅ የአገልግሎት እንቅፋት እንደሆነበት ሐዋርያው ዮሐንስ ይናገራል (3ዮሐ.9-10)።

በሐዋርያት ዘመን አስቸጋሪ ክርስቲያኖች እንደነበሩ በዘመናችንም ይኖራሉ። ስለዚህ ማንም ሊዘጋው የማይችል የተከፈተ የአገልግሎት በር ጌታ እንዲሰጠን በጾምና በጸሎት በጌታ ፊት ልንተጋ ይገባናል (ራዕ.3:8)።

7ኛ. **አጋንንት ከሰዎች ላለመውጣት ሲታገሉን ጾም ይረዳናል፡-**
በአንድ ወቅት ጌታ ደቀ መዛሙርቱን ሁለት ሁለት በማድረግ አጋንንትን እንዲያወጡ በሽተኞችን እንዲፈውሱ ሥልጣን በመስጠት ላካቸው። ደቀ መዛሙርቱም አጋንንት እንኳን በስሙ እንደታዘዙላቸው ደስ እያላቸው ነገሩት (ሉቃ.10:17)። በሌላ ጊዜ ግን አጋንንት የያዘው ሰው እንዲያወጡለት ወደ ደቀ መዛሙርቱ አመጡ፤ ነገር ግን አልቻሉም። ጌታ ግን አጋንንቱን አስወጣው፤ ደቀ መዛሙርቱም እኛ ልናስወጣው ያልቻልነው ስለምንድ ነው? ብለው ሲጠይቁት "ይህ ዓይነቱ ወገን በጸሎትና በጾም ካልሆነ ሊወጣ አይችልም" አላቸው (ማቴ.9:14-29)። አጋንንትን አለማውጣት መንፈሳዊ ድክመት ስለሆነ በእምነት ብርቱና ጠንካራ ለመሆን በጾምና በጸሎት መትጋት አስፈላጊ መሆኑን ከጌታ አባባል እንማራለን።

በመድረክ ላይ ሆኖ የሰይጣን አድራሻ ከጫማዬ ሥር ነው ማለቱ ሰይጣንን አያስፈራራውም። ጌታ ሰይጣንን ከእግራችን በታች ፈጥኖ እንዲቀጠቅጥልን በጾምና በጸሎት ልንተጋ ያስፈልገናል (ሮሜ.10:20)። አጋንንትን ማውጣት ለክርስቲያን ሁሉ የተሰጠ ሥልጣን ነው። ነገር ግን አንዳንዶች በቀላሉ አይወጡም። ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት አጋንንት የያዛቸው ሰዎች ሲገጥሙን በጾም ሆነን ልንጸልይላቸው ይገባል።

8ኛ. **የጌታን ፈቃድ ለማወቅ ስንሻ፡-**
በሕይወቱ የጌታን ፈቃድ ለማወቅ የማይናፍቅ ክርስቲያን የለም። መጽሐፍ ቅዱስም "የጌታን ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ" ይላል (ኤፌ.5:17)። ይሁን እንጂ እንደምንፈልገው የእግዚአብሔርን ፈቃድ መረዳት የሚያቅተን ጊዜ አለ። ቢሆንም በሚያስፈልገን ነገር ሁሉ የጌታን ፈቃድ ለማወቅ የጾም ጊዜ ወስደን ስንጸልይ መንፈሳዊ ሕይወታችን ስለሚነቃቃ የጌታን ድምጽ መስማት እንጀምራለን።

9ኛ. **ወደ አዲስ የአገልግሎት ሥፍራ ስንጠራ፡-**
እግዚአብሔር ካስቀመጠን ሥፍራ ከመንቀሳቀሳችን በፊት ምን ጊዜም ቢሆን የጾምና የጸሎት ጊዜ ልንይዝ ይገባናል። አንዳንድ ጊዜ ካለንበት

ሥፍራ የተሻለ ኃላፊነት የምንቀበልበት መስሎ ስለሚታየን ፈጥነን እርምጃ እንወስድ ይሆናል። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን እንኳን ብናውቅ አዲሱን የሥራ ቦታ ከመረከባችን በፊት አስቀድመን በጾም ሆነን ለእግዚአብሔር አሳልፈን ልንሰጥ ይገባል። በርናባስና ሳውል መንፈስ ቅዱስ እንደጠራቸው ቢያውቁም ከነበሩበት ሥፍራ ከመንቀሳቀሳቸው በፊት ጾመውና ጸልየው መሸኘታቸው የበለጠ ፍሬ እንዲያፈሩ አድርጓቸዋል። ካለንበት የአገልግሎት ደረጃ ዝቅ ብለን እንድናገለግል ብንጠየቅ እንኳን የሥራው ባለቤት አብሮን እንዲሆንና ሁሉንም በጸጋ ለመቀበል እንድንችል በፊቱ የጾም ጊዜ ወስደን ብንጸልይ የበለጠ ፍሬ እንደሚሰጠን ልንዘነጋ አይገባም።

10ኛ. **በቤተሰብ መካከል ችግሮች ሲፈጠሩ:-**

በቤተሰብ መካከል የሚነሳ ችግር አንዳንድ ጊዜ በምክር ብቻ የሚወገድ አይሆንም። ሰይጣን ብዙውን ጊዜ የቤተሰብን ሰላም ለማደፍረስ ይጥራል። በተለይ በባልና ሚስት መካከል ሰላም ሲጠፋ ጸሎታቸው እንደሚከለከል ስለሚያውቅ በተቻለው መጠን እንዳይግባቡ ለማድረግ ይጥራል (1ጴጥ.3:7)። በቤተሰብ ሰላም ከጠፋ ንክኪው ቤተ ክርስቲያን ይደርሳል፤ በቤተሰብ ውስጥ ለሚፈጠር ችግር ሌላ መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ በጾም ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ትልቅ ፈውስ ማግኘት እንደሚቻል ማወቅ አስፈላጊ ነው።

11ኛ. **ለሌሎች ምሳሌ ለመሆን:-**

ጾም እጅግ መንፈሳዊ ድል የምናገኝበት ልምምድ ነው፤ በጾም እየተጋ በሕይወቱ ደካማ ሊሆን የሚችል ማንም አይኖርም። ጾም መንፈሳዊ ሕይወታችንን እጅግ የሚያነቃቃ ልምምድ ነው። ስለዚህ ጾምን ስንለማመድ ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም መነቃቃት ምክንያት እንሆናለን። ይሁን እንጂ "አንተ ግን ስትጾም በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደ ጾመኛ ለሰዎች እንዳትታይ" የሚለውን የጌታ አባባል ብዙ ክርስቲያኖች በተሳሳተ ሁኔታ ይወስዱታል።

ጌታ እንደ ግብዞች ለታይታ መጾም እንደሌለብን ለማስገንዘብ እንጂ ጾምን ስንወስድ ማንም ሰው ጨርሶ ማወቅ የለበትም ለማለት አይደለም። አርባ ቀንና ሌሊት መጾሙን ባይናገር ኖሮ ማን ሊያውቅ ይችላል? ሙሴ ሁለት ጊዜ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት መጾሙን ማወቅ የተቻለው እራሱ ስለተናገረ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ብዙ ጊዜ እንደሚጾም ተናግሯል (2ቆሮ.11:27)። ስለዚህ እኛ ቀደም ብለን ለአዳዲሶች ምሳሌ እንድንሆናቸው መጾማችንን ካልነገርናቸው ማንን አይተው ለጾም ይነሳሳሉ? ለሁሉ ነገር ምሳሌ መሆን እንዳለብን የእግዚአብሔር ቃል ያስተምረናል (1ጴጥ.5:3)።

12ኛ. **ጾም በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መነቃቃት እንዲነሳ ያደርጋል:-**
በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለብ ያለ ሕይወት አስቸጋሪ ነው፤ ያንን የሚቀይርና የሚያቀጣጥል የመንፈስ ቅዱስ እሳት ሲወርድ ብቻ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ "በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ" ይላል (12:13)። ቤተ ክርስቲያን ለአምልኮና ለወንጌል ሥራ የምትነቃቃው የመንፈስ ቅዱስ እሳት ሲገበኛት ነው። ቤተ ክርስቲያን ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ እንድትቀርብ የእግዚአብሔር እሳት ያስፈልጋታል (ኤፌ 5:27፣ ሚል.3:2-3)። ቤተ ክርስቲያን ዘወትር በመንፈስ ቅዱስ እሳት እንድትገበኝ በግልም ሆነ በጋራ የጾም ጊዜ እንዲኖር ያስፈልጋል። በቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር እሳት ሲነሳ ወንጌል ይዛመታል። (ሐዋ.1:8)።

13ኛ. **ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ናፍቆት መግለጫ ነው:-**
በአንድ ወቅት የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደ ጌታ መጥተው "እኛ ፈሪሳውያን ብዙ ጊዜ እንፆማለን የአንተ ደቀ መዛሙርት ግን የማይጾሙት ለምንድን ነው?" እርሱም እንዲህ አላቸው "ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎች ማዘን ይገባቸዋልን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ጊዜ ይመጣል፤ በዚያን ጊዜ ይጾማሉ" ብሎ መልስ ሰጣቸው (ማቴ.9:14, 15)።

ጌታ ራሱን በሙሽራው ደቀ መዛሙርቱን በሚዜዎቹ መስሏቸዋል። ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ ጋር እያሉ ማዘን እንደሌለባቸውና ነገር ግን እርሱ በሚወሰድበት ጊዜ እንደሚጾሙ ተናግሯል። ጌታ ሲናገር "ይጾሙ ይሆናል" ወይም "ሊጾሙ ይችላሉ" በሚል መልኩ አላስቀመጠም። ነገር ግን "ይጾማሉ" አለ። ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ የሆኑ ሁሉ እንደተናገረውም በጾም ይተጉ እንደነበር እናያለን (ሐዋ.13:1-3)። ሙሽራው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አብ ስለሄደ እኛም ልንጾም ይገባናል። በዚህ መልኩ ለጌታ ያለንን ናፍቆት የምንገልጽበት ስለሆነም ጾምን የማይለማመድ ለጌታ ዳግም ምጽአት ናፍቆት የሌለው ብቻ ነው።

በአጠቃላይ ጾምን የምንለማመድባቸው ብዙ የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም

ዋና ዋናዎቹን ባጭሩ ተመልክተናል። ሆኖም በጾም የሚገኘውን ታላቅ መንፈሳዊ በረከት ለማየት የምንችለው ጾምን ስንለማመድ ብቻ ነው። ብዙውን ጊዜ መንፈሳዊውን ነገር በሰው ቋንቋ መግለጽ አይቻልም፤ ይልቁንም በጾም ጊዜ የሚፈሰውን ታላቅ በረከትና መንፈሳዊ ድል ለመግለጽ ፈጽሞ አይቻልም። ነገር ግን ዛሬውኑ ጀምሮ ማየት ይቻላል።

**ለ. ላለመጾም ምክንያትና ሰበብ የሚሆኑ ነገሮች:-**

በአሁኑ ጊዜ ብዙ ክርስቲያኖች ለረጅም ቀናት ጾምን አይለማመዱም፤ ምክንያቶቹ ምን ይሆኑ? ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የተለያዩ ሁኔታዎች አሉ፤ እነዚህን ከዚህ በመቀጠል የምናያቸው ይሆናሉ።

1ኛ. **ጾምን መለማመድ ወግ አጥባቂነት ስለሚመስላቸው:-**

ጾም የድሮ ክርስቲያኖች ልምምድ ብቻ የሚመስላቸው ብዙ ሰዎች አሉ። በአሁኑ ጊዜ በጾም የሚተጉትንም ሲያዩ ወግ አጥባቂዎች አድርገው ያዩዋቸዋል። ስለዚህ ፆምን ከመለማመድ ይቆጠባሉ።

2ኛ. **ጾም የረሃብ ዋጋ ስለሚያስከፍል:-**

ሰዎች ለሚበሉትና ለሚጠጡት የሚጠየቁትን ዋጋ ይከፍላሉ። ኤሳው ለመብል ብኩርናውን ከፍሏል (ዕብ.12:16)። ለጾም ደግሞ የረሃብን ዋጋ መክፈል ግድ ነው። ይህንን ዋጋ ደፍረው የሚከፍሉ ጥቂቶች ናቸው።

ረሃብ የማያሸንፈው ጀግና የለም፤ ለምንም የማይገዛ ሰው ስለ መብል ይገዛል፤ ባለመጾማቸው ለመብል መሸነፋቸውን የማይገነዘቡ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ። ኤሳው ስለ መብል ብኩርናውን በመሸጡ ይስቃሉ፤ ነገር ግን እጾማለሁ ብለው ነገ ሲመጣ በጧቱ በሻይ ተሸንፈው ራሳቸውን ሲያዩ አይገርማቸውም፤ መሸነፍም የማይመስላቸው ብዙዎች አሉ። ከፍተኛ ራስ ወዳድነት ያለው በራስ ላይ ሳይሆን በሆድ ውስጥ ነው። በጾም የሚተጋ ሰው ግን ራስ ወዳድነትን በከፍተኛ ሁኔታ ድል ያደርጋል።

3ኛ. **በጌታ አምኜ ድኛለሁ፤ ሌላ ነገር አያስፈልገኝም በሚል ሰበብ:-**

ጾም ለጌታ ያለንን ናፍቆት የንምገልጽበት ነው ካልን ጾም የሚያስፈልገው በእርግጥ አምኖ ለዳነ ሰው ነው። ስለዚህ ጾምን የምናዘወትረው ደህንነት ለማግኘት ሳይሆን ጸንተን ለመቆም ነው። ደህንነት ለማግኘት ታላቅ ዋጋ ተከፍሏል። ይህንን ከተረዳን መትጋት ያስፈልጋል። የሚተጋ ሰው ብርቱ መሰናክል ሲገጥመው ጸንቶ መቆም ይችላል። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ

ይላል "ስለዚህ ወንድሞች ሆይ መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ፤ እነዚህን ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉም" (2ጴጥ.1:10)። በሌላ ሥፍራ ደግሞ "ሰው በጨለማ ሥፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህንን ቃል እየተጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ" ይላል (2ጴጥ.1:19)። ሐዋርያው ጳውሎስ "ሌሎችን ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሸምሁ አስገዛለሁ" ይላል (2ቆሮ.11:27)። በዚህ ሥፍራ "ሥጋዬን እየጎሰምኹ አስገዛለሁ" ሲል በጾም እንደሚተጋ የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም።

4ኛ. **የጾምን ጥቅም ያለማወቅ፦**
የእግዚአብሔርን ማዳንና ቸርነት ቀምሰን ስላየን እንጂ ማወቅ አንችልም ነበር (1ጴጥ.2:1)። ስለዚህ ጾምን ያልተለማመዱ ክርስቲያኖች ጥቅሙን ስለማያውቁ በጾም የሚተጉትን ዳር ሆነው ቢያዩ አያስገርምም። ነገር ግን ብዙ ክርስቲያኖች የተጠቀሙበት መልካም ልምምድ ቢኖር ጾም ነው።

5ኛ. **ለጾም ጊዜ የለኝም ብሎ ማመካኘት፦**
ጾምን ለመለማመድ ቤት ዘግቶ መቀመጥ የሚያስፈልግ የሚመስላቸው ሊኖሩ ይችላሉ። ረዘም ላለ ጊዜ ቤት ዘግተን በጌታ ፊት የምንቀይበት የጾም ዓይነት መኖሩ አይዘነጋም። ይሁን እንጂ በጾምን ጊዜ የግድ ከእለት ተግባራችን ቀርተን ቤት መዋል አያስፈልገንም። የእለት ተግባራችንን እያከናወንን መለማመድ የምንችለው የጾም ዓይነት ስላለ ስንደርስበት እናያለን።

6ኛ. **የጾም ጸጋ የለኝም በሚል ሰበብ፦**
በጾም ለመትጋት የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ያስፈልገን ይሆናል፤ ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎችን እንደፈቀደ ለእያንዳንዳችን እያካፈለ እንደሚሰጠን ዓይነት አይደለም። ጾም የግል ምርጫ ስለሆነ በጾም ለመትጋት ስንጀምር ለሁላችን ጸጋ ይሞላናል። ጾም ከጸጋ ስጦታዎች አንዱ መስሏቸው ሞክረው ሲከብዳቸው ጾም የጸጋ ስጦታዬ አይደለም ብለው የተታለሉ ወገኖች አይጠፉም። ጾም የግል ውሳኔንና ምርጫን የሚጠይቅ እንጂ የጸጋ ስጦታ ስለ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰበት ቦታ የለም።

7ኛ. **ብዙ ይጾሙ የነበሩ በትምህርት ስተዋል በሚል ምክንያት፦**
በጾም ይተጉ የነበሩ ጥቂት አገልጋዮች እንግዳ የሆነ ትምህርት

ማምጣታቸው አይዘነጋም። እነርሱ ቀድሞውኑ የእግዚአብሔርን ቃል በሥርዓት አልተማሩም ነበርና ልጓም የሚሆናቸው ነገር ባለመኖሩ ስተዋል።

ብዙውን ጊዜ ክርስትያኖች በጾምና በጸሎት ሲተጉ መንፈሳዊ ሕይወታቸው ይጋጋላል፤ በዚያ ሁኔታ ውስጥ ሲሆኑ የሚመራቸው በቃሉ የበሰለ ሰው ከሌለ በሚሰሙት ትምህርት መወሰዳቸው የማይቀር ነው፤ ምክንያቱም ማናቸውም መንፈሳዊ ፕሮግራም ሲጀመር ከፍተኛ ፍንደቃ ስለሚሰማቸው ነው። ያ በረከት ቀድሞውኑ መኖሩን ስለማያስተውሉ በተሰጠው ትምህርት ምክንያት ስለሚመስላቸው ኋላ የስህተት እንደሆነ ቢነገራቸው "ተባርኬበታለሁ" በሚል ምክንያት በረከታቸውን ማረጋገጫ በማድረግ ያለ ምንም መከላከል ይቀበሉታል። ብዙ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ በረከት ካለ ስለሚሰጠው ትምህርት አይጠነቀቁምና በቀላሉ ይስታሉ።

የእግዚአብሔርን ቃል በተመለከተ ቀደም ሲል እንዳየነው ከስሜቱ ይልቅ የሕይወቱ መመሪያ አድርጎ መጽሐፍ ቅዱስን መቀበል ከብዙ የስህተት መንገድ ይጠብቀናል። ይሁን እንጂ እነዚህን የስህተት ትምህርቶች ያመጡት መሠረት ያደረጉትና እጅግ እያጋነኑ የሚያስተምሩት ጾምን ስለሆነ ሰይጣን በዚህ ምክንያት አግኝቶ ብዙ ክርስትያኖችን የቀድሞ ልምምዳቸውን አስጥሏቸዋል። ከላይ እንዳየነው ቀድሞውኑ ጾምን መለማመድ የማይሆንላቸው ወገኖች የሚጾሙትን ሲያዩ "ከእነርሱ ወገን ናችሁ" እያሉ ለመቃወም ምክንያት ሆነላቸው። ስለዚህም ቀስ በቀስ ይህ ስንፍና ወደ ሌሎችም ተዛመተና "ብዙ ይጾሙ የነበሩ ስተዋልና" በማለት ጾምን ብዙ ክርስቲያኖች እርግፍ አድርገው ለመተው በቁ።

8ኛ. **በሕመም ምክንያት:-**
ለመጾም የሚያዳግት የህመም ዓይነት፤ የስኳርና የጨጓራ ህመም ያለባቸው ወገኖች ለመጾም እየፈለጉ ያቃታቸው ይኖራሉ። ይሁን እንጂ ፈጽሞ ከመተው ቀለል ያሉ ምግቦችን በመውሰድ ቢለማመዱ ያንን ጌታ የበለጠ ዋጋ ይሰጠዋል።

9ኛ. **ድሮ ጾሚያለሁ አሁን አይጠበቅብኝም በሚል ሰበብ:-**
በመንፈሳዊ ሕይወት እርጅና የለም፤ የእግዚአብሔር ቃል የሚነግረን ጻድቅ በስተርጅና እንደ ዘንባባ እንደሚያፈራ ነው (መዝ.(92):12-14)። ሰዎች ከእነርሱ በፊት የነበሩትን ማየትና ከእነርሱ መማርን ይፈልጋሉ።

ስለዚህ ዕድሜ አግኝተው በእግዚአብሔር ፊት የቆዩ ጾምን ቢለማመዱ ለሌሎች ምሳሌ የሚሆኑበትን መልካም አጋጣሚ ያገኙ ነበር።

10ኛ. **አሁን አዲስ ክርስቲያን ነኝ፤ በሕይወቴ ስብረታ እለማመዳለሁ በሚል ሰበብ፦**

የአንድ ቤት ጥንካሬ የሚለካው በአመሠራረቱ ነው፤ አንድም ዛፍ ወደ ላይ ቀጥ ብሎ እንዲያድግ ሥሩ ወደ ታች መሰደድ አለበት። መንፈሳዊ ሕይወትም እንዲሁ ነው። "እንግዲህ ጌታ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደተቀበላችሁት በእርሱ ተመስርታችሁ ሥር ሰዳችሁ በእርሱ ታነጹ" ይላል (ቆላ.2:6-7)። መንፈሳዊ ዕድገት የተፈጥሮን ሕግ የተከተለ አይደለም፤ ቶሎ ቶሎ የበላና የጠጣ ቶሎ ቶሎ ያድጋል። አበቃቀሉ ላይ የቀጨጨ ዛፍ ከጊዜ በኋላ የሚመቸው ሁኔታ እንኳን ቢያገኝ እንደሚገባ አያድግም። ስለዚህ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለማደግ ጊዜ የሚጠብቅ ሰው በክርስቶስ ሥር መስደዱ ይቀርና በሌሎች ላይ ተቀጥላ መሆኑ የማይቀር ነው።

11ኛ. **ጾም የሚያዘወትሩ ከእኛ ወገን አይደሉም በሚል ሰበብ፦**

ከላይ ከቁጥር ሰባት ላይ ባየነው ምክንያት ሳይሆን በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ጾም እምብዛም አይታወቅም። ስለዚህ ጾምን ብለማመድ ከእነርሱ ጋር እቆጠራለሁ በሚል ፍራቻ ጾምን የማይለማመዱ ወገኖች ይኖራሉ። በመሠረቱ ጾም የግል ጉዳይ እንጂ የጥቂት ቤተ ክርስቲያን ልምምድ አይደለም። ጾምን ያዘዘ ጌታ ነው፤ የጌታን ቃል ለመታዘዝ ከወደድን ማንንም ሳንፈራ ልንጀምር ይገባናል።

12ኛ **ብጾም በቂ የጸሎት ጊዜ የለኝም በሚል ምክንያት፦**

ብዙ ክርስቲያኖች ጾምና ጸሎት የግድ አብሮ የተያያዘ ይመስላቸዋል። ነገር ግን ጌታ ሁለቱንም ለየራስ ነው ያስተማረው እንጂ "ጾምና ጸሎት" በማለት ትምህርት አልሰጠም በማቴ.6:7-15 ስለ ጸሎት ካስተማረ በኋላ ምዕራፍ 6:16-18 ለይቶ ስለ ጾም አስተምሯል። እግዚአብሔርም ለሁለቱም ልምምዶቻችን ዋጋ የሚከፍለው በተናጠል እንደሆነ በግልጽ አስቀምጦታል። ስለዚህ ለመጸለይ አልጾምኩም ብለን መጸለያችንን እንደማንተው ሁሉ በቂ የጸሎት ጊዜ የለኝም ብለን መጾምን መተው የለብንም። በጾም ጊዜ ረጅም የጸሎት ጊዜ ቢኖረን መልካም ነው፤ ካልሆነም በቂ የጸሎት ጊዜ ስለሌለኝ መጾሙ ዋጋ የለውም የሚለውን አስተሳሰባችንን የግድ መለወጥ ይኖርብናል። ጾምና ጸሎት የሚደጋገፉ

ቢሆኑም ጾም ጸሎትን ጸሎትም ጾምን አይተካም።

**ሐ. ጾምን በደረጃ መለማመድ**

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጾም እንዳለብን ተጽፎ እናገኛለን እንጂ እንዴትና መቼ መጾም እንዳለብን የተሰጠ ሕግ የለም። ሆኖም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሦስት የጾም ዓይነትና ደረጃ መኖሩን እናያለን። የመጀመሪያው ደረጃ ፍጹም የሆነ ጾም ሲሆን የዚህ ዓይነት ጾም ያለ ምግብና ውሃ ለተወሰኑ ቀናት መቆየት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ሙሴ ሁለት ጊዜ አርባ ቀንና ሌሊት ያለ ምግብና ያለ ውሃ በእግዚአብሔር ፊት እንደነበረ እናያለን (ዘጸ.24:18 ዘዳ.10:10)። ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ልዩ መመሪያ ሳናገኝ ከሦስት ቀን በላይ ያለ ውሃ መቆየት አደገኛ ነው።

2ኛ/ ሁለተኛ ደረጃ ሙሉ ጾም የምንለው ሲሆን ይህ ዓይነቱ ጾም ውሃ ብቻ በመጠጣት ለተወሰኑ ቀናት መቆየት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አርባ ቀን የጾመው ውሃ እየጠጣ ነበር የሚሉ ብዙ ሰዎች አሉ። ምክንያቱም "በእነዚያ ቀናት ምንም አልበላም" ስለሚል ውሃ ይጠጣ ነበር ማለት ነው ይላሉ፤ እንደገናም "አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ ተራበ" ስለሚል ውሃ ባይጠጣ ኖሮ አርባ ቀን ለቆየ ሰው ከመብል ይልቅ ውሃ ስለሚጠማው አስቀድሞ "ተጠማ" ይል ነበር ያላሉ (ሉቃ.9:2፣ ማቴ.4:2)። ይሁን እንጂ ውሃ ይጠጣ ነበር ተብሎ ስላልተጻፈ ይህ አባባል ውሃ ስለመጥማቱ በቂ ማረጋገጫ ሊሆነን አይችልም። ውሃ እየጠጣ ጾም ከሆነ ይህን ዓይነት ጾም ሙሉ ጾም ማለት እንችላለን።

በሦስተኛ ደረጃ የምናየው ጾም "በከፊል ጾም" የምንለው ዓይነት ነው። ይህን ዓይነቱን ጾም በሁለት መልክ መውሰድ ይቻላል። አንደኛው እስከ ማታ ለተወሰኑ ቀናት የሚወሰድ ጾም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቀላል ምግቦችን በመውሰድ ወይም ፈሳሽ ነክ ምግቦችን በመውሰድ እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ መቆየት ነው። ዳንኤል ለሦስት ሳምንታት ያህል ሲጾም ቀላል ምግቦችን በመውሰድ እንደጾመ እናያለን (ዳን.10:2-3)።

**መ. ጾምን ለመለማመድ የሚሻ ሰው በሚከተሉት ሁኔታዎች በቀላሉ ወደ ከፍተኛ ደረጃ መድረስ ይችላል:-**

1ኛ. በመጀመሪያ ሳምንት እስከ ምሳ ሰዓት ሳምንቱን ሙሉ ሻይ በመውሰድ መቆየት:-

2ኛ. በሁለተኛ ሳምንት ጧትና በምሳ ጊዜ ሻይ በመውሰድ መቆየት፣

3ኛ. በሦስተኛ ሳምንት ሻይ መጠጣቱን መተው፤ ውሃ በመውሰድ እስከ እራት መቆየት፤

4ኛ. ከዚያም ለሦስት ቀናት በማከታተል በውኃ ብቻ መቆየት፤

5ኛ. በሥራ ላይ እያሉ ከሦስት ቀን በላይ ለመቆየት ከተፈለገ ውሃ በስኳር እያፈሉ ጠዋት፣ ቀንና ማታ አንዳንድ ብርጭቆ በመውሰድ እስከተፈለገ ጊዜ ያለምንም ድካም መቆየት ይቻላል።

6ኛ. ከሦስት ቀናት በላይ በውሃ ብቻ ለመጾም ከታሰበ የእረፍት ጊዜ ወስዶ መቆየት ያስፈልግ ይሆናል፤ ለሁሉም ሊወሰድ የታሰበውን የጾም ዓይነት መወሰን ያስፈልጋል። ብርታት ከተሰማን ከዚያ በላይ መሄድ እንጂ የወሰነውን ጊዜ ሳንጨርስ ምንም ዓይነት ፈተና ቢገጥመንም ማቋረጥ የለብንም።

## ሠ. ለረጅም ጊዜ ስንጾም የሚሰሙን ነገሮች፡-

ለመጀመሪያ ጊዜ ከሦስት ቀን በላይ ውሃ ብቻ እየወሰዱ የሚቆዩ ሰዎች ራስ ምታት፣ ቁርጥማት፣ ድካም፣ ረሃብ፣ ባዶነት፣ እንቅልፍ ማጣት ይሰማቸዋል። (እንቅልፍ ማጣት የረጅም ጊዜ ጾም ስንወስድ ምን ጊዜም ሊኖር ይችላል)። ብዙ ጊዜ ደጋግመን ስንወስድ እንቅልፍ ከማጣት በስተቀር የቀሩት ሁሉ ይወገዳሉ። የምግብ ናፍቆት ብቻ ሲቀር ረሃብ አይሰማንም፤ እንዲያውም በቃላት ለመግለጽ የሚያስቸግር ልዩ ሰማያዊ ነገር ስለሚሞላን እንዳይቋረጥብን ውስጣዊ ሕይወታችን ምግብ አለመውሰድን ይመርጣል።

## ረ. ጾምን ለመውሰድ ስናስብ ልናስተካክላቸው የሚገቡ ነገሮች፡-

ምንጊዜም ቢሆን ጾምን ለመያዝ ስናስብ አስቀድመን ከሰዎች ጋር ያለንን ሁኔታ ማየትና ለማስተካከል መሞከር አለብን። ጌታችን "መባህን በመሰዊያ ላይ ብታቀርብ በዚያ ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ በዚያ በመሰዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፣ አስቀድመህ ከወንድምህ ጋር ታረቅ በኋላ መጥተህ መባህን አቅርብ" ብሎ የተናገረውን ቃል ልናስብ ይገባል (ማቴ.5:23-24)። ጾምን ስንወስድ እራሳችንን ነው ለእግዚአብሔር ሕያው መስዋዕት አድርገን የምናቀርበውና ስለዚህ አቀራረባችን እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኘው መሆን አለበት (ሮሜ.12:1-3)። በእነደዚህ ሁኔታ ሆነን ሳንቀርብ ቀርተን "እግዚአብሔር ለምን መልስ አይሰጠኝም" ማለቱ ዋጋ የለውም።

እስራኤላውያን እየጾሙ ከእግዚአብሔር መልስ ባጡ ጊዜ "ስለምን ጾምን አንተም አልተመለከትከንም?" አሉት። እግዚአብሔርም "በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ" አላቸው (ኢሳ.58:3)። እግዚአብሔር የቀረበለትን መስዋዕት ሁሉ የግድ መቀበል እንዳለበት አድርገን ማሰብ የለብንም። ጾማችንን በደስታ የሚቀበለው እንደፈቃዱ ሆነን ስንቀርብ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። በተለይ በጾም ጊዜ በባልና በሚስት መካከል ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄ አለ፤ ሁለቱም ተስማምተው ለመጾም ካልወሰኑ በስተቀር አንዳቸው ብቻ ፍጹም ጾም ወይንም ሙሉ ጾም ለረጅም ጊዜ ለመውሰድ አይችሉም። ባልና ሚስት በጋራ የሚካፈሉት ብዙ ነገር ስላለ በዚህ ረገድ አንዱ ለሌላው እንቅፋት ማኖር የለበትም (1ቆሮ.7:5)። ይሁን እንጂ የአንዳቸው መበርታት ለሌላውም በረከት ስለሚሆን በኃሳብ መደጋገፍና መፈቃቀድ ይኖርባቸዋል።

ሰ. **ጾም ስንጨርስ ምግብ አወሳሰድ ላይ ልናደርገው የሚገባ ጥንቃቄ፡-**
ብዙ ክርስቲያኖች ፍጹም ወይም ሙሉ ጾም ከወሰዱ በኋላ ምግብ አወሳሰዱ ላይ ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው የተጎዱና ሕይወታቸውንም ያጡ አሉ። ስለሆነም ከጾም በኋላ ምግብ አወሳሰድ ላይ የሚከተሉትን መመሪያዎች መከተል ጠቃሚ ነው።

1ኛ. በውሃ ወይንም ያለ ውሃ ከሦስት እስከ አምስት ቀናት ያህል ከተጾመ፡-
- ሀ) በመጀመሪያው ቀን የፍራፍሬ ጭማቂዎችን ብቻ መውሰድ፤
- ለ) በሁለተኛው ቀን ከአትክልት የተሰራ ሾርባ መውሰድ፤
- ሐ) በሦስተኛው ቀን የተለመደውን ምግብ መመገብ መጀመር ይቻላል፤

2ኛ. ከአምስት እስከ ሰባት ቀን በውሃ ወይም ያለ ውሃ የተጾመ ከሆነ፡-
(በመሠረቱ ከሦስት ቀን በኋላ ያለ ውሃ ለመጾም መደፋፈር አያስፈልግም)
- ሀ) በመጀመሪያው ቀን የፍራፍሬ ጭማቂ መውሰድ፤
- ለ) በሁለተኛው ቀን የአትክልት ሾርባ መውሰድ፤
- ሐ) በሦስተኛው ቀን ማናቸውም ሾርባና አትክልት መብላት፤ ከዚያም ቀስ በቀስ ወደ ተለመደው አመጋገብ መድረስ ይቻላል።

3ኛ. ከሰባት እስከ አስራ አምስት ቀን ለሚጾሙ፡-
- ሀ) በመጀመሪያው ቀን ቀጠን ያለ ጭማቂ መውሰድ፤

ለ) በሁለተኛው ቀን ጭማቂና አትክልት መውሰድ፣
ሐ) በሦስተኛው ቀን የአትክልት ሾርባ መውሰድ፣
መ) በአራተኛው ቀን ማናቸውንም ሾርባና አትክልት በመውሰድ ቀስ በቀስ ወደ ተለመደው አመጋገብ መድረስ ይቻላል።

4ኛ. ከአሥራ አምስት ቀን እስከ ሃያ ቀን ለሚጾሙ:-
ሀ) በመጀመሪያው ቀን ቀጭን ጭማቂ ብቻ መውሰድ፣
ለ) በሁለተኛው ቀን ያለ ውሃ ጭማቂ መውሰድ፣
ሐ) በሦስተኛው ቀን ጭማቂና ቀጠን ያለ የአትክልት ሾርባ መውሰድ፣
መ) በአራተኛው ቀን ማናቸውንም ሾርባ መውሰድ፣
ሠ) ከአምስተኛ ቀን በኋላ ቀስ በቀስ የተለማመድነውን ምግብ መጀመር ይቻላል።

5ኛ. ከሃያ እስከ አርባ ቀናት ለሚጾሙ:-
ሀ) በመጀመሪያው ቀን አንድ ብርጭቆ ጭማቂ ከአንድ ብርጭቆ ውሃ ጋር በቀን አራት ጊዜ መውሰድ፣
ለ) በሁለተኛው ቀን በውሃ ሆኖ ወፈር ያለ ጭማቂ በቀን አራት ጊዜ መውሰድ፣
ሐ) በሦስተኛው ቀን ጭማቂ ብቻውን አራት ጊዜ መውሰድ፣
መ) በአራተኛው ቀን ጭማቂና አትክልት በቀን አራት ጊዜ መመገብ፣
ሠ) በአምስተኛው ቀን ጭማቂ አትክልትና ቀጭን የአትክልት ሾርባ እንደተቻለ ያህል መውሰድ፣
ረ) በስድስተኛው ቀን የአትክልት ሾርባ፣ የተለያዩ አትክልቶችና ጭማቂ መውሰድ፣
ሰ) በሰባተኛው ቀን ቀስ በቀስ ወደ ተለመደው የምግብ ዓይነት መድረስ ይቻላል፣

በተለይ ሦስት ቀንና ከዚያም በላይ የጾም ጊዜ ተወስዶ ቢጨረስ ሻይና ቡና ለተወሰኑ ቀናት አለመውሰድ ጥሩ ነው። ከአሥራ አምስት ቀን በላይ ከሆነ ደግሞ በሁለትና በሦስት ቀናት ያህል ለስላሳ መጠጥ አለመውሰድ ጥሩ ነው። ጾምን ስንጨርስ በጾም ከቆየንባቸው ቀናት ይልቅ የምግብ ፍላጎታችን በጣም ከፍ ስለሚልና ያየነውን ምግብ ሁሉ ለመብላት ስለምንፈተን ከተሰጠው መመሪያ አልፈን እንዳንመገብ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን።

በተጨማሪም ረጅም ጾም ለመውሰድ ስንጀምር ንጽሕናችንን በደንብ መጠበቅ ያስፈልጋል። በመሠረቱ ንጽሕናችንን መጠበቅ ያለብን በጾም ጊዜ ብቻ ሳይሆን እንደ ክርስቲያን ዘወትር መታጠብና ንጹሕ መሆን እንዳለብን የእግዚአብሔር ቃል ያዘናል (ዕብ.10:22)። ይሁን እንጂ በጾም ጊዜ በተለይ አፋችን የተለየ ጠረን ስለሚኖረው ቢቻል የጥርስ ሳሙና በየዕለቱ ደጋግመን መጠቀም አስፈላጊ ሲሆን አለበለዚያም በቀዝቃዛ ውሃ ቶሎ ቶሎ አፋችንን መጉመጥመጥም ይቻላል። ሰውነታችንን ግን በየቀኑ እየታጠብን የምንለብሰውም ልብስ በተቻለ መጠን ንጹህ ሊሆን ይገባዋል።

## ሸ. ለረጅም ቀናት በተደጋጋሚ ጾምን ስንለማመድ የሚሰሙን ነገሮችና ማድረግ ያለብን ጥንቃቄ

ለረጅም ጊዜ ጾምን ደጋግመን ስንወስድ ከወትሮው ይልቅ የተለየ ነገር በሕይወታችን ሊሰማን ይችላል። ለመጀመሪያ ጊዜ ረዘም ላሉ ቀናት የጾም ጊዜ ስንወስድ ረዘም ላለ ጊዜ ተንበርክከን መጸለይና ማንበብ ሊያቅተን ይችላል። ይሁን እንጂ ደጋግመን ረጅም የጾም ጊዜ ስንወስድ ለረጅም ሰዓታት ተንበርክከን መጸለይና ማንበብን ማቋረጥ ባንፃሩ ያቅተናል። ያለ ምንም ማጋነን የእግዚአብሔር እሳት ሲዳስሰን ይታወቀናል።

ጥላቻ፣ ቸኩልነት፣ ትዕግስት ማጣት፣ ስስት፣ ፍርሃት፣ ግብዝነትና ትእቢት እሳት እንዳገኘው ገለባ ይሆናሉ። ሰዎች ቢያከብሩን ራስን ከፍ ማድረግ አይሰማንም፤ ቢያዋርዱን ደግሞ ጥላቻ ውስጣችንን አይሞላም። የገንዘብ ብዛት፣ የትምህርት ደረጃ፣ በስልጣን መመካት የመሳሰሉት ነገሮች በሕይወታችን ሥፍራ አይኖራቸውም። ውስጣችን በሰማያዊ ብርሃን ሲሞላ ይሰማናል፤ የእግዚአብሔርን ቃል ስናነብና ስንሰማ እንዲሁም መዝሙር ሲዘመር ውስጣችን ይቀጣጠላል። ለጸሎት ስንንበረከክ ከእግዚአብሔር ኃይል ጋር እንያያዛለን፤ ስለዚህ ጸሎትን በአጭሩ ማቆም አንችልም። እንደ ተራራ የማይገፉ መስሎ የሚታየን ችግር እንደ ትቢያ አንሶ እናየዋለን።

ቀልዶችና ጨዋታዎች አይጥሙንም፤ ልዩ ሰማያዊ ጸጥታ በውስጣችን ስለሚሰፍን ከሰዎች ተለይተን በጸሎት መቆየትን እንመርጣለን። በዚህ ጊዜ ሰዎች በሕይወታችን በሚያዩት ለውጥ ሊረዱ ሰለማይችሉ ሊተቹን ይጀምሩ ይሆናል። እኛም ከመሰሎቻችን ጋር መሆን ወይንም በዝምታ መቀመጥ ስለምንመርጥ ሳናውቀው ከሌሎች ጋር ያለን ግንኙነት ይቋረጣል። እንደ ድሮው ልንሆንላቸው ያቅተንና ቀስ በቀስ ራስን ማግለል

ሊከሰት ይችላል። ቢሆንም እነዚህ እርምጃዎች እንደ እግዚአብሔር ቃል አለመሆናቸውን አውቀን ቶሎ ማረም ይኖርብናል።

ይህንን የመጀመሪያ ደረጃ ሳንሰናከል ካለፍን የሚቀጥለው ደረጃ ፍጹም ከዚህ የተለየ ይሆናል። እርሱም የጌታን ልብ የምናገኝበት የሕይወት ደረጃ ነው (1ቆሮ.2:16)። እዚህ ደረጃ ላይ ስንደርስ ከመጋጋል አልፈን ሕይወታችን የሰከነ ሆኖ ኃጢአተኞችን የምንሸከምበት ልብ ይኖረናል። ለሰው ሁሉ ፍቅርና ርህራሄ ይሞላናል፤ አመንዝሮች፣ ወሮበሎች እንኳን ያራሩናል፣ እነርሱን ማቅረብ መርከስ መስሎ አይታየንም፣ ሰውን የመጸየፍ ነገር አይኖረንም፣ ሕይወታችን በየዋህነት ይሞላል፣ ሰዎች እንደ መሰላል ቢወጣጡብንም አይከብዱንም፣ እያወቅን ለሌሎች መጎዳት እንጀምራለን፣ ከራሳችን ይልቅ ሌሎችን ደስ ማሰኘት እንመርጣለን (ሮሜ.15:2-3)። የጎዱንን በመበቀል ፈንታ ማዳን እንፈልጋለን በሌሎች ላይ ክፉ ማሰብም ሆነ ሰዎችም ክፉ ይሰሩብናል ብሎ መስጋት ይቀራል፤ እግዚአብሔርንም ደስ ማሰኘት ዘወትር ምርጫችን ይሆናል። በሩቅ የሚያዩን ቢሸሹንም የሚቀርቡን አይለዩንም፤ ንግግራችን ቀርቶ ዝምታችን ይባርካቸዋል። ቃላችን የማይሰለች ስለሚሆን ሁል ጊዜ ከእኛ ጋር መሆን ይመርጣሉ።

በእነዚህ ጊዜያት መገለጥና ራዕይ ስለሚበዛልን በጥንቃቄና በጥበብ በእግዚአብሔር ቃል እየፈተንን ልንይዛቸው ይገባናል። ለማነጽ የሚሆኑትን የሰዎች አእምሮ ወደ እኛ በማይስብበት ሁኔታ ማካፈል ይኖርብናል፣ የበረከት ሕይወት ሲበዛልን ሰዎች ሳንልክባቸው ይሰበሰባሉ። ከእግዚአብሔር የሚፈስልን በረከት ስለማያቋርጥ ሁል ጊዜ አዳዲስ ነገሮች ከውስጣችን ስለሚፈልቁ ደጋግመው ቢሰሙን አንሰለችም፣ ውስጣችን የጋለ እሳት ስለሚሆን የቀዘቀዙ ሰዎች በእኛ ዘንድ አይገኙም።

ወደዚህ ሕይወት ደረጃ ለመድረስ ብዙ መታገስን ይጠይቃል፤ ምክንያቱም ልዩ ልዩ መሰናክሎች አሉበትና፤ ሆኖም ማንም ሰው ጸንቶ ከቆመና ከተጋ ሊደርስበት ይችላል።

## V. በክርስትና ሕይወት ለማደግ አስፈላጊ ነገሮች

1. መንፈሳዊ ሕይወታቸው ሳያድግ አገልግሎታቸውን ብቻ ለማሳደግ የሚሮጡ አገልጋዮች ጠንካራ ተቃውሞ ሲገጥማቸው የሚወስዱት እርምጃ ምንድን ነው?
2. መንፈሳዊ ሕይወቱን የማይመግብ ክርስቲያን አዝማሚያው ምን ሊሆን ይችላል?
3. ጠንካራ እምነት እንዲኖረን የእግዚአብሔር ቃል ያለው አስተዋጽዖ ምንድን ነው?
4. ጨለማ በዋጠው ዓለም ውስጥ ስንኖር የእግዚአብሔር ቃል እንደ ብርሃን ሆኖ የሚያገለግለን በምን መልኩ ነው?
5. የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሰይፍ ሆኖ የሚያገለግለን በምን ሁኔታ ነው?
6. የእግዚአብሔር ቃል እንደ እሳት ሆኖ በሕይወታችን የሚሠራው ምን በማድረግ ነው?
7. ጸሎትን መማር የምንችለው እንዴት ነው?
8. ጥሩ ሰባኪ ለመሆን በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፤ መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥስ ለመግባት መደረግ ያለበት ምንድን ነው?
9. የክርስቶስ አካልና የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የምትሆነውን ቤተ ክርስቲያን ለማነጽ ምን ዓይነት ሰው ያስፈልጋል?
10. በስብከት ዘዴ በተካኑ ሰባኪዎችና በጸሎት በሚተጉ ሰባኪዎች መካከል ያለው የአገልግሎት ውጤት ምን ሊመስል ይችላል? ተወያይበት።
11. ለጸሎት ሰው ከጸሎት ጊዜው የበለጠ የተወደደ ጊዜ የለውም የተባለበት ምክንያቱ ምንድን ነው?
12. በዘመናችን ለጸሎት ጊዜ ማጣት ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል? ተወያይበት።
13. ጾምን አዘውትረን የምንለማመድበት 13 ምክንያቶች ተጠቅሰዋል፤ ከእነዚህ ውስጥ እጅግ አስፈላጊ መስለው የሚታዩት የትኞቹ ናቸው?
14. አንተ በምታገለግልበት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሲሾሙ በጾምና በጸሎት ቆይታ በማድረግ ነውን? ካልሆነ ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል? ተወያይበት።
15. ጾም ለጌታ ያለን የናፍቆት መግለጫ ሊሆን የሚችልበትን ምክንያት ግለጽ።
16. ጾምን የማይለማመዱ ክርስቲያኖች ምክንያታቸው ምን ሊሆን ይችላል?
17. ሐዋርያው ጳውሎስ "ሥጋዬን እየጎሸምኩ እገዛለሁ" ሲል በምን መልኩ ሊሆን ይችላል? ተወያይበት።
18. ጾምን በሦስት ደረጃ ከፍለህ አስረዳ።
19. ጾም የጸጋ ስጦታ ነው ብለህ ታስባለህን? ተወያይበት።
20. በጾም ይተጉ የነበሩ ጥቂት ክርስቲያኖች በትምህርት መሳታቸው ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል?
21. ጾምና ጸሎት የሚደጋገፉ ቢሆኑም የግድ የተያያዙ ሊሆኑ አይችሉም የተባለበት ምክንያት ምንድን ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተደግፈህ አስረዳ።
22. ጾማችን በእግዚአብሔር ፊት እንዲታይ አስቀድመን ልናስተካክላቸው የሚገቡ ነገሮች ምንድን ናቸው?

## VI. በክርስትና ሕይወት ለማደግ እንቅፋት የሚሆኑብን ነገሮች

በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ የሚረዱን ነገሮች እንዳሉ ሁሉ በአንፃሩ ደግሞ እንዳናድግ መሰናክል የሚሆኑብን የተለያዩ ሁኔታዎች አሉ። ይሁን እንጂ ጎልተው የሚታዩ ኃጢአቶች ላይሆኑ ይችላሉ። ክርስቲያን የተገለጠ ኃጢአትን የሚለማመድ ከሆነ በዕድገት መንገድ ላይ ሳይሆን በውድቀት መንገድ ላይ ነው ማለት ይቻላል፤ ውድቀትና ዕድገት ደግሞ የተለያዩ አቅጣጫዎች ናቸው። ለውድቀት የሚዳርጉ ኃጢአቶች ምን እንደሆኑ ማንም ክርስቲያን ያውቃል። ስለዚህም በመሸነፍ ካልሆነ በስተቀር በስህተት፣ በመታለል ወይም ባለማወቅ የጎላ ኃጢአትን የሚፈጽም የለም። ስለሆነም ክርስቲያን ሁሉ ጎልቶ ከሚታይ ኃጢአት ራሱን ጠብቆ ለመኖር ጥረት ያደርጋል።

ነገር ግን በመንፈሳዊ ሕይወታቸውና በአገልግሎታቸው ማደግ እየናፈቁ ያገዳቸው ምን እንደሆነ ለማወቅ ሲጥሩ፣ ምስጢር ሆኖባቸው የሚቸገሩ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ። ስለዚህ በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች እንዳሉ እንመለከታለን።

### 1. <u>የግብዝነት ሕይወት</u>

ግብዝነት ምንድነው? ግብዝነት ሁለት ዓይነት ሰው መሆን ነው፤ አንደኛው እውነተኛ እራሱን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሌላውን መስሎ መታየት ነው። ግብዝነት በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ሲኖር አይታወቅም፤ ስለዚህ ይብዛም ይነስም በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ በተለያየ ደረጃ መኖሩ አይቀርም።

ግብዝነት በራስ ባለመተማመን የሚፈጠር ባሕርይ ነው። ይሉኝታ መለስተኛ ግብዝነት መሆኑን ብዙ ሰዎች አያውቁም። ይሉኝታ በአጭር አነጋገር "ሰው ምን ይለኛል" ማለት ነው። <u>ይሉኝታ ማጣት</u> ከግዴለሽነትና ከራስ ወዳድነት ጋር አንድ መስሎ ሊታይ ይችላል። ግዴለሽነት ደንታ ቢስነት ሲሆን ራስ ወዳድነት ደግሞ ለሌላው አለማሰብና እኔ ብቻ ልጠቀም ባይነት ነው። ይሉኝታ ግን ከላይ እንደተጠቀሰው 'ሰው ምን ይለኛል' በሚል ሳቢያ የሚፈጸም ድርጊት ነው። ስለዚህ <u>ይሉኝታ ማጣት</u> ከግዴለሽነትና ከራስ ወዳድነት ጋር አንድ መስሎን ይሉኝታን ጨርሶ ባንጥለውም ሁል ጊዜ ልናስተናግደው አይገባም። ስለዚህ ሰው ምን ይለኛል ብሎ ያልሆኑትን መሆን ደግሞ ግብዝነት ነው።

ይሉኝታ በባህላችን የተለመደና የሚደገፍ ስለሆነ በመንፈሳዊ አሠራር ውስጥም በቀላሉ መግባት ችሏል። ይሉኝታ በባህል የተፈቀደ ሊሆን ይችል ይሆናል፥ ነገር ግን መንፈሳዊውን ሕይወት በይሉኝታ መለማመድ ከመንፈሳዊ ዕድገት ያግዳል።

አንዳንድ ክርስቲያኖች በይሉኝታ መንፈሳዊውን ነገር ለመለማመድ ይሞክራሉ። ስለሆነም በመንፈስ የተባረከውን ሲያዩ በራሳቸው መባረክ ይጀምራሉ፣ እውነተኛ ፍቅር ሳይኖራቸው ፍቅር እንዳለው ሰው ዓይነት ይሆናሉ፣ በጸጋ የተቀባውን ሲያዩ ያልተሰጣቸውን ጸጋ ለብሰው "መገለጽ" ይሞክራሉ። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔርን በማወቅ ሊያሳድጋቸው፣ በእግዚአብሔር ፍቅር ሊሞላቸው፣ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች ሊያለብሳቸው ሲመጣ እራሳቸው እንዳላቸው ሆነው ሊታዩ ሲሞክሩ ይተዋቸዋል፤ ስለዚህ እውነተኛውን መንፈሳዊ ዕድገት ሳያዩ እድሜያቸውን በከንቱ ይጨርሳሉ።

ግብዝነት በሰው ሕይወት ውስጥ ሲኖር አይታወቅም፤ ስለዚህ ማንም ሰው እኔ ግብዝ ሆኜ ይሆንን? ብሎ ራሱን መጠየቅ አይችልም። የግብዝነትን ሕይወት በሌላ ሰው ሕይወት ውስጥ ማየት የምንችለውን ያህል በራሳችን ሕይወት ውስጥ መኖሩን ግን እንጠራጠራለን፤ ግብዝነት እንደ ጥላቻና እንደ ቂም አይጎረብጥም፤ በእግዚአብሔር ፊት ግን እጅግ አጸያፊ ነገር ነው።

ስለዚህ ነው ጌታ ስለ ግብዝነት አብዝቶ የተናገረው (ማቴ.23:13-36) ምክንያቱም በሰው ሕይወት ውስጥ ያለውን ነገር በግልጽ ያይ ስለነበረ ነው (ዮሐ.2:25)። ደቀ መዛሙርቱንም ከግብዝነት ሕይወት እራሳቸውን እንዲጠብቁ አስጠነቀቃቸው (ሉቃ.12:1)። ሐዋርያው ጴጥሮስ በአንድ ወቅት ይሉኝታ ይዞት ያልሆነውን ሊሆን ሲሞክር ጳውሎስ አይቶት "ይፈረድበት ዘንድ ይገባ ነበርና" ብሎ በሁሉም ፊት በግልጽ ተቃወመው (ገላ.2:11-14)። ከዚያ በኋላ በግብዝነት ምን ያህል እንደተጎዳ ስላየ ክርስቲያኖች ከግብዝነት ሕይወት መራቅ እንዳለባቸው ጻፈላቸው (1ጴጥ.2:1)።

**ግብዝነትን በአራት ክፍለን ማየት እንችላለን፡-**

*ሀ. **ሃይማኖተኛ መሳይ፡-** ሃይማኖተኛ ነኝ ብሎ የሚመጻደቅ ነገር ግን ስለ ሃይማኖቱ እንኳን የማያውቅ ግብዝ የሆነ ሰው አለ።*

ለ. **በሥራዬ እጸድቃለሁ ብሎ የሚያስብ፡-** ደጋግመን እንዳየነው በሥራዬ እጸድቃለሁ ብሎ ማሰብ በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ግብዝነት ነው፤ በሰዎች ፊት ፃድቃን የሚመስሉ ውስጣዊ ሕይወታቸው ሲታይ ግን ክፋት፣ ቅንዓት፣ ምቀኝነትና፣ ተንኮል የሞላባቸው አሉ፤ እንደነዚህ ያሉትን ሰዎች ጌታ በብርቱ ቃል ደጋግሞ ዘልፏቸዋል (ማቴ.7:5፣ 23:13፣ 23:25፣ 27)።

ሐ. **በወንጌል አምናለሁ የሚል ነገር ግን በቅድስና ስለመኖር የማይናፍቅ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ግብዝ ነው**(1ጢሞ.1:5)።

መ. **የጋለ ስሜት ያለው ጉጉ ክርስቲያን፡-** ስለ ፍቅርና እግዚአብሔርን ለማገልገል አብዝቶ የሚናገር፥ ያየውን ሁሉ መሆን የሚፈልግ ጉጉ የሆነ ክርስቲያን አለ፤ ነገር ግን አኗኗሩ ሌሎችን የሚያሰናክል ዓይነት ነው (ሮሜ.14:15)። ይህም ዓይነት ክርስትና በእግዚአብሔር ፊት ግብዝነት ነው (ማቴ.24:51)። "የትእዛዝ ፍፃሜ ግን ከንጹህ ልብና ከበጎ ሕሊና ግብዝነትም የሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር ነው" ይላል (1ጢሞ.1:5)። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያሳድገን፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዲሞላንና የጸጋ ስጦታዎችን እንዲያጎናጽፈን ከፈለግን እራሳችንን ሆነን ልንቀርብ ይገባናል።

## 2. <u>የልምድ ኃጢአት</u>

የልምድ ኃጢአት የቀድሞ መንፈሳዊ ሕይወት ሲቀንስ የሚጀመር ልምምድ ነው። የልምድ ኃጢአት ጎልቶ የሚታይ ኃጢአት ባለመሆኑ ይህ ነው ብሎ በዝርዝር ማስቀመጥ ያስቸግር ይሆናል። ሆኖም ብዙ ክርስቲያኖች የራሳቸው የሆነ የተለያየ የልምድ ኃጢአት ይኖራቸዋል። የልምድ ኃጢአት የሚጀምረው ቀስ በቀስ ነው፤ ኋላ ግን የተለመደ ሆኖ ይቀራል።

ሲጋራ ሲጀምሩት ያስላል እንግዳ ነገር ስለሆነ ሳንባችን አይቀበለውም፣ ኋላ ግን ሱስ ይሆንና ለመተው ቢፈለግም ያስቸግራል። ያለው አማራጭ ተገዢ ሆኖ መኖር ነው፤ ቶሎ ጉዳት ላይ አይጥል ይሆናል እንጂ ቀስ በቀስ በጤንነት ላይ ከፍተኛ ተጽደኖ እንደሚያመጣ የሕክምና ባለሙያዎች ያረጋገጡት ነው። እንዲሁም የልምድ ኃጢአትም ሲጀመር መንፈስ ቅዱስ ይወቅሳል፤ ኋላ ግን ምንም አይደለም በሚል ምክንያት ወይም ሌላ ጊዜ አልደግመውም በሚል ሰበብ ይፈጸማል፤ ከዚያም በመሸነፉ ይቀጥልና ልምድ ሆኖ ይቀራል። መንፈስ ቅዱስም መውቀስን ያቆማል፤

እየቆየ ሲሄድ መንፈሳዊ ዕድገትን ማገድ ይደርሳል።

የልምድ ኃጢአትን በብዙ ነገሮች ልንመስለው እንችላለን። ይኸውም:-

ሀ. **በጥንጣን ይመሰላል** :- ጥንጣን ጥቃቅን ፍጥረታት ሆነው ከብዛታቸው የተነሳ ትልቁን ግንድ ቦርቡረው ባዶ ያደርጉታል፤ የልምድ ኃጢአትም ሲበዛና ሲደጋገም መንፈሳዊ ሕይወትን ቦርቡሮ ባዶ ያስቀራል። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ "የሚቆም የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ" ያለው።

ለ. **በምስጥ ይመሰላል** :- ምስጦች ጥቃቅን ፍጥረታት ሆነው ከመብዛታቸው የተነሳ አንድን ተክል ሥሩን ይቆርጡና በቁሙ ያደርቁታል፤ የልምድ ኃጢአትም በተመሳሳይ መንገድ ቀስ በቀስ መንፈሳዊ በረከትን በማሳጣት ከጊዜ በኋላ ማድረቁ አይቀርም።

ሐ. **በነቀዝ ይመሰላል** :-ነቀዞች ጥቃቅን ፍጥረታት ናቸው፤ ነገር ግን ሙሉ የጎተራ ውስጥ ሰብል በልተው ባዶውን ያስቀሩታል፤ ነቀዝ ያገኘው እህል ቢዘሩት አይበቅልም ገለባ ብቻ ነው የሚቀረው። የልምድ ኃጢአት ሲበዛ እንዲሁ ፍሬ የሌለው ገለባ ብቻ ያደርጋል። በጊዜው ያልተነቀለ አረም ሥሩን ከሰደደ በኋላ ለመንቀል ያስቸግራል፥ ላዩን ተቆርጦ ቢተውት ተመልሶ ማቆጥቆጡ አይቀርም። ከጅምሩ ያልተገታን ልምድ በቀላሉ ለማቆም ያስቸግራል። "ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው ለነገር ሁሉ ይጠቅማል" (1ጢሞ.4:8)።

3. <u>**በደልን መቁጠር**</u>

መንፈሳዊ ሕይወትን ከማደግ ከሚያግደው ዋና ነገር ውስጥ አንዱ በደልን መቁጠር ነው። ብዙ ክርስቲያኖች ሌሎችን ላለመበደል ይጠነቀቃሉ፤ ነገር ግን በሰዎች እንዳይጎዱ ራሳቸውን አይጠብቁም። ይህም በደልን መቁጠር እንዴት እንደሚፈጠር አለማወቅ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ሲልካቸው "እንደ እባብ ልባሞች እንደ እርግብ የዋሆች ሁኑ" አለ (ማቴ.10:16)። እባብ ብልህ የተባለበት ምክንያት ራሱ እንዳይመታ ስለሚጠነቀቅ ነው። ቀጥሎ "ከሰዎች ተጠበቁ" አለ (ማቴ.10:18)። የራስን መንፈሳዊ ሕይወት ለመጠበቅ

በሰዎች ላይ ክፉ አለማሰብና ክፉ አለማድረግ ብቻ በቂ አይደለም፥ እራስንም ከሰዎች መጠበቅ ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም ቂምን የምናተርፈው ሰዎች በሚያደርሱብን ጉዳት ነው።

ከሰዎች ጋር ያለን ሁኔታ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ይነካል። ሰውነታችንን ከሚያቆስል ነገር ራሳችንን መጠበቅ እንዳለብን ሁሉ እንዲሁ ደግሞ ህሊናችንን ከሚያቆስል ነገር ራሳችንን መጠበቅ አለብን። ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች "ከውሾች ተጠበቁ ከክፉዎች ሠራተኞች ተጠበቁ" አላቸው (ፊልጵ.3:2)። ከሚናከሱ ውሾች ካልተጠነቀቅን ተነክሰን እንደማለን፤ እንዲሁ ከክፉ ሰዎች ካልተጠነቀቅን ሕሊናችንን ቆስለን እንደማለን። <u>የህሊና ቁስል የሚያተርፈው ጠባሳ ቂመኝነትን ነው</u>። በህሊና ቆስሎ በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ እጅግ አዳጋች ነው። "ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ" የሚባለውንም የአባቶች ምክር ብንጠቀምበት በዚህ ረገድ ይረዳናል።

4. **<u>መንፈስ ቅዱስን አለመታዘዝ</u>**

ብዙ ጊዜ በተቻለ መጠን የእግዚአብሔርን ቃል ለመጠበቅ ጥረት እናደርጋለን፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን በሕይወታችን መታዘዝ አንለማመድ ይሆናል። መንፈስ ቅዱስ በእኛ የሚኖረው ሊያስተምረን፣ ሊመክረን፣ ሊመራን ጭምር ነው (ዮሐ.16:12-15)።

ስለዚህም በውስጣችን ሲናገረን ምላሽ መስጠት አለብን፤ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ሊጠቀምብን የሚችለው በውስጣችን ድምጹን ሰምተን ለመታዘዝ ስንችል ነው። ለመንፈስ ቅዱስ ምላሽ አለመስጠትና አለመታዘዝ እርሱን ማሳዘንና ማስመረር ይሆናል (ዕብ.3:7፣ ኤፌ.4:30)

መንፈስ ቅዱስን ላለመታዘዝ የሚያደርሰን አንዱ ምክንያት ድምፁን አለመለየት ሊሆን ይችላል። የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ መለየት ከመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት ጋር አብሮ የሚመጣ መሆኑን ቀደም ሲል አይተናል። ለመንፈስ ቅዱስ ድምፅ ባዕድ ሆኖ መቀመጥ ደግሞ መንፈሳዊ ሕይወትን ከማደግ ያግዳል። መንፈስ ቅዱስ ሁል ጊዜ ካለንበት ሥፍራ ወደሚቀጥለው ደረጃ ሊያሳድገን ይፈልጋል፤ ድምፁን አለመስማትና አለመታዘዝ በመንፈሳዊ ሕይወትና በአገልግሎት ከማደግ እንደሚከለክለን አውቀን የመንፈስ ቅዱስን ምሪት መለማመድ ይኖርብናል (ሮሚ.8:14)።

## 5. የእግዚአብሔርን ክብር መጋራት

የእግዚአብሔርን ክብር ለመጋራት የሚፈተኑ ከምዕመናን ይልቅ በመድረክ ላይ የሚታዩ አገልጋዮች ሊሆኑ ይችላሉ። እግዚአብሔር ክብሩን ለመግለጽና ቤተ ክርስቲያን እንድትታነጽ ድንቅና ታምራትን ያደርጋል፤ ጉባኤን ይባርካል። በዚህን ጊዜ የመድረክ አገልጋይ የሆነው ክርስቲያን የተገለጸውን የእግዚአብሔርን ክብር ከራሱ ጋር በማያያዝ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ዋና ርዕስ ሆኖ እንዲቀርብ ይፈልጋል።

እግዚአብሔር ያደረገውን ነገር ሁሉ መግለጽ ተገቢ ቢሆንም ማስታወቂያ ሆኖ እንዳይቀርብ መጠንቀቁ እጅግ አስፈላጊ ነው። ዝና እንዲኖረን ፤ታዋቂዎች እንድንሆን፤ በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት እንድናገኝ ብሎ እግዚአብሔር የሚያደርገው ነገር የለም። ስለ ስሙ መዋረድንና መከራን ለመቀበል ፈቃደኞች ከሆንን ዝናም፤ ክብርም እላይ ይጠብቀናል። "አብረንም ደግሞ እንድንከብር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን" ይላል (ሮሜ.8:17)። በተጨማሪም በራዕይ 3:5 "ድል የነሳው . . . በአባቴና በመላእክቱም ፊት ለስሙ እመሰክርለታለሁ" ይላል።

በእግዚአብሔር በማመካኘት ዝናንና ክብርን ፍለጋ የሚደረግ ነገር ሁሉ ሌብነት ነው። ስለሆነም እግዚአብሔር ክብሩ እንዲገለጽ የሰጠውን መቅረዝ ከሥፍራው መውሰድ ይችላል። ለእግዚአብሔር የሚገባውን ለራስ ጥቅም ማዋል ሌብነት አይደለም ብሎ የሚከራከር አገልጋይ አይኖርም። ነገር ግን "ለእግዚአብሔር ክብር እንዲሆን ነው" እየተባለ ለእግዚአብሔር መዋል የሚገባውን ክብር መጋራት በብዙዎች ዘንድ የተለመደ ሆኗል። በሐዋርያትም ዘመን እንደዚህ ዓይነት አገልጋዮች መኖራቸውን ሐዋርያው ጳውሎስ አልሸሸገም (2ቆሮ.10:12)። በዚህ የሚፈተን አገልጋይ ንቅቶ ንስሐ በመግባት ራሱን ካላስተካከለ መንፈሳዊ ዕድገቱን ማቆሙ አይቀርም።

## 6. የዚህ ዓለም የባለ ጠግነት አሳብ

"በእሾህ መካከል የተዘራው ይህ ቃሉን የሚሰማ ነው የዚህ ዓለም አሳብና የባለጠግነት መታለል ቃሉን ያንቃል የማያፈራም ይሆናል" (ማቴ.13:22)። ጌታ የዘሪውን ምሳሌ የተናገረው ምን ሊያስተምር እንደሆነ ለማንም ክርስቲያን ግልጽ ነው። ይህ ምሳሌ ቃሉን ሰምተው የተቀበሉትን ክርስቲያኖች የሚመለከት ነው። በተለይ በእሾህ መካከል የወደቀውን ዘር ምሳሌ ልብ ብለን ብናይ የተዘራው ዘር ፍሬ እንዳያፈራ እሾህ አንቆት

እንዳስቀረው ሁሉ በዚህ ዓለም የባለጠግነት አሳብ የሚያዙ ክርስቲያኖች ሕይወታቸው ማደግና ማፍራት እንደማይችል ያሳያል። በባለጠግነት ምኞት የተያዘ ሰው ሸክሙ የከበደ መንገዱም የማይደረስበት እሩቅ አገር የሚሄድን ሰው ይመስላል። ንጉሡ ሰሎሞን በመክብብ 2:26 ላይ ሰውን ደስ የሚያሰኝና እርካታ የሚሰጥ ነገር ካለ መርምሮ ለማግኘት ብዙ እንደጣረ ይናገራል።

የተለያዩ ውብ የሆኑ መኖሪያ ቤቶችን ሠራ፣ ዛፎችንና የተለያዩ ፍሬ የሚሰጡትን አትክልቶች በማስተከል አካባቢው ገነት እስኪመስል ድረስ አደረገ፣ ዛፎችን ለማጠጣት መስኖዎችንና ግድቦችን አሠራ፣ ወንዶችንና ሴቶች ሠራተኞችን በብዛት ቀጠረ፣ የፍየል የበግና የከብት መንጋን አረባ፣ ይህ ሁሉ እርካታ የሚሰጥ ሆኖ አላገኘውም፤ ቀጥሎም ብዙ ወርቅና ብርን አከማቸ፣ በአገር ውስጥ አሉ የተባሉትን ድምጻውያን ዘፋኞችን አዘጋጀ፣ ብዙ ሴቶችንም አገባ፣ ዓይኑ ያየውን ነገር ሁሉ ሰበሰበ ነገር ግን ዘላቂ ሰላምና ደስታን ሊሰጡት አልቻሉም፤ ይህን ካደረገ በኋላ ሁሉም ዋጋ ቢስና ነፋስን እንደመከተል ነው ብሎ ደመደመ (መክ.2:1-11)። ይህንን ክፍል ያላነበበ ክርስቲያን የለም፤ ነገር ግን ይህንኑ መልሶ ማድረግ ነፋስን ለመጨበጥ የሚሮጥን ሰው መምሰል ነው፤ ይህ ደግሞ እጅግ ሞኝነት ነው፤ ለዚህም ነው ጌታ የባለጠግነት መታለል ያለው (ማቴ.13:22)።

ሰው በማግኘት ለምን አይረካም? ምክንያቱም ሰው ሕይወቱ እንደ እንስሳ በምድር ተወስኖ የሚቀር አይደለም፤ ሰማያዊ ወይም መንፈሳዊ ክፍል አለው፤ ያ መንፈሳዊ ክፍል በዚህ ምድራዊ ነገር ሊሞላና ሊረካ አይችልም፤ ፍጹም የሆነውን ይፈልጋል። ያ ፍጹም የሆነው ደግሞ ሰማያዊ ነው። ስለዚህ ሰው ሰማያዊውን በረከት በሙላት ሲያገኝ ሕይወቱ ያርፋል፤ አለበለዚያ ዕድሜ ልኩን እየተታለለ ይኖራል።

እግዚአብሔር የሰው ምድራዊ ምኞት በምድራዊ ነገር እንደማይሞላ ስላወቀ ሰማያዊውን በረከት አዘጋጀለት "በክርስቶስ በሰማያዊ ሥፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ"(ኤፌ.1:3)። የሰው ሁሉ ችግር ማጣት ሳይሆን ችግሩ ምኞቱ ነው፤ ምኞቱ የሞተለት የችግረኝነት ስሜት አይሰማውም፤ ሰው ግን በምኞቱ ሲሞላ "ማጣት" ይሰማዋል፤ የተመኘውን ሲያገኝ ሌላ ምኞት ይቀጥላል፤ አንድ ከተማ ለአንድ ሰው ቢሰጠውም ምኞቱ አይቆምም። ስለዚህ ከችግረኝነት ለመላቀቅ የሚያስፈልገው ማግኘት ሳይሆን ከምኞት

መላቀቅ ነው።

ከዚህ የሚያሳርፈን ምን እንደሆነ ጌታ ስላወቀ "ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ" ብሎ ይጋብዛል (ዮሐ.7:37)። ደግሞም "መንፈሱና ሙሽራይቱም፡- ና ይላሉ። የሚሰማም፡- ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፥ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ" (ራዕ.22:17)።

ሰው ግን ይህንን ስላልተገነዘበ በውስጡ ያለውን ምኞት በዚህ ዓለም ባለጠግነት ሊሞላ ሲጥር አልሞላ እያለው እየባዘነ ይኖራል (ኤር.2:13)። መንፈሳዊን በረከት አብዝተው መፈለግ ትተው ምኞታቸውን በዚህ ዓለም ባለጠግነት ሊሞሉ ሲጥሩ ባዶነት ይሰማቸውና በሰይጣን ወጥመድ ሊያዙ ይችላሉ (1ጢሞ.6:9)።

እውነተኛ ሰላምና እርካታ በምድራዊ ነገር የሚገኝስ ቢሆን ኖሮ የአሁኑ ዘመን ሰዎች በደረሱበትና በነገሩን ነበር። የዚህ ዓለም ተመራማሪዎች ለዚህ ዓለም ያበረከቷቸው ብዙ ጠቃሚ ነገሮች ቢኖሩም፤ ለአንድ ሰው እንኳን የሚሆን ሰላምና እርካታ የሚሰጥን የሕይወትን ውኃ ሊያገኙ አልቻሉም። ምክንያቱም የሕይወት ውኃ ምንጭ የሚገኘው አንድ ቦታ ብቻ ስለሆነ ነው (ዮሐ.7:37)።

ክርስቲያን በመታለል ከእግዚብሔር ጋር የሚጣላበት መንገድ በዚህ ዓለም ምኞት በመያዝ ነው (ሮሜ.8:7፤ 1ዮሐ.2:15-16)። ብዙ ክርስቲያኖች የሚታለሉትም ደግሞ ለእግዚአብሔር ባለጠጋዎች ሊሆኑ ስለሚፈልጉ ነው። ነገር ግን ማንም ሰው በባለጠግነቱ የእግዚአብሔርን ጉድለት አይሞላም፤ ድሃም በመሆን ከለጋስነት አያስቀርም።

የመቄዶንያ ክርስቲያኖች እጅግ ድሆች እንደነበሩ ሐዋርያው ጳውሎስ ይመሰክራል። ነገር ግን ሌሎች ወገኖቻቸውን ለመርዳት እርሱን አጥብቀው ይለምኑት ስለነበር አስደንቆታል። ምንም እንኳን እጅግ ድሆች ቢሆኑም ለወገኖቻቸው ያደረጉት ልግስና እጅግ የበዛ ነበር (2ቆሮ.8:1-4)።
በዚህ ዓለም ባለጠጋ ለመሆን የሚመኙ የሚያዙበት ወጥመድ እንደሚበዛ ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት እንዲህ አለ "ዳሩ ግን ባለጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በፈተናና በመፍረስ ሰዎችን በሚያስምጥና በሚያሸንፍ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመዱም ይወድቃሉ" (1ጢሞ.6:9)። ይቀጥልና "አንተ ግን የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከዚህ

ሽሽ፤ ጽድቅና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም፥ ፍቅርንም፥ መጽናትንም፤ የዋህነትንም ተከተል" ይላል (1ጢሞ.6:11)።

ዲያብሎስ የዚህ ዓለም አምላክና ገዢ እንደሆነ ተጽፏል (ዮሐ.21:31፤ 16:11፤ 1ቆሮ.4:4)። ይህ ማለት ዲያብሎስ ይህንን ዓለም እንዲያስተዳድር ተሰጥቶታል ማለት አይደለም። ነገር ግን የዚህን ዓለም ሰዎች በምድራዊ ነገር አእምሮዋቸውን እንደሚገዛ ለመግለጽ ነው (ራዕ.12:9)። ስለዚህ በዚህ ዓለም አሳብና የባለጠግነት መታለል የሚነዳ ክርስቲያን በሰይጣን ወጥመድ ፈጥኖ መያዙ አይቀርም። በዚህ መንገድ ጌታንም ሊሸነግል ቃጥቶት ነበር (ማቴ.4:4)።

ሰይጣን የእግዚአብሔርን ልጆች ኃይሉን ተጠቅሞ ሊይዛቸው አይችልም። ነገር ግን የዚህን ዓለም ክብርና ባለጠግነት በማሳየት ዝንጉ የሆኑትን በወጥመድ እንዲገቡ መሸንገልና ማታለል ይችላል። ለዚህም ነው "የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ" ተብሎ የተፃፈልን (ኤፌ. 2:11)። በሌላም ሥፍራ "በመጠን ኑሩ ንቁም ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና" ይላል (1ጴጥ. 5:8)። ስለዚህ በመጠን መኖርን የማይፈቅዱትን ክርስቲያኖች ዲያብሎስ የዚህን ዓለም ክብርና ባለጠግነት እያሳየ እንዲባዝኑ በማድረግ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲዳከሙ ያደርጋቸዋል።አንተ ግን የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከዚህ ሽሽ!

## 7. <u>በእግዚአብሔር ላይ ማጉረምረም</u>

"ከእነርሱ አንዳንዶቹ እንዳንጎራጎሩ በሚያጠፋውም እንደጠፉ አታንጎራጉሩ" (1ቆሮ.10:10)።
"የጎመጁ ሕዝብ በዚያ ተቀብረዋልና፤ የዚያ ሥፍራ ስም የምኞት መቃብር ተብሎ ተጠራ" (ዘኍ.11:34)።

ሰው በእግዚአብሔር ላይ ለምን ያጉረመርማል? በእግዚአብሔር ላይስ የሚያጉረመርም እንዴት ዓይነት ሕዝብ ነው? ብንል በእግዚአብሔር ላይ የሚያጉረመርም እግዚአብሔርን የሚያውቅ ሕዝብ ሆኖ እናገኘዋለን። እግዚአብሔርን የማያውቅ ሕዝብ እግዚአብሔር ለእርሱ ምኑም እንዳይደለ ያስባልና በእግዚአብሔር ላይ ሊያጉረመርም አይችልም። እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ላይ ሊያጉረመርሙ የቻሉት ስላወቁት ነው። ከባርነትና ከታላቅ መከራ ሲያድናቸው አይተውታል። ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር

ላይ ማጉረምረም የሚያስችላቸው መብት አልነበራቸውም፤ እርሱም ያዳናቸው ከታላቅ ምህረቱና ከቸርነቱ የተነሳ እንጂ ማድረግ የሚገባቸውን ነገር አድርገው አይደለም። በተመሳሳይ መልኩ በአሁኑም ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ የሚያጉረመርሙ የእርሱን ምህረትና ማዳን ያዩና የተለማመዱ ሰዎች ብቻ ናቸው። ሆኖም እግዚአብሔርን የሚያውቁ ሰዎች ለምን በእግዚአብሔር ላይ ያጉረመርማሉ? ብለን ብንጠይቅ ሦስት የተለያዩ ሁኔታዎች መኖራቸውን እንደርስበታለን።

ሀ. ጸጸት ነው:-

ለጸጸት ምክንያት የሚሆኑን ብዙ የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ምናልባት ስለ ጌታ ብለን ጊዜያዊና ምድራዊ የሆኑ ለሥጋ የሚጠቅሙንን ነገሮች ትተን ሊሆን ይችላል (ማር.10:29-30)። እነዚህን ነገሮች ሰይጣን ወደ አእምሯችን እያመጣ ሊፈትነን ይሻል፤ "ውሻ ወደ ትፋቱ ይመለሳል፤ ደግሞ የታጠበች እርያ በጭቃ ለመንከባለል ትመለሳለች" የሚለውን ቃል ረስተን እንጸጸት ይሆናል (2ቆሮ. 2:22)። በዚህን ጊዜ ከዕድገታችን አንድ እርምጃ ወደ ኋላ መራመድ ጀመርን ማለት ነው።

ለ. እግዚአብሔር የሰጠን ተስፋ ሲዘገይብን:-

"የምትዘገይ ተስፋ ልብን ታሳዝናለች" (ምሳ.13:12)። እግዚአብሔር የሰጠን ተስፋ የሚዘገይበት ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም እግዚአብሔርም እምነታችንን ለማሳደግ አንዳንዴ ያዘገይብናል።

በእኛ ግምት እግዚአብሔር የሰጠን ተስፋ ቶሎ ሲፈጸም እምነታችን የሚጨመርና የሚያድግ ይመስለናል። እግዚአብሔር የተናገረንን ወዲያው ሲፈጽመው ማየት ጊዜያዊ አድናቆት ይሰጠን ይሆናል እንጂ እምነትን አይጨምርልንም። እግዚአብሔር አብርሃምን እንዴት በእምነት እንዳሳደገው ብናይ ትልቅ ትምህርት እናገኛለን።

እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጅ እንደሚሰጠውና በልጁም አማካይነት ዘሩን እንደሚያበዛ ተናግሮት ነበር (ዘፍ.12:12፤ 15:1-7)። እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ከሃያ አምስት ዓመት በላይ ዘገየበት፤ በዚህም ምክንያት አብርሃም በሚስቱ ምክር የራሱን የሥጋ እርምጃ ወሰደና እስማኤል ተወለደ (ዘፍ.16:1-3፤ 4:28-29)። ነገር ግን ሳራ መውለድ በማትችልበት ዕድሜ እግዚአብሔር እንደሰጠው የተስፋ ቃል ሳራ ይስሃቅን ወለደች፤ ይስሃቅ ካደገ በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን "ልጅህን ሰዋልኝ" ብሎ

ፈተነው (ዘፍ.22:1-22) አብርሃም ሳይጠራጠርና ሳያጉረመርም ይስሃቅን ለመሰዋት አቀረበ፤ እዚህ ጋ ልብ ብለን እንድናስበው የምፈልገው ነገር አለ፡- አብርሃም ይህንን እርምጃ ለመውሰድ የቻለው ምን አስቦ ነው? ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው አብርሃም ይህንን እርምጃ ለመውሰድ የቻለው እግዚአብሔር ይስሃቅን ከሙታን እንኳን አስነስቶ ሕዝብ ሊያደርገው ይችላል ብሎ ነው (ዕብ.11:17-19)። የይስሃቅ መወለድ ከተፈጥሮ ሕግ በላይ በእግዚአብሔር ተዓምር እንደሆነ አይቷልና።

አብርሃም ልጅ እንደሚወልድ ተስፋ በተሰጠው በአንደኛውና በሁለተኛው ዓመት ልጅ ወልዶ ቢሆን ኖሮ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ነው በማለት ትልቅ እምነት ላይሆንለት ይችላል። ምክንያቱም ልጅ መውለድ የተፈጥሮ ሕግ መሆኑን ያውቃልና። ስለሆነም በዚህን ጊዜ ልጅህን ሰዋልኝ ቢለው ምናልባት እግዚአብሔርን ስለሚፈራ ለመስዋዕት ያቀርብ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ይስሃቅ ከሙታን ተነስቶ ታላቅ ሕዝብ ሊሆን ይችላል የሚል እምነት ላያድርበት ይችላል። እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ዘግይቶ ቢደርስም እግዚአብሔር ከተፈጥሮ ሕግ በላይ ሆኖ ስላየው ከሙታን እንኳን አስነስቶ የገባውን ቃል ሊፈጽም ይችላል ብሎ ይስሃቅን አቀረበ። የነሙሴን፣ የነዮሴፍን፣ የነዳዊትን ታሪክ ብንመረምር በዚህ ሁኔታ ተፈትነው በእምነታቸው እንዳደጉና እንደተመሰገኑ እናያለን (ሐዋ.7:22-37፣ ዘፍ.37:5-41፣ ዕብ.11:22፣ 1ሳሙ.16:1-2፣ 20:1-3፣ 2ሳሙ.2:4፣ 5:3)።

በዚህ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች ግን ችኩልነት ያጠቃናል (2ጢሞ.3:4)፤ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርገን መጠበቅ ብዙ ጊዜ አይሆንልንም። በመጨረሻው ዘመን ስላለነው ጌታ ሲናገር እንዲህ ብሏል "ነገር ግን የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆንን?" (ሉቃ.18:8)። ስለዚህ ብዙ ጊዜ ታግሶ ከእግዚአብሔር ጋር በእምነት መሄድ ያቅተንና እናጉረመርማለን። እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቅ ሰው ግን የተባረከ ነው (ኢሳ. 30:18)። "በለሱን የጠበቀ ፍሬዋን ይበላል፤ ጌታውንም የሚጠብቅ ይከብራል (ምሳ.27:18)።

### ሐ. የምንፈልገው ነገር ሳይሳካ ሲቀር:-

በኑሯችን ስንቸገር፣ በህመም ስንሰቃይ፣ በብሶት እንሞላና በእግዚአብሔር ላይ ማጉረምረም እንጀምራለን። ይህንን ባሕርይ ያዳበርነው ከወላጆቻችን ጋር በነበረን ሁኔታ ሊሆን ይችላል። ልጆች ሳለን መልካም ነገር ከወላጆቻችን ሲደረግልን በማየት የሚቸግረንና የሚጎድለን ነገር ሲኖር

በማልቀስና በማጉረምረም ወደ ወላጆቻችን ስንቀርብ ወላጆቻችንም እኛን ዝም ለማሰኘት የጠየቅነውን ያደርጉልን ይሆናል። በዚህ ሁኔታ ስላደግን እራሳችንንም ችለን መኖር ስንጀምር በዚሁ መልኩ ወደ አለቆቻችንና ወደ ባለ ሥልጣናት እንቀርባለን። ብሶትና ማጉረምረም ስናበዛ ጉዳያችን ይፈጸም ይሆናል። ችግርና ፈተና ሲበዛብን ወደ እግዚአብሔርም በማጉረምረም የምንቀርበው ከዚህ ተነስተን ነው። እግዚአብሔርን በመልካምነቱ ብዙ ጊዜ ስላየነው ችግርና ፈተና ሲበዛብን ብሶታችንንም ደጋግመን በመግለጽ ዘንበል እንዲልልን እንፈልጋለን። ይህ መንገድ ከሰዎች ጋር ባለን ሁኔታ ይሰራ ይሆናል፤ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ሁኔታ ግን አያስኬደንም።

እግዚአብሔር ሩኅሩኅ አባት ስለሆነ ብሶትና ማጉረምረማችን አይስማማውም፣ ስለሆነም ብሶት ስናበዛና ማጉረምረም ስንጀምር በመካከላችን ክፍተት ይፈጠራል ከዚያም ዕድገታችን ማቆም ይጀምራል። ማጉረምረም እግዚአብሔርን ያስቆጣዋል እንጂ ሩኅሩኅ አያደርገውም፤ "ከእነርሱ አንዳንዶቹ እንዳጉረመረሙና በአጥፊው እንደጠፉ እናንተም አታጉረምርሙ፤ ይህ ሁሉ ነገር የደረሰባቸው ለእኛ የማስጠንቀቂያ ምሳሌ እንዲሆን ነው፣ የተጻፈውም በዘመናት መጨረሻ ላይ ለምንገኘው ለእኛ ትምህርት እንዲሆነን ነው" ይላል (1ቆሮ.10:10-11፣ የ1980 ዓ.ም. ትርጉም)

አንድ ሰው እኔ የማጉረመርመው የደረሰብኝ ጉዳት ትልቅ ስለሆነ እግዚአብሔር በጊዜው ስላልደረሰልኝ ነው ሊል ይችል ይሆናል። እስራኤላውያን ያጉረመረሙት እጅግ በችገራቸውና የሚያደርጉት ባጡ ጊዜ እንደነበር መዘንጋት የለብንም። ሆኖም በማጉረምረማቸው ቀጣቸው (ዘጸ.17:1-2፣ ዘኁ.14:26-29)። ስለዚህ እኛም በእግዚአብሔር ላይ ለማጉረምረም ችግራችንን ምክንያት ልናደርግ አንችልም፤ በዚህ ሁኔታ ብዙዎቻችን ተታለናል። የእግዚአብሔርን ማዳን ለማየት ከፈለግን ማድረግ ያለብን በምስጋና ሆነን ወደ እርሱ መቅረብ ነው። "ምስጋና የሚሰዋልኝ ያከብረኛል የእግዚአብሔርን ማዳን ለእርሱ የማሳይበት መንገድ በዚህ አለ" ይላል (መዝ.49:23)።

ለዚህ ትልቅ ማስረጃ የሚሆነን የጳውሎስና የሲላስ ልምምድ ነው፤ እነርሱ ወንጌልን ሊሰብኩ በመንፈስ ቅዱስ ተልከው ሳለ ትልቅ መከራ ደረሰባቸው። ልብሳቸውን ተገፈው፣ በበትር ተደብድበው፣ በወኅኒ

ተጥለው፣ ከግንድ ጋር ተጠርቀው ታሰሩ። በደረሰባቸው መከራ እንደ ሰው አስተሳሰብ ማጉረምረም ነበረባቸው፤ እነርሱ ግን በዜማ እግዚአብሔርን ያመስግኑ ጀመር፤ በዚህን ጊዜ የወኅኒው ቤት እስኪናወጥ በሮቹም እስኪከፈቱ ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥ ሆነ (ሐዋ.16:22-27)። ጳውሎስና ሲላስ በደረሰባቸው መከራ ቢያጉረመርሙ ኖሮ ይህንን የሚመስል የእግዚአብሔር ታላቅ ተዓምር ማየት ባልቻሉም ነበር። ማጉረምረም ስንጀምር ከእግዚአብሔር ፊት በማፈግፈግ ላይ መሆናችንን መገንዘብ ይኖርብናል። ስለዚህ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለማደግ ከፈለግን ከማጉረምረም ሕይወት መመለስ አለብን።

በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንዳናድግ ወጥመድ ከሆኑብን ነገሮች አምልጠን በማያቋርጥ ሁኔታ ማደግ የሚያስችለን ምን ይሆን? በመጀመሪያ ለመንፈሳዊ ዕድገት ስለሚጠቅሙን መንፈሳዊ ልምምዶች በምዕራፍ አምስት ያየነውን ማስታወስ የግድ አስፈላጊ ነው። እነዚያን መንፈሳዊ ልምምዶች አጥብቀን የምንለማመዳቸው ከሆነ የመንፈስ ቅዱስ እሳት በሕይወታችን መቀጣጠል ይጀምራል።

በመንፈስ ቅዱስ እሳት ውስጥ ሆኖ የእግዚአብሔርን ክብር መስረቅ የማይቻል ነው። ግብዝነት፣ ቂምና ጥላቻ የልምምድ ኃጢአቶች ሁሉ እሳት እንዳገኛቸው ገለባ ይሆናሉ። ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ "<u>በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ</u>" ይላል (ሮሜ.12:1)። በመንፈስ ቅዱስ እሳት የተቀጣጠለ ክርስቲያን በሥጋዊ ስሜት አይሸነፍም (ገላ.5:16)። ሁለንተናው በእሳት የተቀጣጠለ ግንድ የሚሰማው የእሳቱ ስሜት ነው፤ እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ እሳት የተቀጣጠለ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ስሜት ይሞላል። ስለዚህ የራስን ክብር ከመፈለግ ይልቅ ክርስቶስን ለማክበር ራስን ዝቅ ለማድረግ አይቸገርም (ዮሐ.15:19፣ 1ቆሮ.12:1-3)። በመንፈስ ቅዱስ የተቀጣጠለ ክርስቲያን ከጥላቻ ይልቅ ፍቅር ይሞላዋል፣ ከሃዘን ይልቅ ደስታ ያበዛል፣ ችኩላን በትዕግስት ይተካል፣ ትዕቢት ለየዋህነት ሥፍራ ይለቃል፣ በአጠቃላይ ሕይወቱን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ይሞላዋል። በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደተተከለች ፍሬዋንም በጊዜው እንደምትሰጥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል (መዝ.1:3)።

## VI. በክርስትና ሕይወት ለማደግ እንቅፋት የሚሆኑብን ነገሮች

1. ክርስቲያን ደጋግሞ ኃጢአት ሲያደርግ በምን መንገድ ላይ ያለ ይመስልሃል?
2. በክርስትና ሕይወት እያለን እንደሚገባ ለማደግ እንዳንችል እንቅፋት ሊሆኑብን የሚችሉ ነገሮች ምንድን ናቸው?
3. ይሉኝታ መለስተኛ ግብዝነት ሊሆን ይችላል ያልንበት ምክንያት ምንድን ነው?
4. በሥራዬ እጸድቃለሁ ብሎ የሚያስብ ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ እንዴት ይታያል?
5. የልምድ ኃጢአት አጀማመሩ እንዴት ነው?
6. በደልን መቁጠር ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነታችንን ሊነካ ስለሚችል ምን ማድረግ አለብን?
7. ሕሊናችን እንዳያድፍ ሰዎችን ላለመጉዳት መጠንቀቅ ብቻ በቂ ሊሆን ይችላልን? በቂ ካልሆነ በተጨማሪ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል? ከሌሎችም ጋር ተወያይበት።
8. ብዙ ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስን አለመታዘዛቸው ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል? ተወያይበት።
9. በመድረክ የሚያገለግሉ አገልጋዮች የእግዚአብሔርን ክብር የሚጋሩት ምን በማድረግ ነው?
10. ከክርስቶስ ጋር ለመውረስ የመረጠ አገልጋይ መወሰን ያለበት ነገር ምንድን ነው?
11. የዚህ ዓለም የባለጠግነት ኃሳብ በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንዳናድግ ማነቆ ሊሆንብን የሚችለው እንዴት ነው? ተወያይበት።
12. ምኞት እስካለ ድረስ የችግረኝነት ስሜት መፈጠሩ አይቀርም፤ ከችግረኝነት ስሜት ለማምለጥ መፍቴሄው ምንድን ነው? ተወያይበት።
13. የዚህ ዓለም ጠበብት ዘላቂ የሆነ ሰላምና ደስታ የሚገኝበትን መንገድ ያልደረሱበት ምክንያት ምንድን ነው?
14. በእግዚአብሔር ፊት ለጋስ ለመሆን ባለጠጋ መሆን ያስፈልጋል ብለህ ታስባለህ? ከሌሎች ጋር ተወያይበት።
15. እግዚአብሔር ባለጠግነት እንዲሰማን ምን አደረገ? ኤፌ.1:3 ተመልከት።
16. ሰው ምኞቱን በዚህ ዓለም ነገር ሊሞላ ሲጥር መታለሉ እንዴት ነው? ተወያይበት።
17. ዲያብሎስ የዚህ ዓለም ገዢ የተባለበት ምክንያት ምን በማድረጉ ነው? በዚህ ረገድ ክርስቲያን በሰይጣን ወጥመድ እንዳይያዝ የሐዋርያው ጳውሎስ ምክር ምንድን ነው? (1ጢሞ.6:9-11) ተመልከት።
18. እግዚአብሔር የሰጠንን ተስፋ ማዘግየቱ ለጥቅማችን ስለመሆኑ አብርሃምን ከገጠመው ተሞክሮ ምን ትማራለህ? ተወያይበት።
19. የማጉረምረምን ልምድ ያካበትነው እንዴት ነው?
20. ማጉረምረም እግዚአብሔርን የሚያስቆጣው ለምንድን ነው?
21. በክርስትና ሕይወት እንዳናድግ ወጥመድ ከሚሆኑብን ነገሮች ለመዳን መለማመድ ያለብን ነገር ምንድን ነው?

## VII. የታማኝ ክርስቲያን ዋጋ

"እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ" (ራዕ.22:21)። ከጌታ እጅ ደመወዙን ለመቀበል የሚዘጋጅ ክርስቲያን ሕይወቱን በጥንቃቄ መጠበቅ ይኖርበታል። "ሙሉ ደመወዝን እንድትቀበሉ እንጂ የሠራችሁትን እንዳታጠፉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ" (2ዮሐ.8)።

ጌታ ሲገለጥና ሁላችን በፊቱ ስንሰበሰብ ሁለት የተለያየ ነገር ሊገጥመን ይችላል፤ አንደኛው በክፉ ሥራችን መገሰጽ ሲሆን ሁለተኛው በታማኝነትና በመልካም ሥራችን የተዘጋጀልንን ደመወዝን መቀበል ይሆናል። ስለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ "መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን ብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና" ይላል (2ቆሮ.5:10)፤ በተጨማሪም (ሮሜ.14:10-13፣ 1ዮሐ.2:28) ተመልከት።

አንዳንድ ክርስቲያኖች ደኅንነት ካገኘሁ ለሽልማቱ ግድ የለኝም የሚሉ አልታጡም። ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ስንፍና ብቻ ሳይሆን ጌታ ላዘጋጀው ዋጋ አድናቆት ማጣት ስለሆነ አጥብቀን ልናስብበት ይገባናል። ጌታ ሲገለጥና በፊቱ ስንሰበሰብ ዋጋ ለመቀበል የሚያበቃ ሥራ ምንድን ነው? ለአገልግሎቱ ከተጠሩት በተጨማሪ ሌሎች ክርስቲያኖችም ደመወዝ ይቀበሉ ይሆን? ጌታስ ለታማኝ ክርስቲያኖች የሚከፈለው ደመወዝ ምን ይሆን? የሚሉ ጥያቄዎችን መሠረት በማድረግ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠውን መልስ በጥንቃቄ ቀጥለን እንመለከታለን።

1. የአዲስ ኪዳን ሕዝብ ሁሉ አገልጋይ መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። የሚከተሉትን ጥቅሶች በጥንቃቄ ተመልከት 1ጴጥ.2:9፣ 4:10፣ ራዕ.5:9-10፣ ዮሐ.15:18።

መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ ልዩ ልዩ ጸጋን መስጠቱ ሁሉም ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቤት አገልጋይ መሆኑን ያሳያል (1ቆሮ.12:4-11)። እያንዳንዱ ክርስቲያን በተሰጠው ጸጋ በታማኝነትና በትጋት የሚያገለግል ከሆነ ከጌታ ደመወዝ አለው።

"በሩጫ ውድድር ሁሉም እንደሚሮጡና ከእነርሱም አንዱ ብቻ ሽልማት እንደሚቀበል ታውቁ የለምን? ስለዚህ እናንተም ሽልማት ለመቀበል ሩጡ" (1ቆሮ.9:24 የ1980 ዓ.ም. ትርጉም) ክርስቶስ ዋጋ የሚሰጠን ከሌሎች ጋር በማወዳደር ሳይሆን እንደ ሩጫችን መጠን ነው። ይሁን እንጂ ክርስቶስ የሚከፍለውን የመጨረሻ ዋጋ የዚህ ዓለም መንግሥታት ተባብረው ጥበባቸውንና ሃብታቸውን አንድ ላይ አድርገው ማዘጋጀት አይችሉም፤ የተባበሩት መንግሥታት ለሯጮች ሽልማት ቢያዘጋጁ ብዙዎቹን ለማወዳደር ዕድሉም አቅሙም ላይኖራቸው ይችላል። ነገር ግን በጌታ እጅ የመጨረሻዋን ሽልማት ሳይሆን ከፍተኛውን ዋጋ ከእጁ ለመቀበል መዘጋጀት እንችላለን። ጌታም ለድል ሕይወት የሚያበቃ ጸጋንና መንፈስ ቅዱስን ሰጥቶናል። ከእኛ የሚጠብቀው ነገር ቢኖር ታማኝነትና ትጋት ነው፤ ታማኝ ለመሆን የሚያስከፍለው ዋጋ ደግሞ ራስን መካድ ነው።

2. ከጌታ እጅ ደመወዝ ለመቀበል የሚያበቃንና ልንሳተፍበት የሚገባ ሥራ ምን ይሆን? ከጌታ እጅ ዋጋ ለመቀበል የሚያበቃን ሥራ ምን እንደሆነ ሁሉንም በዝርዝር ለማወቅ ያዳግተን ይሆናል፤ ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱትን ማየት እንችላለን።

**ሀ. የጸሎት ዋጋ**

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ.6:7 ላይ የተናገረውን ብናይ በታማኝነት ለሚጸልዩ እግዚአብሔር ዋጋ እንደሚከፍላቸው ተናግሯል። "ስትጸልዩ እንደ ግብዞች አትሁኑ፤ ለሰው ይታዩ ዘንድ በምኩራብና በመንገድ ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉና እውነት እላችኋለሁ፤ <u>ዋጋቸውን ተቀብለዋል</u>። አንተ ግን ስትጸልይ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ በስውር የሚያይህ አባትህ በግልጥ <u>ይከፍልሃል</u>" ይላል። በተጨማሪም "ጌታቸው በመጣ ጊዜ <u>ሲተጉ</u> የሚያገኛቸው እነዚያ ባሪያዎች ብፁዓን ናቸው፤ እውነት እላችኋለሁ ታጥቆ በማዕድ ያስቀምጣቸዋል፤ ቀርቦም ያገለግላቸዋል" ይላል (ሉቃ.12:37)። ልንገነዘብ የሚገባው በዚህ ቃል መሠረት ያለ ጥርጥር በጸሎት ስለ መትጋት ነው። ስለዚህ በጸሎት የሚተጉ ከጌታ የታመነ ዋጋ አላቸው።

**ለ. የጾም ዋጋ**

በዚሁ በማቴዎስ ምዕራፍ ስድስት ውስጥ ለሰዎች ለመታየት ሳይሆን

በታማኝነት በጸሎት ለሚተጉ ደመወዝ እንደሚከፈላቸው ከተናገረ በኋላ በታማኝነት በጾም ለሚተጉም ደመወዝ እንዳላቸው ይናገራል።

"ስትጦሙም እንደ ግብዞች አትጠውልጉ ለሰዎች እንደጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፉሉና እውነት እውነት እላችኋለሁ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ስትጦም በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደ ጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ፤ ራስህን ተቀባ ፊትህንም ታጠብ፣ በስውር የሚያይህ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል" ይላል (ማቴ.6:16-18)። ቀደም ሲል እንዳየነው ብዙ ክርስቲያኖች ጾምና ጸሎት የማይነጣጠሉና አንድ እንደሆኑ ይገምታሉ። ጾምና ጸሎት የሚደጋገፉ ቢሆኑም ዋጋቸው ለየራስ ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች ለጾምና ለጸሎት ዋጋ እንዲሰጥ አያስተውሉም፤ ይሁን እንጂ ጌታ የሰጠው የተስፋ ቃል የሚፈጸም መሆኑን በእምነት መቀበል ይኖርብናል።

ሐ. **የወንጌል አገልግሎት ዋጋ**

በጥቅሉ አገልግሎት ሲባል ሁሉንም ይይዛል፤ በዚህ ምዕራፍ ነጠል አድርጎ ለማየት የተፈለገው የወንጌል አገልግሎትን ነው፤ የወንጌል አገልግሎት ምዕመናንን ከማፍራት አንስቶ ደቀ መዝሙር በማድረግ ለአገልግሎት እስከ ማድረስ ያለውን ያጠቃልላል። ስለሆነም የወንጌል አገልጋይ ደመወዝ ከፍ ያለ መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል (ዳን.12:3፣ ራዕ.3:5፣ ሉቃ.10:32 ጋር አገናዝብ)። የወንጌል ባለ አደራ ብዙ ዋጋ መክፈል ይጠበቅበታል (ማቴ.10:37፣ 2ጢሞ.4:5) የዚያኑ ያህል ደግሞ ጌታ ታማኝ ለሆኑ አገልጋዮች የከበረ ዋጋ ይከፍላቸዋል (ማቴ.24:45)።

የሐዋርያው የጳውሎስ የወንጌል አገልጋይነት:-

1ኛ. ለጦርነት ያሰለፈውን አዛዡን ደስ ለማሰኘት እራሱን የሰጠ ወታደር፣
2ኛ. በሩጫ የሚወዳደር ሯጭ (አትሌት)፣
3ኛ. ታታሪ ገበሬን መምሰል እንዳለበት ያስገነዝበናል (2ጢሞ.2:37)።

እነዚህ ሦስት የሥራ መስኮች እጅግ አድካሚ ስለሆኑ ብዙ ሰዎች የእነርሱ ደጋፊ መሆን ይመርጣሉ እንጂ ሊሰለፉባቸው አይፈቅዱም። ከእነዚህም ይልቅ እጅግ አድካሚና መከራ የሞላበት ሥራ የወንጌል አገልግሎት ነው። እነዚህን ጥቅሶች መርምር (2ጢሞ.1:9፣ 2:3፣ 1ጢሞ.6:12፣

ሉቃ.14:27-30፣ ዮሐ.12:24)። ጌታ በክብር ሲመጣ ድል አድራጊ ክርስቲያኖች ደመወዛቸውን ከእጁ ለመቀበል ሲቀርቡ ባዶ እጃቸውን የሚመለሱ ወገኖች ምን ያህል ይጸጸቱ ይሆን!

ሐዋርያው ጳውሎስ ከጌታ ሙሉ ደመወዙን ለመቀበል ትጋትን ያሳይ እንደነበረና እንደሚጠነቀቅ ሲገልጽ እንዲህ አለ "ወንጌልን ብሰበክ እንኳን የምመካበት የለኝም፤ ግድ ደርሶብኝ ነውና፤ ወንጌልንም ባልሰብክ ወዮልኝ። ይህን በፈቃዴ ባደርገው ደመወዝ አለኝ፤ ያለፈቃዴ ባደርገው መጋቢነት በአደራ ተሰጥቶኛል። እንግዲህ ደመወዜ ምንድር ነው? ወንጌልን እየሰበክሁ በወንጌል ካለኝ መብት በሙሉ እንዳልጠቀም <u>ወንጌልን ያለ ዋጋ ብናገር ነው</u>" (1ቆሮ.9:16-18)። ወንጌልን እየሰበከ ከቤተ ክርስቲያን ደመወዝን መቀበል መብቱ ሆኖ ሳለ በመብቱ አለመጠቀሙ ከጌታ ሙሉ ደመወዝ እንደሚሰጠው አስቦ ነው። ነገር ግን እንደሚገባ ሳያገለግሉ ከፍ ያለ ደመወዝ እየተከፈላቸው የሚኖሩ አገልጋዮች ያለ አግባብ ስለ ተቀበሉት ደመወዝ በጌታ ፊት ይጠየቁ ይሆን?

ስለ ወንጌል ብዙ ተጋድለው በመጨረሻዋ ሰዓት ትንሽ ሲቀራቸው የሰሩትን ሁሉ አጥፍተው ባዶ የሚቀሩ አገልጋዮች ምን ይሰማቸው ይኖሩ ይሆን? "ሙሉ ደመወዝ እንድትቀበሉ እንጂ የሠራችሁትን እንዳታጠፉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ" ይላል (2ዮሐ.8)። ይህ ዘመን እጅግ ካልተጠነቀቅን ያዘናጋል። ስለ ወንጌል እውነት ሳይሆን ስለ ራሳችን ሥፍራ ተጋድሎ በማድረግ ዘመናችንን የምንጨርስ ከሆነ በጌታ ፊት ምንኛ እናፍር ይሆን?

"አሁንም ልጆች ሆይ በሚገለጥበት ጊዜ እምነት እንዲሆንልን በመምጣቱም በእርሱ ፊት <u>እንዳናፍር</u> በእርሱ ኑሩ" ይላል (1ዮሐ.2:28)። ከጌታ እጅ ዋጋ ለመቀበል ያሰበ አገልጋይ ምርጫውን ማስተካከል ያለበት አሁን ነው። ዋጋ የሚሰጠን ብዙ ዘመን በማገልገላችን ብቻ ሳይሆን በተሰጠን ጊዜ ውስጥ በታማኝነት መቆማችን ነው። (ማቴ.20:1-16) ከአሁን በኋላም ቢሆን ምርጫችንን ለማስተካከል ጊዜ አለን።

ለአገልግሎት መጠራት ብቻውን ዋጋ ለመቀበል አያስችልም፤ የአገልግሎት ጥሪ ከኃላፊነት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ለአገልግሎት የተጠራ አገልጋይ ኃላፊነቱን እንዴት እንደተወጣ ተጠያቂ ይሆናል (ማቴ.25:14-30) በአገልግሎቱ ታምኖ የቆየ ከሆነ ደግሞ ከታመነው ጌታ የከበረ ዋጋ አለው (ኢሳ.10:10፣ ራዕ.22:12)።

### መ. ቅዱሳንን በመርዳት ዋጋ መቀበል

"ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ዋጋው አይጠፋበትም" (ማቴ.10:42)። የታመነ አገልጋይ በዚህ ዓለም ሲኖር ጌታን ደስ እያሰኘ ለማገልገል የሚከፍለው ዋጋ መከራን ነው (ገላ.1:10፤ 2ጢሞ.3:12)። አገልጋይ ለተጠራበት አገልግሎት በታማኝነት ከቆመ የከበረ ዋጋ ይጠብቀዋል። ከታመነ አገልጋይ ጋር ረዳቱ ሆኖ የቆመ ደግሞ የእርሱን ዋጋ ያገኛል። እግዚአብሔር ፃድቅ አምላክ ስለሆነ ሥራው ሁል ጊዜ ትክክል ነው፤ በመሆኑም የአገልጋይን ዋጋ ለመቀበል እንዳንችል ለአገልግሎት አልተጠራንም ለሚሉ ከታማኝ አገልጋይ ጋር ዋጋ አብረው ለመቀበል እንዲችሉ መንገዱ አዘጋጅቷል። ከላይ እንዳየነው እግዚአብሔር ቅዱሳንን ሁሉ እንዲያገለግሉ ይፈቅዳል፤ ግማሹን ወንጌል ለዓለም እንዲሰብክ ጠራ፣ የተቀሩት በጉልበታቸውና በገንዘባቸው ለወንጌል ስብከትና አገልግሎት የተጠሩትን እንዲረዱ ጠራ፤ ከሁሉም የሚጠበቀው ታማኝነት ነው። ሁሉም ለተጠሩበት ከታመኑ የማይጠፋ ዋጋን ይቀበላሉ። በማቴዎስ 10:40-42 ላይ የሚያስገነዝበን ሰብዓዊነት አስገድዶን በምናደርገው ችሮታ ሳይሆን የጌታ ደቀ መዛሙርት በመሆናቸው ምክንያት አውቀን ስለምናደርገው እገዛ ዋጋ እንዲከፈለን የገባው ቃል ነው።

በሰብዓዊነት ለተቸገሩ ልንራራ እገዛም ልናደርግ ይገባናል፤ በዚህ ረገድ ዋጋን እናገኝበታለን፤ ነገር ግን ከላይ የተጠቀሰው ቃል የሚያረጋግጥልን ነብዩን ነብይ በመሆኑ ምክንያት፣ ተቀብሎ እገዛ የሚያደርግ የነብዩን ዋጋ እንደሚቀበል ነው፤ ጻድቅን ጻድቅ በመሆኑ ምክንያት ተቀብሎ የሚያግዝ የጻድቁን ዋጋ እኩል እንደሚቀበል ነው። በአጠቃላይ የጌታ ባሪያዎች አገልጋይ በመሆናቸው ምክንያት የሚቀበልና የሚያግዝ የነዚያን አገልጋይ ዋጋ አብሮ እንደሚቀበል የተሰጠ የተስፋ ቃል ነው። ይህንን ማድረግ ደግሞ የታመነ አገልጋይ ከሚቀበለው መከራና ከሚከፍለው ጋር ሲታይ እጅግ የቀለለ ነው።

የፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች ለሐዋርያው ጳውሎስ በችግሩ ጊዜ ደርሰው ያደረጉለት ስጦታ ከእርሱ አልፎ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ ስጦታ ስለመሆኑ ሲገልጽ "መስዋዕት የሚሆን ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኘውን ስጦታችሁን ከአፍሮዲጡ ተቀብዬ ተሞልቻለሁ" ይላል (ፊል.4:18)። በዚህም ምክንያት የፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች በመስጠትና በመቀበል ስሌት ከእርሱ ጋር እንደተካፈሉ ያረጋግጥላቸዋል (ፊል.4:14)።

የቆሮንቶስን ክርስቲያኖች ዳግም በብርቱ ይወቅሳቸዋል። ከመልእክቱ እንደምንረዳው በቸገረው ጊዜና በሚያገለግልበት ወቅት በቸልታ ሳያዩት አልቀሩም (1ቆሮ.9:1-7)። ስለሆነም "እኛ መንፈሳዊን ነገር የዘራንላችሁ ከሆንን የእናንተን የሥጋዊ ነገር እኛ ብናጭድ ትልቅ ነገር ነውን?" ይላቸዋል (1ቆሮ.9:11)። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ሌሎች አገልጋዮችን ይረዱ እንደነበረ ከጻፈው መልእክት እንረዳለን (1ቆሮ.9:12)። ሌሎች በእርሱ አገልግሎት ላይ መጥተው ባለ መብት ሆነው ደመወዝ ሲቀበሉ እርሱን ግን ቸል ማለታቸው የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ምክንያታቸው ምን ይሆን?

የአገልግሎት ዋጋ በሰዎች ስሌት የሚከፈል ቢሆን ኖሮ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ታላቅ ዋጋ እየከፈሉ የሚያገለግሉ አገልጋዮች ምን ያህል በተሰማቸው? በዚህ ዓለም አንዱ የዘራውን ሌላው ልጪድ ይላል፤ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተፈጸመው ይህ ነው፤ በጌታ ዘንድ ግን እንዲህ አይሆንም፤ እርሱ ለሁሉም እንደ ሥራው ዋጋን ሊከፍል ይመጣል። ስለዚህ "እግዚአብሔር ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአቸው ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመጸኛ አይደለም" ይላል (ዕብ.6:10)።

### 3. የታማኝ ክርስቲያን ዋጋ ምንድን ነው?

ለታማኝ ክርስቲያኖች የሚጠብቃቸው ክብርና የሚከፈላቸው ዋጋ የዚህ ዓለም ገንዘብ ባለመሆኑ ለመረዳት ያስቸግረናል። ያን ሰማያዊና ዘላለማዊ "የሆነውን ዋጋ ምን እንደሆነ ለማወቅ ቀርቶ መገመትም ያስቸግረናል። ጌታ የሚከፍለው የመጨረሻውን ዋጋ የዚህ ዓለም መንግሥታት ተባብረው እንኳ ቢሆን ሊያዘጋጁት አይችሉም። ይህንን ከተገነዘብን የመጨረሻውን ዋጋ ሳይሆን የመጀመሪያውንና የላቀውን ዋጋ ለመቀበል በታማኝነትና በትጋት የተሰጠንንና የተጠራንበትን አገልግሎት ልንፈጽም ይገባናል።

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ተግቶ የሚሰራው ሞያና ችሎታ ስላለው ብቻ ሳይሆን ደመወዙን እያሰበ ነው። በተመሳሳይ መልኩ የአገልግሎት ጥሪና ጸጋ ወይም ሰፊ የአገልግሎት በር ስላገኘን ብቻ ሳይሆን ከጌታ የምንቀበለውን ዋጋ እያሰብን ማገልገል ይኖርብናል። ይህንን ማድረግ ጌታ ላዘጋጀልን ዋጋ ትልቅ ግምትና አድናቆት መስጠታችን ስለሆነ በዚህ ጌታ ደስ ይለዋል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ እስከ መጨረሻው ታምነው ለቆሙት የሚከፈለውን ዋጋ ለማብራራት መሞከር እጅግ ማሳነስ መስሎ ስለታየኝ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶቹን እንዳለ ማስቀመጥ መልካም መስሎ ታይቶኛል። ለታመኑ ክርስቲያኖች የከበረ ዋጋ እንደሚያቆያቸው ብዙ ሥፍራ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰ ቢሆንም በዓይነታቸው ተጠቃቅሰው የምናገኛቸው ጥቂቶቹን ጌታ በኤሽያ ለነበሩ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መጋብያን በላከው መልእክት ውስጥ ነው። የመልእክቱ ይዘት በወቅቱ የነበሩት የሰባቱን አብያተ ክርስቲያናት መጋብያንን ሁኔታ የሚገልጽ ቢሆንም የተሰጠው ተስፋ ግን በዘመናት ላሉ ለታመኑና ሥራውን ለጠበቁ ክርስቲያኖች ሁሉ ነው። ስለሆነም ከላይ እንደተጠቀሰው በራዕይ መጽሐፍ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ለታመኑና ለድል አድራጊዎች የተሰጠውን ተስፋ ብቻ በመቀበል እናያለን።

ሀ. በእግዚአብሔር ገነት ካለው የሕይወት ዛፍ መብላት:- "መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ ድል ለነሳው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ" (ራዕ.2:7)።

ይህ የሕይወት ዛፍ በኤደን ገነት የነበረውንና አዳም በመብላቱ ለዘላለም እንዳይኖር የተከለከለውን ያሳስበናል (ዘፍ.3:22)። ሆኖም ይኼኛው የሕይወት ዛፍ ምድር የምታበቅለው ስላልሆነ በኤደን ገነት ከነበረው ጨርሶ የተለየ መሆኑን እንገነዘባለን።

ለ. የሕይወት አክሊል:- ". . . እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን <u>የሕይወት አክሊል እሰጥሃለሁ</u>" (ራዕ.2:10) ይህ የተስፋ ቃል በሰርምኔስ ለነበረው መጋቢ በግል የተሰጠ የተስፋ ቃል ይመስላል። የሌሎችን ሁሉ ስንመለከት "እሰጥሃለሁ" በሚል ቃል አይደመደምምና።

ይህ የሕይወት አክሊል ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ጢሞ.4:7 ላይ "የጽድቅ አክሊል" ከሚለው ጋር አንድ መሆኑንና አለመሆኑን እርግጠኛ አይደለሁም። ሐዋርያው ጳውሎስ የጠቀሰው የጽድቅ አክሊል ከሆነ ግን የታመኑትን ክርስቲያኖች ሁሉ ያመለክታል። ቀጥሎ ያለውን የተስፋ ቃል ስንመለከት ድል የነሳ በሁለተኛ ሞት አይጎዳም" ይላል። ይህ ግን ለሁሉም ስለመሆኑ ግልጽ ነው።

ሐ. ነጭ ድንጋይና በእርሱ ላይ የተጻፈ አዲስ ስምና የተሰወረ መና:- "መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ ድል ለነሳው ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ፤ ነጭ ድንጋይ እሰጠዋለሁ፤ በድንጋዩ ላይ ከተቀበለው በቀር አንድም እንኳን የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፏል (ራዕ.2:17)።

እዚህ ላይ የተጠቀሰው ተስፋ ሁለት የተለያዩ ስጦታዎች እንደሆኑ ያመለክታል "አንድስ እንኳን የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም" የሚለው ጌታ አዲስ ስም እንዳለውና ያንንም አዲስ ስም ማንም ሊያውቀው የሚችል እንደሌለ ያመለክታል። ይህ የተሰወረ መና እና በነጭ ድንጋይ ላይ የተፃፈው የጌታ አዲስ ስም ልንረዳው ከምንችለው በላይ እጅግ የላቀና የከበረ ስጦታ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ አሁን ለማወቅና ለመረዳት ስለሚያዳግቱን አድናቆት ላይዘን ይችል ይሆናል።

መ. አሕዛብን በብረት በትር የመግዛት ሥልጣን:- "ድል ለነሳውና እስከ መጨረሻው ሥራዬን ለጠበቀው እኔ ደግሞ ከአባቴ እንደተቀበልሁ በአሕዛብ ላይ ሥልጣንን እሰጠዋለሁ፤ በብረትም በትር ይገዛቸዋል እንደ ሸክላ ዕቃም ይቀጠቀጣሉ የንጋትንም ኮከብ እሰጠዋለሁ" (ራዕ.2:26-28)።

በዚህ ሥፍራ የተሰጠው የተስፋ ቃል ሥልጣን ለማግኘት ስለሆነ ከሌላው ይልቅ ይገባን ይሆናል። ይህንን የሚመስል የተስፋ ቃል በሌላም ሥፍራ ተጽፎ እናገኛለን (ራዕ.20:1-4፤ ዳን. 7:22፤ ማቴ.25:21)። ይህ ሥልጣን ግን ምንጊዜም የሚሻር አይሆንም።

ሠ. በነጭ ልብስ መጎናጸፍና በአብ ፊት ምስክርነት ማግኘት:- "ድል የነሳው እንዲሁ በነጭ ልብስ ያጎናጽፋል፤ ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም፤ በአባቴና በመላእክቱም ፊት ለስሙ እመሰክርለታለሁ" (ራዕ.3:5)።

ጌታ ለድል አድራጊው ክርስቲያን በአባቱና በመላእክቱ ፊት ምስክርነት መስጠት ከሉቃስ 12:8 ላይ ከተጻፈው ጋር ይመሳሰላል። እስቲ እናስብ! እልፍ አእላፋት መላእክት በተሰበሰቡበት፤ እግዚአብሔር በታላቅ ዙፋን ላይ ተቀምጦ፤ የጌቶች ጌታ የነገሥታት ንጉሥ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ለታማኝ ክርስቲያን ምስክርነት ሲሰጥ! እጅግ የሚያስደንቅ ነው!

ረ. በእግዚአብሔር መቅደስ አምድ መሆን:- "ድል የነሳው በአምላኬ መቅደስ ዓምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ። ወደፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም የአምላኬ ስምና የአምላኬ ከተማ ስም ማለትም ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ የምትወርደውን አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን፣ አዲሱንም ስሜን በእርሱ ላይ እጽፋለሁ" (ራዕ.3:12)። በምዕራፍ 2:17 ላይ ስለተጠቀሰው አዲስ ስም በድጋሚ ይጠቅሳል። በ2:17 ላይ በነጭ ድንጋይ ላይ ተነፃፊውን አዲሱን ስሙን እንደሚሰጥ ሲያመለክት በዚህ ሥፍራ ደግሞ አዲሱን ስሙን በእርሱ ላይ እንደሚጽፍ ያሳያል። በተጨማሪም የአዲሲቷ ኢየሩሳሌም በእርሱ ላይ መጻፍና በእግዚአብሔር መቅደስ አምድ እንዲሆን ሲደረግ ሦስት ተደራራቢ ሽልማት መስጠቱን ያሳያል።

ሰ. በጌታ ዙፋን ላይ መቀመጥ:-"እኔ ደግሞ ድል እንደነሳሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ ድል ለነሳው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ" (ራዕ.3:21)። ከሁሉም እጅግ የሚደንቅ ለማሰብና ለመረዳት የሚያዳግት የተስፋ ቃል ነው!

ፍጡር የሆነ ሰው ምን ያህል ክብር ቢሰጠው ይሆን ጌታ በተቀመጠበት ዙፋን ላይ እንዲቀመጥ የሚሰጠው? ይህ እንዴት ይፈጸም ይሆን? ይህንን መረዳት እጅግ አዳጋች ነው። አስበን ልንደርስበት የምንችል አይመስለኝም፤ እንዴት እንደሚፈጽመው እርሱ ያውቃል፣ እርሱ ራሱ በዙፋኑ ላይ ተምቀጦ ለማየት መብቃት ታላቅ ብጽእና ነው ይህንን ሁሉ ልናይ ግን ጊዜው ቅርብ ነው። ሰባተኛው መለከት ሲነፋ የዓለም መንግሥታት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች። ከዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሳል። የሚሉ ታላላቅ ድምፆችን ስንሰማ ደስታችን ምን ያህል የላቀ ይሆን! (ራዕ.11:15)። "እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ይላል አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ና! (ራዕ.22:20)።

አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ጌታ ክብርና ምስጋና ይሁን!!

## VII. የታማኝ ክርስቲያን ዋጋ

1. ክርስቶስ ሲገለጥ ከእጁ ዋጋ ለመቀበል ከሚቀርቡት አንዱ ለመሆን እንደምትችል አስበህ ታውቃለህ?
2. ሽልማት ባላገኝም ደኅንነት ማግኘቴ ብቻ ይበቃኛል ብሎ ማሰብ ከምን የመነጨ ኃሳብ ሊሆን ይችላል?
3. ክርስቶስ ሲገለጥና በፊቱ ስንሰበሰብ ምን ዓይነት ሁኔታ ሊገጥመን ይችላል?
4. ጌታ ሲገለጥ ከእጁ ዋጋ ለመቀበል የሚያስችለንን ሥራ በዝርዝር ባናውቅም አራት ዋና ዋና ጉዳዮችን ግለጽ።
5. ክርስቶስ ዋጋ የሚሰጠን ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ሥራችንን በማወዳደርና ባስገኘነው ብልጫ ይመስልሃል? ካልሆነ የበለጠ ዋጋ የምናገኘው በምን መሠረት ሊሆን ይችላል?
6. ጌታ ለአገልግሎት ለሾማቸው የሚሰጠውን ዋጋ ለማግኘት ምን የተመቻቸ ሁኔታ አለ?
7. ክርስቶስ የሚሰጠውን የመጨረሻ ዋጋ የዚህ ዓለም መንግሥታት ተባብረው ሊያዘጋጁ እንደማይችሉ አስበህ ታውቃለህ?
8. የጾምና የጸሎት ቀን ለየብቻ መሆናቸውን ጌታ ከተናገረው ቃል አስረዳ።
9. ከጌታ ሙሉ ደመወዙን ለመቀበል እንዲችል ሐዋርያው ጳውሎስ የወሰደው እርምጃ ምን ነበር?
10. ስለ ወንጌል እውነት ሳይሆን ስለ ራሳቸው ሥፍራ ተጋድሎ በማድረግ ጌታን ያገለገሉ የሚመስላቸው በጌታ ፊት ሲቆሙ ምን የሚገጥማቸው ይመስልሃል?
11. ከጌታ እጅ ዋጋን ለመቀበል ያሰበ አገልጋይ ምርጫውን ማስተካከል ያለበት መቼ ነው? ከሌሎች ጋር ተወያይበት።
12. ጌታ ለሾማቸው አገልጋዮች ሽልማት መስጠቱ ማዳላት ነው የሚል ሰብዓዊ አስተሳሰብ ያለው ሰው ቢገጥምህ ምን መልስ ትሰጠዋለህ?
13. በማቴ.10:42 ላይ ያለውን ቃል እንዴት ትረዳዋለህ?
14. የጌታ አገልጋይ በዚህ ዓለም ሲኖር ጌታን ደስ እያሰኘ ለመኖር የሚከፍለው ዋጋ ምን ሊሆን ይችላል?
15. ጌታ ሲገለጥ ለታማኝ ክርስቲያኖች የሚሰጠውን ሽልማት ለማብራራት ቢፈለግ እጅግ ማሳነስ ሊሆን ይችላል የተባለበት ምክንያት ምንድን ነው?
16. ጌታ በእስያ ለነበሩ ሰባት አብያተ ክርስቲያናት መላእክት ለድል አድራጊ ክርስቲያኖች ስላዘጋጃቸው ሽልማቶች ምን ያህል የከበሩ መሆናቸውን ማወቅ ቢያዳግትም ከእነዚህ ውስጥ አንተን ያስደንቅህ የትኛው ነው?
17. አንተ ከጌታ የከበረውን ዋጋ ለመቀበል ምን እያደረግህ ነው?

ጌታ ይርዳህ!

# እ ር ማ ት

| ገጽ | ስህተት | ትክክለኛ ቃል |
|---|---|---|
| 1 | የማናገኝበት | የምናገኝበት |
| 4 | ጥቅሉን | ጥቅሱን |
| 12 | ይሰለቅ | ይሰቀል |
| 22 | የሰመነትን | የሰሙትን |
| 23 | አማልክቶችን | ምልክቶችን |
| 29 | ስያሜ | ስሜት |
| 33 | የማይችሉ | የሚችሉ |
| 35 | ዮሐ.2:26-27 | 1ዮሐ.2:26-27 |
| 49 | የወጡ | ያልወጡ |
| 69 | ተጽሯል | ተጽፏል |
| 74 | ለመወለድ | በመወለድ |
| 74 | ባይሆንም | ቢሆንም |
| 77 | እያደረጋችሁ | እያደጋችሁ |
| 117 | ሮሜ 10:20 | ሮሜ 16:20 |
| 153 | ተጽደኖ | ተጽዕኖ |
| 153 | ተምቀጠ | ተቀምጠ |
| 154 | ቀን | ዋጋ |
| (ቁ.8) | | |

ጥያቄ ወይም አስተያየት ቢኖራችሁ በደስታ እቀበላለሁ።

አድራሻ፡ የፖ.ሣ.ቁ. 30194

አዲስ አበባ